# ምክር ፈላጊዎችን እንዴት እናማክር?

ጸሐፊ፡- ከበደ በከሬ

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 2001 ዓ.ም.

# ምክር ፈላጊዎችን እንዴት እናማክር?

ይህንን መጽሐፍ ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት
ወይም እንደገና ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።

በመጀመሪያ ነሐሴ 1994 ዓ.ም. ታተመ

ለሁለተኛ ጊዜ ታርሞና ተሻሽሎ በ2001 ዓ.ም. ታተመ

በድህነት ውስጥ እየኖሩ ያላቸውን ነገር በማካፈል፣ ራሳቸው ተምረው የትምህርትን ጣዕም ሳይቀምሱ በማስተማር፣ ከወላጆቻቸው እምብዛም ፍቅር ሳያገኙ እድገው እኔን በፍቅር በማሳደጋቸው፣ በወጣትነት ዘመኔ ከጎኔ በመሆን በግሩም ምክር በመደገፋቸው እና ላሳዩኝ የቤተሰብ ምሳሌነት ይህን መጽሐፍ ለውድ ወላጆቼ

ለአቶ በከሬ ቱሊ ኩምሳ
እና
ለወ/ሮ አዊኔ ቱሶ አባጋሮ

ማስታወሻነት አበረክታለሁ!

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RPRP- 38 3M

## ማውጫ


መግቢያ ———————————————————— 5

ምዕራፍ 1፡ የማማከር መሠረታዊ ግንዛቤ ---------------------------- 7
1.1. ማማከር ምንድነው?
1.2. መጽሐፍ ቅዱስ ስለማማከር ምን ይላል?
1.3. የማማከር አስፈላጊነት
1.4. የማማከር ዓላማዎች

ምዕራፍ 2፡ የሥነልቦና አማካሪ ባሕርያት ----------------------------32
2.1. የሥነልቦና አማካሪ ማን ነው?
2.2. የመልካም አማካሪ ባሕርያት
2.3. አማካሪ ስለራሱ ማወቅ የሚገባቸው ነገሮች

ምዕራፍ 3፡ የማማከር ሂደት ----------------------------------------51
3.1. የማማከር ሂደት ምንድነው ?
3.2. ሰዎች ስለማማከር አገልግሎት እንዴት ያውቃሉ ?
3.3. ማማከር የሚሰጥበት ቦታ
3.4. የማማከር አገልግሎት በምን ጊዜ ይሰጣል?
3.5. ማማከር ለምን ያህል ሰዓት ይሰጣል?
3.6. የማማከር አገልግሎት ለምን ያህል ጊዜ ይሰጣል?
3.7. ሰላምታ መለዋወጥ
3.8. ከምክር ፈላጊዎች ጋር ግንኙነትን መገንባት
3.9. የምክር ፈላጊዎችን መሠረታዊ መረጃዎችን መሰብሰብ
3.10. በጋራ የማማከር እቅድ ማውጣት
3.11. የምክር ፈላጊዎችን ችግር በጥልቀት በማሰስ መፍትሔ መፈለግ
3.12. የማማከር ውይይትን መደምደም

ምዕራፍ 4 ፡ የማማከር ዘዴዎች ---------------------------------- 70

ምዕራፍ 5 ፡ የማማከር ሥነምግባራት ------------------------------85

ምዕራፍ 6 ፡ ወጣቶችን ማማከር ---------------------------- 91
6.1. ወጣቶች አነማን ናቸው?
6.2. የወጣትነት ዘመን ልዩ ባሕርያት
6.3. ወጣቶች ምን ዓይነት አማካሪ ይፈልጋሉ?

ምዕራፍ 7 ፡ የጋብቻ ችግሮችን ማማከር ----------------------------103

7.1. የጋብቻ ችግሮችን ለይቶ ማውጣት
7.2. የጋብቻ ችግሮችን ለማማከር የሚረዱ አሳቦች

ዋቢ መጻሕፍት -----------------------------------------------132




## መግቢያ

እያንዳንዱ ሰው በዚህ ዓለም በሚኖርበት ጊዜ የራሱ የሆነ ችግር አለው፡፡ ዓይነቱና መጠኑ ይለያይ እንጂ ችግር የማያጋጥመው ሰው የለም፡፡ የአንዳንዱ ችግር ለሰው ልጅ የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ ፍላጎቶች እንደ ምግብ፣ ልብስና መጠለያ የማጣት ችግር ነው፡፡ የአንዳንዱ ደግሞ ለሰራስ ደህንነትና ዋስትና ማጣት ነው፡፡ ሌሎች ችግሮች ደግሞ ተገቢ ማሕበራዊ ግንኙነት መመሥረት ወይም መጠበቅ ካለመቻል የሚመጣ የብቸኝነትና የፍቅር ማጣት ችግሮች ናቸው፡፡ እንዲሁም አንዳንድ ችግሮች ደግሞ ሰው የሚፈልገውን ዓይነት ሰው እንዳይሆን የሚያጋጥሙ ናቸው፡፡ መቼም የችግር ዓይነትና መንስኤዎቹ ብዙ በመሆናቸው ሁሉንም መጥቀስ የሚቻል አይደለም፡፡

ለአንዳንድ ችግር መፍትሔ ለማግኘት ጓደኛን እናማክራለን፡፡ ሌሎች ምስጢራዊ የሚሆኑትን ችግሮችን ደግሞ ለማንም ሳንናገር ተሸክመን እንዞራለን፡፡ ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ ማግኘት ካልቻልን ውስው አድረው ሌሎች ችግሮችን ይወልዳሉ፡፡ አንድ ችግር ሌላውን ችግር እየወለደ ሲሄድ በመጀመሪያ ቀላል የነበረው ችግር ውስብስብ እየሆነ ይሄዳል፡፡ ይህ እንዳይሆን መፍትሔ ለማግኘት የሚያግዘውን የማማከር አገልግሎትን ማግኘት ነው፡፡ የማማከር አገልግሎት፣ ምክር ፈላጊ በነጻነት ችግሩን መናገርና ከአማካሪው ጋር በመሆን ለችግሩ መፍትሔ የሚፈልግበት ሂደት ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ምክር ፈላጊው ለችግሩ መፍትሔ ማግኘት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጠውን እምቅ ችሎታ በመጠቀም በሕይወቱ ስኬታማ ለመሆን የሚረዳውን ግንዛቤ ያገኛል፡፡

በማማከር አገልግሎት ላይ የተሰማሩ አገልጋዮች ምክር ፈላጊዎችን በሚገባ ለማገልገል ስለማማከር አገልግሎት ማወቅ የሚገባቸው መሠረታዊ ነገሮች አሉ፡፡ ይህ «ምክር ፈላጊዎችን እንዴት እናማክር?» የሚለው መጽሐፍ በማማከር አገልግሎት የተሰማሩ አገልጋዮች ሊያውቁ የሚገባቸውን መሠረታዊ የማማከር ጽንሰ ሃሳቦችን ይዟል፡፡ በተጨማሪም አገልጋዮች እንደ አማካሪዎች ሊኖሩአቸው የሚገባቸውን መልካም ባሕርያትን፣ ማማከር ከየት ጀምሮ የት እንደሚያበቃ እንዲሁም ምክር ፈላጊዎች ራሳቸውን ሊገልጹ የሚችሉባቸውን መንገዶች ያብራራል፡፡ አማካሪዎች በማማከር ሂደት ውስጥ የሚጠቀሙባቸው የማማከር ዘዴዎችና ስልቶችም ተጠቅሰዋል፡፡

አማካሪዎች የማማከር አገልግሎትን እንዴት መስጠት እንደሚችሉ ለማሳየት ወጣቶችንና የጋብቻ ችግር ያለባቸውን ሰዎች እንዴት ማማከር እንደሚቻል ምሳሌዎችን ያቀርባል፡፡ በመጨረሻም አማካሪዎች በማማከር አገልግሎት ውስጥ መከተል ወይም ማክበር የሚገባቸው መሠረታዊ ሥነምግባራት ተጠቅሰዋል፡፡

እንግዲህ በአገራችን በማማከር አገልግሎት መስክ ያለውን የመጽሐፍ እጥረት እንደሚቀርፍ በማሰብ ከትምህርትና ከአገልግሎት ልምድ የተገኙትን ሃሳቦች በማከል ይህን መጽሐፍ ለማቅረብ ተሞክሯል።

ይህ ሁለተኛው እትም ታርሞና ተሻሽሎ የወጣ ሲሆን ከመጀመሪያው በብዙ መልኩ የተለየ ነው። ስለመጽሐፉ አስተያየት ወይም ጥያቄ ቢኖራችሁ በመልዕክት ሳጥን ቁጥር 121174 አዲስ አበባ ብላችሁ መጻፍ የምትችሉ መሆኑን በደስታ አገልጻለሁ።

ከበደ በከሬ
2001 ዓ.ም.



# ምዕራፍ 1

## የማማከር መሠረታዊ ግንዛቤ

### *1.1. ማማከር ምንድነው?*

ማማከር፣ ከሥነልቦና የትምህርት መስኮች ውስጥ አንዱ ሲሆን ትኩረት ያደረገው በተለያየ ዓይነት ችግር ውስጥ ያሉ ሰዎች ችግሮቻቸውን ማሸነፍና ጤናማ የሆነ ሕይወት መምራት እንዲችሉ መርዳት ላይ ነው። ማማከር፣ በብዙ የሥነልቦና ባለሙያዎች እና በተለያዩ ጸሐፊዎች በተለያየ ሁኔታ የሚተረጎም ቢሆንም መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ግን ተመሳሳይነት ይታያል። የማማከር ትርጉሞች መብዛትና በአተረጓጎም መጠነኛ ልዩነቶች መኖር ከጸሐፊዎቹ አመለካከትና ከሥነልቦና ጽንሰ-ሐሳብ የመነጨ ነው። እያንዳንዱ ባለሙያ ማማከርን ከተለያየ አቅጣጫ በመመልከቱ ልዩነቶች ሲፈጠሩ ችለዋል።

ከኮሌጅ ተማሪዎች ጋር በነበረኝ የማስተማር ቆይታ ብዙ አገልጋዮች ማማከር የሚለውን ሃሳብ ለምክር ፈላጊዎች ችግር ወዲያውኑ መፍትሔ መስጠት እንደሆነ ያስባሉ። በእነርሱ አይታ ምክር ፈላጊዎች ችግር ይዘው ሲመጡ አማካሪው ደግሞ መፍትሔ ይሰጣቸዋል። ለችግሮች ሁሉ መፍትሔ የሚሆነው ነገር ከአማካሪው ዘንድ እንደሚገኝ አድርገው ይመለከቱታል። አንድ ሰው ልብስ የሚፈልግ ከሆነ ወደ ሱቅ ሄዶ የተዘጋጁትን ልብሶች ገዝቶ እንደሚሄድ ዓይነት ነው። ምክር ፈላጊው ከአማካሪው መፍትሔ እንደሚያገኝ ጠብቆ ይመጣል፤ አማካሪው «መፍትሔውን» የሚሰጥበት ሂደት እንደሆነ ይታሰባል።

> *«ነጻ ከሆነ ምክር ነው፣*
> *በክፍያ ከሆነ ማማከር ነው፤*
> *ከሁለት አንዱን መጠቀም*
> *ተዓምር ነው»*
>
> *ሻክ አዳምስ*

በዓውዳችሁ ሰዎች ስለማማከር የሚሉትን ነገሮች መጠየቅና ማበተዋል ይቻላል። ስለማማከር አገልግሎት ትክክለኛ ያልሆኑ ግንዛቤዎች ምን እንደሆኑ መለየት ሰዎች ስለማማከር አገልግሎት ሚዛን የጠበቀ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ይረዳል። ከዚህ በታች የተሰጡትን ነጥቦች አበተውል። እነዚህ ሐሳቦች ማማከርን በትክክል ሲገልጹ የሚችሉ ነገሮች ናቸውን?

- √ ማማከር ለምክር ፈላጊዎች ቃለመጠይቅ ማድረግ ነው።
- √ ማማከር የምክር ፈላጊዎችን ችግር ካዳመጡ በኋላ ተገቢውን መፍትሔ መስጠት ነው።
- √ ማማከር ለምክር ፈላጊው ገንቢና ጠቃሚ የሆኑትን ምክሮችን እንዲሁም አዳዲስ መረጃዎችን መስጠት ነው።
- √ ማማከር በተዘዋዋሪ መንገድ ማለትም ምክር ፈላጊው በሚገባ ሳያስተውል በጥበብ በመጠቀም ምንም ጉዳት በማያስከትል

ሁኔታ የአመለካከት፣ የአስተሳሰብና የባሕርይ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ ነው።

- √ ማማከር ምክር ፈላጊው ሥርዓት ያለው ሕይወት እንዲኖር የመግራት ስልት ነው።
- √ ማማከር ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ሐሳብ ለምክር ፈላጊው ማቃበል ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ነገሮች ስየብቻቸው ማማከርን በሙሳት መግለጽ ባይችሉም ማማከርን ለመግለጽ ሲረዱ የሚችሉ ሐሳቦች ናቸው። ለምሳሌ ያህል ማማከር ቃለመጠይቅ ማድረግ ነው የሚለው ሐሳብ እውነትነት አለው። በማማከር አገልግሎት ውስጥ አማካሪ ጥያቄዎችን ይጠይቃል። ሂደቱ ግን ጥያቄ ከመጠየቅ የጠለቀ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ ከሚታዩ ክንውኖች መካከል አንዱ ጥያቄ መጠየቅ ይሆናል፡፡ አንድ ከስተት ብቻ በሆነ ሐሳብ ማማከርን መተርጎም ሙሉ እይታን አይሰጥም።

> *«ምክር ትንሽ ተንቀሳቃሽ ሣንቲም ነው»*
> *አምብሮስ ቢአርስ*

ማማከር ጓደኞች ከሚኖራቸው ውይይትም የተለየ ነው። ወዳጃሞች አብረው በሚሆኑበት ጊዜ ስለችግሮቻቸው ይነጋገራሉ። በዚህ የውይይት ሂደት ውስጥ ለችግሮቻቸው መፍትሔዎችን ማግኘት ይችላሉ። ሆኖም ለችግር መፍትሔ የሚገኝበት ማንኛውም ግንኙነት የማማከር አገልግሎት ላይሆን ይችላል። በጓደኞች ውይይት ውስጥ በሁኔታዎች በስሜት የመወሰድ ሁኔታ ይታያል፡፡ በውይይቱ ጊዜ አንዱ በሌላው ችግር የተሰማውን ስሜት እንደ ልቡ የመግለጽና በሚቻለው አቅሙ ሁሉ ለመርዳት ዝግጁነቱን ሲያሳይ ይችላል። በዚህ ሂደት ውስጥ የሚኖረው ወሰን ግልጽ አይደለም። በማማከር ሂደት አማካሪው፣ ምክር ፈላጊው ለራሱ ችግር መፍትሔ እንዲፈልግ ያግዛል እንጂ ችግሩን እንደ ግል ችግሩ በማየት ኃላፊነት አይወስድም።

በጓደኞች ውይይት ሁለቱም እኩል የመጠቀም ሁኔታ ይታያል። በማማከር አገልግሎት ውስጥ በዋነኛነት የሚጠቀመው ምክር ፈላጊው ነው። አማካሪው በግንኙነቱ ውስጥ የገባው ምክር ፈላጊውን ለመርዳት ነው እንጂ ለግል ጥቅሙ አይደለም። ከዚህም በተጨማሪ በማማከር ውስጥ ምክር ፈላጊው ችግሩን ለአማካሪው ይነግራል እንጂ አማካሪው ችግር ቢኖረውም እንኳ ለምክር ፈላጊው አይነግረውም።

የጓደኝነት ግንኙነት በዘላቂነት ወይም ሳልተወሰነ ጊዜ ሊቆይ የሚችል ሲሆን የማማከር ግንኙነት ግን ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ነው። የአማካሪና የምክር ፈላጊ ግንኙነት የሚኖረው ምክር ፈላጊው ለችግሩ መፍትሔ እስኪያገኝ ድረስ ነው። የማማከር ግንኙነት ምክር ፈላጊው ለችግሮቹ መፍትሔ አግኝቶ ግንኙነቱ እንደማያስፈልገው ሲለማው ወይም መፍትሔም ባይገኝ ግንኙነቱ የሚፈለገውን ውጤት ማስገኘት የማይችል እንደሆነ ሲታወቅም ይቋረጣል።



*በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ማማከር የሚለው ሐሳብ የእግዚአብሔርን ቃል ማዕከል በማድረግ የተለያዩ ገንቢ የሆኑ ዘዴዎችን በመጠቀም ምክር ፈላጊው በሂደት ስለችግሩና መንስኤዎቹ በቂ ግንዛቤ በማግኘት ትክክለኛውን መፍትሔ ወደ ማግኘት እንዲደርስ የሙያ/የአገልግሎት/ ብቃት ባለው ባለሙያ/አገልጋይ/ ምስጢር በጠበቀ ሁኔታ የሚሰጥ አገልግሎት ነው።*

ከላይ በተጠቀሰው ገለጻ ውስጥ ስለማማከር የተጠቀሱ ብዙ ፍሬ ሐሳቦች አሉ። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡-

*ማማከር የሁለትዮሽ ግንኙነት ነው፡-* በዚህ ግንኙነት ውስጥ ሁለት ሰዎች ይገኛሉ። እነርሱም አማካሪውና ምክር ፈላጊው ናቸው። አማካሪ የተባለው ሰው ስለማማከር አገልግሎት ብቃት ያለው ባለሙያ ወይም አገልጋይ ሲሆን ምክር ፈላጊ ደግሞ በሕይወት ጎዳና ላይ በገጠመው ችግር ወደፊት መሄድ አቅቶት እገዛ ፍለጋ ወይም አሁን ካለበት ፍሬያማነት ወደ ተሻለ ስኬት ለመሸጋገር ምክር ፈልጎ የሚመጣ ሰው ነው። ምክር ፈላጊው በራሱ ፈቃድ ወደ ማማከር አገልግሎት መምጣት አለበት ወይም አገልግሎቱን ለመቀበል ፈቃደኝነት መኖርና መግለጽ አለበት። በሁለቱም መካከል ተገቢው ውይይት ይደረጋል፣ መፍትሔም ይፈለጋል እንዲሁም ግንኙነቱም በመከባበር ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

*ማማከር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፡-* በአማካሪውና ምክር ፈላጊው መካከል ባለው ግንኙነት አማካሪው ለምክር ፈላጊው መፍትሔ ሰጪ ሳይሆን ምክር ፈላጊው የችግሩን ትክክለኛ ምንነትና መንስኤዎቹን በትክክል በመረዳት መፍትሔውን መፈለግ እንዲችል ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው። ለችግሩ መፍትሔ የሚፈልገውና የሚያገኘው ምክር ፈላጊው ሲሆን አማካሪው በዚህ ሂደት አብሮት በመጓዝ የሚረዳው ሰው ይሆናል። ይህ ሐሳብ ምክር ፈላጊው የራሱን ችግር መረዳትና መፍታት የሚያስችለው አምቅ ችሎታ እንዳለው ያሳያል። ስለዚህ ማማከር ምክር ፈላጊው በእጁ ባለው አምቅ ችሎታ በመጠቀም ከሕይወት ጋር በተሻለ ሁኔታ ትግል ማድረግ እንዲችል ሙያዊ እገዛ መስጠት ነው።

*ማማከር የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል፡-* አማካሪ ምክር ፈላጊውን በሚረዳበት ወቅት የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል። እነዚህ ዘዴዎች ምክር ፈላጊው ችግሩን እንዲረዳ እንዲሁም እንዲፈታው የሚያግዙ ሲሆኑ በይዘታቸውና በአቀራረባቸው ሥነምግባርን የጠበቁ መሆን ይገባቸዋል። የማማከር ዘዴዎች ከምክር ፈላጊው ችግርና ዓውድ ጋር የሚጣጣሙ ሲሆኑ ይገባቸዋል።

*ማማከር አገልግሎት ነው፡-* በችግር ውስጥ ያለውን ሰው ወደ መልካም ሁኔታ የማውጣት ወይም አንድ ሰው የተሻለ ፍሬያማ እንዲሆን የሚያግዝ ሥራ ነው። ይህ ለጥቅም ተብሎ የሚሰጥ ሳይሆን ሌላውን ሰው ለመርዳት ከሚመነጭ በጎ አሳብ ነው። አገልግሎት ያለኘውም በአብዛኛው ተመጣጣኝ የሆነ ብድራት ሳይጠበቅ ለሌላው ሰው ጊዜ፣ እውቀት፣ ጉልበትና ሙያዊ

መስጠት ማሰት ምክር ፈላጊው በራሱ ነጻ ምርጫ እንዲወስን ያደርገዋል። በዚህ ዓይነት ሂደት ሰተወሰነ ሐሳብ የሚኖረው መሰጠት ከፍተኛ ይሆናል።

ሙሴ ምንም ያህል የእግዚአብሔር ሰው ቢሆንም ድክመት ነበረው። ድከመቱን ሰማረም የሚያስችለውን ምክር ሲያገኝ ተቀበሰው፣ ተግባራዊም አደረገ፣ ችግሩም ተፈታ። የአማካሪው አቀራረብም ሰዚህ እስተዋጽኦ አድርጎሰታል። ይህ የማማከር አገልግሎት ሰትልልቅ የሃይማኖት መሪዎች፣ አገልጋዮች፣ መንፈሳዊ ሰዎችና የሕዝብ መሪዎች ጭምር አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል። ሰዎች ምንም ያህል እውቀት፣ ከፍተኛ ሥራና እምነት ቢኖራቸውም ፍጹማን ባሰመሆናቸው ምክር ያሻቸዋል።

***ኢዮብና ጓደኞቹ***- ኢዮብ በመንፈሳዊ ሕይወቱ በእግዚአብሔር ፊት የተመሰከረሰት ሰው ነበር። በሕይወቱ የተሰያዩ ፈተናዎች ቢፈራረቁበትም በእምነቱ ጸንቶ መቆም የቻለ ሰው ነበር። ኢዮብ በመከራ ውስጥ በነበረበት ወቅት ወዳጆቹ እርሱን ሰማጽናናት መጡ። እነዚህ ጓደኞቹ ወደ እርሱ በመጡበት ጊዜ «ሰሰባት ቀንና ሌሊትም ከእርሱ ጋር በምድር ላይ ተቀመጡ፣ ሕመሙም እጅግ እንደበዛ አይተዋልና ከእነርሱ አንድ ቃል የሚናገረው አልነበረም» (ኢዮ2:13)። በመጀመሪያ ሁሉም በዝምታ የተዋጡ ነበር። ምክንያቱም ኢዮብ የነበረበት ሁኔታ እጅግ አሰቃቂ በመሆኑ ነበር።

እነዚህ አማካሪዎች በኢዮብ ዓውድ ውስጥ በመግባት ከእርሱ ጋር በምድር ላይ ተቀመጡ። ራሳቸውን እርሱ ወዳሰበት ሁኔታ አወረዱ። በዚህ ድርጊታቸውም እርሱን ሰመርዳት ያላቸውን ዝግጁነት ገለጡ። ኢዮብ የሚናገር ነገር ካሰው ሰማዳመጥ የተዘጋጁ መሆናቸውን ገለጹሰት። ኢዮብም ይህን ሰሰተረዳ በውስጡ የተሰማውን ስሜት መግለጽ ጀመረ። በውስጡ የታመቀው ስሜት መርዛማ ነበር። ኢዮብ በመርገም ቃላት የተሞላ ነበር (ኢዮ3:1)።

የኢዮብ አማካሪዎች የእርሱን መከራና ስቃይ የተረዱበት መንገድ መንፈሳዊ ማስተዋል የጎደለው ነበር። እነርሱ እንደ ኢዮብ ሰእግዚአብሔር ቅን የሆነ ነገር ባሰመናገራቸው የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ላይ ነዶ ነበር (ኢዮ42:7)። ሆኖም የእነርሱ በስቃዩ ጊዜ ከእርሱ ጋር መገኘት ኢዮብ በውስጡ የተሰማውን ስሜት በሚገባ እንዲገልጽ ረድቶታል። በኢዮብ ሁኔታ ተገኝተው የእርሱ ስቃይ ሰመረዳት ጥረት ማድረጋቸው የሚደነቅ ነው። ኢዮብ መናገር ሲጀምርም ዝም ብሰው በትኩረት ሲያዳምጡና እንደ እስፈላጊነቱ ደግሞ የራሳቸውንም ግንዛቤ ሲናገሩ ነበር። በኢዮብ ላይ የደረሰው ችግር መንስኤው ምን እንደሆነ ከራሳቸው ልምምድ እንጻር ተመለከቱ (ኢዮ4:8)። በዚህ ችግር ውስጥ ኢዮብ ሊማረው የሚገባው የእግዚእብሔር ሐሳብ ይኖር እንደሆነ በማሰብ አስሳ ሰማድረግ ሲነሱ አይታዩም።

በተሰያየ ችግር ውስጥ ገብተው ከተቸገሩ ሰዎች ዘንድ መገኘት በራሱ በቃላት ተናግሮ ከማጽናናት የሚሻልበት ወቅት አሰ። እንዳንድ አማካሪዎች የማማከር ብቃት ቢኖራቸውም የእግዚእብሔርን ሐሳብ ሊስቱ ይችላሉ።



የማማከር ዘዴዎችንና ሰልቶችን ማወቅ ብቻውን መልካም መንፈሳዊ አማካሪ ላያደርግ ይችላል።

***ሳኦልና ዳዊት***- ንጉሥ ሳእል በስሜት መሰሳቸት ወይም በትካዜ የተያዘ ሰው ነበር። ይህም የሰሜት መውደቅ የመጣበት የእግዚአብሔር መንፈስ ሰሰተለየውና ክፉ መንፈስ ሰለገባበት ነበር። ከዚህም የተነሣ እንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ሰመግደል ይነሳሳል። በትካዜ መንፈስ ሰተያዘው ንጉሥ ሳእል አማካሪ ሆኖ የቀረበው ዳዊት ነበር። ዳዊት ሙዚቃን በመጠቀም ንጉሡን ያጽናናው ነበር። ይህ የዳዊት የማማከር ዘዴ ሰንጉሥ ሳኦል በሚገባ ጠቅሞት ነበር (1ሳሙ16:23፣18:10)።

የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ቢሆንም ሳእል *አማካሪው* ሆኖ ከቀረበው ከዳዊት ጋር የነበረው ግንኙነት መልካም እልነበረም። ሳእል እንደ ምክር ፈሳጊ የራሱን ችግር አማካሪው ያመጣበት እንደሆነ በማሰብ እርሱን ሰመግደል ሙከራ ያደርግ ነበር። ዳዊት ግን እንደ መልካም አማካሪ ምክር ፈላጊውን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እስከ መጨረሻው ድረስ ተቀበሰው። የምክር ፈሳጊውን ችግር በሚገባ ሰሰተረዳ ምክር ፈላጊውን በምንም መልኩ መጉዳት ወይም መበቀል አልፈሰገም።

ምክር ፈላጊ፣ አማካሪውን ሰመጉዳት የሚያሰብበት ሁኔታ ቢኖር እንኳ አማካሪ በእርሱ ላይ የጥቃት እጸፋ ሰመውሰድ ማሰብ የሰበትም። ምክር ፈሳጊው አማካሪውን ሰማጥቃት እንዲነሳሳ የሚያደርገው የራሱ ችግር ነው እንጂ አማካሪውን ሆን ብሎ ሰመጉዳት አስቦ ላይሆን ይችላል። ስለዚህ የምክር ፈሳጊውን እርምጃ እንደ ግል ጥቃት በመውሰድ ሰመበቀል ማሰብ አያስፈልግም።

ዳዊት ጎልያድ የሚባሰውን ጠላት በመግደሉ በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትና አክብሮት በማግኘቱ ሳኦል ቅር ተሰኝቶበት ነበር። እንደ አማካሪ ከምክር ፈሳጊው ጋር ከማማከር ግንኙነት ውጭ የሚገናኝበት ሁኔታ ካሰው ይህን ሰው ማማከር የሰበትም። የፍላጎት ግጭት ሰሰሚያጋጥም ግንኙነቱን ሚዛናዊነት ባሰው ሁኔታ ሰማካሄድ ያዳግታል። በውጭ ያላቸው ግንኙነት ወደ ማማከር እገልግሎት አብሮአቸው ይመጣል።

በማማከር ሂደት የተለያዩ ዓይነት ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል። አማካሪ ከምክር ፈሳጊዎች ችግር ጋር የሚጣጣም ዘዴን በመጠቀም ሊረዳቸው ይችላል። ዳዊት በገና በመጠቀም ሰሳእል የሰጠው አገልግሎት እረፍት ይሰጠው ነበር። ሙዚቃ መጫወት በራሱ እንድ የማማከር ስልት ነው። ይህ በተፈጥሮ ሰዎችን የማነቃቃት ኃይል ስላሰው በመንፈስ መውደቅ ውስጥ ሰገቡት ወይም በጭንቀት መንፈስ ሰተያዙት ሰዎች እረፍትን ይሰጣቸዋል። አማካሪው እንዲህ ዓይነት ችግር ያላቸው ምክር ፈላጊዎች ሙዚቃ ማዳመጥ የሚችሉበት ሁኔታ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻችላቸዋል።

አንዳንድ ምክር ፈላጊዎች አማካሪው ላይ አደጋ ሊያደርሱ ስለሚችሉ አስፈላጊው የደህንነት ዋስትና መኖሩን አስቀድሞ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በተለይ ምክር ፈላጊዎች የአእምሮ መታወክ ወይም የፀረ-ማሕበራዊ ስብእና እንዳላቸው የሚያሳዩ ምልክቶች ወይም መረጃዎች በሚኖሩበት ጊዜ ለአደጋ ሊያጋልጥ ከሚችል ሥፍራና ግንኙነት ራስን መጠበቅ ተገቢ ነው።

*ዮሴፍና ፈርዖን*፦ ዮሴፍ ባላጠፋው ጥፋት በእስር ቤት እንዲታሰር ያደረገው የፈሪዖን አገልጋይ ነበር። በዚህ ወቅት ደግሞ ፈሪዖን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ገብቷል። ሕልም አይቶ ሕልሙን ግን ሊፈታለት የቻለ ሰው አልነበረም። ዮሴፍ ሕልሙን እንዲፈታለት በተጠየቀ ጊዜ ፈቃደኛ ነበር። ሕልሙን መፍታት ብቻም ሳይሆን የሕልሙን ፍቺ ተግባራዊ ለማድረግ ማለትም በግብጽ ምድር ሊመጣ ካለው ረሃብ ለመዳን መወሰድ የሚገባቸውን ጠቃሚ እርምጃዎችንም ሰንጉሡ መከረው። ግብጻውያን በእርሱ ላይ ያደረሱትን በደል በመቁጠር ለእነዚህ ሰዎች በጎ የሆነውን ነገር አልመክርም ብሎ አላሰበም። በቅንነት መልካም የሆነውን ምክር በለመከረው ንጉሡ፣ ዮሴፍ ራሱ ኃላፊነት ወስዶ ሥራውን እንዲሠራ በግብጽ ምድር ላይ ሾመው (ዘፍ41:33-36)።

ዮሲፍ ይህን ዓይነት ምክር ሊሰጥ በልበ ሙሉነት ይናገር ነበር። በዚህም የምናገረውን ነገር የሚያውቅ እንዲሁም ድፍረት ያለው ሰው መሆኑን ገለጸ። በምክር ይዘቱ ውስጥ የመምራትና ማስተዳደር ስጦታ ያለው መሆኑም ተንጸባርቋል። እንዲህ ዓይነት መጥፎ ዜናን ለንጉሥ መናገር የሚያስፈራ ቢሆንም ዮሴፍ ችግሩን ብቻ ሳይሆን ለችግሩ መፍትሔ ሊሆን የሚችለውንም ሐሳብ ይዞ ነበር። በአገር ደረጃ ሊመጣ የሚችለውን ቀውስ መፍታት የሚቻልበትን የመፍትሔ ሐሳብ በማቅረቡ በምክር ፈላጊው ዘንድ የነበረው ተቀባይነት ከፍ ያለ ሆነ። ከዚህም የተነሣ ምክር ፈላጊ የነበረው ንጉሥ የዮሴፍን ሐሳብ ተቀበለ።

ምክር ፈላጊዎች የአማካሪን ምክር ለመቀበል ስለእርሱ ማንነትና የምክሩን ይዘት ብስለትና አዋጪነትን ይመለከታሉ። በተለይ ከዚህ በፊት ብዙ አማራጭ መንገዶችን በራሳቸው ወይም ከሌሎች ሰዎች አግኝተው ሞክረው ያልተሳካላቸው ሊሆንና አሁን ያገኙት ደግሞ በፊት ከሰሙትና ካዩት ነገር የተሻለ ሆኖ ሲያገኙት የመቀበልና ተግባራዊ የማድረግ ዕድላቸው ከፍ ይላል።

መልካም አማካሪ ለምክር ፈላጊዎች መስጠት የሚችለውን ጠቃሚ ምክር ያለፈውን በደል በመቁጠር አይከለክልም። ለምክር ፈላጊዎች ይጠቅማል የሚባለውን ነገር ባለመስጠት ለመበቀል ማሰብ የአማካሪ ባሕርይ አይደለም። እነዚያ ምክር ፈላጊዎች ወይም ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ከፉ በደል ያደረሱበት ቢሆንም አማካሪ ማድረግ የሚገባውን መልካም ነገር ከመፈጸም አይመለስም። አማካሪ ቂመኛ አይደለም።

*ሽማግሌዎችና ሮብዓም*፦ ሮብዓም የሚባል የሰሎሞን ልጅ አባቱ ከሞተ በኋላ በእርሱ ፈንታ በእስራኤል ላይ ነገሠ። እርሱ ከነገሠ በኋላ ሕዝቡ ወደ



እርሱ በመምጣት በአባቱ ዘመን ብዙ ይጨነቁና ይበዘበዙ እንደነበር በመግለጽ አስተዳደራዊ ማሻሻያዎች እንዲደረጉላቸው ጠየቁ። ንጉሥ ሮብዓምም ገና ወደ ሥልጣን የመጣ በመሆኑ ምን ይመልስላቸው እንደሚገባ አላወቀም። ከዚያም ለሕዝቡ ቀጠሮ ሰጠና ራሱ ምክር ለመጠየቅ በአባቱ ዘመን አማካሪዎች ወደነበሩ ሽማግሊዎች ሄደ። እነርሱም ንጉሡ ሮብዓም ማድረግ የሚገባውን መልካም ነገር ነገሩት። የምክራቸው ዋና መልዕክት ንጉሡ ሕዝቡን በትሕትና መምራት፣ በመገዛት መግዛት እንዲሁም ሕዝቡ የሚፈልገውን ነገር ማድረግ እንደሚገባው የሚያሳስቡ ናቸው። እነዚህ አማካሪዎች ከነገሥታት ሁሉ በላይ ጠቢብ የነበረውን አባቱን ሲመክሩ የነበሩ በመሆናቸው ካላቸው እውቀትና ልምድ በመነሳት የተሻለ የተባለውን ምክር መከሩት (1ነገ12:6-9)።

ንጉሡ ሮብዓም መልካም ምክር ቢያገኝም ያገኘውን ምክር ተቀብሎ ተግባራዊ ለማድረግ ግን ፈቃደኛ አልነበረም። የሽማግሌዎቹ ምክር ከእርሱ የአመራር ፍልስፍና ጋር የሚጣጣም ሆኖ አላገኘውም ነበር። ስለዚህ የእነርሱን በመተው ጓደኞቹን አማከረ። ጓደኞቹ ደግሞ እርሱ የሚፈልገውን ዓይነት ምክር መከሩት (1ነገ12:10-11)። ከዚህ በፊት ከደረሰባቸው በደል የበለጠ እንደሚፈጽምባቸው ለሕዝቡ ሲናገር ሕዝቡ ከእርሱ ተከፍሎ ሌላ መንግሥት መሠረተ።

አማካሪ ይመክራል እንጂ በምክር ፈላጊው ሥፍራ ሆኖ ምክሩን ተግባራዊ አያደርግም። መልካም ምክር ተቀብሎ የማይተገብር ሰው አደጋ ላይ ይወድቃል። «ምክረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው» እንደሚባለው ይሆናል።

በአማካሪና በምክር ፈላጊዎች መካከል የትውልድ ክፍተት ሲኖር የአስተሳሰብ ልዩነትም ይኖራል። ስለዚህ አማካሪው በተቻለ መጠን በማማከር ግንኙነት ውስጥ ክፍተቱን ለማጥበብ ራሱን በምክር ፈላጊዎቹ ዓውድ ውስጥ ለማስገባት ጥረት ቢያደርግ ወደ ተገቢው አቅጣጫ ስመምራት ያግዘዋል።

ምክር ፈላጊዎች ወደ አንድ አማካሪ በሚመጡበት ጊዜ ከሌሎች የተለያዩ አማካሪዎች ጋር ግንኙነት ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ ሊሆን ይችላል፣ ወይም ከአንድ አማካሪ ጋር ግንኙነታቸውን ከጨረሱ በኋላ ወደ ሌላ አማካሪ ሊሄዱ ወይም በአንድ ጊዜ ከሁለት የተለያዩ አማካሪዎች ጋር ግንኙነት ሊያደርጉ እንደሚችሉ ማሰብ ያስፈልጋል። የአንዱን አማካሪ ሐሳብ ከሌሎቹ ጋር ያነጻጽሩና ጥሩ ነው ብሰው የሚያስቡትን ወይም የማረካቸውን አሳብ ይቀበላሉ። ስለዚህ እነርሱን ከመርዳት አንጻር አንድ አማካሪ ሌሎች አማካሪዎች ሊመክሩት ይችላሉ ብሎ የሚያስባቸውን አቅጣጫዎች በግንኙነቱ ውስጥ ማንሳቱ ጠቃሚ ይሆናል።

*የኢየሱስ ምሳሌነት*፦ በወንጌላት ታሪክ ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ከተለያዩ ሰዎች ጋር በነበረው ግንኙነት የአንድ መልካም አማካሪ ባሕርያትን አሳይቷል። እርሱ የወንጌል አስተማሪና ሰባኪ ነበር። እንደ አንድ

የአገልግሎት መበኩም ለሰዎች ችግር ትኩረት በመስጠት የሚያዳምጥ ልብ ነበረው። ሰዎች ወደ እርሱ ለርዳታ ሲጮኹ ይሰማቸዋል (ማር10:49)። ኢየሱስ ያሳየው መልካም የማማከር ባሕርይ ሁሉንም ሰው ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ መቀበል ነው። ሰዎች የሚያደርጉትን ድርጊት ሳያጸድቅ ወይም ሳይኮንን በመጀመሪያ ሰዎቹን ወደ ራሱ ያቀርባቸዋል። ሰዎቹን ከተቀበለና ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ከመሠረተ በኋላ ድርጊታቸውንና ማንነታቸውን እንዲያዩ እንደ መስታወት ይሆንላቸዋል።

ሰዎችን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ከመቀበሉ የተነሣ ወደ ሃይማኖት አስተማሪዎች ለመቅረብ የሚፈሩት ኃጢአተኞች ወደ እርሱ መቅረብን አልፈሩም። ይህን የተመለከቱ ሰዎችም ኢየሱስ እርሱ የኃጢአተኞች ወዳጅ ነው የሚል ስም ሰጡት (ማቴ9:10-13)። ኢየሱስ ሰዎችን ከድርጊታቸው ለይቶ የማየት ችሎታ ነበረው። ሰዎች አስፈላጊውን ምክር ቢያገኙ የሚሠሩትን ክፉ ሥራ በመተው መልካም ነገር ማድረግ እንደሚችሉ ያምን ነበር። በታመነዝር ተገኝታለች ተብላ ተከሳ ወደ እርሱ የቀረበችውን ሴት ኢየሱስ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ተቀበላት። ከሳሾቿ የጠበቁት እርሱ እንዲፈርድባት ነበር። ሆኖም ኢየሱስ ሰዎቹ ራሳቸውን መመልከት የሚችሉበትን ዓውድ ፈጠረላቸው። እነርሱም እንደ እርሷ ኃጢአተኞች እንደሆኑ እንዲገነዘቡ አደረገ። በእርግጥም ራሳቸውን በሚገባ ሲመለከቱ ከእርስዋ የተለዩ አልነበሩም። ስለዚህ ትተዋት ሄዱ። ኢየሱስም ሴትየዋ ወደፊት እንዲህ ያለውን ኃጢአት እንዳትሠራ በመምከር እንዴት ሕይወትዋን በመልካም መንገድ መምራት እንደሚገባት መክሮ አሰናበታት (ዮሐ8:7-11)።

አማካሪ፣ ሰዎች እንደሚለወጡና ከዛሬ ይልቅ ነገ የተሻለ ሕይወት መኖር እንደሚችሉ ሊያምን ይገባል። የኢየሱስ አሠራር፣ ሰዎችን በፈጸሙት በደል ከመኮነን ይልቅ ስለወደፊት ሕይወታቸው እንዲያስቡና ካለፈው ነገር ተምረው የወደፊቱን ማስተካከል እንዲችሉ መርዳት የተሻለ እንደሆነ ያስገነዝበናል።

*ገማልያልና የጉባኤ መሪዎች*:- በዘመኑ የነበሩ የሃይማኖት መሪዎች የክርስቶስን ወንጌል የሚሰብኩትን ሐዋርያት ለማጥፋት በተለይ ደግሞ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ለመግደል ምክክር ሲያደርጉ በመካከላቸው የነበረው ገማልያል የሚባል ሰው በጣም የሚገርም ምክር ለጉባኤው አባላት መከራቸው (የሐ/ሥ5:35-39)።

> *«የአንድ ምክር መልካምነት የሚታወቀው በዓላማው ሳይሆን በውጤቱ ነው።»*
> ሲሴሮ

ይህ ምክር የመነጨው እርሱ ከሚከተለው የማለዘብ ተግባርና ማንኛ ውንም ነገር ጥቃት በሌለበት መንገድ ማከናወን የተሻለ መሆኑን ከሚያምን አእምሮ ነው። ሰዎች በስሜት በተለይም በቁጣና በንደት ውስጥ ሆነው የሚወስዱት እርምጃ በኋላ ጸጸት የሚያመጣ ጉዳይ መሆኑን በመገንዘቡ እነዚህ ውሳኔ የሚሰጡ ሰዎች ወደ ስህተት እንዳይገቡ መከራቸው። የመጀመሪያ ትኩረቱ የሰዎቹን ስሜት በማብረድ ላይ ነበር (5:34)። ምክር



ፈላጊዎች አሁን ከሚሰማቸው ስሜት እለፍ ብለው ማየት እንዲችሉ፣ እንዲሁም አሁን ከሚገኙበት ስሜት ቢወጡ ትክክለኛ እርምጃ ሊወስዱ እንደሚችሉ እንዲያስቡ ማድረግ የአንድ መልካም አማካሪ ባሕርይ ነው።

የሰዎቹ ስሜት ትንሽ ለከን ሲል አማካሪው ገማልያል ጉዳዩን በምን ሁኔታ ማስተናገድ እንደሚገባቸው ቀና የሆነውን አቅጣጫ አሳያቸው። የሚወስዱትን እርምጃ በመሠረታዊ ምክንያቶች ላይ በመመርኮዝ መውሰድ እንደሚገባቸው ለማሳየት ምክንያቶችን አቀረበ። ምክንያቱን ያቀረበው ሰዎቹ በስከነ መንፈስ ማዳመጥ ከቻሉ በኋላ ነው። በቅድሚያ ስሜት ማርገብ ከዚያም በምክንያቶች ላይ መነጋገር የሚለውን መርህ ተከተለ።

የምክሩ ጥቅል ይዘት «ለስትክክለኛነቱ ጠብቀን እንመልከት» የሚል ነው። አዳዲስ ነገሮችን ለማጥፋት ከመሞከር ትክክለኛ መሆኑንና አለመሆኑን ጊዜ እስኪለይ ድረስ እንታገስ የሚል እይታ አለው። ይህንንም ሐሳቡን ለማጽናት ሁሉም ሰዎች የሚያውቁትን ተጨባጭ ምሳሌዎችን በማንሳት ለማስረዳት ጥረት አድርጓል (የሐ/ሥ5:36-37)። በቆይታ የሚታይ ውጤት መጠበቁ ከመቻቻል አንጻር ጥሩ ነገር ቢኖረውም እንደ አስፈላጊነቱና ዓውዱን ግንዛቤ ውስጥ ባላስገባ ሁኔታ ከተገበረ ጥፋት ሊያስከትል ይችላል። ውሳኔው የሚሰጥበት መሠረታዊ የሆነ ምክንያት በተለይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ካለ ቶሎ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። በገማልያል ሁኔታ ይህ መርህ ተገቢ ነበር።

በእርግጥ ገማልያል የእግዚአብሔር ሰው ስለመሆኑ የተመሰከረለት ነገር ባለመኖሩ ይህን ምክር የመከረው በልቡ ውስጥ ካለው ቅን ሐሳብ የተነሣ እንደሆነ ማሰብ ይቻላል። በእኛ እይታ መንፈሳዊ ያልሆኑ ሰዎችም መልካም ምክር ሲመክሩ እንደሚችሉና በእነርሱም እግዚአብሔር ተጠቅሞ ፈቃዱን ሊገልጥ እንደሚችል ማስታወስ ጠቃሚ ነው። ምክር ፈላጊዎች ከስሜት ባሻገር ያለውን ነገር መመልከት እንዲችሉ ለመርዳት፣ አማካሪ ጥበብ ያለውና ትዕግስተኛ መሆን አለበት።

በማማከር አገልግሎት ታሪኮችን መጠቀም አስፈላጊ የሚሆንበት ወቅት ይኖራል። ምክር ፈላጊዎች የሚያውቁትን ወይም ሊረዱ የሚችሉትና ከእነርሱ ችግር ጋር ግንኙነት ያላቸውን ታሪኮች በመጠቀም ስለራሳቸውና ስላሉበት ሁኔታ ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲረዱ ማድረግ ይቻላል። ይህ ምክር ፈላጊዎች ሁኔታቸውን በመገንዘብ ትክክለኛ የሆነ ውሳኔ መወሰን እንዲችሉና ዐይኖቻቸው ተከፍተው ያሉበትን ዓውድ በተለየ አቅጣጫ እንዲያዩ ያግዛቸዋል። ታሪኮችን በአግባቡ መጠቀም፣ ምክር ፈላጊዎችን «ለካስ እንዲህም ሊሆን ይችላል!» ብለው እንዲያስቡና ወደ ትክክለኛው መረዳትና ውሳኔ እንዲመጡ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች መልካም የማማከር አገልግሎት ምን እንደሆነ የሚያሳዩ ናቸው። የእግዚአብሔርን ቃል ማዕከል በማድረግና ክርስቲያናዊ ሥነምግባርን በጠበቀ መልኩ የተሰጡ ናቸው። ሰዎች የራሳቸውን ችግር ለመፍታት እንዲሁም አማካሪዎችም ጠቃሚ የሆኑትን

ምክሮች ለመምከር የእግዚአብሔር አብሮነት አስፈላጊ መሆኑን ይጠቁማሉ:: ሰዎች ችግሮቻቸውን ለመፍታት የሚያስችል ችሎታና ብቃት እንዳላቸው ቢታመንም የእግዚአብሔር እርዳታ አስፈላጊ መሆኑንና እርሱ ካልታከለበት ዘላቂነት ያለው ውጤት እንደማይገኝ ያስገነዝባሉ:: መልካም የማማከር አገልግሎት ሁለንተናዊ ይዘት አለው:: ሰዎች በመንፈስ፣ በነፍስና በምድራዊ ኑሮአቸው የተሻለ ሕይወት እንዲኖሩ በሁሉም አቅጣጫ የሚያስታጥቃቸው ነው:: በዚህ አገልግሎት ውስጥ የሚያገለግሉ አማካሪዎች ለግል ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው ብለው ምክር ፈላጊዎችን እንዲሁም ሌሎች ሰዎችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጎዳን ሐሳብና ድርጊት አይመክሩም:: ምክራቸው በይዘትና በአካሄዱ ፈሪሃ እግዚአብሔር ይታይበታል::

ይህ መልካም የማማከር አገልግሎት የሚለጠው ከእግዚአብሔር ዘንድ በሚሰጥ ጥበብና ማስተዋል ነው:: አማካሪዎች ይህን ስጦታቸውን ለማሳደግና ተገቢውን ብቃት ለማግኘት ሥልጠና አስፈላጊ ቢሆንም ከትምህርት የተገኘ ጥበብ ብቻውን ሰዎች የተፈጠሩበትን ዓላማ ከግብ እንዲያደርሱ ሊያደርግ አይችልም:: ከትምህርት የተገኘው እውቀት የእግዚአብሔርን ሐሳብ በማይቃረን መልኩ ሰበጎ ሥራ እንዲውል በማድረግ ሰዎችን መጥቀም ይቻላል:: በዚህ መልካም የማማከር ሂደት ውስጥ የዓላማ ንጽሕና፣ ግልጽነት፣ ታማኝነትና ፍትሕ ይታያል::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመልካም ምክር ምሳሌዎችን ብቻ ሳይሆን ክፉ ምክሮችንም መመልከት እንችላለን:: ከእነዚህም ክፉ ምክሮች መካከል የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው::

***የኢዮናዳብ ምክር፡-*** አምኖን የሚባል ጓደኛው እህቱን በመውደድ በጭንቀት ውስጥ በነበረበት ወቅት ወደ እርሱ በመሄድ ችግሩን እንዲነግረው ጠየቀ:: አምኖንም የክሳቱ ምክንያት ምን እንደሆነ በግልጽ ነገረው:: ከዚያም ኢዮናዳብ ብልህነቱን በመጠቀም ለአምኖን ችግር መፍትሔ የሚሆነውን አማራጭ መንገድ አሳየው:: አምኖን እርሱ የመከረውን ምክር በመጠቀም ከእህቱ ጋር መተኛት ቻለ:: ኢዮናዳብ እንደ አንድ አማካሪ ያደረጋቸው ነገሮች አሉ:: የምክር ፈላጊውን ችግር ለማወቅ ያለውን ግንኙነት በመጠቀም ጠየቀው:: አስቀድሞ አምኖን ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ የተመለከታቸው ነገሮች ነበሩ:: ከመመልከት ያገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ ምክር ፈላጊው በግልጽ አውጥቶ እንድነግረው ጠይቆ ትክክለኛውን የችግሩን መንስኤ ለማግኘት ችሏል:: ከዚያም ለችግሩ «ትክክለኛ» የሆነውን መፍትሔ ማቅረብ ችሏል:: ኢዮናዳብ የሰጠው ምክር አምኖን የሚፈልገውን ነገር እንዲያገኝ ከማድረግ አንጻር ተወዳዳሪ የሌለው ሐሳብ ነው:: አምኖን ከእህቱ ጋር እንዲተኛ አድርጓል (2ሳሙ13:1-18)::

ነገር ግን ኢዮናዳብ እንደ አንድ አማካሪ ማየት የነበረበት ሌሎች ጉዳዮች ነበሩ:: ምክሩ በምክር ፈላጊውና በሌሎች ላይ አሁን እንዲሁም በቀጣይነት ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳት አልገለጸም:: ትኩረት ያደረገው ምክር ፈላጊው አሁን ያለበትን ስሜት ለማስተንፈስና ጊዜያዊ እርካታ ሊሰጥ በሚችል ጉዳይ



ላይ እንጂ በዘላቂነት ሊጠቅም የሚችለውን ነገር በመፈለግ ላይ አልነበረም:: ምክር ፈላጊውን በእውነት ከመጋፈጥ ይልቅ እርሱ የሚፈልገውን ነገር እንዲያገኝ ሁኔታዎችን ያመቻቸ በመሆኑ ሚዛናዊ እይታ የጎደለው አካሄድ ነው:: በተለይ ምክር ፈላጊውን ለመጥቀም ብሎ በሌላ ሰው ላይ ግፍ እንዲፈጸም ሁኔታዎችን ያመቻቸ በመሆኑ ከሥነምግባር የጎደለ ተግባር ነው::

ከዚህ ክፍል ስለማማከር አገልግሎት የተለያዩ ነገሮችን ማስተዋል እንችላለን:-

- √ ምክር ፈላጊዎች ያላቸውን ችግር ለመረዳት እነርሱንና ሁኔታዎቻቸውን በጥሞና መመልከት፣ ከዚያም እንደ አስፈላጊነቱ ተገቢውን ጥያቄ መጠየቅ ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ያግዛል::
- √ በማማከር ግንኙነት የሚቀርበው አማራጭ መፍትሔ የምክር ፈላጊዎችን ችግር በጊዜያዊነት የሚፈታ ብቻ ሳይሆን መሠረታዊ መንስኤዎቹን ሊፈታ የሚችል እንዲሆን በቂ ጊዜ ወስዶ መሥራት ያስፈልጋል::
- √ ለምክር ፈላጊዎች ችግር እንደ አማራጭ መፍትሔ የሚቀርበው ሐሳብ እነርሱን በዘላቂነት የሚጠቅም መሆኑንና በማንኛውም መልኩ ሌሎችን የማይጎዳ መሆኑን በጥንቃቄ ማጤን ሊዘነጋ የማይገባ ጉዳይ ነው::
- √ ምክር ፈላጊዎች ለጊዜያዊ የስሜት እርካታቸው ከፍተኛ ትኩረት በሚሰጡበት ወቅት በዘላቂነት የሚጠቅማቸውን መፍትሔ ለመፈለግ ፈቃደኞች ሳይሆኑ ይችላሉ::
- √ ጓደኛን ወይም የቅርብ ቤተሰብ አባል የሆኑትን ሰዎች ማማከር ሚዛናዊነትን ጠብቆ ለመሄድ አዳጋች ስለሚሆን፣ ከዚህ ግንኙነት የሚወጣውም የመፍትሔ ሐሳብ ወደ አንድ አቅጣጫ (ምክር ፈላጊውን የሚያስደስት) ያዘነበለ እንዲሆን ስለሚያደርግ ወደ ሌሎች አማካሪዎች መምራት የተሻለ ነው::
- √ ከብዙ አቅጣጫዎች በጥንቃቄ ሳይጠና ተግባራዊ የሚሆን የመፍትሔ ሐሳብ ብዙ ውስብስብ ችግሮችን ያስከትላል:: ስለዚህ አንድን አማራጭ የመፍትሔ ሐሳብ ወዲያውኑ ተግባራዊ ከማድረግ አስቀድሞ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት መፈተሽ ያሻል::

***የአኪጦፌል ምክር፡-*** ይህ ሰው የንጉሥ ዳዊት አማካሪ ሆኖ ለብዙ ዓመታት ያገለገለ ሰው ነበር:: በአንድ ወቅት ልጁ ሥልጣኑን ለመቀማት በዳዊት ላይ በተነሣበት ጊዜ አኪጦፌል አባቱን ትቶ ከአቤሴሎም ጋር ተባበረ:: በዚያን ዘመን ደግሞ የእርሱ ምክር የእግዚአብሔርን ምክር እንደ መጠየቅ ነበር:: ምክሩ የበሰለ ከመሆኑ የተነሣ ተግባራዊነቱ አምብዛም አያጠያይቅም:: አቤሴሎም ምን ማድረግ እንዳለበት ሲጠይቀው አኪጦፌል ዳዊትን አጅግ ሊያስነውርና ሊጎዳ የሚችል ምክር መከረው:: ልጅ ከአባቱ ቁባቶች ጋር ሰዎች እያዩ በአደባባይ ከእነርሱ ጋር እንዲተኛ መከረው:: አቤሴሎምም ይህንን አደረገ:: ከዚያም ዳዊትን ለመያዝ እርሱን ተከተሉት

የሚል ምክር መከረው፡፡ ሆኖም አቤሴሎም የሌላን ሰው ምክር በመጠየቅ ይህን ምክር ሳይቀበለው ቀረ፡፡ ምክሩም ተቀባይነት እንዳላገኘ ባወቀ ጊዜ አኪጦፌል ራሱን ገደለ (2ሳሙ·16፡15-23)፡፡

አኪጦፌል የዳዊት አማካሪ ቢሆንም በልቡ ውስጥ ግን በዳዊት ላይ ቂም ነበረው፡፡ እርሱ የቤርሳቤህ አያት በመሆኑ ዳዊት ኦሪዮንን ገድሎ እርስዋን ማግባቱን አልወደደም፡፡ ሆኖም አቅም ስላልነበረው ዝም ብሎ ያገለግለው ነበር፡፡ ዳዊትን ለማጥቃት ምቹ ሁኔታዎች እንደተመቻቹለት ሲያውቅ ጥበቡንና ልምዱን በመጠቀም በዳዊት ላይ ሴራ ጀመረ፡፡ አማካሪ ወገንተኛ መሆን የለበትም፡፡ እንዱን ለመጥቀም ብሎ ሌላውን መጉዳት የለበትም፡፡ አንድ አማካሪ በውስጡ ትክክለኛ ያልሆነ ዓላማ ስመያዝ ከምክር ፈላጊዎች ጋር መሆን አይገባውም፡፡ ስለእነርሱ ያለው አመለካከት ሚዛናዊ ካልሆነ ራሱን መፈተሽና መፍትሔ ሊፈልግለት ይገባል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ አገልግሎቱን ከቀጠለ ራሱንም ሌሎችንም ሰዎች በችግር ውስጥ ያስገባል፡፡

*የሮብዓም ጓደኞች ምክር፦* ሮብዓም በገጠመው ችግር ምክንያት የአባቱ አማካሪዎች የነበሩትን ሽማግሌዎች ምክር ትቶ ወደ ጓደኞቹ ዘንድ በመሄድ ምክር ሊጠይቃቸው እርሱ መስማት የሚፈልገውን ዓይነት ምክር መከሩት፡፡ በእርግጥ የእነርሱ ምክር የመነጨው ከሚያምኑበት ርዕዮተ ዓለም ነው፡፡ ወጣቶች በመሆናቸው ለወጣት አእምሮ የሚመቸውን ሁኔታ ተመለከቱ፡፡ ሥልጣንን በመጠቀም ሕዝብን ወደሚፈለገው ግብ መምራት ይቻላል የሚል ግምት ነበራቸው፡፡ ሆኖም ውጤቱ ለሮብዓም የሚጠቅም ሆኖ አልተገኘም (1ነገ12፡7)፡፡

አማካሪዎች የሚያምኑበት የሕይወት ፍልስፍና እንዲሁም ዕድሜያቸውና ልምዳቸው በሚሰጡት የማማከር አገልግሎት ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ በመሠረተ ሐሳብ አማካሪዎች፣ ምክር ፈላጊዎች መስማት የሚፈልጉትን ዓይነት አማራጭ መፍትሔዎችን መስጠት የለባቸውም፡፡ አማካሪ የሚያስፈኛቸውም ምክር ፈላጊዎች ከተመለከቱበት እይታ ውጭ የሆኑትን ሌሎች አማራጮችንና የእያንዳንዱን አማራጭ ጥቅምና ጉዳት ዘርዝር አድርጎ ማሳየት መቻላቸው ነው፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምክሮች ሰዎች ከእግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ ውጭ የሆነ እርምጃ እንዲወስዱ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ቃሉን ማዕከል ያደረጉ ምክሮች አይደሉም፡፡ ሰዎች በራሳቸው ሰብዓዊ አእምሮ የእግዚአብሔርን ሐሳብ ከግንዛቤ ውስጥ ሳያስገቡ የሰጡት ምክር በመሆኑ መጨረሻቸው ያመረ አይደለም፡፡ ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለበት ምክር የምክር ፈላጊውን ፍላጎት በማርካት ላይ ትኩረት ያደረገ ስለሚሆን ለሌሎች ሰዎች ፍላጎት መሟላት ወይም መጎዳት አያስብም፡፡ ይህ ዓይነቱ ምክር በምንም መልኩ ቢሆን ምክር ፈላጊው የሚፈልገው ነገር ከግብ እንዲደርስ በመፈለግ ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡

ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለው አካሄድ ከመሆኑም ባሻገር በማማከር ሥነምግባር ትክክል አይደለም፡፡ ማማከር የምክር ፈላጊው ፍላጎት



ከግብ እንዲደርስ ብቻ የሚሰጥ አገልግሎት አይደለም፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ምክር ፈላጊው ያለው ፍላጎት ለእርሱም ሆነ ለሌሎች የማይጠቅም ሆኖ ሲገኝ ወይም አሁን የሚጠቅም መስሎ የኋላ ኋላ ግን ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ እንዲተውም ይደረጋል፡፡ ፍላጎቱን ማሟላት የችግሩን ምልክት ከማከም ያለፈ መሠረታዊ የችግሩን መንስኤ የሚነቅል እርምጃ አይደለም፡፡ ስለዚህ በማማከር ትኩረት የሚደረገው ትክክለኛ ያልሆነ ፍላጎት እንዲፈጠር ያደረገው መሠረታዊ መንስኤ ተለይቶ መፍትሔ እንዲያገኝ ጥረት ይደረጋል፡፡

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለማማከር አገልግሎት ብዙ ነገሮችን እንደሚናገር መመልከት እንችላለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ልጆች የሕይወት ጥያቄዎች ሙሉ መልስ እንደሚሰጥና የትክክለኛ ሕይወትና ኑሮ መለኪያ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ይህ ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስ ለችግሮች ሁሉ ዝርዝር መግለጫን ይሰጣል ማለት ሳይሆን ለሁሉም ችግር መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉትን መርሆዎች ይዟል፡፡ ሌሎች ትምህርቶች የሚሰጡትን እውቀቶች እንጠቀማለን፡፡ «ሁሉም እውነት የእግዚአብሔር እውነት ነው» የሚለው አባባል እውነትነት አለው፡፡ እኛም ለማማከር አገልግሎት የሚረዱትን ከትምህርት መስኮች የተገኙትን መረጃዎችን የእግዚአብሔርን ቃል እውነትነት እስከጠበቁ ድረስ እንጠቀምባቸዋለን፡፡

### *1.3. የማማከር አስፈላጊነት*

የማማከር አገልግሎት ለምን ያስፈልገናል? የማማከር አገልግሎት በዚህ በድሕረ ዘመናዊነት ወቅት የተፈጠረ አዲስ አገልግሎት ሳይሆን ከጥንትም የነበረ ነው፡፡ ሆኖም በተለያየ ዘመን ማማከር የሚሰጥበት ዓውድና አማካሪዎች ያላቸው ብቃት ተመሳሳይ ነው ማለት አይደለም፡፡ ከጥቂት ዓመታ በፊት በልምድ ይደረግ የነበረው የማማከር አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ በጥናትና በምርምር በተገኙ ውጤታማ ዘዴዎች እየተሰጠ ይገኛል፡፡

የማማከር አገልግሎት ለሰዎች ሁሉ ያስፈልጋል፡፡ ከእነዚህም የሚከተሉት ምክንያቶች በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ለሰዎች ማማከር የሚያስፈልገው፣

*ሰዎች ሁሉ ደካማ ጎን ስለ ላላቸው ነው፦* ዓይነቱና መጠኑ ይለያይ እንጂ በዚህ ዓለም ላይ ከችግር ነጻ የሆነ ሕይወት የሚኖር ሰው የለም፡፡ በሕይወት ውስጥ ሰው ለብቻው ማሸነፍ የማይችለው ዓይነት ችግር ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ችግሮቹ የሞራል ውድቀት፣ ከሰዎች ጋር ያለ ግንኙነት መበላሸት፣ በሥራ ስኬትን ማጣት፣ ከትዳር ጓደኛ ጋር ተጣጥሞ ለመኖር አለመቻል፣ በመንፈሳዊ ውድቀት ውስጥ መግባት፣ ወይም ውሳኔ ለማድረግ አለመቻል እና የመሳሰሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሰዎች በእንዲህ ዓይነት ችግሮች ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ ከእነርሱ ጋር በመሆን አማራጭ ሐሳቦችን በማሳየት ወደ ትክክለኛው መፍትሔ መድረስ እንዲችሉ የሚያግዛቸው አማካሪ ያስፈልጋቸዋል፡፡ የማማከር አገልግሎት ለሰዎች ትክክለኛ

ማንነታቸውን፡ ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን በሚገባ አውቀው ባላቸው ጠንካራ ጎን በመጠቀም ድክመታቸውን ማሻሻል እንዲችሉ ያግዛቸዋል።

*ማማከር ምስጢር የጠበቀ አገልግሎት ስለሆነ ነው፦* ሰዎች ለማንም ሰው መግለጽ ያልቻሉትን ምስጢራቸውን መናገር የሚችሉበት ሥፍራ ነው። በዚህ ግንኙነት የምክር ፈላጊዎች ምስጢር ስለሚጠበቅ ያለ ምንም ፍርሃት ለማንም ያላካፈሉትን ገመናቸውን ማውራት ይችላሉ። በሌሎች ሰብዓዊ ግንኙነቶች በእንዲህ ዓይነት ያለስጋት የግል ምስጢርን ማውራት የሚቻልበት ዓውድ ባለመኖሩ ሰዎች ወደ ማማከር አገልግሎት ይመጣሉ።

*የማማከር አገልግሎት በግል ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ስለሆነ ነው፦* የማማከር አገልግሎት ምክር ፈላጊዎች ጉዳያችን ነው ብለው በሚያመጡት ነገር ላይ ትኩረት ያደርጋል። ከዚህም የተነሣ የምክር ፈላጊውን ትክክለኛ ጉዳይ በዝርዝር በመመልከት ወደሚፈለገው ግብ ለመሄድ ያበችላል። በጉባኤ በሚደረጉ አገልግሎቶች ለምሳሌ በስትዳር በሚሰጡ ትምህርቶች ሰዎች ስትዳር ችግራቸው መፍትሔ የሚሆኑ መርሆዎችን ለማግኘት ይችላሉ። ሆኖም የግል የትዳር ችግራቸውን በመፍታት ረገድ ፍላጎታቸውን ከማርካት አንጻር የተሟላ አይሆንም። የተማሩትንም ትምህርት ከሕይወታቸው ጋር በማዋሃድ ሊወስዱ የሚገባቸውን ተከታታይ እርምጃዎችን በግልጽ ሰማሳየት፣ በግላቸው የማማከር አገልግሎት ማግኘት በተሻለ ሁኔታ ይጠቅማቸዋል።

የማማከር አገልግሎት የምክር ፈላጊዎችን ችግር በጥልቀት ለመረዳት ዕድልን ይሰጣል። ከማማከር ውጭ በሚደረጉ አብዛኛዎቹ ግንኙነቶች ውስጥ የግል ችግሮቻቸውን አውጥተው አይናገሩም። ምክንያቱም ተገቢው ጊዜና አክብሮት ሳይሰጣቸው ስለሚችል ነው። የምክር ፈላጊዎችን ችግር በመፍታት ሂደት ለመርዳት በጥልቀት ማዳመጥና መረዳት ያበፈልጋል። ከምክር ፈላጊዎች ጋር ጊዜ በመውሰድ ችግሮቻቸውን መረዳት፣ እግዚአብሔር በሕይወታቸው ውስጥ ያለውን ዓላማውንና ፈቃዱን እንዲሁም ለችግሮቻቸው መፍትሔ የሚሆኑትን አማራጮችን ለማውጣት ዕድልን ይሰጣል።

የማማከር አገልግሎት በትምህርት ቤት የተማሪዎችን፣ በሥራ ቦታ የሠራተኞችን እንዲሁም በቤተክርስቲያን የምዕመናንን የግል ችግሮች ለማወቅና መፍትሔዎችን እንዲያገኙ ለመርዳት አስፈላጊ ነው። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ካልተመቻቸላቸው ሰዎች ምንም ችግር እንደሌላቸው አስመስለው ይኖራሉ። ሆኖም በውስጣቸው ያመቋቸው ችግሮቻቸው በሕይወታቸው፣ በትምህርታቸው፣ በሥራቸው፣ በማህበራዊና በመንፈሳዊ ግንኙነቶቻቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከትላል።

*ማማከር የሁለትዮሽ ግንኙነት ስለሆነ ነው፦* በማማከር አገልግሎት ውስጥ አማካሪውና ምክር ፈላጊው አንድ ላይ ሆነው በምክር ፈላጊው ችግር ዙሪያ ይወያያሉ። አንዱ ዝም ብሎ የሚናገርበትና ሌላው አድማጭ የሚሆንበት ሂደት ሳይሆን ሁለቱም እንደ አስፈላጊነቱ ገንቢ ተሳትፎ



የሚያደርጉበት ግንኙነት ነው። አንዱ ሲናገር ሌላው ያዳምጣል፣ አንዱ ሲያዳምጥ ሌላው ይናገራል። በዚህ ግንኙነት፣ ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረግ የሚጠበቅበት ምክር ፈላጊው በመሆኑ ራሱን ለመግለጽ ሰፊ ዕድል ያገኛል።

በማማከር አገልግሎት የሚተላለፈው መልዕክት «ይህን አድርግ» ወይም «ይህን አታድርግ» የሚል ትዕዛዝ ወይም ዲስኩር አይደለም። ምክር ፈላጊው ስለችግሩ ለመናገርና ለማሰብ ዕድል አለው። አማካሪው ከእርሱ ጋር በመሆን ለችግሮቹ መፍትሔዎችን ማፍለቅ እንዲችል ያግዘዋል። ምናልባት አማራጭ የመፍትሔ ሐሳቦችን ማምጣት ቢያስፈልግም ለምክር ፈላጊው ምንም ዓይነት ውሳኔን አይወስንለትም። አንድን ነገር ለመቀበል ወይም ላለመቀበል እንዲሁም ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ሙሉ መብት ያለው ምክር ፈላጊው ነው። ምክር ፈላጊው በሂደቱ ውስጥ ባገኘው ግንዛቤ በመጠቀም በሕይወቱ ይጠቅመኛል ብሎ ያሰበውን እርምጃ መውሰድ ይችላል።

> *«ምክር የመስጠት እውነተኛ ምስጢሩ በታማኝነት ከሰጠህ በኋላ ተቀባይነት ቢያገኝም ባያገኝም መሐል ስፋሪ መሆንና ሰዎችን በምትፈልገው መንገድ ለማስተካከል ግፊት ለማድረግ አለመጣጣር ነው።»*
>
> *ሎጋን ፐርሳል ስሚዝ*

*የማማከር አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለሆነ ነው፦* እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለቤተክርስቲያን ከሰጣቸው የጸጋ ስጦታዎች መካከል አንዱ የማማከር አገልግሎት ነው (ሮሜ12:8)። መንፈስ ቅዱስ ራሱ ግሩምና ድንቅ መካሪ ነው። ስለዚህ ቤተክርስቲያን በሌሎች የጸጋ ስጦታዎች እንደምትጠቀም የማማከር አገልግሎት ጸጋ ያላቸውንም አገልጋዮች ማበረታታትና ጸጋቸውን እንዲገልጡ ማሰልጠን ይገባታል።

*ኢየሱስ አድርጎ እንድናደርግ የመከረን አገልግሎት ስለሆነ ነው፦* እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ዋጋን ይሰጣል። ኢየሱስ በምድር ላይ በሥጋ ይመላለስ በነበረበት ወቅት ብዙ ሰዎችን አንድ ላይ ያስተምር፣ በጋራ ምክር ይሰጣቸው ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ለግለሰቦች የግል ፍላጎትና ችግርም ተገቢውን ምላሽ ይሰጥ ነበር። ደቀመዛሙርቱንም ያገኛቸውና ለአገልግሎቱ የጠራቸው በየግላቸው ነው። እያንዳንዳቸው በየራሳቸው ሁኔታ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ወደ እነርሱ በመሄድ ጠራቸው። ጴጥሮስ ዓሣ ያጠምድ ነበር (ማቴ4:18)፤ ማቴዎስ ደግሞ ቀረጥ ይሰበስባል (ማቴ9:9) እንዲሁም ሌሎችንም በየሁኔታዎቻቸው ውስጥ ተገኝቶ ጠራቸው።

- √ መንፈሳዊ ችግር የነበረውን የአይሁድ አለቃ ኒቆዲሞስን ያነጋገረውና እውነትን እንዲገነዘብ ያደረገው በግል ከእርሱ ጋር በነበረው ውይይት ነው (ዮሐ3:1-21)
- √ በኃጢአት ምክንያት ከማህበረሰቡ የተገለለችና የሕይወት ትርጉም የጠፋባትን ሴትም ያገኛት ለብቻዋ ሳለች ነበር። ቀስ በቀስ ራስዋን በትክክል መረዳት እንድትችል በማድረግ ሕይወትዋን ወደ መልካም ግብ መምራት ቻለ። በግል ከእርሱ ጋር በነበራት ግንኙነት

ሕይወትዋ በመለወጡ ወደ አደባባይ በድፍረት ለመውጣት ቻለች:: በምስጢር የሚያደርገው አገልግሎት የሰዎችን ሕይወት ይለውጥና ለምስክርነት ያበቃል (ዮሐ4:7-26)

- √ ቀረጥ ይሰበስብ (ከሚፈቀድለት በላይ እየሰበሰበ ለራሱ ያስቀር) ስለነበር በሥራው ምክንያት በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያልነበረውን ዘኬዎስን ያገኘውና ሕይወቱን የለወጠው ከእርሱና ከቤተሰቡ ጋር በነበረው ግንኙነት ነበር (ሉቃ19:1-9)
- √ በሰዎች ዘንድ ምንም ተስፋ ያልነበረውን ማየት የተሳነውን በርጠሜዎስንም በግል አነጋግሯል:: በልመና ሥራ ይተዳደር የነበረውን የዝቅተኛ የማህበረሰብ ክፍል አባል የሆነው በርጠሜዎስ ወደ እርሱ ሲጮኽ ኢየሱስ ለማና ቆመለት:: ወደ ራሱም ጠርቶ የሚፈልገውን ነገር ጠየቀው፣ አደረገለትም:: ሰዎች ሰምተው ምላሽ ሊሰጡ ከማይፈልጓቸው ሰዎች ጋር በግል ለመሆን ፈቃደኛ ነበር (ማር10:46-42)

የእነዚህ ሰዎች ችግር በዓይነቱና በመጠኑ የተለያየ ነበር:: እነዚህን ሰዎች አንድ ላይ ቢያገኛቸውና ቢያስተምራቸው ኢየሱስ ሁሉንም ፍላጎት ሊያረካ የሚችልበት ዕድል ጠባብ ይሆናል:: ስለሆነም እያንዳንዳቸውን ባሉበት ሁኔታ በግላቸው ማግኘትን መረጠ:: ለብቻቸው ለላገኛቸውና አስፈላጊውን ምክር በሰለጣቸው ለችግሮቻቸው ፍጹም የሆነ መፍትሔን ማግኘት ችለዋል::

ኢየሱስ እንደ መልካም እረኛ ዘጠና ዘጠኙን በጎች በተራራ ላይ ማለትም ለሕይወታቸው በማያስጋ ሁኔታ ውስጥ ትቶ የጠፋውን አንድ በግ ፍለጋ እንደሚሄድ (ሉቃ15:3-7) መናገሩ ለአንድ ግለሰብ ሕይወት ከፍተኛ ዋጋ መስጠቱን ያመለክታል:: ብዙ አገልጋዮች ለአደባባይና ለመድረክ አገልግሎት ብቻ ከፍተኛ ግምት በመስጠት በግል የሚሰጠውን የማማከር አገልግሎት ችላ ማለታቸው አገልግሎታቸው ሙሉ እንዳይሆን አድርጓል:: ብዙ ምዕመናን በግል ጉዳዮቻቸው የሚያማክሩአቸውን አገልጋዮች በማጣት የግል ችግሮቻቸውን አምቀው ይዘው በጭንቀትና በውጥረት ውስጥ ይኖራሉ:: እንዳንዶች ደግሞ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች የሚያደርጉትን መልካም ነገር ባለማወቅ ተገቢ ያልሆኑ ምርጫዎችን መርጠው እየባዘኑ ናቸው::

ከአንድ ሰው ጋር ብዙ ጊዜ ማሳለፍ አገልግሎት መስሎ የማይታያቸው አገልጋዮች አሉ:: ሆኖም ጌታ ኢየሱስ ይህን ያደርግ ስለነበር የእርሱን ፈለግ በመከተል የተለያየ ችግር ያላቸውን ምዕመናን በግል ማማከር አስፈላጊ ነው:: እግዚአብሔር በእነዚህ አማካሪዎች በመጠቀም ጥልቅ ስሆነው የሰዎች ችግር ትክክለኛ ምሪትን ይሰጣቸዋል:: ብዙ ሰዎችን አንድ ላይ ሰብስቦ ማገልገል ጠቃሚ ቢሆንም በግል የሰዎችን ሕይወት መንካት የሚቻልበት አገልግሎት ካልታከለበት የሰዎችን ሕይወት ለውጦ ወደሚፈለገው ግብ ለማድረስ የሚኖረው አቅም አናሳ ይሆናል:: ስለዚህ በሁለቱም መካከል ሚዛን የጠበቀ ግንኙነት መኖር አለበት::



### *1.4. የማማከር ዓላማዎች*

ወደ ማማከር አገልግሎት ሄደው የማያውቁ ሰዎች በማማከር ጊዜ ምን ይደረጋል ብለው ይጠይቃሉ:: ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ ምን ዓይነት ነገሮች እንደሚከናወኑ አያውቁም:: ይህ ዓይነቱ ግራ መጋባት የምክር ፈላጊዎች ብቻ ሳይሆን ገና ጀማሪ የሆኑ አማካሪዎችም በማማከር ሂደት ሊከናወኑ ስለሚገባቸው ዓላማዎች ኩልል ያለ ግንዛቤ ላይኖራቸው ይችላል:: የማማከር ዓላማ የሚባለው አገልግሎቱ ከተሰጠ በኋላ በምክር ፈላጊው ሕይወት ውስጥ የሚታዮትን ለውጦችን ወይም ፍሬዎችን የሚያመለክት ነው:: አጠቃላይ ከሆኑ የማማከር ዓላማዎች መካከል የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው:-

*የባሕርይ ለውጥ ማምጣት:-* ሰዎች የሚፈለገውን ሕይወት ለመኖር ለዚያ የሕይወት ዘይቤ የሚመቸውን ባሕርይ ማሳደግ አለባቸው:: ለባሕርይ ለውጥ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ መሠረታዊ እርምጃ ነው:: የሰዎች ድርጊት የሚለወጠው ልባቸው ሲለወጥ ነው:: ምክንያቱም መልካምም ሆነ ክፉ ድርጊት የሚመነጨው ከልብ በመሆኑ ነው (ማር7:21-23):: ፍሬያማ ሕይወት ለመኖር ተገቢ ድርጊት ያስፈልጋል፤ ይህ ደግሞ ልብ ሲለወጥ ተከትሎ የሚመጣ ውጤት ነው:: የባሕርይ ለውጥ የሚፈለገው ምክር ፈላጊው ፍሬያማ ሕይወት እንዳይኖር ያደረገውን ምላሾቹን እንዲለውጥ ለማድረግ ነው:: ከቤተሰብ፣ ከማህበራዊ ግንኙነቶቹ፣ ከሥራ ቦታ፣ ከትምህርት ቤት፣ ከቤተክርስቲያን እና ከሌሎችም ሁኔታዎች የሚመጡበትን ሁኔታዎች ገንቢ በሆነ መንገድ ማስተናገድ እንዲችል መሠረታዊ እርምጃዎችን የሚማርበት ዓውድ ይሆናል::

የሰው አስተሳሰብ እንዲለወጥ ከሚረዱ ነገሮች ዋነኛው የእግዚአብሔር ቃል ነው:: ቃሉ ለሰዎች አዲስ ግንዛቤና እይታን ይሰጣቸዋል:: ይህ ተስፋ አለን (ሕዝ11:19-20)::

የሰው ባሕርይ በአንድ ጊዜ አይለወጥም:: የባሕርይ ለውጥ ከሚፈለግበት ውጤት የሚደርሰው ቀስ በቀስ በሂደት ነው:: ስለዚህ ትዕግሥት ያስፈልጋል:: የባሕርይ ለውጥ ሲባል ክፉ ድርጊትን መተው ብቻ ሳይሆን ከዚያም አልፎ የመጀመሪያውን ድርጊት ተቃራኒ የሆነውን መልካም ነገር ማድረግ ነው:: ለምሳሌ አንድ ሰው የስርቆት ባሕርይ ካለው የባሕርይ ለውጥ አመጣ የሚባለው ስርቆት ሲያቆም ሳይሆን በእጅ በትጋት በመሥራት ከሚያገኘው ውጤት ለሌሎች ማካፈልን ሲማር ነው:: በፊት የሌሎችን ያለ ፈቃድ ይወስድ ነበር፤ አሁን ደግሞ የራሱ የሆነውን ነገር ለሌሎች ለማካፈል ፈቃደኛ ይሆናል ማለት ነው (ኤፌ4:26-27)::

*መልካም የአእምሮ ጤንነት ማምጣት:-* በዚህ ዓለም ጤናማ ሕይወት ለመምራት የአእምሮ ጤንነት ያስፈልጋል:: ይህ ምክር ፈላጊዎች ለራሳቸው፣ ለሰዎችና አካባቢያቸው ሚዛናዊ የሆነ ግንዛቤ አግኝተው ሕይወታቸውን መምራት እንዲችሉ መርዳት ነው:: ወደ አንድ ነገር ብቻ ያላዳላ ወይም ሁለንተናዊ እይታ ያለው ሕይወት ለመኖር ከእግዚአብሔር፣

ከራስ፣ ከሰዎች እንዲሁም ከአካባቢ ጋር ተስማምቶ ለመኖር የሚያስችል አስተሳሰብና ተግባር ያስፈልጋል። እነዚህ የሕይወት ገጽታዎች ሁሉ አስፈላጊ ናቸው። መንፈሳዊነት ከመጠን ሲያልፍ ሌሎች ይጎዳሉ፤ የእነርሱ መጎዳት ደግሞ መንፈሳዊነቱን ይጎዳል። በሁሉም መካከል ሚዛን ያስፈልጋል። ስለዚህ የአእምሮ ጤንነት መታወክ የሚያመጡ ነገሮችን ለመከላከል እንዲሁም ከተከሰተ ደግሞ ለመቅረፍ የማማከር አገልግሎት አስፈላጊ ነው።

*ለችግሮች መፍትሔ መፈለግ፦* ምክር ፈላጊዎች ወደ አማካሪው ይዘው የሚመጡት ችግሮች ይኖራሉ። ከእነዚህም ችግሮች መካከል በተለያዩ ሁኔታዎችና ምክንያቶች በፍርሃት መንፈስ መያዝ፣ ጭንቀት፣ የግንኙነት መበላሸት፣ በተለያዩ ሱሶች ተይዞ መውጣት አለመቻል፣ በአፍላ ፍቅር ተይዞ ግራ መጋባት፣ የትዳር ጓደኛ መምረጥ አለመቻል፣ በሥራ ቦታ ከሰዎች ጋር መግባባት አለመቻል፣ በሥራ ስኬት ማጣትን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። በማማከር ወቅት ለእነዚህና ለመሳሰሉት የምክር ፈላጊው ችግር ለሆኑት ጉዳዮች መሠረታዊ መፍትሔዎች ይፈለጋሉ። ምክር ፈላጊውና አማካሪው አንድ ላይ በቅንጅት በመሥራት ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ ማግኘት ይችላሉ። በመሠረተ ሐሳብ ዓይነቱ ይለያይ እንጂ መፍትሔ የማይገኝለት የምክር ፈላጊ ችግር አይኖርም።

ምክር ፈላጊዎች በግላቸው ጥረት አድርገው መፍታት ያልቻሉትን ችግር ይዘው መቀመጥ የለባቸውም። የማማከር አገልግሎት ቢያገኙ ችግሮቻቸውን በሚገባ ተረድተው፣ መንስኤዎቹን ቆፍረው አውጥተው፣ መፍትሔውንም አግኝተው ሕይወታቸውን በሚፈልጉት መልካም አቅጣጫ መምራት ይችላሉ። ከዚህ አንጻር ሲታይ የማማከር ቁልፍ ሚናው ከምክር ፈላጊዎች ጋር ሆኖ ለችግሮቻቸው መፍትሔ መፈለግ ነው።

*በሕይወት ፍሬያማ ለመሆን፦* ማማከር ምክር ፈላጊው የራሱ ችግር ካደረሰበት ውስንነትና አካባቢያዊ ተጽዕኖዎች ተላቆ፣ ለሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ከሕይወት ጋር በተሻለ ሁኔታ ትግል እንዲያደርግ አማራጮችን ይሰጠዋል። በሕይወቱ ውጤታማ እንዳይሆን ያደረጉትን መሰናከሎች ለይቶ ያውቃል፣ እንዴት ማስወገድ እንደሚችላቸው ይለማመዳል፤ ከዚያም እግዚአብሔር ወዳቀደለት ግብ ይገሰግሳል። ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ለመድረስ የተሰጡትን ስጦታዎች በመጠቀም ከውስጣዊና ውጫዊ ተጽዕኖዎች ጋር ገንቢ ትግል ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ ትግል ውስጥ ደግሞ ብዙ ውጣ ውረዶች ይኖራሉ። በእነዚህ ነገሮች ተስፋ ሳይቆርጡ ወደ ታለመው ግብ ለመድረስ የአማካሪ አብሮነት ጠቃሚ ነው።

ማማከር የሕይወት ብስለትን ያመጣል። ሰዎች በሕይወታቸው ጠለቅ ወዳለው ልምምድ ውስጥ ገብተው ተገቢውን ራእያቸውን ከግብ ለማድረስ የማማከር አገልግሎት ይጠቅማቸዋል። ፍሬያማነት ከብስለት ጋር ተያያዥነት አለው። አሁን በሕይወት መንገድ ላይ የገጠሙትን ችግሮች መቅረፍ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ዓላማ ስኬት ደግሞ በእቅድ መሥራት



ያስፈልጋል። የወደፊቱን ነገር ሳይዘነጋ ዛሬ ያጋጠሙትን ችግሮች ይፈታል። የዛሬውን ችግሩን ለመፍታት የሚያስፈልገውን እርምጃ ሳይወስድ ደግሞ ነገ ከዛሬ የተሻለ ይሆናል ብሎ አያልምም።

ምክር ፈላጊዎች በልባቸው ያሰቡት መልካም ነገር ከግብ የሚደርሰው በዚህ ሂደት የማማከር አገልግሎት ሲያገኙ ነው (ምሳ15:22)። ብዙዎች ውጤታማ ሳይሆኑ የሚቀሩት ችሎታ ወይም ምቹ ሁኔታዎች በማጣታቸው ሳይሆን ችሎታቸው ምን እንደሆነ ለይቶ ባለማወቅ፣ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ባለማስተዋልና ያገኙትን መልካም ዕድል ለሕይወታቸው ዕድገት በቀጣይነት መጠቀም ባለመቻላቸው ነው፡ የማማከር አገልግሎት ይህን ክፍተት ይሞላል።

ከዚህ አንጻር ማማከር የሚያስፈልገው ከተለያዩ ሥነልቦናዊና መንፈሳዊ ችግር ውስጥ ለገቡት ሰዎች ብቻ ሳይሆን በሕይወታቸውም የበለጠ ፍሬያማ ለመሆን ለሚፈልጉ ሰዎችም እንደሆነ መመልከት እንችላለን።

*ምክር ፈላጊውን መደገፍ፦* በማማከር አገልግሎት ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ ስሜታዊ፣ መንፈሳዊ፣ ማሕበራዊ እንዲሁም ቁሳዊ ድጋፍ የሚሰጥበት ወይም እንዲሰጥ ሁኔታዎች የሚመቻቹበት ሁኔታ ይኖራል። አንዳንድ ምክር ፈላጊዎች በሕይወታቸው እጅግ ተጎድተው ወይም ተስፋ ቆርጠው ስለሚመጡ ድጋፍ ያሻቸዋል። ይህ ድጋፍ «አይዞህ» ወይም «አይዞሽ» ማለት ሳይሆን በሕይወት ጎዳና ላይ እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ቢያጋጥሙም በትዕግሥት ከተያዙ የሚያልፉ ወይም የማይሰወጡም ከሆነ ራስን ለውጦ ከእነርሱ ጋር መኖር እንደሚቻል ማሳየት ነው። የሕይወትን አዎንታዊ ገጽታም መመልከት እንዲችሉ ፍንጭ መስጠት ነው።

በተለያዩ ዓይነት ችግሮች ውስጥ ገብተው «ከእንግዲህ እኔ ምንም ተስፋ የለኝም» ብለው እንዲሁ የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ ወደ ማማከር አገልግሎት የሚመጡ ምክር ፈላጊዎች ይኖራሉ። ለእነዚህ ምክር ፈላጊዎች ችግሮቻቸውን በአንድ ጊዜ መፍታት የሚቻልበት ሁኔታ ባይኖርም አማካሪው ከእነርሱ ጋር አብሮ በመጓዝ የሕይወትን አዎንታዊ ገጽታ ማየት እንዲችሉ ያግዛል።

አንዳንድ ምክር ፈላጊዎች አሁኑኑ ቁሳዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ዓይነት ሲሆኑ ይችላሉ። በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ አማካሪ ለምክር ፈላጊዎች ቁሳዊ ድጋፍ አያደርግም። ለእነርሱ ስጦታ መስጠት የማማከር ሂደቱን ሚዛናዊነት ያሳጠዋል። ምክር ፈላጊዎች በእርሱ/እርስዋ ላይ ጥገኞች እንዲሆኑና ራሳቸውን ሆነው በሂደቱ ውስጥ እንዳይሳተፉ እንቅፋት ይሆናል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ምክር ፈላጊዎች ቁሳዊ ድጋፍ ማግኘት በሚችሉበት ጉዳይ ላይ መነጋገርና እነርሱ ለራሳቸው እንዲፈልጉ ማድረግ የተሻለ ነው። እንዲህ መሆን የማይቻል ከሆነ ደግሞ አማካሪው ሰጪው በማይታወቅበት ሁኔታ ለምክር ፈላጊዎቹ መስጠት ይቻላል። እንዲህ ዓይነት ምክር ፈላጊዎች በተለይ በዓውዳችን ብዙ በመሆናቸው የአማካሪው ለጋሽነት የሚያዛልቅ እርምጃ አይደለም።

*ለምክር ፈላጊው ጥብቅና መቆም፡-* አንዳንድ ጊዜ አማካሪ ለምክር ፈላጊዎች ጥብቅና ይቆማል፡፡ ምክር ፈላጊዎች ያሉበት ሁኔታ ከመብት አንጻር ሲታይ መደረግ የሌለበት ነገር ሲሆን ለመብቶቻቸው አበፈላጊ ወደሆነው ባለሥልጣን በመሄድ መከራከር እንዲችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ በምክር ፈላጊዎች ላይ የሚደረገው ውጫዊ የሆኑ የመብት ረገጣዎች እንዲነሡ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ይህ ጥብቅና መቆም በተለያዩ መንገዶች ይከናወናል፡ ከተመሳሳይ የሥራ ባልደረቦች ወይም ከመሰል ድርጅቶች ጋር በግል መነጋገር፣ የውይይት መድረኮችን በጉዳዮ ላይ ማዘጋጀት፣ ለሚመለከተው ክፍል ጉዳዮን በቃል ወይም በጽሑፍ ማሳወቅ ሊሆን ይችላል፡፡

በማማከር አገልግሎት የሚሰጠው ጥብቅና በአብዛኛውም ምክር ፈላጊዎች ለራሳቸው መብት መቆም እንዲችሉ ማስታጠቅ ነው፡፡ ለምሳሌ አንዲት ሴት በባልዋ የምትደበደብ ከሆነችና ወደ ማማከር አገልግሎት ከመጣች አማካሪው «ትዳርሽ ይሻልሻልና ዝም ብለሽ ታገሺ» አይላትም፡፡ ተደፍራ የመጣች ሴት ካጋጠመው አማካሪው አስፈላጊውን የማማከር አገልግሎት በመስጠት ሂደት ውስጥ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ የምትችልበትንም መንገድ እንድታይ ያግዛታል፡፡ በአብዛኛው አማካሪው በምክር ፈላጊዎቹ ቦታ ሆኖ አይቆምም፤ ሆኖም ከበስተጀርባ ሆኖ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ይህ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሥራ ሳይሆን የማማከር ሥነምግባርም የሚጠይቀው ኃላፊነት ነው፡፡

*ተገቢ ውሳኔዎችን ለመወሰን መርዳት፡-* ማንኛውም ሰው በሕይወት ጎዳና ላይ ብዙ ውሳኔዎችን ይወስናል፡፡ ሕይወት በውሳኔ የተሞላች ናት፡፡ ውሳኔ የሌለበት እርምጃ የለም፡፡ ውሳኔዎች ደግሞ ውጤት አላቸው፡፡ በጥሩ ሁኔታ ታስቦበት የተወሰነ ውሳኔ መልካም ውጤት ሲኖረው እንዲሁም ብዙ ሳይታሰብበት የተወሰነው ደግሞ ክፉ ብድራት አለው፡፡ ስለዚህ ምክር ፈላጊዎች በሕይወታቸው ወሳኝ የሆኑ ውሳኔዎች በሚወስኑበት ጊዜ የማማከር አገልግሎት ያስፈልጋቸዋል፡፡

አማካሪ ለምክር ፈላጊዎች ውሳኔ ባይወስንም ትክክለኛ ውሳኔ እንዲወስኑ የተሻለውን አማራጭ አብሮአቸው በመሆን እንዲመርጡ ያግዛቸዋል፡፡ ምክር ፈላጊዎች የሚወስኑት ውሳኔ የሚያስከፍላቸውን ዋጋ፣ የሚፈጀውን ጊዜና ጉልበት ከወዲሁ በማወቅ እንዲወስኑ ይረዳቸዋል፡፡ አማካሪው ምክር ፈላጊዎች ተገቢውን ውሳኔ ለመወሰን እንዲችሉ ትክክለኛውን መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ፣ የራሳቸው ወቅታዊ ስሜታቸው ጫና እንዳያደርግባቸው የሰከነ ስሜትና ሚዛናዊ አእምሮ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ እንዲሁም ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ ምክር ፈላጊዎች ያላቸውን እምቅ ችሎታዎችን/ዕድሎችን ይፈትሻል፡፡

ምክር ፈላጊዎች አንድን ውሳኔ ለመወሰን በሚያስቡበት ጊዜ ከአማካሪው ጋር በመሆን በእነዚህ እርጃዎች ውስጥ ያልፋሉ፡



- √ የምክር ፈላጊዎችን ዓላማ፣ እሴቶችና ዋናውን ጉዳይ ለይቶ ማወቅ፣
- √ ለጉዳዩ የሚበቃውን ተገቢ ጊዜና ኃይል መስጠት፣
- √ ሁለቱም በጋራ ሆነው ለጉዳዮ አማራጭ የመፍትሔ ሐሳቦችን ማፍለቅ፣
- √ በእያንዳንዱ አማራጭ መፍትሔ ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን መሰብሰብ፣
- √ አማራጭ መፍትሔዎችን አንድ በአንድ ጥቅምና ጉዳታቸውን ማውጣት፣
- √ አማራጭ መፍትሔዎቹን ከምክር ፈላጊዎቹ እሴት፣ ዓላማና ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ መገምገም፣
- √ ጊዜያዊ አማራጭ መፍትሔን ለማግኘት አነስተኛ ጥቅምና ከፍተኛ ጉዳት ያላቸውን መለየት፣
- √ ምክር ፈላጊዎችን ይህን መንገድ በመከተል ሌላ ጊዜ በራሳቸው መፍትሔዎችን እያወጡ መወሰን እንደሚችል ማስገንዘብ

በአጠቃላይ ምክር ፈላጊዎች ውሳኔ ማድረግ የሚቀላቸው አጠቃላይ የሆነውን አቅጣጫቸውን ሲያውቁ በመሆኑ ሂደቱን አስቀድሞ ለእነርሱ ማሳወቁ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ምክር ፈላጊዎች ውሳኔ ለመወሰን ሊቸገሩ ይችላሉ፡፡ አማካሪው ምክር ፈላጊዎች ውሳኔ መወሰን ሊያቅታቸው ምክንያቱን ለማወቅ እርምጃ መውሰድ ይገባዋል፡፡ ምክር ፈላጊዎች ተገቢውን ውሳኔ በተገቢው ወቅት እንዳይወስኑ እንቅፋት ከሚሆኑ ነገሮች መካከል ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

*ስለጉዳዮ ሌሎች ሰዎች ያላቸው አመለካከት፡-* በምክር ፈላጊዎቹ ቅርብ ያሉ ሰዎች ማለትም እንደ ቤተሰብ፣ ጓደኛና የሥራ ባልደረቦች እነርሱ ለማድረግ ስላሰቡት ጉዳይ ያላቸው አመለካከት ጥሩ ካልሆነ ውሳኔ ለማድረግ ይቸገራሉ፡፡ በዚህ ወቅት ምክር ፈላጊዎች እነዚህ ሰዎች የማይቀበሉትን ዓይነት ውሳኔ ቢወስኑ የሚያመጣባቸውን ኪሣራና ብድራት በሚገባ ለማወቅ ጊዜ ይወስዳሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በውስጣቸው የሚያምኑበትን ሳይሆን ሌሎች ከእነርሱ የሚጠብቁትን ነገር ለማድረግ ይወስናሉ፡፡ የራሳቸውን አመለካከት ትተው ሌሎች ሰዎችን ለማስደሰት የማያምኑበትን ነገር ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ጲላጦስ የሰዎችን አመለካከት በመከተል የማያምንበትን ውሳኔ ወስኖ ነበር (ማቴ27፡19-26)፡፡

*ምክር ፈላጊዎች የማይፈልጉትን እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ሲሆን፡-* አንዳንድ ጊዜ ውሳኔዎች ምክር ፈላጊዎች መሥራት የማይሹትን ነገር እንዲሠሩ የሚጠይቁ ይሆናሉ፡፡ ሥራውን ለመሥራት ውሳኔውን ላለማድረግ ይፈልጋሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ልጅ የቤት ሥራ መሥራትና ማጥናት የሚያስጠላው ነገር ግን ሁልጊዜ ከሠፈር ጓደኞቹ ጋር መሆን የሚያስደስተው ከሆነ ትምህርት ቤት ለማቋረጥ ወይም ለመቀጠል በሚያስብበት ጊዜ ሊቸገር ይችላል፡፡ ትምህርት እንዲቀጥል መወሰን እርሱ የሚጠላቸውን ነገሮች እንዲያደርግ ያደርጋል፡፡

*ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው አማራጮች ሲያጋጥሙ*፦ ምክር ፈላጊዎች ተመሳሳይ ውጤት ካላቸው አማራጮች መካከል የትኛውን መምረጥ እንደሚገባቸው ለመወሰን ያቅታቸዋል። ለምሳሌ ያህል፡ መጠነኛ ደመወዝና የዕድሜ ልክ ጡረታ ከሚያስገኝ ሥራና ከፍተኛ ደመወዝ ግን ጡረታ ከሌለው ሥራ መካከል አንዱን መምረጥ ያስቸግራል። በአንድ ጊዜ ሁለት ነገሮችን በተመሳሳይ ደረጃ መውደድ ለውሳኔ አስቸጋሪ ነው። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ስለሁለቱም ተጨማሪ መረጃዎችን በመፈለግ የተሻለውን አንዱን መምረጥ ይቻላል።

እንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጥሩ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱን መምረጥ ብቻ ሳይሆን ሁለት ከማይፈለጉ ነገሮች መካከልም አንዱን መምረጥ የሚያስፈልግበት ሁኔታ ያጋጥማል። ንጉሥ ዳዊት ከእግዚአብሔር ዘንድ ከመጡበት መቅሰፍቶች መካከል አንዱን እንዲመርጥ በተጠየቀበት ጊዜ የትኛውን እንደሚመርጥ ባለማወቅ እጅግ ተጨንቆ ነበር (2ሳሙ24:13-14)። ሆኖም ግራና ቀኙን አይቶ ካመዛዘነ በኋላ አንዱን መረጠ (2ሳሙ24:15)።

*በሁኔታዎች ተጽዕኖ ሥር መሆን*፦ ምክር ፈላጊዎች የራሳቸው የሆነ ነጻነት እንዳላቸውና መጠቀም እንደሚችሉ የማይሰማቸው ከሆነ ውሳኔ ለመወሰን ይቸገራሉ። በእነርሱ የመወሰን መብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያደርግ አካል ሲኖር ውሳኔ ለመወሰን አይችሉም። ምክንያቱም መብታቸውን ተግባራዊ እንዳያደርጉ የተጣለባቸው ገደብ በመኖሩ ነው። ለምሳሌ በገጠር ያለች አንዲት ሴት ልጅ ትምህርት መማር ከፈለገች በራስዋ ፈቃድ መማር አትችልም። በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ የሚሰጡት ወላጆችዋ እንደሆኑ ስለሚታመን ለእርስዋ ዕድል አይሰጣትም። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ያሉ ምክር ፈላጊዎች የራሳቸውን ውሳኔ መወሰን የሚችሉት ተገቢ በሆኑ መንገዶች ተጽዕኖዎቹን በማስወገድ ነው። በመንፈሳዊ እይታ ደግሞ ሰዎች በክፉ መንፈስ ተጽዕኖ ሥር በሚሆኑበት ጊዜ የሚፈልጉትን ገንቢ ውሳኔ ለማድረግ አቅም ያጣሉ።

*የስብዕና ችግር*፦ አንዳንድ ሰዎች ከስብዕና ችግር የተነሣ ምንም ውሳኔ በራሳቸው ማድረግ ይሳናቸዋል። ይህ ዓይነቱ የስብዕና ችግር የጥገኝነት ባሕርይን ያስከትላል። ያለ ሌሎች ሰዎች ተከታታይ ምክርና ድጋፍ በስተቀር የዕለት ተዕለት ሥራዎቻቸውን ለማከናወን የሚያስችል ቀላል የሚባሉ ውሳኔዎችን ለማድረግም ይቸገራሉ። ለምሳሌ ዝናብ በሆነ ቀን ጃንጥላ ይዘው ወደ ሥራ ቦታ መሄድ ወይም ገበያ ከሄዱ በኋላ ቡናማ ወይም ጥቁር ጫማ መካከል አንዱን መርጦ ለመግዛት ሲቸገሩ ይታያሉ። በሕይወታቸው ሌሎች ሰዎች ኃላፊነት ወስደው እንዲመሩአቸው ይፈልጋሉ። እነዚህ ሰዎች በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎችን ሰዎች ለማስደሰት የሚኖሩ በመሆናቸው ባይፈልጉትም ሌሎች ያሉአቸውን ነገሮች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይቀበላሉ።

*የውሳኔውን ውጤት መፍራት*፦ ውሳኔዎች ሁሉ ውጤት አላቸው። አንዳንድ ሰዎች ከመጠን በላይ ባለፈ ፍርሃት ውስጥ ሆነው «ይህ ቢሆን



እንዲህ ይሆናል» «ያ ቢሆን እንዲያ ይሆናል» ብለው ሳያቋርጡ ያስባሉ። በዚህ አሳባቸው ውስጥ አንዳንድ ከሁኔታው ጋር ግንኙነት የሌለውንም ነገር እያገናኙ ስለሚያስሳስሉ አንድ እርምጃ መውሰድ የሚያስችላቸው ፍርሃትና ጥርጣሬ ውስጥ ይገባሉ። ይህ ፍርሃት በራስ የመተማመን መንፈስ ወይም ተገቢ መረጃ ከማጣት የሚመነጭ ሲሆን ይችላል።

እንግዲህ የማማከር አገልግሎት ምክር ፈላጊዎች ይዘው የሚመጡትን ጉዳይ መሠረት በማድረግ፣ ሥነምግባር ባለው ሂደት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንዲችሉ እገዛ የሚደረግበት ሥራ ነው። አማካሪው ከምክር ፈላጊዎቹ ጋር አብሮ የሚጓዝ ሁኔታ አመቻቺ እንጂ ውሳኔ ሰጪ አይደለም። በማማከር ሂደት ውስጥ አማካሪው የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ ስለማማከር ሂደት ከማየታችን በፊት ስለአማካሪው ባሕርያት በጥልቀት መረዳት አስፈላጊ ነው። የሚቀጥለው ምዕራፍ በዚህ ርዕስ ላይ ሰፋ ያለ ትምህርት ይዟል።

# ምዕራፍ 2

## የሥነልቦና አማካሪ ባሕርያት

### *2.1. የሥነልቦና አማካሪ ማን ነው?*

በአጠቃላይ አነጋገር አማካሪ ማለት ስለአንድ ነገር ጠለቅ ያለ እውቀትና ልምድ ኖሮት ያን ጉዳይ በተመለከተ ጠቃሚ ምክር ሊሰጥ የሚችል ባለሙያ ማለት ነው፡፡ ስለሚያማክረው ጉዳይ ሰፊ እውቀት ያለው በመሆኑ ጉዳዩን ከብዙ አቅጣጫዎች በመመልከት ጥቅሙንና ጉዳቱን ለይቶ ማሳወቅ የሚችል ሰው ነው፡፡

በማማከር አገልግሎት ውስጥ አማካሪ የሚባለው በአብዛኛው ከሥነልቦና ሥራ ጋር በተገናኘ መልኩ ነው፡፡ የሥነልቦና አማካሪ ማለት ከምክር ፈላጊዎች በቂና ሚዛናዊነት ያለው ግንዛቤ በማግኘት ምክር ፈላጊዎች የራሳቸውን ችግሮችና መንስኤዎቻቸውን በትክክል ተረድተው ተገቢውን መፍትሔ ፈልገው ማግኘት እንዲችሉ ሁኔታዎችን የሚያመቻች አገልጋይ ወይም የሥነልቦና ባለሙያ ነው፡፡

የሥነልቦና አማካሪ በተናጠል ለግለሰቦች እንዲሁም ተመሳሳይ ችግር ያላቸውን ምክር ፈላጊዎችን አንድ ላይ በመሰብሰብ የማማከር አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡ አማካሪ ምክር ፈላጊዎች በትምህርት ቤት፣ በሥራ ቦታዎችና በአገልግሎት ሰጪ ተቋሞች አካባቢ በመሆን በዚያ ያሉትን ወይም እዚያ የሚመጡትን ሰዎች መርዳት ይችላል፡፡ አማካሪ ምክር ለጥቶ መሸኘት ብቻ ሳይሆን ምክር ፈላጊዎች በማማከር ሂደት ያገኙትን ግንዛቤ ምን ያህል እንደ ተጠቀሙበት፣ የማማከር ዘዴዎች ምን ያህል ስኬታማ እንደሆኑ እንዲሁም አገልግሎት በሚሰጥበት አካባቢ ያሉትን የብዙዎች ችግርና መንስኤዎቹ ምን እንደሆኑ ለማወቅ ክትትልና ጥናት ያደርጋል፡፡

አማካሪ የተለያዩ የማማከር ዓይነቶችን መስጠት ይችላል፡፡ እነዚህ ተግባሮች ተቀራራቢና ተደጋጋፊ ናቸው፡፡ (1) አማካሪ፣ አጠቃላይ የችግር መንስኤ በሆኑት ጉዳዮች ላይ ትምህርቶችን ይሰጣል፡፡ ሰዎች ወደ ችግር እንዳይገቡ እንዲሁም ሕይወታቸውን በመልካም አቅጣጫ መምራት እንዲችሉ ያስተምራል፡፡ (2) አማካሪ፣ ችግርን አስቀድሞ የመከላከል ምክር ይሰጣል፡፡ አማካሪው በሚያገለግልበት አካባቢ ሰዎችን የሚያጠቃ ችግር በሚኖርበት ጊዜ ሰዎች በዚያ ችግር እንዳይጠቁ የመከላከል ትምህርት ይሰጣል፡፡ ሰዎች ችግሩን እንዴት መከላከል እንደሚችሉ ገንቢ አርምጃዎችን ያስተምራል፡፡ (3) በችግር ውስጥ የገቡ ሰዎች ከዚያ ለመውጣት የሚችሉበትን አማራጭ መንገዶችን ያሳያቸዋል፡፡



### *2.2. የመልካም አማካሪ ባሕርያት*

የማማከር አገልግሎት የሚኖረው አማካሪ ሲኖር ነው፡፡ አንድ አማካሪ አገልግሎቱን በሚገባ መወጣት የሚችለው እንደ አማካሪ መልካም ባሕርያት ሲኖረው ነው፡፡ አንተ አንድ ምስጢራዊ የሆነ የግል ጉዳይ ቢኖርህ ለማን ትነግራለህ? ምን ዓይነት ሰው ትፈልጋለህ? ምክር ፈላጊዎች ለማማከር የሚፈልጓቸው ሰዎች/አማካሪዎች/ ማንነት ምን ይመስላል? ከሌሎች የሚለዩአቸው ባሕርያት ምንድናቸው ?

የማማከር አገልግሎት ስኬታማነት በከፊል በአማካሪው ማንነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ መልካም የሚባሉ የአማካሪ ባሕርያት በተፈጥሮ ያገኛቸው ብቻ ሳይሆኑ በሂደት የሚገኙ ናቸው፡፡ ከእናቱ ማህጸን ሲወጣ ጥሩ አማካሪ ሆኖ የሚወለድ ሰው የለም፡፡ የአንድ ጥሩ አማካሪ ባሕርያትን ለመያዝ በሂደት መሠራትን ይጠይቃል፡፡

እያንዳንዱ ሰው ጥሩ አማካሪ ስለሚባለው ሰው በአእምሮው ውስጥ የሚኖረው ሥዕላዊ መግለጫ ይኖራል፡፡ ባሕርያቱ ዓውዳዊ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ በእያንዳንዱ ዓውድ ውስጥ ያለውን የመልካም አማካሪ ባሕርያትን መዘርዘር አስቸጋሪ ቢሆንም በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ አንድ አማካሪ ሊኖረው የሚገባውን ማንነት ለመግለጽ ይሞከራል፡፡ እነዚህ ባሕርያት ለማማከር አገልግሎት ውጤታማነት የሚያግዙ፣ በተፈጥሮ ወይም ከልምድ የተገኙና ሁልጊዜ የሚሻሻሉ ናቸው፡፡

#### *እውነተኛነት*

አማካሪ ማለት ሰዎች በሚቸገሩበት ጊዜ የተለያዩ ምትሐታዊ ዘዴዎች በመጠቀም መፍትሔዎችን የሚሰጣቸው ሳይሆን የራሱ ስብዕና እንዲሁም የሕይወት ዘይቤ ያለው ሰው ነው፡፡ ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበት እምነትና የአገልግሎት ዘይቤ አለው፡፡ ክርስቲያን አማካሪ ከሆነ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ያምናል፡፡ በዚያ ውስጥ የሚገኘውንም እውነት በሕይወቱ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ለሰዎች የሚሰጠውም አገልግሎት የሚመነጨው ከዚህ እምነቱ ነው፡፡ እምነቱን በሕይወቱ በተጨባጭ የሚኖርበት ከሆነ በችግር ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለመርዳት አቅም ይኖረዋል፡፡ እምነቱና ኑሮው ካልተገናኙ ግን በሌሎች ላይ ሊያመጣ የሚችለው አምንታዊ ተጽዕኖ አናሳ ይሆናል፡፡ ለክርስቲያን አማካሪ ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ መንፈሳዊ ልምምድም አስፈላጊ ነው (የሐሥ19:15-16)፡፡

የሚያምነውን በሕይወቱ የማይኖር ሰው ምክር ፈላጊዎችን በተገቢው ሁኔታ ሊረዳቸው አይችልም፡፡ ለራሱ መኖር ያልቻለ ሰው እንዴት ሌሎችን በሚፈለገው መጠን መርዳት ይችላል? ስለዚህ አማካሪ በሕይወቱ ውስጣዊና ውጫዊ ገጽታዎች መካከል መጣጣም ሲኖረው ያስፈልጋል፡፡ በአእምሮው ውስጥ ያለው እምነት/ፍልስፍና በድርጊቱ የሚገለጽ መሆን አለበት፡፡

በእምነቱና በሕይወቱ መካከል መጣጣም ሲኖር እንደ «አንድ» ሰው መኖርና ማገልገል ይችላል፤ ምስክርነቱም በሌሎች ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ያመጣል።

የአንድ አማካሪ ውስጣዊና ውጫዊ ሕይወቱ መጣጣም አለበት ማለት በሌላ አነጋገር አማካሪ ራሱን ሆኖ መኖር አለበት ማለት ነው። ምክር ፈላጊዎችን ለመርዳት ብቻ ብሎ በእውነት ያልሆነውን ሰው መስሎ መመሳሰስ የለበትም። እውነተኛ ማንነቱን ክዶ ሌላ ለመሆን ጥረት ማድረግ በራሱ ችግር ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ምክር ፈላጊዎችን መርዳት አይቻልም። አማካሪ በሌላ ጊዜ የሌለውን ባሕርይ በማማከር ወቅት ብቻ የሚያሳያቸው ከሆኑ ግብዝነት ነው። በተለይ ምክር ፈላጊዎቹ ከማማከር ውጭ ሕይወቱን የሚያውቁ ወይም ማየት የሚችሉ ከሆነ በእንዲህ ዓይነት ማንነት በአገልግሎቱ ፍሬ ማፍራት አይታሰብም። ስለዚህ ሌሎችን ለመርዳት ከመሄዱ በፊት በራሱ ላይ መሥራት ይገባዋል።

በማማከር አገልግሎት ውስጥ አማካሪው ራሱን ሆኖ መገኘት አለበት ማለት በውስጡ የሚሰማውን ሐሳብና ስሜት መግለጽ አለበት ማለት ነው። ከምክር ፈላጊዎች ጋር ባለው ግንኙነት በውስጡ የሚሰሙት ስሜቶች ይኖራሉ። እነዚያን ስሜቶች በማፈን ለማማከር ጥረት ለማድረግ ቢሞክር በሂደት አገልግሎቱን የሚጎዱ ሁኔታዎች ይከሰታሉ። እነዚህ ስሜቶች ለለምክር ፈላጊዎች ያለው አይታና የሚሰማው ስሜት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል በምክር ፈላጊው ላይ የቁጣ ስሜት ሊፈጠር ወይም ተቃራኒ ጾታ ሊሆን በውስጥ የወሲብ ስሜት መቀስቀስ ዓይነት ሁኔታዎች ሲከሰቱ አማካሪ እውነተኛ መሆን አለበት ስለተባለ መግለጽ አለባቸውን? አንድ አማካሪ «ባሕርዬ ነው» ብሎ በማማከር ሂደት ውስጥ የማይፈለጉ ድርጊቶችን ማድረግ የለበትም። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ስሜቶች መገለጽ ቢኖርባቸውም የሚገለጹት ለምክር ፈላጊዎቹ ሳይሆን በሌላ ተገቢ ሥፍራ ነው። እውነተኛ ለመሆን መገለጽ አለባቸው፤ ሆኖም በምክር ፈላጊዎቹ ፊት መናገር ትክክለኛ ቦታው አይደለም። ይህን ለመግለጽ ተገቢው ሥፍራ የት እንደሆነ በዚሁ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ እናገኘዋለን።

እውነተኛ ሆኖ መገኘት የራስንም የእውቀት፣የልምድና የብቃት ውስንነትንም በማወቅ ለምክር ፈላጊዎቹ የሚበጀውን እርምጃ መውሰድንም ያመለክታል። አማካሪ ሁሉንም ነገር አያውቅም፤ ለሁሉም ችግሮች መፍትሔ እንዲገኝ ሁኔታዎችን ሊያመቻች አይችልም። ስለዚህ ከብቃቱ በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥመው ይህን ጉዳይ ለመፍታት በሚደረገው ሂደት ብቃት እንደሚያንሰው በመግለጽ ከእርሱ የላቀ እውቀትና ልምድ ወዳለው ሌላ አማካሪ ሊመራው ይገባል። አማካሪ «ይህን ችግር እኔ መያዝ አልችልም»፣ ወይም «ይህ ጉዳይ ከአቅሜ በላይ ነው»፣ «በዚህ ጉዳይ ላይ አገሌ ወይም አገሊት ከእኔ የተሻሉ ናቸው» ብሎ መናገር መቻል አለበት። እንዲህ ለማድረግ የማይቻል ከሆነ አስቀድሞ እራሱ በማማከር አገልግሎት ውስጥ በማለፍ ችግሮቹን መፍታት ያኖርበታል።

የአማካሪው እውነተኛነት የሚታየው ከምክር ፈላጊዎቹ ውጭ በሥራ ባልደረቦቹም ዘንድ ነው። ለሰራሱና ለለአገልግሎቱ በባልደረቦቹ



በሚጠየቅበት ጊዜ የሆነውን ነገር ግልጽ አድርጎ መናገር የሚችል መሆን አለበት። የራሱን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በግልጽ መናገር የሚችል ከሆነ ራሱን ይበልጥ እየተቀበለና ትክክለኛ ማንነቱ ጎልቶ እየወጣ ይሄዳል። ከዚህም በተጨማሪ ከሌሎች ሰዎች ስለራሱ የሚያገኘው መረጃ፣ ሕይወቱን እንዲፈትሽና የበለጠ ራሱን እንዲያውቅ ያግዘዋል። አማካሪው ስለራሱ ከሚሰው በላይ ስለእርሱ ሌሎች የሚሉት ነገር መስታወት ሆኖ ራሱን በሚገባ እንዲያይ ያደርጋል። ይህ ደግሞ ዕለት ተዕለት ሕይወቱ በተሻለ የባሕርይ ቀርጻ ሂደት ውስጥ እንዲያልፍ ለለሚያግዝ ግብዝነትና ተለዋዋጭነት የሌለበትን ማንነት በመያዝ እንዲመላለስና እንዲያገለግል ዕድል ይሰጠዋል።

## *ሁኔታዎችን ከምክር ፈላጊው እይታ የመተርጎም ባሕርይ*

በማማከር ሂደት ውስጥ እማካሪ የምክር ፈላጊዎችን አጠቃላይ ሁኔታ ከችግሩ ጋር በማማያዝ ይተረጉማል። ምክር ፈላጊዎች ችግሮቻቸውን ከተናገሩ በኋላ አማካሪው የመተርጎም ሥራ ይጀምራል። በትርጉም ወቅት አማካሪው የምክር ፈላጊዎቹን ሁኔታ በራሱ እይታ ወይም በምክር ፈላጊው እይታ ሊመለከት ይችላል። አማካሪው የምክር ፈላጊዎቹን ችግር ከራሱ እይታ አንጻር መመልከትና መተርጎም የለባቸውም፤ ምክንያቱም እምብዛም ጥቅም ለለማይኖረው ነው። አማካሪው ከእውቀቱ፣ ከልምዱና በግል ሕይወቱ ከገጠማቸው ሁኔታዎች በመነሳት የምክር ፈላጊዎችን ችግር መተርጎም አይገባውም ። ነገር ግን ራሱን በምክር ፈላጊዎች ሥፍራ በማስቀመጥ ከእነርሱ እይታ አንጻር ችግሮቻቸውን ማየት ቢችል ይበልጥ ይረዳቸዋል።

አማካሪው የሌሎችን ችግር ከራሱ አይታ እንዲመለከት ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ ራሱን በሚገባ አለማወቁ ነው። አማካሪ የራሱ የሆነ ችግር ይኖረዋል። ነጻ በሆነ አእምሮ የምክር ፈላጊዎቹን ዓለም ከመመልከት ይልቅ የራሱን መነጽር ተጠቅሞ የእነርሱን ችግር እንደ ራሱ ችግር ይመለከታል። ይህ ደግሞ አማካሪው የምክር ፈላጊዎችን ችግር ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ በመረዳት እንዳይረዳቸው እንቅፋት ይሆናል። እንግዲህ እንዲህ ዓይነቱን ችግር ለማስወገድ እማካሪው ከራሱ ችግር ጎጆ ውስጥ መውጣት አለበት። እርሱም ራሱ የማማከር አገልግሎት ሊያስፈልገው ነው።

አማካሪው የምክር ፈላጊዎችን ችግር ከራሱ እይታ እንዲተረጉም ከሚያደርጉ ነገሮች ሌላው፣ አማካሪው ብዙ ልምድና እውቀት ያለው መሆን ነው። ከማማከር ልምዱ በመነሳት፣ የምክር ፈላጊዎችን ችግር ሌሎችን ያስተናግድ በነበረው መንገድ ለማስተናገድ ጥረት ያደርጋል። የሰዎችን ችግር ለመተርጎም የሚያስችለውን ቀመር እንዳዘጋጀ ሰው በአንድ መንገድ /ዘዴ/ ብቻ ችግሮችን ለመረዳትና ለመፍታት በሚያደርገው እርምጃ ከምክር ፈላጊዎች ጋር ያለው ግንኙነት ይበላሽበታል።

አማካሪው በዕድሜ የበለሰ ሆኖ ምክር ፈላጊዎቹ ደግሞ ወጣቶች በሚሆኑበት ወቅት አማካሪው የወጣቶቹን ችግር በራሱ እይታ የማየት

ሁኔታ ያጋጥማል። በእንዲህ ባለ ሁኔታ የአማካሪውና የምክር ፈላጊው ዓለም የተለያየ በመሆኑ የአነጋገር፣ የአመለካከትና የፍላጎት ልዩነት በመካከላቸው ይኖራል። አማካሪው ምክር ፈላጊ ወጣቶቹን ለማስተማር፣ ለመገሰጽና ችግሮቻቸውን እንደ ቀላል ነገር የመቁጠር አዝማሚያ ሲያሳይ አማካሪው ሊጠቅማቸው እንደማይችል በመረዳት ይሸሹታል። እንዲህ ዓይነቱ አማካሪ ከልምዱ በመነሳት ለወጣት ምክር ፈላጊዎች ሊያካፍላቸው የሚችላቸው ነገሮች ቢኖሩትም እነርሱን ለመረዳትና ለመርዳት ግን በእነርሱ ሥፍራ ሆኖ ችግራቸውን መመልከት ቢችል ወደሚፈለገው የማማከር ውጤት ያመራል።

እንግዲህ መልካም ባሕርይ ያለው አማካሪ ምንም ያህል ልምድና ብስለት ቢኖረውም ምክር ፈላጊዎች የእርሱን መነጽር ወስደው ዓለማቸውን እንዲያዩ ማድረግ ሳይሆን እርሱ የራሱን መነጽር አውልቆ የእነርሱን በመውሰድ በዚያ የእነርሱን ዓለም ለማየት ጥረት ያደርጋል። የአማካሪው ብስለትና ብቃት አንዱ የሚለካው በዚህ ነው።

### *ሚዛናዊ አመለካከት*

የአማካሪ አመለካከት በማማከር ሂደት ውስጥ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ አለው። ብዙዎች ስለአማካሪው እውቀትና ልምድ ቢመሰክሩለትም ሚዛናዊ እይታ ከሌለው ብዙዎችን ሊረዳ አይችልም። እውቀትና ልምድ ያለ ሚዛናዊ አመለካከት የሚፈለገውን ውጤት አያስገኝም። ስለዚህ ጤናማ የሆነ የሕይወት ፍልስፍና ያለውና ይህንን በተግባር የሚያሳይ መሆን አስፈላጊ ነው። አንድ አማካሪ ከማማከር ጋር በተገናኘ ሁኔታ ሊኖረው የሚገባው አመለካከት/እይታ፣

- √ ምክር ፈላጊዎች ሁሉ ዋጋ ያላቸው ሰብዓዊ ፍጡራን ናቸው። ስለዚህ ለሁሉም ተገቢ አክብሮት ይገባል።
- √ ምክር ፈላጊዎች በእምነት/ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፤ ሁሉም ተገቢውን የማማከር አገልግሎት ማግኘት አለባቸው፣ በሂደቱ ላይ አሉታዊ ጫና ሊደረግባቸው አይገባም።
- √ ለሁሉም ሰው ተገቢውን ሙያዊ እንክብካቤ መስጠት የሙያ ግዴታና ሰብዓዊነትም ነው።
- √ ምክር ፈላጊዎች ችግሮቻቸውን መፍታት የሚችሉበት እምቅ ችሎታ አላቸው። በማማከር ሂደትም ይህን መጠቀም እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል።
- √ ሰለዎች ሕይወት ሰኬት ሁለንተናዊ እይታ አለው። ሰዎች በግል፣ በማህበራዊና መንፈሳዊ ሕይወታቸው ፍሬያማዎች እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

አማካሪ በአመለካከቱ በሰዎች መካከል ልዩነትን የማያደርግ፣ በአቀራረቡ ደግሞ ለሁሉም ተንከባካቢ፣ ሰምክር ፈላጊዎች ሁሉ ቅን አይታና ልባዊ ፍቅር ያለው፣ ሰምክር ፈላጊዎች ሁሉ ችግሮቻቸው ተፈትተው ሕይወታቸው ሰምልሞ ማየት የሚናፍቅና በዚህ ደስ የሚለው እንዲሁም



በመስተንግዶው አድልዎ የማያደርግ ሊሆን ይገባል። እንዲህ ዓይነት አመለካከት በሚኖርበት ጊዜ የማማከር አገልግሎት ፍሬ ያለው ይሆናል።

አማካሪ በሚያገለግልበት ማህበረሰብ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ማለትም የተማሩትንና ያልተማሩትን፣ ሀብታምና ደሃ፣ ወንድና ሴትን እንዲሁም ወገንና ባዕድን በሚያስተናግድበት ጊዜ ልዩነት ማድረግ የለበትም።

### *ግትርነት የማይታይበት*

አማካሪ ግትር መሆን የለበትም። አማካሪ በአሠራሩ ምክር ፈላጊዎችን የበለጠ ለመረዳትና ለመርዳት በአቀራረቡ እንደ ሁኔታው አቋሙን ማለሳለስ ይኖርበታል። ይህም ማለት ሰብዓዊ ርኅራኄ በማሳየት፣ መሥመሩን ሳይለቅ ወይም መሠረታዊ አቅጣጫውን በመያዝ በተለያዩ መንገዶች በመጠቀም ወደሚፈለገው ግብ መሄድ ማለት ነው። አንዳንዶች፣ ለችግር መፍትሔዎችን ማግኘት የሚቻለው በአንድ መንገድ ብቻ እንደሆነ ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ መስመራቸውን ለቀው ምክር ፈላጊዎች ወደሚወስዱአቸው ሁሉ ይሄዳሉ። ሁለቱም መንገዶች ወጣ ያሉ አቀራረቦች ናቸው።

እኔ ባደግኩበት አካባቢ ያስተዋልኩት አንድ ነገር ነበር። አንዳንድ ሀብታም ገበሬ የሆኑ ሰዎች በቅሎ ይኖራቸዋል። አንዳንዱ ሰው በቅሎ ላይ መውጣትን የለመደው ከሆነ የሚወጣው በግራ በኩል ብቻ እንደሆነ ያስባል። ለማጅ ሰው ሊመጣ በቅሎ ላይ የሚወጣው በግራ በኩል ነው ብሎ ያስተምራል። በቀኝ የለመደውም በቅሎ ላይ የሚወጣበት ትክክለኛው አቅጣጫ በቀኝ በኩል እንደሆነ ያምናል፣ ያስተምራልም። እነዚህ ሁለቱም አቅጣጫዎች ትክክል ናቸው። በቅሎ ላይ በግራም በቀኝም መውጣት ይቻላል። አንዱ ብቻ ነው ትክክል ብሎ ማለት በሌላ በኩል ግብ መድረስ አይቻልም እንደ ማለት ነው። ምክር ፈላጊዎች ለችግሮቻቸው መፍትሔ እንዲያገኙ መርዳት የሚቻልባቸው አያሌ መንገዶች አሉ። ስለዚህም አማካሪ ግትርነትን በማስወገድ የተለያዩ አቀራረቦችን መከተልና ሰየሁኔታው የሚሻለውን መንገድ መምረጥ ይችላል።

ግትር ባሕርይ ያላቸው አማካሪዎች ምክር ፈላጊዎችን ለማወቅና ለመርዳት እምብዛም አይቀናቸውም። በአእምሮአቸው ውስጥ ቀድሞ ሥፍራ በያዘው አሳብ ብያኔ ለመስጠት ይቸኩላሉ። በራሳቸው «ትክክለኛ ነው፣ እንዲሁም ለሌሎች ያስፈልጋቸዋል» ብለው ከሚያምኑት መረጃ ውጭ የሆኑትን ነገሮች ሰማስተናገድ ፍላጎት የላቸውም። የምክር ፈላጊዎችን ችግር እንዳለ ሰመቀበል አእምሮአቸው ክፍት አይደለም።

### *ሰዎችን የመሳብ ችሎታ ያለው*

ምክር ፈላጊዎችን የመሳብ ችሎታ ያላቸው አማካሪዎች ተወዳጅነት አላቸው። ይህ ችሎታ ሰዎች ወደ አማካሪው እንዲመጡና ለችግራቸው

መፍትሔ እስኪያገኙ ድረስ በማማከር ሂደት ውስጥ እንዲቆዩ የሚያደርጉ ባሕርያት ናቸው። ከእነዚህ ባሕርያት አንዳንዶቹ ውጫዊ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ውስጣዊ ናቸው። ከውጫዊ ባሕርያት መካከል የአማካሪው ቁመና፣ አለባበስ፣ አቀራረብና ዝናው ሲሆኑ ውስጣዊ የሚባሉት ደግሞ ተንከባካቢነት፣የማማከር እውቀት፣ ልምድና ብቃቱ ናቸው።

ሰዎች ወደ አማካሪ የሚመጡት የተለያዩ ሁኔታዎችን በመምረጥ ነው። ምርጫቸው እንደየምክር ፈላጊዎቹ ባሕርይና ባሕላዊ ሁኔታ የተለያየ ነው። በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ሰዎች ወደ አንድ አማካሪ ለመሄድ ሲፈልጉ የሚያነሱአቸው ጥያቄዎች ይኖራሉ። ከአነዚህም መካከል የአማካሪው ትምህርት፣ ልምድ፣ ዕድሜ፣ ጾታ፣ ሃይማኖትና የሌሎች ሰዎች ምስክርነት የሚጠቀሱ ናቸው። በእነዚህ ጉዳዮች መልስ ሲያገኙ ከፍላጎታቸው ጋር የሚጣጣም ሆኖ ሲያገኙት ወደ አማካሪው ይሄዳሉ።

*ትዕግስተኛ*

የማማከር አገልግሎት ትዕግስትን ይጠይቃል። ይህን በሁለት መልክ መመልከት ይቻላል። በአንድ በኩል የማማከር አገልግሎት ፍሬው ወዲያውኑ ላይታይ የሚችል ሥራ በመሆኑ ቶሎ ውጤቱን ማየት የሚፈልግ ሰው በአገልግሎቱ ውስጥ ሳይዘልቅ ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ምክር ፈላጊዎች የሚያመጡአቸው አንዳንድ ጉዳዮች በአማካሪው ውስጥ የሚፈጥሩት ስሜት ትዕግስትን የሚፈታተኑ መሆናቸው ነው። ስለዚህ በማማከር ሂደት ውስጥ ስለሚኖረው ትዕግስት ከሚፈጸሙ ከስተቶችና ከአገልግሎቱ ጸባይ ጋር በማማያዝ መመልከት እንችላለን።

ምክር ፈላጊዎች ወደ ማማከር አገልግሎት የመጡት ለችግራቸው መፍትሔ ፈልገው ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ችግራቸውንም በግልጽ መናገር አይፈልጉም። በቀጥታ ችግራቸውን «የእኔ ችግር እንዲህ ነው» ብለው ለመናገር ፈቃደኞች አይሆኑም። ዋናውን ነገር ትተው ዙሪያ ጥምጥም ይዞራሉ። በዚህ ጊዜ የአማካሪው ትዕግስት ይፈተናል። «ችግርህን ከነገርከኝ በግልጽ ንገረኝ፣ አለበለዚያ ...» ማለት የለበትም። ምንም ቢሆን አማካሪ ትዕግስት ካለው ምክር ፈላጊዎች ዋናው ነገር ደብቀው ከሚናገሩአቸው ነገሮች በመነሳት ስለእነርሱ መረጃዎችን መሰብሰብ ይችላል። ለማማከር የሚመጡ ሰዎች ችግራቸውን በትክክል ላያውቁትም እንደሚችሉ መረዳት፣ እና ድብቅ ባሕርይ ያላቸው ሰዎችም መኖራቸውን ማወቁ አማካሪው በትዕግስት እንዲይዛቸው ያደርገዋል። አንዳንድ ጊዜ ምክር ፈላጊዎች ወደ ማማከር አገልግሎት የሚመጡት ግራ ተጋብተው ስለሆነ የትኛው ዋና ችግራቸው እንደሆነም አያውቁትም። ስለዚህ ከመሰላቸው ነገር ጀምረው መተረክ ይቀጥላሉ።

የማማከር ሂደት በሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ አጥጋቢ ውጤት ላያስገኝ ይችላል። ምክር ፈላጊዎች ቶሎ ለውጥ እንዲያሳዩ መርዳት ቢቻልም ብዙ ሁኔታዎች ፍሬው የሚታይበትን ጊዜ ርዝመት ይወስናሉ። ስለዚህ ትዕግስት ያለው አማካሪ ለጊዜው በአገልግሎቱ የሚረካበትን ጊዜያዊ



ውጤት ከመሻት ይልቅ በረጅም ጊዜ የሚገኝ ለውጥን ይመርጣል። ገንቢና ዘላቂነት ያለው ለውጥ የሚመጣው ተመጣጣኝ ጊዜ ተወስዶ ከተሠራበት ብቻ እንደሆነ በትክክል ይረዳል።

በተጨማሪም በማማከር አገልግሎቱ የሚያበረታታው አካል ወይም ሰው ባይኖርም ይህ ራእዩና ጸጋው ስለሆነ ከሰዎች ዘንድ ምንም «አይዞህ ባይ» ባያገኝም በጽናት አገልግሎቱን መስጠት አለበት። እርሱ የሚሠራቸውን ሥራዎች ብዙዎች ሳያውቁት ይችላሉ። ስለማማከር አገልግሎት አጠቃላይ ሐሳብ ቢኖራቸውም በዚህ አገልግሎት ውስጥ ምን ያህል ሰዎች ተጠቃሚ እንደሆኑና ለውጡ ምን ያህል እንደሆነ መገምገም የሚቻልበት መንገድ ቀላል ባለመሆኑ ላያደንቁ ይችላሉ። ይህ ሲሆን አገልግሎቱን ለማቋረጥ የማያስብ በትግዕስት የሚጸና ሰው መሆን አለበት።

ትዕግስት ከስሜት ስክነትም ጋር የተያያዘ ነው። በማማከር አገልግሎት ውስጥ የሚከሰቱ አንዳንድ ነገሮች ስሜትን የሚረብሹ ናቸው። አማካሪው ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ ሂደቱን እንዳይመራ ስሜታዊ እንዲሆኑ ሲያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ሲፈጠሩ አማካሪው ሁኔታዎችን በትክክል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መመልከትና ተገቢውን እርምጃ መውሰድ የሚችል ሲሆን የስሜት ስክነት አለው ማለት ነው። ይህም ማለት ያልተጠበቁ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ረጋ ባለ መንፈስ ወደ ትክክለኛው ግብ መድረስ መቻል ማለት ነው።

ወደ ማማከር አገልግሎት የሚመጡ ምክር ፈላጊዎች የተለያየ አስተሳሰብና ችግር አላቸው። እነርሱ ይዘው የሚመጡት ሐሳብና ችግር ከአማካሪው አስተሳሰብና እምነት ጋር አብረው የማይሄዱ ሲሆኑ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ አማካሪው የራሱን አስተሳሰብና እምነት በመያዝ የማያምንባቸውና የማይቀበላቸው ነገሮች ቢሆኑም የአከራሪነት መንፈስ ሳይታየው በተረጋጋ መንፈስ ምክር ፈላጊዎቹ ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ መምራት አለበት።

በተለይ አንዳንድ ምክር ፈላጊዎች ይዘው የሚመጡት ጉዳይ የአማካሪው ስሜት የሚረብሹ ሲሆኑ ይችላሉ። «ሰዎች እንዲህ ያደርጋሉ» ተብሎ የማይታሰበውን ጉዳይ ይዘው ይመጣሉ። ለምሳሌ ያህል አንዲት ሴት መጥታ «እኔ ትዳር ከመሠረትኩ ሰባት ዓመት ሆኖኛል! ነገር ግን እስካሁን ድረስ ወሲብ አልፈጸምኩምና ምን ላድርግ?» ብላ ልትጠይቀው ትችላለች።

አንድ የታወቀ አገልጋይ ይመጣና «እኔ ባለትዳር ነኝ። ከማገለግላቸው ክብዙ ሴቶች ጋር ዝሙት ፈጽሜአለሁ። አሁን በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ገብቻለሁ። እባክህን እርዳኝ!» ይላል። ሌላው ጎልማሳ «እኔ ከሌላ ሴት ልጅ ወልጃለሁ፣ ነገር ግን ባለቤቴና ልጆቼ አያውቁም። አሁን የህሊና ወቀሳ እየተሰማኝ እንዲሁም ብታወቅብኝስ እያልኩ በፍርሃት ውስጥ ነኝ። እባክህን እድነኝ!» ብሎ ሊመጣ ይችላል።

ችግሮች መፍትሔ የሚሰግስ ሰው እንደሆነ አድርጎ ራሱን እንዳይቆጥር ያደርገዋል።

በአጠቃላይ አማካሪ ባሰው ብቃት ተጠቅሞ በተለያየ ችግር ውስጥ ወድቀው ሕይወታቸውን በተገቢው ደረጃ መምራት ያልቻሉት ምክር ፈላጊዎች ከወደቁበት እንዲነሱ፣ የሕይወት ራእያቸውን እንዲያድሱ፣ እና እስፈላጊውን ተግባራዊ እርምጃ ወስደው ካሰሙት ግብ መድረስ እንዲችሉ በትጋት ይሠራል። እሁን በሕይወታቸው ስኬታማ እየሆኑ ያሉ ደግሞ ከሆኑት በላይ መሆን እንዲችሉ ከጎናቸው ሆኖ ይደግፋቸዋል።

*የምክር ፈላጊዎችን የሕይወት ፍልስፍና ማክበር*

አማካሪ የራሱ የሆነ የሕይወት ፍልስፍና እንዳለው ሁሉ ምክር ፈላጊዎችም የራሳቸው የሕይወት ፍልስፍናና ዘይቤ አላቸው። አማካሪ በሚሰጠው የማማከር አገልግሎት ወቅት በምክር ፈላጊዎች የሕይወት ፍልስፍና ላይ እሉታዊ ጫና ማድረግ የለበትም። የራሱን እሴት (ሥነምግባር) በምክር ፈላጊዎች ላይ መጫን አይገባውም። በማማከር አገልግሎት ውስጥ እማካሪው ለምክር ፈላጊዎች ስለእሴት አያስተምራቸውም። ስለእነርሱ የሕይወት ፍልስፍና የሚወሳው ችግራቸውን ለማወቅ በሚደረግበት ውይይት ውስጥ ነው። ምናልባት የሕይወት ዘይቤያቸው የችግራቸው መንስኤ የሚሆን ሁኔታ ካለ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በመነጋገር ግንኙነቱን ነቅሶ በማውጣት እንዴት መቅረፍ እንደሚቻል ማሳየት ይቻላል። የምክር ፈላጊዎቹ የሕይወት ፍልስፍና በሕይወታቸው ላይ እሉታዊ ተጽዕኖ ሳይኖረው በገንቢ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ የሚቻልበትን እማራጭ መንገድ መፈለግ ይቻላል።

ማማከር ስለእሴት ትምህርት የሚሰጥበት ዓውድ አይደለም። አማካሪው ከአጠቃላይ ሥነምግባር አንጻር ትክክልና ስህተት የሆነውን ነገር ከምክር ፈላጊዎቹ እይታ አንጻር ማንሳት ይችላል። እነዚህም ነገሮች የሚነሱት ከችግሮቻቸው ጋር ተያያዥነት ሲኖራቸው እንጂ እማካሪ ስለእሴቶቹ የግድ መጠየቅ አይጠበቅበትም። አማካሪዎች እሴት-ነክ የሆኑ ነገሮችን ከምክር ፈላጊዎች ጋር ሲነጋገሩ የሚከተሉትን ሐሳቦች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይችላሉ፡-

- √ እያንዳንዱ ሰው ሰግል ሕይወቱ የሚስማማው የሕይወት ፍልስፍና ይኖረዋል። የእንዱ ለሌላው ላይስማማ ይችላል። በአንዱ ሌላው እይመዘንም።
- √ ሁሉም አማካሪ በሁሉ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ትክክለኛና የዳበረ የሕይወት ፍልስፍና ወይም እሴት እለው ለማለት አይቻልም።
- √ ሰዎች ስለእሴት የሚማሩት በቤተሰብ፣በትምህርት ቤትና በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ነው እንጂ በማማከር ክፍለ ጊዜ አይደለም።
- √ የእሴት/ሥነምግባር/ ትምህርት የሚሰጠው በጥቂት ጊዜያት ውስጥ በሚደረገው የማማከር አገልግሎት እይደለም። የሥነምግባር ትምህርት ከተለያዩ ሰዎች ጋር ግንኙነት ማድረግን ይጠይቃል።



- √ አንድ ሰው በሌላው ሰው እሴት/ሥነምግባር እይታ ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫና ማድረግ ሰብዓዊ መብትን መጋፋት ነው። ማንም የሰዎችን ሰብዓዊ መብት በማይነካ ሁኔታ የግል የሕይወት ፍልስፍና ሲኖረው ይችላል።
- √ ምክር ፈላጊዎች የፈሰጉትን ሥነምግባር የመከተል መብት ቢኖራቸውም በማማከር ግንኙነት ውስጥ ከአማካሪው ተምረው ተግባራዊ ለማድረግ የሚወስዱት የሥነምግባር ግንዛቤዎች ይኖራሉ።

እንግዲህ አማካሪ ከላይ የተጠቀሱት መልካም ባሕርያት ቢኖሩት ምክር ፈላጊዎችን በሚገባ መርዳት ይችላል። እነዚህ ባሕርያት በአንድ ጊዜ ወደ ፍጹምነት የሚመጡ ሳይሆኑ በሂደት የሚዳብሩ ናቸው። መልካም ባሕርይ ለማዳበር እንዲሁ በራሳቸው እንዲመጡ ከመጠበቅ ሁልጊዜ በዓላማ በግል የባሕርይ ቀረጻ ሥራ ማካሄድ ይገባል። በግል ራስን በመፈተሽ፣ ከምክር ፈላጊዎች በሚገኘው እስተያየት፣ በሌሎች የማማከር የሥራ ባልደረቦች በመገምገምና የተሰያዩ አማካሪዎችን ታሪክ በማንበብ፣ የራስን ባሕርይ ለአገልግሎቱ በሚመች ሁኔታ ማዘጋጀት ይቻላል።

## *2.2. አማካሪ ማወቅ የሚገባው መሠረታዊ ነገሮች*

አንድ እማካሪ በየትም ሥፍራ ከማንኛውም ምክር ፈላጊ ጋር ቢሠራ ማወቅ የሚገባቸው መሠረታዊ ነገሮች አሉ። እነዚህ ነገሮች ለማማከር አገልግሎት ፍሬያማነት የሚረዱ በመሆናቸው ተገቢውን ግንዛቤ ማግኘት ይጠበቅበታል።

*ስለነባራዊ ማሕበራዊ እውነታዎች ማወቅ አለበት፡-* እማካሪ በሚያገለግልበት አካባቢ የሚገኙትን ነባራዊ ማሕበራዊ እውነቶች በትክክል መረዳት ያስፈልገዋል። ከእነዚህም ጥቂቶቹ አብዛኛው ሰው የሚሠራቸው ሥራዎች፣ ያሉ የሥራ ዕድሎች፣ እነማን ምን እንደሚሠሩ፣ በቅርብ ጊዜ የተከናወኑ ማሕበራዊ ለውጦች፣ ሥራ ላይ ሊያውሉ የሚችሉ ኗሪ አምቅ ሀብቶች፣ የተሰያዩ ማሕበረሰብ ክፍሎች ባሕሎች፣ የትምህርት ሥርዓቶችንና የመሳሰሉትን ማሕበራዊ ጉዳዮችን በሚገባ ማወቅ ለአገልግሎቱ እስፈላጊ ነው።

አማካሪ፣ ይህን እውቀቱን መሠረት በማድረግ ምክር ፈላጊዎችንና ያሉበትን አጠቃላይ ዓውድ በሚገባ መረዳት ይችላል።

*የሥነልቦና እውቀት ሊኖረው ይገባል፡-* የማማከር አገልግሎት ከሥነልቦና ትምህርት ጋር ተያያዥነት አለው። ሥነልቦና ማለት ስለሰዎች አእምሮ ሥራና ድርጊታቸውን የሚያጠና ሳይንስ ነው። ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ለምን ያደርጋሉ? ለሚለው አጠቃላይ ጥያቄ መልስ ለመስጠት የተሰያዩ ጥናቶችን ያደርጋል።

ከማማከር ጋር ቀጥታ ተያያዥነት ያላቸው የሥነልቦና ትምህርቶችን ለምሳሌ ያህል ስለሰዎች ሰብዕና (እንዴት እንደሚያድግ፣

እንደሚለወጥና ዓይነቶችን እንዲሁም በስብዕና ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉትን ነገሮች ለይቶ) ማወቅ ጠቃሚ ነው። ሰዎች እንዴት አንድን ነገር እንደሚማሩም ማወቅ ያስፈልጋል። የሥነልቦና ትምህርት መማር የባሕርይ ለውጥ ሂደትን በትክክል ለማወቅ ይረዳል ። ሰዎች የባሕርይ ለውጥ ለማምጣት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው፣ ለባሕርይ ለውጥ የሚያግዙ መርሆዎችን ለማወቅና ሰዎችን በዚህ ሂደት እንዴት መርዳት እንደሚቻል ግንዛቤን ይሰጣል ። ለአማካሪ በሥነልቦና መዛባቶች፣ መንስኤዎቻቸውን፣ ምልክቶቹንና እንዴት መከላከል ወይም በዚህ ችግር የተያዙትን እንዴት መርዳት እንደሚቻል መረዳት አስፈላጊ ነው። እነዚህ ነገሮች ለምሳሌ ያህል የተጠቀሱ እንጂ ብዙ የሥነልቦና ትምህርቶችን መማር ምክር ፈላጊዎችን ይበልጥ ለመረዳትና ለመርዳት ይረዳል።

*የማማከር አገልግሎት ሥርዓቶችን ማወቅ አለበት*:- አንድ አማካሪ በስለማማከር አገልግሎት ማወቅ የሚገባቸው መሠረታዊ ሥርዓቶች አሉ። የማማከር ሥነምግባር፣ አገልግሎቱ የሚሰጥባቸውን ሥፍራዎች፣ ከሌሎች አማካሪዎች ጋር ሊኖረው የሚገባውን የሥራ ግንኙነት፣ አገልግሎቱን በተሻለ ሁኔታ መስጠት የሚቻልበትን መንገድ ማወቅ አለበት። በማማከር ጽንሰ-ሐሳቦችና ዘዴዎች ላይ ያለውን እውቀትና ልምዱንም ማሳደግ ይኖርበታል።

የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ አማካሪ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሐሳቦች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በመከታተል ማግኘትና ራሱን ማሻሻል ለአገልግሎቱ ስኬት ወሳኝ ነው። በየጊዜው በማማከር ዙሪያ የሚወጡትን ጥናታዊ ጽሑፎችን በማንበብ፣ ዓውደ ጥናቶችንና ሥልጠናዎችን በመካፈል ለአገልግሎት ጠቃሚ እውቀት ማሳደግ ይችላል። ከዚህም በላይ በሌሎች አማካሪዎች የተጻፉትን ጠቃሚ መጽሐፎችን ሁልጊዜ በማንበብ ራሱንና አገልግሎቱን እየመዘነ ወደ ተሻለ ደረጃ ማደግ ይችላል።

### *2.3. አማካሪ ስለራሱ ማወቅ የሚገባቸው ነጥቦች*

በማማከር አገልግሎት ውስጥ የአማካሪው ማንነትና ባሕርይ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ተመልክተናል። ስለዚህ አማካሪ ስለራሱ ማንነትና ባሕርይ በሚገባ ማወቁ ጠቃሚ እርምጃ ነው። ስለማማከር ሥልጠና ከሚሰጥበት አንዱ ትምህርት ራስን ማወቅ ነው። ለአማካሪነት የሚሰጡ ሥልጠናዎችና ትምህርቶች፣ አማካሪ ራሱን በሚገባ እንዲያይና እንዲፈትሽ ዕድል ይሰጡታል። በእነዚህ ትምህርቶችና ከሌሎች ሠልጣኞች ጋር በሚኖረው ግንኙነት የራሱን ትክክለኛ ማንነትና ባሕርይ እንዲሁም በአገልግሎቱ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን አዎንታዊና አሉታዊ ውጤቶችን መረዳት ይችላል።

አንድ አማካሪ ስለራሱ ማወቅ የሚገባቸው ነጥቦች አያሌ ሲሆኑ የሚከተሉት ለምሳሌ ያህል የሚጠቀሱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።



### *አማካሪ የሆነበትን ምክንያት ማወቅ*

በቅድሚያ አንድ አማካሪ ወደ ማማከር አገልግሎት እንዲገባ ያደረገው ምክንያት/ ውስጣዊ ዒላማው ምን እንደሆነ በትክክል መረዳትና መግለጽ መቻል አለበት። ሰዎች አማካሪ የሚሆኑበት ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ ዓላማዎች አሉ። ብዙ ጊዜ ሰዎች የራሳቸውን ዓላማ ሲፈትሹ ትክክለኛውን ነገር ለማግኘት ይቸገራሉ። ምክንያቱም ዓላማቸው ሁልጊዜ ትክክለኛ ይመስላቸዋል። በቅንነት ሰዎችን ለመርዳት ከሚል ዓላማ በመነሳት ወደ ማማከር አገልግሎት መግባት መልካምና የሚደገፍ ሲሆን ስውር የሆነ ዓላማ ካለ ግን በአገልግሎቱ ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከትላል።

በአጠቃላይ ሰዎች ወደ ማማከር አገልግሎት ከሚገቡባቸው ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል:-

*ግንኙነትን በመፈለግ*:- እያንዳንዱ ሰው ከሌሎች ጋር ቅርበት ያለው ግንኙነትን ለመመሥረት ይፈልጋል። ለአንዳንድ አማካሪዎች ምክር ፈላጊዎች ለአጭር ጊዜም ቢሆን ጓደኞች ይሆኑላቸዋል። አማካሪ ከምክር ፈላጊዎች ውጭ ሌሎች የቅርብ ግንኙነቶች ከሌሉት እነዚህን ሰዎች በተገቢው ጊዜ አገልግሎ መልቀቅ አይፈልግም። ምክንያቱም እንደ ጓደኞቹ ስለሚያስብ አብሮአቸው መቆየትን ይፈልጋል። ይህ ብቻ ሳይሆን ከጓደኞቹ ጋር የሚሠራቸውን ሥራዎች ለማድረግ ሊፈተን ይችላል።

*ለግል ችግር መፍትሔ ለማግኘት*:- እያንዳንዱ ሰው በሕይወቱ ያልተፈወሰ ቁስል ይኖረዋል። እያንዳንዱ ሰው ከቁስሉ ለመፈወስ የሚወስደውም እርምጃ የተለያየ ነው። ጥቂት አማካሪዎች ወደ ማማከር አገልግሎት ውስጥ በመግባት ሌሎችን በሚያማክሩበት ጊዜ ለራሳቸው መፍትሔዎችን ለማግኘት ጥረት ያደርጋሉ። አማካሪው ለራሱ ችግር መፍትሔ ለማግኘት በማለት ምክር ፈላጊዎችን ራሱ ወደሚፈልግበት አቅጣጫ የሚመራቸው ከሆነ እምብዛም አይረዳቸውም። በማማከር ጊዜ እንዲህ ዓይነት ችግር እንዳይከሰት፣ አማካሪ ከመሆን በፊት ለግል ችግር ወደ ማማከር አገልግሎት መሄዱ ያልተፈወሰና ትኩረት የሚሻ የግል ቁስል ለመረዳትና ለመፈወስ ዕድል ይሰጣል።

*መረጃ ለማግኘት*:- አንዳንድ አማካሪዎች የግለሰቦችን የግል መረጃ ለማወቅ ጉጉት አላቸው። በማማከር አማካይነት ካልሆነ ሊሰሙ የማይችሉትን መረጃ ለማግኘት ብለው ወደ ማማከር አገልግሎት ይገባሉ። በዚህ ዓይነት ዓላማ ወደ ማማከር የሚገባ አማካሪ ምክር ፈላጊዎች መናገር ከሚፈልጉት መረጃ አልፎ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለውን ነገር ለማወቅ ጥያቄዎችን ይጠይቃል። ምክር ፈላጊዎችን መርዳት ረስቶ የመረጃ ፍላጎቱን ለማሟላት እርምጃ ይወስዳል። ከዚህም የተነሣ ምክር ፈላጊዎች ወደ እንደዚህ ዓይነት አማካሪ መሄድን ያቆማሉ።

*ችግር ፈቺ ለመሆን-* አንዳንድ አማካሪዎች በችግር ውስጥ የገቡትን ሰዎች ከገቡበት መከራ በማውጣት «ጀግና» ለመባል ወደ ማማከር አገልግሎት ይገባሉ። ለሰዎች «አዳኝ» የመሆን ፍላጎት አላቸው። ምክር ፈላጊዎች ራሳቸው ችግሮቻቸውን ለመፍታት እርምጃ እንዲወስዱ አያደርጉም። ይልቅስ አማካሪዎች ኃላፊነት ወስደው የምክር ፈላጊዎችን ችግር ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ። ለጊዜው ምክር ፈላጊዎችም የሚፈልጉትን ነገር ያገኙ ሲመስላቸው ይችላል። ሆኖም በዘላቂነት የማይረዳቸው ይልቁንም ጥገኝነትን የሚያስድግ እርምጃ እንደሆነ ያስተውሉታል። በአብዛኛው አማካሪው ምክር ፈላጊዎችን በዚህ መንገድ መርዳት ካልቻለ የበደለኛነት፣ የብቃት ማነስና ግራ መጋባት ስሜት ይሰማዋል።

አንዳንድ አማካሪ ወደ ማማከር አገልግሎት በተለየ መንገድ መግባት ይችላል። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ወደ ማማከር አገልግሎት የገባው ባልታሰበ መንገድ ነበር። በመጀመሪያ የሥነልቦና ትምህርትን የመረጠው በጓደኛ ምክር ነበር። ከዚያም ትምህርቱን እጅግ እየወደደ ሄደ። በዚህ ሂደትም ስለራሱ ብዙ ነገሮችን ለማወቅ ችሏል። በሥነልቦና ትምህርት የኮሌጅ ትምህርቱን ሲጨርስ ደግሞ በውስጡ በነበረው ሸክም ወንጌልን በማስተማር ላይ ተሠማራ። ለአምስት ዓመታት በተለያዩ ሥፍራዎች ሲያገለግል በቆየበት ጊዜ የማማከር አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቢኖሩም በዕድሜ ወጣት ስለነበር በእርሱ ብቃት አምነው አገልግሎት ያገኙ ጥቂቶች ብቻ ነበሩ። በተለይ በዚያን ወቅት ጥቂት ወጣቶችን በማማከር ያገለግላቸው ነበር። ከዚያ በኋላ የመጋቢነት ማማከር በመማር ወደ አገልግሎቱ ገባ።

እንግዲህ አንድ አማካሪ ለምን ወደ ማማከር አገልግሎት ውስጥ እንደሚገባና በአገልግሎቱም ውስጥ እንደሚቆይ መመስስ መቻል አለበት። ጤናማ የሆኑ ዓላማዎች ከሌሉ ሲኖሩ ለራስም ሆነ ለምክር ፈላጊዎች ጥቅም ስለማይኖረው ለውጥ ማድረግ ይገባል።

### *የማይስማሙትን ስሜቶችን ለይቶ መገንዘብ*

አንድ አማካሪ በማማከር ሂደት ውስጥ አማካሪ የማይስማሙት ስሜቶች ሲኖሩት ይችላሉ። እነዚህ ስሜቶች ምን ምን እንደሆኑ ለይቶ ማወቅ፣ ከምክር ፈላጊዎች ለሚመጡ ስሜት ቀስቃሽ ነገሮች ተገቢውን አጸፋ ለመስጠት ያዘጋጃል። አንዳንድ ምክር ፈላጊዎች ተገቢ ያልሆነ ስሜት በአማካሪው ውስጥ እንዲቀሰቀስ የሚያደርጉ ሐሳቦችን ሲያቀርቡና ድርጊቶችን ሲፈጽሙ ይችላሉ። እነዚህን ነገሮች ሆን ብለው አስበውበት ወይም ሳያውቁ ከችግራቸው ጋር በተያያዘ ሁኔታ መግለጽ ይችላሉ። አማካሪው የራሱን ስሜቶች በትክክል ለይቶ የማያውቅ ከሆነ ስሜቶችን የሚቀሰቅሱ ነገሮችን እንዳይፈጽሙ ምክር ፈላጊዎች ላይ ጫና ያሳድራል። ይህ ደግሞ በማማከር ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን ያስከትላል።



የአማካሪው ስሜቶች ከምክር ፈላጊዎቹ ጋር እንዳይቀጥል የሚያደርጉ ሲሆኑ እነርሱን ወደ ሌላ አማካሪ መምራት ይኖርበታል እንጂ አብሮአቸው ቢቆይ ሊረዳቸው አይችልም። ሌላ አማካሪ ማግኘት የማይችል ሲሆን ደግሞ እርሱን በዚህ ችግር ሊረዳው የሚችል አማካሪ ፈልጎ በማማከር ሂደት ውስጥ በገጠመው ችግር ዙሪያ እስፈላጊውን የማማከር አገልግሎት ለራሱ ማግኘት ይጠበቅበታል። ለራሱ ችግር መፍትሔ የሚያገኝበት ሁኔታ ከተመቻቸለት ከእነዚያ ምክር ፈላጊዎች ጋር መቀጠል ይችላል።

አንዳንድ ጊዜ በማማከር ግንኙነት ውስጥ አማካሪው ለለምክር ፈላጊዎች የሚሰማው ስሜት ጠንካራና ግራ የሚያጋባ ሊሆን ይችላል። አማካሪው ለምክር ፈላጊዎች ተገቢ ያልሆኑ ስሜቶችን ማሳየት ሲጀምር ምክር ፈላጊዎቹ በአማካሪው ሕይወት ያልታወቀ አንድ ነገር እንዲቀሰቀስ ምክንያት ሆነዋል ማለት ነው። አማካሪም ምክር ፈላጊዎችን ከዚህ በፊት በሕይወት ዘመኑ ከገጠሙት ሰዎች መካከል እንደ አንዱ ማሰብ ይጀምራል። ከዚያ ሰው ጋር እንደሚነጋገር ዓይነት በማሰብ ከምክር ፈላጊዎቹ ጋር ንግግር ውስጥ ይገባል። ምክር ፈላጊዎች አማካሪው ከሚያስባቸው ከእነዚያ ሰዎች ጋር ምንም ግንኙነት ባይኖራቸውም ማንነታቸው፣ ንግግራቸው ወይም ድርጊታቸው እነዚያን ሰዎች ሊመስል ይችላል። በዚህም እነዚያን ሰዎች እንዲያስታውስ ይቀሰቅሱታል። በዚህ ጊዜ አማካሪው ትክክለኛውን የማማከር አገልግሎት እየሰጠ አይደለም።

አማካሪው በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሲሆን ለግል ሕይወቱ የማማከር አገልግሎት ማግኘት እንደሚያስፈልገው ያመለክታል። በሕይወቱ ውስጥ የማያውቃቸውን ደካማ ጎኖቹን በማወቅ ምክር ፈላጊዎችን ይበልጥ ማገልገል እንዲችል ዕድል ይሰጠዋል። አማካሪ፣ ምክር ፈላጊ ሆኖ በማማከር ሂደት ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ ለራሱ ጠቃሚ ግንዛቤ ከማግኘቱም በላይ ለምክር ፈላጊነት ሂደት ውስጥ ሲያልፍ የሚፈጠሩት ስሜቶችን ከልምዱ ይረዳል። ይህ አንድ ጊዜ ብቻ ተደርጎ የሚተው ሳይሆን በማማከር አግልግሎት ውስጥ እስካለ ድረስ ከእርሱ የተሻሉ አማካሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር በአገልግሎቱ ውስጥ የሚገጥሙትን ጉዳዮች በግልጽነት የሚነጋገርበት ሁኔታ ያስፈልገዋል።

አማካሪ ለራሱ የማማከር አገልግሎት ከማግኘቱም በተጨማሪ መንፈሳዊ ድጋፎችን የሚያገኝበትን መንገድ መፈለግ ይችላል። ክርስቲያን አማካሪ ከሆነ የእግዚአብሔርን ቃል በማሰላሰል የራሱን ትክክለኛ ማንነት ይበልጥ መረዳት ይችላል። በጸሎት ደግሞ ለአገልግሎቱ የሚበቃውን ጸጋ ከእግዚአብሔር ዘንድ በመለመን በእምነት ወደፊት ይጓዛል።

### *ለምክር ፈላጊዎች የሚሰጠው አጸፋ*

አንድ አማካሪ ለምክር ፈላጊዎች ንግግርና ድርጊት ሲሰጥ በሚገባው አጸፋ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። በተለይ እነርሱ ስለአማካሪው ካላቸው እይታ (ሥዕል) በተቃራኒ ሁኔታ የሚሰጠው አጸፋ

የማማከር ሂደትን ያደናቅፋል:: ምክር ፈላጊዎች ስለአማካሪው የተለያየ አመለካከትና አስተሳሰብ ይኖራቸዋል:: አንዳንዶች አማካሪውን ሲያንቋሽሹ፣ ሌሎች ደግሞ ያሞጋግሱታል:: የምክር ፈላጊዎቹ አስተያየት ስለአማካሪው ከሚናገሩት በላይ ስለራሳቸው ብዙ ነገሮችን ይገልጻል::

ምክር ፈላጊዎች ስለአማካሪው ያላቸው አስተሳሰብና ስሜት የሚመነጨው እነርሱ ከሌሎች ሰዎች ጋር ከሚኖራቸው ግንኙነት ነው:: ከሌሎች ሰዎች ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ከአማካሪ ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ ያንጸባርቃሉ:: ብዙውን ጊዜ እነዚህ ስሜቶች የቀድሞ ግንኙነት ነጸብራቆች ናቸው እንጂ ከአማካሪው ጋር በቀጥታ የተገናኙ ሳይሆኑ ይችላሉ:: ለምሳሌ በልጅነቱ ዘመን በአምባገነን ቤተሰብ ያለነጻነት ያደገ ሰው አማካሪውን እንደ አባቱ አምባገነን እንደሆነ ሲናገር ይችላል:: ምክር ፈላጊዎች ለምን እንዲህ ብለው እንደሚናገሩና እንዲህ ዓይነት ስሜትም እንደሚሰማቸው በግልጽ አያውቁትም:: አስተሳሰባቸው የመነጨው በአእምሮአቸው ውስጥ ታፍኖ ከተቀመጠው መረጃ ነው:: ትንሽ ጠንከር ያለባቸውን ሰው እንደ ወላጅ አባታቸው ጨካኝ እንደሆነ መናገር እንጂ ለምን እንዲህ እንደሚያስቡ አያውቁትም::

ምክር ፈላጊዎች ስለአማካሪ ተገቢ ያልሆነ ስሜት ሲሰማቸው አማካሪው ምን ማድረግ አለበት? ምክር ፈላጊዎች መልካም ወይም ክፉ ስሜት ቢሰማቸው ዋናው ነገር አማካሪው ይህንን የሚያስተናግድበት ሁኔታ ነው:: ለምሳሌ አንድ ምክር ፈላጊ ከአማካሪው ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥ «አንተ እንደማትወደኝ አውቃለሁ» ብሎ ስሜቱን በግልጽ ቢነግረው አማካሪው «እንዲህ ለማለት የቻልከው ከምን ተነስተህ ነው?» ብሎ በመጠየቅ ምክር ፈላጊው የስሜቱን መንስኤ እንዲፈትሽ ዕድል ሲሰጠው ይችላል::

አንዳንድ ጊዜ ምክር ፈላጊዎች ለራሳቸው ጥሩ የሆነ አስተሳሰብ እንደሌላቸው እንዲያስቡ የሚያደርጋቸው እነርሱ ያደጉበት ባሕል ነው:: እያንዳንዱ ሰው ያደገበትን ባሕል አይታ ይዞ ስለሚያድግ አማካሪውን ለሚመስሉ ሰዎች ሲሰማ ያደገውን አስተሳሰብ በመያዝ ይመራበታል::

እንግዲህ በአጠቃላይ አማካሪ ምክር ፈላጊዎች ስለእርሱ ያላቸውን ሐሳብና ስሜት በማማከር ሂደት ውስጥ በመወያየት መንስኤው ምን እንደሆነ በማወቅ የተሻለ ግንዛቤ እንዲያገኙ መርዳት ይችላል:: አማካሪ ስለምክር ፈላጊዎች ጥሩ እይታ ሳይኖረው በማማከር ግንኙነት ውስጥ ከእነርሱ ጋር መቆየት የለበትም:: እንዲህ ማድረግን የማማከር ሥነምግባር አይፈቅድም:: ምክር ፈላጊዎች ስለአማካሪው በሚያስቡትና በሚሰማቸው ስሜት ባይከነኑም ግን ትክክለኛ ያልሆነ ግንዛቤያቸው በሂደት እንዲስተካከል አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው:: የአማካሪ ማንነት የሚሰካውም ምክር ፈላጊዎች በሚሰጡት የስሜት ምላሽ አይደለም::



*የተቃራኒ ጾታ ግንኙነት አያያዝ*

ለማማከር አገልግሎት የሚመጡ ሰዎች ከአማካሪው ጋር በጾታ ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ሲሆኑ ይችላሉ:: በማማከር ግንኙነት ውስጥ በተቃራኒ ጾታ መፈተን ሲያጋጥም ስለሚችል እንደ እንግዳ ነገር ሊታይ አይገባም:: ምክር ፈላጊዎች በአማካሪው ሲፈተኑ እንደሚችሉ ሁሉ አማካሪውም በምክር ፈላጊዎች ሲፈተን ይችላል:: በማማከር ውስጥ የተቃራኒ ጾታ ስበት ከምክር ፈላጊዎቹ ወይም ከአማካሪው ሲጀምር ይችላል:: በመጀመሪያ ደረጃ መታወቅ ያለበት አንድ አማካሪ ከምክር ፈላጊዎች ጋር በማንኛውም ዓይነት የወሲብ ግንኙነት ማድረግ ኢሥነምግባራዊ ድርጊት መሆኑን መረዳት አለበት:: እንዲህ እድርጎ መገኘት በአማካሪው ሕይወት፣ በምክር ፈላጊዎች፣ በማማከር አገልግሎት እንዲሁም የማማከር አገልግሎት በሚሰጥበት ድርጅት/ቤተክርስቲያን ላይ ኪሣራን ያስከትላል:: ስለዚህ ይህን ከወዲሁ በማወቅ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ጠቃሚ ነው::

አንድ አማካሪ በማማከር ሂደት በወሲብ ሲፈተን ምን ማድረግ እንዳለበት በትክክል ካወቀ ሲያጋጥመው ከሚችለው አደጋ ማምለጥ ይችላል:: እንዲህ ዓይነት ስሜት በውስጡ ሲፈጠር አማካሪው ጉዳዮን ለግል አማካሪው በማቅረብ ሲወያይበት ይገባል እንጂ ጉዳዩን ከምክር ፈላጊዎቹ ጋር ማውራት የለበትም፤ ቢያደርግ ወደማይፈለግ ሁኔታ ያመራል:: የወሲብ ስሜቱ ከምክር ፈላገው የተነሣ ከሆነ አማካሪው ከግል አማካሪው ጋር ከተወያየ በኋላ በማማከር ሂደት ውስጥ ለውይይት ማቅረብ ይችላል:: በዚህ ሂደት አማካሪው ማድረግ ከሚገባቸው ነገሮች መካከል የሚከተሉትን ማድረግ ይችላል:-

- √ የምክር ፈላጊዎችን የወሲብ ሕይወት በአጠቃላይ በማለስ አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት ያስፈልጋል::
- √ የማማከር ሂደት የተቀራረበ ግንኙነት በመሆኑ ምክር ፈላጊዎች የጠበቀ ግንኙነትን ከወሲብ ግንኙነት ጋር ለማገናኘት ሲያስቡ ይችላሉ:: የመቀራረብ ምልክትና ምስጢርን ያለ ምንም ሐፍረት ማውራት መቻል የወሲብ ፍላጎት መኖሩን አያመለክትም:: የምክር ፈላጊዎቹን ግራ መጋባት፣ፍርሃትና ያልተፈለጉ ድርጊቶችን በማሳየትና ይፋ በማድረግ ለውይይት ማቅረብ ይችላል
- √ ምክር ፈላጊዎቹ ዋናውን ጉዳይ በመተው ወይም ጠምዘዝ በማድረግ ስለወሲብ ሕይወታቸው ማውራት ሲጀምሩ አማካሪው በተጀመረው ዋና ችግር (ሐሳብ) ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በማስገንዘብ የተነሣውን የወሲብ ጉዳይ በተመለከተ ከዋናው ጉዳይ በኋላ ማንሳት እንደሚቻል መጥቀስ ይችላል
- √ በማማከር ግንኙነት ውስጥ አማካሪና ምክር ፈላጊዎች በምንም ዓይነት ሁኔታ የወሲብ ግንኙነት ማድረግ እንደሌለባቸው በተደጋጋሚ ተገቢ በሆነ መንገድ መግለጽ አስፈላጊ ነው::
- √ በማማከር ሂደት ውስጥ የሚነሱትን ወሲብ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን በትክክል መዝግቦ ማስቀመጥ ጠቃሚ ነው:: አማካሪው በግል

ከአማካሪው ጋር በሚኖረው ግንኙነት መረጃዎችን ሲጠቀምበት ይችላል:: አንዳንድ ምክር ፈላጊዎች ደግሞ ስለወሲብ ጉዳዮች አያነሱ በማውራት በአማካሪው ላይ ተገቢ ያልሆነ እርምጃ (ለምሳሌ ለወሲብ ጠየቀኝ ወይም አስገድዶ ደፈረኝ ብለው የስም ማጥፋት ወይም ክስ) መውሰድ ስለሚችሉ ራስን ለመከላከል ያግዛል::

እንግዲህ በማማከር አገልግሎት ውስጥ አማካሪው የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ስለራሱ በትክክል ማወቅና ሁልጊዜ የሚያድግ ባሕርይና ብቃት ያለው ለመሆኑ ጥረት ማድረግ ለፍሬያማ ማማከር መሠረት ነው:: የአማካሪ ባሕርይ በአንድ ጊዜ ተሠርቶ የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም:: ዕለት ዕለት ራስን መፈተሽንና ውሳኔ ማድረግን ይጠይቃል::



## ምዕራፍ 3

## የማማከር ሂደት

### *3.1. የማማከር ሂደት ምንድነው?*

የማማከር ሂደት ማለት በማማከር ወቅት አማካሪውና ምክር ፈላጊው የሚያደርጉትን ከንውን የሚያሳይ እርምጃ ነው:: ይህ ሂደት በአገልግሎቱ ውስጥ ሁለቱ ከተገናኙበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚለያዩበት ጊዜ ድረስ ያለውን ያጠቃልላል:: ማማከርን ከየት ልጀምር? እንዴት ልቀጥል? እንዴት እና የት ላቁም? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሣሉ:: እነዚህ ጥያቄዎች የማማከር ሂደት አካል ናቸው:: የማማከር ሂደት ለጀማሪ አማካሪ ውስብስብ ቢመስልም በአገልግሎቱ እየቆየ ሲሄድ ጠቃሚ ልምዶችን እያገኘ እንዴት ጀምሮ እንዴት እንደሚያቆም ይረዳል:: በማማከር ወቅት የሚደረጉ ሁኔታዎች ስሌቱን ስለሚወስኑ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እነዚህን ዝርዝር ነገሮች እንመለከታለን::

የማማከር አገልግሎትን ሂደት መጀመር የሚቻልባቸው ብዙ አማራጭ መንገዶች አሉ:: እያንዳንዱ አማካሪ ከራሱና ከዓውዱ ጋር የሚስማማውን የአጀማመርና የአፈጻጸም ሂደት ሊከተል ይችላል:: እያንዳንዱ የማማከር ሂደት የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን አለው:: አንዳንድ አማካሪዎች አንድን አካሄድ ከለመዱት እርሱን እንደ ዋና መመሪያቸው በማድረግ ይጠቀማሉ:: አንዳንዶች ደግሞ የራሳቸው የሆነ ነገር ባይኖራቸውም የተለያዩ አካሄዶችን አንድ ላይ በማሰባሰብ ይጠቀማሉ:: በአብዛኛው የማማከር ሂደት በአማካሪው ብቃት፣ በምክር ፈላጊዎቹ ችግርና አገልግሎቱ በሚፈጸምበት ዓውድ ይወሰናል::

አንድ ምክር ፈላጊ ጨለማን እንደሚፈራና ሌሊት ወደ ውጭ መውጣት ወይም በጨለማ ቤት ውስጥ መግባት የማይችል ከሆነ እንዴት መርዳት ይቻላል? ሌላው ምክር ፈላጊ ደግሞ የበታችነት ስሜት ስለሚሰማው በሕይወቱ ፍሬያማ መሆን ያልቻለ ቢሆን እንዴት መርዳት ይቻላል? እነዚህን የተለያየ ችግር ያላቸውን ምክር ፈላጊዎች በተመሳሳይ ዓይነት የማማከር አካሄድ መርዳት አይቻልም:: ለመጀመሪያው ምክር ፈላጊ የባሕርይ ለውጥ ማምጣት በሚያስችል ሂደት መሄድ ይጠቅማል:: ጨለማን መፍራት የተማረውን ትምህርት ማስተው ነው:: ይህን ፍርሃቱን ለማስተው ምክር ፈላጊው መውሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች አሉ:: ፍርሃትን እንደተማረ ሁሉ አለመፍራትንም የሚማርበት ሂደት ውስጥ ይገባል::

ለሁለተኛው ምክር ፈላጊ ደግሞ ወደኋላ ተመልሶ የልጅነት ዘመኑን በተለይ ደግሞ የአስተዳደግ ሁኔታውን የሚቃኝበት የማማከር አካሄድ ይጠቅማል:: የልጅነት ዘመኑ ግንኙነቶች አሁን ባለው ሕይወት ላይ ያመጡትን አሉታዊ ተጽዕኖዎችን በመገንዘብ የአስተሳሰብ ለውጥ ማድረግ የሚያስችል አካሄድ የበለጠ ይረዳዋል:: ስለዚህ የማማከር አካሄድ አመራረጥን የሚወስኑ የተለያዩ ሁኔታዎች ስለሚኖሩ እነዚህን በማጠቅ

እንደ አስፈላጊነታቸው መጠቀም እንጂ ሁሉንም በወጥነት ለማስተናገድ መሞከር ጥሩ ውጤት አያስገኝም።

ማማከር ሂደት በመሆኑ በአንድ ጀምበር የሚፈለገው ውጤት አይገኝም። አንድን ምክር ፈላጊ በማማከር ወደሚፈለገው ግብ ለመድረስ ረጅም ጊዜ ሊፈጅ ይችላል። ሁለቱም በጋራ ሆነው የምክር ፈላጊውን ችግር፣ መንስኤዎቹንና መፍትሔዎቹን ቆፍረው አግኝተው፣ እንዴት ተግባራዊ መሆን እንዳለበት እስኪያቅዱ ድረስ ብዙ ጊዜያት ይወስዳል። የችግሩ መንስኤ ቶሎ መታወቅ ብቻም ሳይሆን የምክር ፈላጊው የመረዳት ፍጥነትም በሂደቱ ርዝመት ላይ ተጽዕኖ ያመጣል። ስለዚህም አማካሪው ምክር ፈላጊው ያለበትን እውነታ እስኪረዳ ድረስ ይጠብቃል። በአንድ ጉዳይ ላይ ምክር ፈላጊው የባሕርይ ለውጥ እንዲያመጣ መሥራት ረጅም ጊዜን ይጠይቃል።

### *3.2. ሰዎች ስለማማከር አገልግሎት እንዴት ያውቃሉ?*

የማማከር አገልግሎት የሚኖረው ምክር ፈላጊዎችና አማካሪዎች ሲገናኙ ነው። ምክር ፈላጊዎች አገልግሎቱን ለማግኘት የሚመጡት አስቀድሞ መረጃ ሲኖራቸው ነው። ይህን መረጃ ለምክር ፈላጊዎች እንዴት ማሳወቅና አገልግሎቱን እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል?

የማማከር አገልግሎትን ለሰዎች ለማስተዋወቅ ተገቢ የሆኑትን የመረጃ ማስተላለፊያ መንገዶችን መጠቀም ይቻላል። እያንዳንዱ አማካሪ ከዓውዱ ጋር የሚስማማውን መንገድ በመጠቀም ምክር የሚፈልጉ ሰዎች ሰምተው አገልግሎቱን እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በትምህርት ቤት አካባቢ የሚያገለግል አማካሪ ለተማሪዎች የሚመቸውን ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት የማማከር አገልግሎት የሚሰጥበትን ቀናትና ሰዓታት በማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም ከቢሮው በር በመለጠፍ ማሳወቅ ይችላል። በተጨማሪም ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ወደ ማማከር አገልግሎት እንዲልኩ አስፈላጊውን መረጃ ለመምህራን መስጠት ወይም ተማሪዎች በተሰበሰቡበት ዓውድ ስለአገልግሎቱ መንገር መረጃውን ለማሰራጨት ያግዛል።

በሃይማኖት ተቋማት የሚያገለግል አማካሪ ደግሞ ተቋሙ ውስጥ ያሉትን የመረጃ አውታሮችን በመጠቀም ስለአገልግሎቱ ማስተዋወቅ ይችላል። የምዕመናንን ጉባኤ፣ መጽሔቶችና ጋዜጦችን እንዲሁም አንድ በአንድ መልዕክቱ ለሁሉም እንዲዳረስ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። በሌሎች ድርጅቶችም ውስጥ የሚሠሩ አማካሪዎች በዓውዳቸው ተገቢ የሆኑትን የመረጃ አውታሮች መጠቀም ይችላሉ።

ስለማማከር አገልግሎት መረጃዎች የሚተላለፉባቸው መንገዶች የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን አላቸው። በተለይ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎች የማማከር አገልግሎት መጀመሩን ከሰሙ ባንዴ ሊጨናነቅ ይችላል። አንዳንዶች በማማከር ምን የተለየ ነገር ይደረግ ይሆን? ብለው ለማወቅ



ካላቸው ጉጉት የተነሣ ይመጣሉ። አንዳንዶች ደግሞ እስካሁን ድረስ መፍትሔ ያላገኙላቸውን ችግሮቻቸውን ይዘው ለመፍትሔ ፍለጋ ይመጣሉ። እንዲሁም ሌሎች ደግሞ እንዲሁ ለመሰለል ሊሉ መጥተው ሊያጨናንቁ ይችላሉ። ስለዚህ ስለአገልግሎቱ በአንድ ጊዜ መለከት ከመንፋት ይልቅ ቀስ በቀስ ሰዎች እንዲያውቁ ማድረጉ የተሻለ ነው።

በአብዛኛው ሰዎች ወደ ማማከር አገልግሎት የሚመጡት ከተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ወይም የመረጃ አውታሮች ካገኙት መረጃ ሳይሆን በአገልግሎቱ ተጠቅሞ ከሚመሰክር ሰው ከሰሙት መረጃ በመነሳት ነው። ስለዚህ ባገኙት መረጃ መሠረት የሚመጡትን ጥቂት ምክር ፈላጊዎች በማገልገል በሚገኘው ፍሬ ብዙዎችን ወደ አገልግሎቱ መሳብ ይቻላል። ምክር ፈላጊዎች ወደ ማማከር አገልግሎት ከመምጣታቸው በፊት ስለአማካሪው ታማኝነት፣ ሰው አክባሪነት፣ ምስጢር ጠባቂነት፣ ልምድና ብቃት መረጃዎችን ከሚያውቁት ወይም ከሚያምኑት ሰው መስማት ይፈልጋሉ።

ስለሆነም ብዙ ሰዎች አንድ ላይ መጥተው የአማካሪውን ብቃት ከሚፈታተኑ ይልቅ ቀስ ብሎ ማደግ ጥሩ ነው። በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን እንደታወጀው አማካሪው ምክር ፈላጊዎችን ማስተናገድ ካልቻለ ውጤቱ አሉታዊ ይሆናል። ማስታወቂያው «ወደዚያ አማካሪ እንዳትሄዱ ተጠንቀቁ» የሚል ማስጠንቀቂያ ሊያስከትል ስለሚችል የማስተዋወቅ መረጃዎችንና ዘዴዎቹን በማስተዋል መምረጥ ተገቢ ይሆናል።

አማካሪው ለመጀመሪያ ጊዜ ባገኛቸው ምክር ፈላጊዎች አገልግሎቱን ቢጀምር እነርሱ ስለማማከር አገልግሎቱ አስተዋዋቂዎች ይሆናሉ። ለምሳሌ አንድ የኩላሊት በሽታ ያለበት ሰው አንድ ክሊኒክ ሄዶ በጥሩ ሁኔታ ከተስተናገደና ተገቢውን ሙያዊ እንክብካቤ አግኝቶ ከተመለሰ እንዲሁም የታዘዘለትን መድኃኒት ሐኪሙ በነገረው መሠረት ተጠቅሞ ከበሽታው መዳን ቢችል ያ ክሊኒክ ባለውለታው እንደሆነ ያስባል። የተፈወሰው ሰው ከማሰብ አልፎ የክሊኒኩ ባለቤት በማዕዘን ላይ ካቆማቸው የማስታወቂያ ጽሑፎች የበለጠ ያስተዋውቃል። ሰውም የሚፈልገው እንዲህ ዓይነቱን ሕያው ምስክርነት ነው። በዚህ ዓይነት መንገድ መጠቀም ረጅም ጊዜ ሊፈጅ የሚችል ቢሆንም አማካሪው የሰዎች ጋጋታ ሳይበዛበት በየጊዜው ጥቂት በጥቂት የሚመጡትን ምክር ፈላጊዎች እየተቀበለ በማማከር ሂደት ውስጥ ቢያልፍ ብዙ ፍሬ ያፈራል፤ እንዲሁም አገልግሎቱም እየተስፋፋ ይሄዳል።

እኔ በማገለግልበት በሃይማኖት ተቋማት አካባቢ በአብዛኛው ሰዎች ስለማማከር አገልግሎት እምብዛም ሳያውቁ አገልግሎቱን ያገኛሉ። አገልግሎቱ ከሰዎች/አማካሪዎች/ ጋር የተያያዘ ነው። ከምዕመናን ጋር ስለተለያዩ የግል ጉዳዮች በማውራት ሂደት ውስጥ አንዳንዴ ምስጢራዊ የሆነ ጉዳያቸውን መናገር ይጀምራሉ። በዚህ ጊዜ በቀጥታ በማማከር አገልግሎት ውስጥ ይገባል። የግንኙነቱ ዓላማ ማማከር ሳይሆን እንዲሁ የግል ጨዋታ ነገር ይሆንና መሐል ላይ አቅጣጫውን ይቀይራል።

አማካሪው መንፈሳዊ አገልጋይ ከሆነ ደግሞ ምዕመናንን በቤታቸው በሚጎበኝበት ጊዜ የሚነሡትን ጉዳዮች መሠረት በማድረግ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ዕድል ያገኛል። በዚህ ላይ ጥንቃቄ ሊወሰድበት የሚገባው ጉዳይ ምዕመናን የተናገሩትን ችግር በመንተራስ በጥድፊያ ለማማከር አገልግሎት ወደ ቢሮ እንዲመጡ ጥሪ አለማድረግ ነው። ምክር ፈላጊዎች አንድን ችግር ሲናገሩ ወዲያውኑ ከማማከር ጋር ማያያዝ አማካሪው ስውር የሆነ ዓላማ እንዳለው ያስመስለዋል። በዚህ ዓይነት መንገድ ወደ ማማከር አገልግሎት የሚመጡ ምክር ፈላጊዎች በአማካሪው ግፊት እንጂ በራሳቸው ተነሳሽነት እንደመጡ አይሰማቸውም። የማማከር ግንኙነት ፍሬያማ የሚሆነው ምክር ፈላጊዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ሲመጡ በመሆኑ በራሳቸው ፍላጎት ወደዚያ ማሰብ እንዲችሉ ማመልከት የተሻለ ነው። ምክር ፈላጊዎቹ ወደ ማማከር አገልግሎት የሚመጡት ስለጥቅሙ በሚገባ ሲረዱ በመሆኑ ያንን ሲገባቸው በሚችል መልኩ መግለጽ አስፈላጊ ነው። ከዚያ ባለፈ ሁኔታ የመምጣቱ እርምጃ ከራሳቸው እንዲጀመር መጠበቁ ጥሩ አካሄድ ነው።

የማማከር አገልግሎትን በትምህርት፣ ሥልጠና ወይም በሰብከት ጊዜ በተዘዋዋሪ መንገድ በመጥቀስ ማስተዋወቅም ይቻላል። በሰዎች ፊት የመቅረብ ዕድል ያላቸው አገልጋዮች/አማካሪዎች/ ባገኙት አጋጣሚ በመጠቀም ስለማማከር ጥቅም ከራሳቸው ወይም ከሚያውቁት ታሪክ በመነሳት ለሰዎች አስፈላጊ መሆኑን መግለጽ ይችላሉ። በአጠቃላይ ተገቢ በሆኑ መንገዶች ሁሉ በአካባቢያችን ያሉ ሰዎች ከዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስተዋወቅ ይበረታታል። አንዳንድ ጊዜ አማካሪዎች እያሉ ከምክር ፈላጊዎች ጋር ስለማይተዋወቁ፣ ሰዎች መፍትሔ ማግኘት በሚችሉ ችግሮች ተይዘው በሕይወታቸው ላይ ብዙ ኪሣራ ሲደርስ እንመለከታለን።

### *3.3. ማማከር የሚሰጥበት ቦታ*

በመሠረተ ሐሳብ ማማከር በየትኛውም ሥፍራ ሊሰጥ ይችላል። አማካሪና ምክር ፈላጊዎች ተገናኝተው መነጋገር በሚችሉበት ቦታዎች ሁሉ (ለምሳሌ ያህል በሜዳ ላይ፣ በመንገድ ላይ እየተራመዱ፣ በመኪና ውስጥ አብሮ እየተጓዙ፣ በአውሮፕላን እየበረሩ፣ በመዝናኛ ሥፍራዎች፣ በአገልግሎት መስጫ ቦታዎች ወረፋ እየጠበቁ፣ የሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎችን እየጠበቁና በመሳሰሉት ሥፍራዎች) ማማከርን ማካሄድ የሚቻል ቢሆንም ሁሉም ሥፍራዎች ለአገልግሎቱ ምቹ ናቸው ማለት አይደለም።

የማማከር አገልግሎት በተለመደበት ማሕበረሰብ ውስጥ ምክር ፈላጊዎች ማማከርን ሲፈልጉ ወደ አማካሪው ቢሮ በመምጣት አገልግሎቱን ያገኛሉ። እንደ ዓውዳችን የማማከር አገልግሎት በዘመናዊና ሥርዓት ባለው መልኩ መስጠት ባልተለመደበት ሁኔታ ደግሞ ምክር ፈላጊዎች ወደ አማካሪው ቢሮ እንዲመጡ መጠበቅና በዚያ ብቻ ለመስጠት ማሰብ እምብዛም ላይሳካ ይችላል።



የማማከር አገልግሎት የሚሰጥበት ክፍል ማራኪና ከማንኛውም ጫጫታ ነጻ መሆን አለበት። ቢሮ ውስጥ ሲሆን የወንበሮቹ አቀማመጥ፣ የክፍሉ ቀለምና በግድግዳ ላይ ያሉ ሥዕሎችና ቅርጻ ቅርጾች የሰላምን መንፈስ የሚፈነጥቁና ለታቀደው የማማከር ውይይት ምቹ ቅደመ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ሊሆኑ ይገባል። በክፍሉ ውስጥ ያለው ብርሃን መሐከለኛ ቢሆን ይመረጣል። ምክር ፈላጊዎቹን ከአማካሪው በሚመቻቸው ርቀት ላይ ማስቀመጥ እንዲቻል ወንበሮቹ ተንቀሳቃሽ ቢሆኑ ይመረጣል። በተለይም በመጀመሪያዎቹ አካባቢ ምክር ፈላጊዎች ለአማካሪው በጣም ቀረብ ብለው መቀመጥን አይፈልጉም። ቀስ በቀስ በመካከላቸው ያለው ርቀት እየጠበበ ይመጣል።

የአማካሪው ጠረጴዛ በሥርዓት የተቀመጠና ንጹሕ መሆን አለበት። ብዙ ወረቀቶች በጠረጴዛ ላይ መኖራቸው አማካሪው በሥራ የተጠመደ ወይም ዝርክርክ መሆኑን ያመለክታል። ይህ ሁኔታ ደግሞ አማካሪው ምክር ፈላጊዎችን እንደሚገባ ሊረዳቸው በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ እንደሆነ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። ስለዚህ በተቻለ መጠን ክፍሉን ለማማከር ምቹ አድርጎ ማለናዳት ተገቢ ነው።

የማማከር አገልግሎት የሚካሄድበት ክፍል ሰዎች ወዲህና ወዲያ ሲያልፉ የሚያንኳኩት ወይም ሰዎች በበራፉ ላይ በብዛት የሚተላለፉት መሆን የለበትም። በክፍሉ ውስጥ ስልክ ካለ በማማከር ጊዜ መዝጋት አስፈላጊ ነው። ክፍሉ ከሰዎች እይታ በጣም የተሰወረ መሆን የለበትም። እንዲህ ሲሆን ምክር ፈላጊዎች ነጻነት አይሰማቸውም።

### *3.4. የማማከር አገልግሎት በምን ጊዜ ይሰጥ?*

በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ የማማከር አገልግሎትን በማንኛውም ጊዜ መስጠት ይቻላል። አንዳንዶች ከሰዎች ጋር በተገናኙበት ዓውድ (ለምሳሌ ሠርግ፣ ለቅሶ፣ ለአግለግሎት ወረፋ እየጠበቁ...) ለማማከር ጥሪት ያደርጋሉ። እነዚህ ጊዜያት ለማማከር ምቹ ጊዜያት አይደሉም፣ ነገር ግን በሌላ ጊዜ ለመገናኘት ቀጠሮ ለመያዝ መጠቀም ብልህነት ነው። በተገኘው አጋጣሚ አማካሪና ምክር ፈላጊዎች ሲገናኙ ለሁለታቸው የሚመች ቀጠሮ መያዝ ያስፈልጋል። ቀጠሮ በሌሎች አገልግሎቶች ውስጥም አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ በማማከርም ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው። በማማከር ውስጥ ቀጠሮ መያዝና ማክበር ካለው ጥቅሞች መካከል የሚከተሉት በዋናነት የሚጠቀሉ ናቸው፡-

- ምክር ፈላጊዎች ለአማካሪው የሚኖራቸው አክብሮት እንዲጨምር ያደርጋል፣
- አማካሪው ለምክር ፈላጊዎች ጉዳይ ትኩረት መስጠቱን ያሳያል፣
- ምክር ፈላጊዎችን እንደ አመጣጣቸው ቅደም ተከተል በተገቢው ሁኔታ ለማስተናገድ ይረዳል። ለእያንዳንዱ ምክር

ፈላጊ በአንድ ጊዜ የሚበቃውን ጊዜ በመመደብ አስፈላጊውን አገልግሎት ስመስጠት ያግዛል፣

- ❖ ምክር ፈላጊዎች በሚመቻቸው ጊዜ ከአማካሪው ጋር ስመገናኘት ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፣
- ❖ ምክር ፈላጊዎችና አማካሪው ስለቀጠሮው እያሰቡ አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ይረዳል።

### *3.5. ማማከር ለምን ያህል ሰዓት ይሰጣል?*

አንድ የማማከር ክፍለ ጊዜ ምን ያህል ሰዓት መቆየት አለበት? የማማከር ውይይት ከመጀመሩ በፊት ውይይቱ ለምን ያህል 'ሰዓት መደረግ እንዳለበት መታወቅና አማካሪው ለምክር ፈላጊዎች መግለጽ አለበት። ሁለቱም በዚህ ጉዳይ ላይ በመስማማት ውይይታቸውን ይጀምራሉ።

በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ ከአንድ ምክር ፈላጊ ጋር የሚካሄደው የማማከር ውይይት የሚቆየው ለአንድ ሰዓት ነው። ከጥንዶች እንዲሁም ከቤተሰብ ወይም ከቡድን ጋር ሊሆን ከአንድ ሰዓት ተኩል እስከ ሁለት ሰዓት መሄድ ይቻላል። አንድ ክፍለ ጊዜ ከተወሰነው ሰዓት በላይ ከተራዘመ ምክር ፈላጊዎች ሐሳብን ከመደጋገም በስተቀር አዳዲስ ሐሳቦችን የማፍለቅ ሁኔታ አይታይባቸውም። ምክር ፈላጊዎች ማማከር ሲጀምሩ ምን ያህል ሰዓት ከአማካሪው ጋር እንደሚቆዩ ስለሚያውቁ አማካሪው ሰዓቱ ሲደርስ ማቆም ይችላል። «አሁን ባቆም ምን ይሰማቸው ይሆን?» የሚል ስጋት አይኖርበትም።

የተመደበው ሰዓት ማብቃቱን ለማረጋገጥ አማካሪው እየደጋገመ የእጅ ሰዓቱን ከሚያይ ይልቅ ማየት በሚቻል አቅጣጫ የተሰቀለ የግድግዳ ሰዓት ቢኖረው የተሻለ ነው። የእጅ ሰዓትን አውልቆ በጠረጴዛው ላይ ለማየት በሚያመች ሁኔታ በማስቀመጥ መጠቀምም ይቻላል። በዚህ ሁኔታ ከምክር ፈላጊዎቹ ጋር እየተነጋገረ ሰዓቱንም መከታተል ይችላል። ብዙ ምክር ፈላጊዎች ሲጀምሩ ዋና ነው ብለው የሚያስቡትን ነገር አይናገሩም። ወሳኝ የሆኑ ሐሳቦችን የሚያቀርቡት ሰዓቱ ሲያልቅ አካባቢ ነው። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ምክር ፈላጊዎች ውይይቱን ሲጀምሩ በመጨረሻ ላይ መናገር የሚፈልጉትን ነገር ቀድመው እንዲናገሩ ማበረታታት ጠቃሚ ነው። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ወሳኝ ሐሳቦች የሚወጡት ምክር ፈላጊዎቹ ከአማካሪው ጋር ያላቸው ግንኙነት ጠንካራ ሲሆን በመሆኑ መቼና የት ይህን ማድረግ የተሻለ እንደሆነ ማጤን ተገቢ ነው።

ምክር ፈላጊዎች በውይይቱ ክፍለ ጊዜ በመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ላይ ጠቃሚ የሆኑ አዳዲስ ሐሳቦችን ማምጣት ከጀመሩ የውይይቱን ጊዜ ከማራዘም ይልቅ ነጥቦቹን መዝግቦ በመያዝና በሚቀጥለው የማማከር ክፍለ ጊዜ እንደሚያነሱት በመስማማት የዕለቱን ግንኙነት ማቆም ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜ፣ ለውይይት የተመደበውም ሰዓት ቢያልቅ፣ ምክር ፈላጊዎቹ ያነሱት ሐሳብ በራሳቸው ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ነገር ከሆነ ሰዓት አልቋል ብሎ ዝም ብሎ መልቀቅ ተገቢ አይሆንም።



ለምሳሌ ምክር ፈላጊዎች ለችግራቸው መፍትሔ ካላገኙ ራሳቸውን ለማጥፋት ወይም ለችግራቸው መንስኤ እንደሆነ የሚያስቡትን ሌላውን ሰው ለማጥቃት እቅድ እንዳላቸው ከገለጹ በስምምነት ተጨማሪ ጊዜ ወስዶ ተገቢውን የመከላከል እርምጃ መውሰድ የግድ ይሆናል።

### *3.6. የማማከር አገልግሎት ለምን ያህል ጊዜ ይሰጣል?*

አንድ ምክር ፈላጊ ከአማካሪው ጋር ለምን ያህል ጊዜ ቢገናኝ ለችግሮቹ መፍትሔ ሊያገኝ ይችላል? በአብዛኛው የማማከር አገልግሎት ርዝመቱ የሚወሰነው በምክር ፈላጊዎቹ ችግር ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም ችግሩን ለመፍታት አማካሪው ባለው ብቃት ነው። የምክር ፈላጊዎቹ ችግር ውስብስብ ያለ ከሆነም ረጅም ጊዜ ሊቆይ ይችላል። ችግሩ ቀላል ከሆነ ደግሞ በአንድ ክፍለ ጊዜም መፍትሔ ማግኘት ይቻላል። አማካሪው የምክር ፈላጊዎቹን ችግር መፍታት የሚያስችለው ብቃት ከሌለው ግንኙነቱ ይቋረጣል።

ማማከር ሂደት ነው የተባለውም በአብዛኛው በአንድ ክፍለ ጊዜ መፍትሔ ማግኘት ስለማይቻል ነው። ምክር ፈላጊዎች በየሳምንቱ ለአንድ ሰዓት ከአማካሪው ጋር በመገናኘት ችግሩን ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ። ምክር ፈላጊዎቹ ለችግሩ መፍትሔ እያገኙ ሲሄዱ በሳምንት ከመገናኘት ይልቅ በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ መገናኘት ከዚያም እንደ አግባቢነቱ እየቀነሱ በመሄድ ማቆም ጥሩ አካሄድ ነው። ይህ አካሄድ የምክር ፈላጊዎቹ ለችግሩ መፍትሔ አግኝተው ሕይወታቸውን በሚፈልጉት አቅጣጫ መምራታቸውን ለመከታተል ይረዳል።

ከልምድ እንዳስተዋልኩት አብዛኛ ምክር ፈላጊዎች ወደ አማካሪው መመላለስ አይፈልጉም። በአንድ ጊዜ ግንኙነት ለችግራቸው መፍትሔ ማግኘትን ይፈልጋሉ። በባሕላዊ የማማከር አገልግሎት፣ አማካሪ ከምክር ፈላጊዎች ጋር ብዙ ሰዓታትን ያሳልፋል። ባሕላዊ ሽማግሌዎችም የሰዎችን ችግር በአንድ ጊዜ ለመፍታት ብዙ ሰዓታትን ያጠፋሉ። አንዳንድ ጊዜ ቀኑን ወይም ሌሊቱን ሙሉ ይቆያሉ። ቀጠሮ የሚያዘው ችግሩ አልገፋ ብሎ ምንም አማራጭ ሲጠፋ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ባለጉዳዮችም ከመሰላቸታቸው የተነሣ የቀረበውን መፍትሔ እሺ ብለው ይቀበላሉ። ሆኖም ችግሩ ምንም ያልተፈታ በመሆኑ ከሰዓታት ወይም ቀናት በኋላ ያገረሻል። በአንድ ጊዜ ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮች ቢኖሩም ችግሮችን ደረጃ በደረጃ በሂደት ለመፍታት መሞከር ውጤታማ ስልት ነው።

እንግዲህ አንድ አማካሪ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ዙሪያ አስፈላጊውን ዝግጅት ካደረገ በኋላ ቀጣዩ እርምጃ ከምክር ፈላጊዎች ጋር ተገናኝቶ ማማከርን መቀጠል ነው። ማማከር ከየት ወዴት ይሄዳል? የት ተጀምሮ የት ያቆማል? ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው። በመሠረቱ የማማከር ሂደት ሦስት ደረጃዎች አሉት። ከምክር ፈላጊዎች ጋር ግንኙነት መጀመር፣ የምክር ፈላጊዎችን ችግር በስፋት መፈተሽና አማራጭ

መፍትሔዎችን ማፍለቅ እና ሂደቱን ማጠቃለል ናቸው፡፡ በእነዚህ ደረጃዎች ብዙ ተግባሮች ያከናወናሉ፡፡

### *3.7. ሰላምታ መለዋወጥ*

ምክር ፈላጊዎች ከአማካሪው በተሰጣቸው ቀጠሮ መሠረት የማማከር አገልግሎት ወደሚሰጥበት ሥፍራ ይመጣሉ፡፡ ግንኙነት የሚጀምረው በሰላምታ ነው፡፡ የሰላምታ አሰጣጥ እንደየባሕሉ ይለያያል፡፡ አማካሪው ለምክር ፈላጊዎቹ ባሕል ተገቢውን አክብሮት በመስጠት ተገቢ በሆነ መንገድ ሰላማቸውን ይጠይቃል፡፡ በማማከር ሂደት ሰላምታ የሚሰጠው በአብዛኛው እጅ በመጨበጥ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ በማይመችበት ጊዜ በቃል ሰላምታ በመጠየቅ እንዲቀመጡ መጋበዝ ይቻላል፡፡ ከምክር ፈላጊዎች ጋር ትከሻ ለትከሻ ወይም ጉንጭ ለጉንጭ መሳሳም ጠቃሚ ላይሆን ይችላል፡፡ በተለይ ተቃራኒ ጾታ በሚሆኑበት ጊዜ የሚፈጥረው ስሜት ለማማከር ሂደቱ እንቅፋት ይሆናል፡፡

የሰላምታ አሰጣጥ የግንኙነት ጥልቀትን ስለሚያመለክት አማካሪ በደንብ ከሚያውቃቸው ምክር ፈላጊዎች ጋር የሞቀ ሰላምታ ማቅረብ ይችላል፡፡ ለምክር ፈላጊዎች የሚሰጠው የሰላምታ አሰጣጥ እንደ ትውውቅና ጾታ ብቻም ሳይሆን በዕድሜምም የተለያየ ነው፡፡ አማካሪው በዕድሜ ከእርሱ በታች ወይም ከእርሱ እኩያ ወይም ከእርሱ በላይ የሆኑትን ምክር ፈላጊዎች ሰላምታ የሚጠይቅበት መንገድ ይለያያል፡፡ እያንዳንዱ ባሕል ለዚህ ተገቢ ነው ብሎ የተቀበለው ነገር በመኖሩ ያንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአገልግሎት ሥነምግባሩ መሠረት ደረጃውን በጠበቀ ሙያዊ መንገድ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ የሰላምታ አሰጣጥ የራሱ የሆነ መልዕክት ስለሚኖረው አማካሪ በዓውዱ ተገቢ በሆነ መንገድ ምክር ፈላጊዎችን ሰላምታ መጠየቅ አለበት፡፡ በዚህ ወቅት የሚደረገው ነገር ሁሉቱንም ለፈተና የማያጋልጥና ለማማከር አገልግሎትም ተግዳሮት የማይፈጥር ሊሆን ይገባል፡፡

### *3.8. ከምክር ፈላጊዎች ጋር ግንኙነትን መገንባት*

በማማከር ሂደት ወሳኝ ሚና የሚጫወተው አንዱ የአማካሪውና የምክር ፈላጊዎቹ ግንኙነት በመሆኑ ይህንን በሚገባ መገንባት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክር ፈላጊዎች የእንግድነት ስሜት ስለሚሰማቸው በተገቢው ፍጥነት ለመሄድና ራሳቸውንም በሚገባ ለመግለጽ ፈቃደኞች አይደሉም፡፡ አማካሪው በሁኔታዎች ላይ ባልተመሠረተ ፍቅር ምክር ፈላጊዎችን ሊወዳቸውና ሊቀበላቸው ራሳቸውን ለማማከር ሂደቱ እየሰጡ ይመጣሉ፡፡ በሆኑትና ባደረጉት ነገር እንደማይኮነኑ ሊረዱ በግንኙነቱ ውስጥ ራሳቸውን ሆነው መታየት ይጀምራሉ፣ እውነት የሆነውን ነገር ለአማካሪው ይናገራሉ፣ እንዲሁም የሚስማማቸውንም መፍትሔ በመጠቆም ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡



አብዛኛውን ጊዜ በዓውዳችን ለማማከር የሚመጡ አንዳንድ ሰዎች ስለማማከር ምንም ግንዛቤ የሌላቸው ወይም የተዛባ አስተሳሰብ ያላቸው ናቸው፡፡ አማካሪው ችግሮቻቸውን ሳይገልጹ እንዲሁ በማወቅ መፍትሔ እንደሚሰጣቸው ያስባሉ፡፡

*አንድ ጊዜ አንዲት ሴት ከሌላ አማካሪ ተልካ ወደ እኔ መጣች፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ «ዛሬ ወደ እኔ ያመጣሽ ጉዳይ ምንድነው?» ብዬ ጠየኳት፡፡ ከዚያም የችግርዋን ዋና ጉዳይ ነገረችኝ፡፡ በመቀጠልም አንዳንድ ጥያቄዎች ስጠይቃት «እኔ እኮ የምፈልገው ወደፊት ሕይወቴን እንዴት መምራት እንዳለብኝ እንድታሳየኝ ነው» በማለት ለተጠየቀችው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ እንዳልሆነች ገለጸችልኝ፡፡ እኔም እርስዋ ችግርዋንና መንስኤዎቹን መናገር እስካልፈለገች ድረስ ለሕይወትዋ መመሪያ ሊሆኑ የሚችሉትን ሐሳቦችን መስጠት የምችልበት ምንም አቅም እንደሌለኝ በመግለጽ ለመለያየት ተስማማን፡፡* እንዲህ ዓይነቱ ችግር የሚከሰተው ከፍርሃት በመነጨ ሊሆን ቢችልም በአብዛኛው ግን ማማከር ምን እንደሆነ በትክክል ካለማወቅ የሚመነጭ ነው፡፡

ስለዚህ አማካሪ የማማከርን ምንነት ለምክር ፈላጊዎች ማስረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ ምክር ፈላጊዎች ስለማማከር ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤ ሳይኖራቸው ሂደቱ ከቀጠለ ተገቢውን ውጤት ማግኘት አዳጋች ነው፡፡ እንግዲህ ስለማማከር ማስረዳት አስፈላጊ ከሆነ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ለይቶ መንገር ያስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያ ምክር ፈላጊዎች ስለማማከር ያላቸውን ግንዛቤ ወይም ከዚህ በፊት የማማከር አገልግሎት አግኝተው እንደሆነ በመጠየቅ እነርሱ ዘንድ ምን እንዳለ ለመረዳት ያግዛል፡፡ የተሳሳተ ግንዛቤ ካላቸው ለማስተካከል፣ ምንም ግንዛቤ ከሌላቸው ደግሞ ተገቢውን መረጃ ለመስጠት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

በዓውዳችን ካለኝ የማማከር አገልግሎት ልምድ በመነሳት ምክር ፈላጊዎች ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ሐሳቦች ከመጀመሪያው ጀምረው እንዲያውቁ ማድረግ ጠቃሚ ነው እላለሁ፡፡

- ❖ ማማከር ጥንቆላ አይደለም ወይም የሰውን አእምሮ በማንበብ ወይም የጤና ምርመራ በማድረግ መድኃኒት ማዘዝ ሳይሆን ምክር ፈላጊዎች ችግሮቻቸውን በራሳቸው መፍታት እንዲችሉ የሚረዳ የሥነልቦና እርዳታ መስጠት ነው፡፡
- ❖ የማማከር ሂደት የሚሽከረከረው በምክር ፈላጊው ላይ ነው፡፡ አማካሪ መሪ ሲሆን ምክር ፈላጊው ሂደቱን «የሚቆጣጠር» ባለጉዳይ ነው፡፡ ምክር ፈላጊው ይናገራል፣ ይጠይቃል፣ ይከራከራል... መልካም እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
- ❖ ማማከር የራሱ የሆነ ሥነምግባር አለው፡፡ በተለይ በማማከር አገልግሎት ምስጢር መጠበቅ ከፍተኛ ሥፍራ አለው፡፡ አማካሪ የምክር ፈላጊዎችን መረጃዎች ከተወሰኑ ሁኔታዎች በስተቀር

ለማንም ሰው አሳልፎ አይናገርም:: የማማከር አገልግሎት ምስጢራዊ ግንኙነት ነው::

- ምክር ፈላጊዎች ለችግሮቻቸው የመፍትሔ ባለቤቶች ናቸው:: አማካሪ መፍትሔ ሰጪ ሳይሆን መፍትሔዎችን የሚያስፈትሽ መሪ ነው:: አማካሪ ምክር ፈላጊዎች ያሉትን መፍትሔዎች እንዲያስሱና እንዲሁም የተገኙ መፍትሔዎች ደግሞ መሥራትና አለመሥራታቸውን ከእነርሱ ጋር በመሆን ይፈትሻል::
- አማካሪ በምክር ፈላጊው አምነት ላይ ተገቢ ያልሆነ ተጽዕኖ ባያደርግም መንፈሳዊ አስተሳሰቡ በሕይወቱ ላይ ያመጣውን ጥቅምና ጉዳት መመዘን እንዲችል ሁኔታዎችን ያመቻቻል::
- በማማከር ግንኙነት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪና «ይሻለኛል» የሚለውን መምረጥ የሚችለው ምክር ፈላጊው ነው:: አማካሪው በሂደቱ የሚረዳው እንጂ ውሳኔ የሚወስንለት አለመሆኑ በግልጽ ሊታወቅ ይገባል::
- ምክር ፈላጊው የማማከር ሂደቱ ካልተስማማው በማንኛውም ጊዜ ሊያቋርጥ ወይም ወደ ሌላ አማካሪ ለመሄድ መጠየቅ ይችላል::

እነዚህና የመሳሰሉትን ሐሳቦች በቅድሚያ ለምክር ፈላጊዎች ማሳወቁ ለግንኙነቱ መጠናከርና ለውጤቱ መሳካት ጉልህ ሚና ይጫወታል:: ሁሉንም በአንድ ጊዜ መናገር ምቹ በማይሆንበት ሁኔታ እንደ አስፈላጊነቱ በሂደት አንድ በአንድ መግለጽ ይቻላል::

### *3.9. የምክር ፈላጊዎችን መሠረታዊ መረጃዎችን መሰብሰብ*

የማማከር አገልግሎት ስኬታማ እንዲሆን ምክር ፈላጊዎች ተገቢ መሠረታዊ መረጃዎችን መስጠት አለባቸው:: ስለእነርሱ በቂና አስፈላጊ መረጃዎች ካልተገኙ ለችግሮቻቸው መፍትሔ መፈለግ አይቻልም:: ስለዚህ ከተቻለ በመጀመሪያ ክፍለ ጊዜ ምክር ፈላጊዎች ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ወይም ስለራሳቸውና ስለችግሮቻቸው ዓይነትና መንስኤዎችን እንዲናገሩ ማበረታታት ያስፈልጋል:: ምክር ፈላጊዎች እንዲሞሉ የሚጠየቀው ቅጽ እነዚህን ነጥቦች የያዘ ነው:: (ቅጹን በገጽ 58 ላይ ይመልከቱ)

ምክር ፈላጊዎች በማማከር ጊዜ ስለራሳቸውና ስለችግራቸው መረጃ የሚሰጡት በአብዛኛው በመናገር በመሆኑ በግልጽ መናገር እንዲችሉ ማደፋፈር ያስፈልጋል:: ሰዎች በውስጣቸው ያለውን አሳብና ስሜት በንግግር መግለጽ እንዲችሉ ሆነው የተፈጠሩ በመሆናቸው ምክር ፈላጊዎችን በዚህ አንጻር ማበረታታትና እንዲናገሩም ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ተገቢ ነው:: ለዚህ የሚረዱትን ዘዴዎች በማማከር ዘዴዎች ውስጥ እንመለከታለን::



**ስለምክር ፈላጊዎች መሠረታዊ መረጃዎችን የመሰብሰቢያ ቅጽ**

- ስምናሙሉ አድራሻ
- ጾታ
- ዕድሜ
- ሃይማኖት
- ያደገበት ባሕላዊ ዓውድ
- የወሊብ ዝንባሌ
- ሥራ/መተዳደሪያ
    - መደበኛ ሥራ
    - መደበኛ ያልሆኑ ሥራዎች
- ትምህርት/ሥልጠና
    - የትምህርት ደረጃ
    - የተሰየ ሥልጠና/ሙያ
- የትዳር/ግንኙነት ሁኔታ
    - ያገባ
    - ያላገባ
    - የልጆች ብዛት
- የቅርብ ተጠሪዎች ስምና አድራሻ
- ዋና ችግር እንደሆነ የቀረበው አሳብ/አሁን ምክር ፈላጊው የመጣበት ጉዳይ
- የቤተሰብ ዳራ
    - ወላጆች/አባትና እናት
        - በሕይወት መኖራቸውን
        - ትምህርታቸው
        - ሥራቸው
        - ዕድሜያቸው
    - ወንድሞችና እህቶች
- መሠረታዊ የእድገት ታሪክ
    - የእድገት ሥፍራ
    - በማን፣ከማን ጋር አደገ?
    - ወላኝ የሕይወት ምዕራፎች
    - መልካምና ክፉ ገጠመኞች
- ጤንነት፣ የአካል አቋም
- የአእምሮ ችሎታና ክህሎቶች
- የባሕርይ ችግሮች
- የፍልቀ-ስሜት ሁኔታዎች
- በምክር ፈላጊው ላይ ጫና የሚፈጥሩ ውስጣዊና ውጫዊ እውነታዎች
    - ከስውነት ጋር የተያያዙ ጫናዎች
    - ሥነልቦናዊ ጫናዎች
    - ከማሕበራዊ ኑሮ ጋር የተገናኙ ጫናዎች
    - ከሥራ ጋር የተያያዙ ጫናዎች
- የምክር ፈላጊው ጠንካራ ነገሮች
- በአካባቢው ያሉ ድጋፍ ሊሰጡ የሚችሉ ነገሮች
    - ቃለመጠይቁን ያደረገው አማካሪ ስም
    - ሥፍራ
    - ፊርማ
    - ቀን

አማካሪ ምክር ፈላጊዎችን ለመረዳት ከሚፈልጋቸው መረጃዎች መካከል አንዱ የእምነት ጉዞአቸውን ማወቅ ነው። የእምነት ታሪክ ከልጅነት ይጀምራል። ምክር ፈላጊዎች በልጅነታቸው ወቅት ምን ዓይነት ልምምድ ነበራቸው? ስለፈጣሪ፣ ስለሃይማኖት መሪዎች/አገልጋዮች/ እንዲሁም ስለመንፈሳዊ ልምምድ የነበራቸውን መልካምና መጥፎ ትዝታዎችን ማወቅ ጠቃሚ ነው። አሁን ስላለፈው አስተሳሰባቸው ወይም ልምምዳቸው የሚሰማቸው ስሜት ምን እንደሆነ መጠየቅ ሁኔታው የአሁን ጊዜ እንደሆነ እንዲታወሳቸውና ስሜታቸው እውን ሆኖ እንዲወጣ ያደርጋል።

ምክር ፈላጊዎች ይከታተሉት የነበረው እምነት ወግንና ሥርዓትን እንዲያከብር የሚያስገድዱ ወይስ በነጻ ፈቃድ ላይ የተመሠረቱ ናቸው? አማኞች ጥፋት አጥፍተው ቢገኙ ምን ዓይነት ቅጣት ወይም የእርምት እርምጃ ይወሰድባቸዋል? ስለዚህ ጉዳይ ምክር ፈላጊዎቹ ምን ይሰማቸዋል? ምክር ፈላጊዎች በእምነታቸው ውስጥ ያከናወኑት መልካም የተባሉ ነገሮች አሉ? ከእነርሱ የሚጠበቅ ነገር ሆኖ ማከናወን የተሳናቸውስ ነገር ምን አለ? እምነቱ ለሁለንተናዊ ሕይወታቸው ዕድገት ምን አበረከተ? መሠረታዊ ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ እንዴት ረድቶአቸዋል? ምክር ፈላጊዎች ከእምነቱ እናገኛለን ብለው ተስፋ አድርገው ሳያገኙ የቀሩ ነገሮችም ግልጽ ቢሆኑ ጥሩ ነው።

የምክር ፈላጊዎችን የእምነት ታሪክ ማጥናት አባልነቱን ከአንድ እምነት ወደ ሌላ ቀይረውም እንደሆነ ያሳያል። የአባልነት ለውጥ አድርገው ከሆነ ለምን እንዳደረጉ ይታወቃል። ቀድሞ የነበሩበትን እምነት ለማደስ ገንቢ እርምጃዎችን ወስደው አቅቶአቸው ነው ወይስ ምንም ነገር ሳያደርጉ በግላቸው ወደ ሌላው በመሄድ መሸሸን መረጡ? ምክር ፈላጊዎች በእምነቱ ውስጥ ለማመንና ለመቀበል የሚቸገሩባቸው ጉዳዮች አሉ? እነዚህን ነገሮች እንዴት እያስተናገዱአቸው ነው? በእነዚህ ጥያቄዎች አማካኝነት የምክር ፈላጊዎችን እምነት በማጥናት ርዕዮተ ዓለማቸው ምን እንደሚመስልና ከችግሮቻቸው ጋር ያላቸውን ተያያዥነት ማውጣት ይቻላል። ከእነዚህ መረጃዎች ለምክር ፈላጊዎቹ ችግር መንስኤ ወይም መፍትሔ የሚሆኑ ነገሮች ይገኛሉ።

ስለዚህ ለእያንዳንዱ ርዕስ ጉዳይ ተገቢውን ጊዜ በመስጠት አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች መሰብሰብ ምክር ፈላጊዎችን በሚገባ ለመረዳትና ችግሮቻቸውንም በመፍታት ሂደት ገንቢ አስተዋጽኦ ለማድረግ ይረዳል። እነዚህ መሠረታዊ መረጃዎች አማካሪ ስለምክር ፈላጊዎቹ አጠቃላይ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖረው ይረደዋል። ከዚህ በመቀጠል የሚመጣው የምክር ፈላጊዎችን ችግር በስፋትና በጥልቀት ማለስና ዓላማ አውጥቶ በዚያ መሠረት መሥራት ነው።



### *3.10. በጋራ የማማከር እቅድ ማውጣት*

አማካሪውና ምክር ፈላጊዎች በማማከር ሂደት ውስጥ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው አብረው ዕቅድ ያዘጋጃሉ። ምክር ፈላጊዎች ይዘው የመጡትን ዋና ችግር ለመፍታት ተገቢ የሆኑ ዕቅዶችን በጋራ በማውጣት ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን እርምጃዎች ይወስዳሉ። ዕቅድ ወጥቶለት ከአንድ የታለመ ግብ ለማድረስ የማይሠራ ከሆነ ማማከር ፍሬያማ ሊሆን አይችልም። አንዳንድ ጊዜ ምክር ፈላጊዎች ወደ አማካሪው ዘንድ እንዲመጡ ያደረጋቸው ችግር ምን እንደሆነ በግልጽ ሳያውቁት ይችላሉ። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም በመጀመሪያዎቹ የማማከር ክፍለ ጊዜያት ምክር ፈላጊዎች ስለችግሮቻቸው ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዲያገኙ መርዳት ተገቢ ይሆናል።

ምክር ፈላጊዎች ዕቅድ ወደ ማውጣት ውስጥ ቶሎ እንዲገቡ በማሰብ ማጣደፍ አይገባም። አማካሪው በምክር ፈላጊዎቹ እርምጃ ይንቀሳቀሳል። ቶሎ መፍትሔ ተገኝቶ በምክር ፈላጊዎች ሕይወት ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ በማሰብ ማጣደፍ የታሰበውን ሳይሆን ያልተፈለገውን ውጤት ያስከትላል። ልጅ ዛሬ ተረግዞ ዛሬ እንደማይወለድ ሁሉ ምክር ፈላጊዎችም በፈለጉበት ጊዜ ቶሎ ለችግሮቻቸው መፍትሔ ማግኘት አይችሉም። በቂ ጊዜ ተሰጥቶት በሂደት የሚፈጸም ዕቅድ ጥሩ ውጤት ይኖራዋል። የምክር ፈላጊዎችን ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በእነርሱ እርምጃ መንቀሳቀስን ከእግዚአብሔር የእረኝነት ተግባር መማር እንችላለን። «መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፣ ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል፣ የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል» (ኢሳ40:11)። ስለዚህ አማካሪ በምክር ፈላጊዎቹ እርምጃ በመሄድ ዕቅድ ማውጣትና ለተግባራዊነቱ አብሮ መሥራት ይገባዋል።

ስማማከር ሂደት የሚነደፉ ዕቅዶች ከምክር ፈላጊዎች ወቅታዊና መሠረታዊ ችግር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። በተመጣጣኝ የጊዜ ገደብ ውስጥ መፍትሔ ሊፈለግላቸው የሚችላቸው እና ምክር ፈላጊዎች ባላቸው ችሎታና ግብአቶች ሊደርሱባቸው የሚችሉ መሆን አለባቸው። ዕቅዶቹ ጥቅል ሳይሆኑ ዘርዘር ባለ መልኩ የተቀመጡና አማካሪውም ባለው ችሎታ ምክር ፈላጊዎች ከታለመው ግብ እንዲደርሱበት አስፈላጊ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚችልበት ሊሆኑ ይገባቸዋል።

አማካሪውና ምክር ፈላጊዎች በጋራ ያወጡትን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሁለቱ የመግባባት ችሎታና መተባበር ወሳኝነት አለው። ጥሩ ዕቅድ ቢወጣም የሁለቱ ቀና ትብብር የማይኖር ከሆነ የሚፈለገው ውጤት አይገኝም። አማካሪው ምክር ፈላጊዎችን በተገቢ ሁኔታ በማዳመጥ፣ በሁኔታዎች ላይ ባልተመሠረተ አቀባበል በመቀበልና ለዐውዱ ምቹ የሆኑትን ስልቶች በመጠቀም ዓላማ አድርገው ወደተነሱበት ግብ እንዲደርሱ መምራት ይችላል። ሁለቱም ያወጡትን የማማከር ዕቅድ እንደ አስፈላጊነቱ በመስማማት መለወጥና ማሻሻል ይችላሉ። ምክር ፈላጊዎች ደረጃ በደረጃ

ለችግሮቻቸው መፍትሔ እያገኙ በሚሄዱበት ጊዜ የመጨረሻው ዒላማቸው ዘንድ ለመድረስ አስፈላጊውን ዋጋ ይከፍላሉ።

### 3.11. የምክር ፈላጊዎችን ችግር በጥልቀት ማሰስና መፍትሔ መፈለግ

በዚህ ጊዜ አማካሪውና ምክር ፈላጊዎች ያቀዱትን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ አብረው ይሠራሉ። ተገቢውን ወሰን በመጠበቅ ምክር ፈላጊዎች ለለችግሮቻቸው በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ይደረጋል። የምክር ፈላጊዎች ስሜት፣ ሐሳብና ድርጊቶች ምን እንደሆኑ በጥልቀት ይፈተሻል። በሁለቱ መካከል ባለው ግንኙነት ምክር ፈላጊዎች በውስጣቸው ያለውን ስሜትና ሐሳብ እንዲገልጹ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። እነዚህ ፍልቀ-ስሜቶች በሚገለጹበት ጊዜ አማካሪው «ይህ ትክክል ነው»፣ «ይህ ትክክል አይደለም»፣ «እንዲህ ሊሰማህ አይገባም» የሚል አስተያየት ሳይሰጥ እንዲገለጹ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ምክር ፈላጊዎች ተገቢውን መፍትሔ ማግኘት የሚችሉት ለለችግሩ የተሰማቸውን ስሜት በነጻነት መግለጽ ሲችሉ ነው። ለለዚህ አማካሪ ምክር ፈላጊዎች ባለፈው ጊዜ የተሰማቸውን ስሜት በቃላት እንዲገልጹ ብቻ ሳይሆን ሁኔታው አሁን እንደተከሰተ በማሰብ ስሜታቸውን መግለጽ እንዲችሉ ማድረግ በቂ ግንዛቤ ለማግኘት ጠቃሚ እርምጃ ነው።

ምክር ፈላጊዎች ስሜታቸውን ብቻ ሳይሆን አስተሳሰባቸውንም መግለጽ አለባቸው። ከስሜት ሥር የተሸፈኑ ሐሳቦች ሲወጡ የችግሮችን መንስኤዎች ማወቅ ይቻላል። እነዚህ ሐሳቦች በትክክል ሲታወቁ የትኞቹ ሐሳቦች በተጨባጭ እውነታዎች ላይ የተመሠረቱና የትኞቹ ከተሳሳቱ አይታዎች እንደመነጩ አውቆ ተገቢውን የማስተካከል እርምጃ መውሰድ ይቻላል። እንደ ክርስቲያን አማካሪ የምክር ፈላጊዎች ሐሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ምን እንደሚመስል በመገንዘብ ተገቢው የአእምሮ ተሐድሶ ይታቀዳል። በሰዎች አእምሮ ውስጥ ያለው አስተሳሰብ ድርጊታቸውንና የሕይወት ዘይቤያቸውን ይወስናል። የድርጊትና የባሕርይ ለውጥ እንዲመጣ የእነዚህ መሠረት የሆኑ አስተሳሰቦች ተለይተው መውጣት አለባቸው።

አስተሳሰብ የሰዎችን ሕይወት ይወስናል። ሰው የሆነውን የሚሆነው በአስተሳሰቡ ምክንያት ነው። ሰው በልቡ ውስጥ ያለውን ሐሳብ ይተገብራል። በሰዎች መካከል ልዩነት የሚያመጣው በእነርሱ ላይ የደረሰው ችግር መጠን መለያየት ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው ሰዎች ስለደረሰባቸው ሁኔታ ያላቸው አስተሳሰብ ነው። ሁለት ተመሳሳይ ነገር የገጠማቸው ሰዎች ሁኔታውን የሚረዱበት መንገድ የተለያየ መሆን በሕይወታቸው ላይ ያለውን ተጽዕኖ ይለያያል። አማካሪ ትኩረት የሚያደርገው ምክር ፈላጊዎች ስለችግራቸው ያላቸው አስተሳሰብ ምን እንደሆነ፣ ምን ያህል በተጨባጭ እውነታ ላይ የተመሠረተና ከዚህ በፊት እንዴት ለማስተናገድ ጥረት እንደተደረገ በመረዳት ላይ ነው።

በምክር ፈላጊዎች ላይ የደረሰው ነገር ምን እንደሆነ መረዳት በራሱ በቂ ባለመሆኑ ለለሆነው ነገር ያላቸው እይታ በግልጽ መታወቅ አለበት።



ከዚህ አንጻር መፍትሔዎች ሲታሰቡ አንዳንድ ጊዜ የችግራቸውን መንስኤዎች ማስወገድ የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል። በዚህን ጊዜ ምክር ፈላጊዎች ስለሁኔታው ያላቸውን አስተሳሰብ መለወጥ መፍትሔ ይሆናል። ምክር ፈላጊዎች ስለችግራቸው ያላቸውን አስተሳሰብ መለወጥ እንደ ዋና የመፍትሔ ሐሳብ ተደርጎ የሚወሰደው ችግሮቹ/መንስኤዎቹ/ የማይለወጡ ዓይነት ሲሆኑ ነው። ለማይለወጥ ችግር መፍትሔው የራስን እይታ መለወጥ ይሆናል፤ ይህ ደግሞ ረጅም ጊዜ የሚወሰድ ተግባር ነው።

ምክር ፈላጊዎች ስለችግራቸው፣ ከዚህ በፊት ከነበራቸው እይታ የተለየ ግንዛቤዎች ማግኘት ሲጀምሩ የታሰመውን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። ምክር ፈላጊዎች በአስተሳሰባቸው ከተያዙበት ውስንነት ይወጣሉ። ሁኔታዎችን በአንድ አቅጣጫ ብቻ ከማየት ወጣ ብለው ከተለያዩ አቅጣጫዎች በማየት ወደፊት ይንቀሳቀሳሉ። እንዲህ ዓይነት መረዳት በሚኖርበት ጊዜ ምክር ፈላጊዎች ለለራሳቸው፣ ለለችግራቸውና ለለሁኔታዎች በአጠቃላይ የሚሰማቸው ስሜት የተለየ ይሆናል። ይህ መረዳት ምክር ፈላጊዎች ከዚህ በፊት ያደርጉ ከነበሩት በተለየ ሁኔታ ለመኖር ጥረት እንዲያደርጉም ልባቸውን ያነሳሳል።

ምክር ፈላጊዎች ለለችግሮቻቸው ተገቢውን ግንዛቤ እንዲያገኙ በማድረግ፣ አስቀድሞ ይመለከቱ ከነበሩበት እይታ በተለየ መልኩ መመልከት እንዲችሉ ለመርዳት ተጨባጭ እውነታዎችን ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ እንዲረዱ ማገዝ ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ እንደ ምክር ፈላጊዎቹ ችግርና ዓውድ ተገቢውን እውነት ማስጨበጥ ይጠቅማል። አንድን እውነታ በሚገባ ለመረዳት ያለውን የመረጃ እጥረት መሙላትና ከምክር ፈላጊዎች ዓውድና ችግር ጋር በማገናኘት እንዴት በእውነቱ መኖር እንደሚቻል ማስተማር ተገቢ ነው። ምክር ፈላጊዎች ለለራሳቸው፣ ለለችግራቸውና ለለሚኖሩበት ዓለም የተለየ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሊረዳ የሚችለውን እውነት እንዲጨብጡ ማድረግ አሁን የገጠማቸውን ችግር ብቻ ሳይሆን ወደፊት የሚያጋጥማቸውን ሁኔታ በተለየ ሁኔታ መመልከት እንዲችሉ ከማድረግ አንጻር ዘላቂ ጥቅም አለው። «ለምክር ፈላጊዎች የአስተሳሰብ እይታ ለፋት አስፈላጊ ነው» የሚባለው እውነት እንደ አማካሪውና ምክር ፈላጊው ርዕዮተ ዓለም የተለያየ ቢሆንም ለክርስቲያን አማካሪ ይህ «እውነት» የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ መርሆዎችን ያመለክታል።

አማካሪ የምክር ፈላጊዎችን ስሜትና አስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊት ይለማመዱአቸው የነበሩት ወይም/እና አሁንም የሚለማመዱአቸው ባሕርያቶች ምን እንደሆኑ ለይቶ ለማወቅ ይሠራል። እነርሱ ይዘው ከመጡት ጉዳይ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተያያዥነት ያላቸውን ባሕርያቶችን/ድርጊቶችን/ በግልጽ ያወጣቸዋል። ችግሮቹ እንዲፈጠሩ ያደረጉ ባሕርያቶች ምንድናቸው? ችግሩ ሲከሰት ምን ዓይነት እርምጃ ወሰዱ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ይፈልጋል። ከእነዚህ መልሶች በመነሳት ምክር ፈላጊዎች ችግሮቻቸውን ለመፍታት ወደፊት ምን ለማድረግ እንደሚያስቡ ይፈትሻል። ችግሮቹን ለመፍታት ከዚህ በፊት ሲያደርጉአቸው ከነበሩት

ድርጊቶች ምን የተለየ ነገር ለማድረግ ያስባሉ? በዚህ ዓይነት መንገድ የምክር ፈላጊዎችን የቀደሙ ድርጊቶች በማወቅ ወደፊት ችግሩን ለመፍታት ሊወሰዱ የሚገባቸውን ተገቢ እርምጃዎች (ድርጊቶችን) ለይቶ ማውጣት ይቻላል።

በዚህ ሂደት አማካሪ ምክር ፈላጊዎች ሊያደርጉት የሚገባውን ተገቢውን ድርጊት በቀጥታ ሊነግራቸው አይገባም። አማካሪው እነርሱ ማድረግ የሚገባቸውን ከነገራቸው ትዕዛዝ መስጠት ይሆናል። ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ምክር ፈላጊዎቹ በራሳቸው ለይተው ማውጣት እንዲችሉ ከእነርሱ ጋር ሆኖ መምራት የተሻለ ውጤት ስለሚኖረው እነርሱን «እንዲህ አድርግ»፣ «እንዲህ አታድርግ» ብሎ ትዕዛዛዊ መልዕክት መስጠት አይደገፍም። አማካሪው፣ ምክር ፈላጊዎች የሚያደርጉትን ነገር ከነገራቸው ሐሳቡ የራሳቸው እንደሆነ ስለማይቀበሉት ተግባራዊ ለማድረግ የልብ ተነሳሽነት አይኖራቸውም። የተነገራቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ሲነሱ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ቢሳካላቸው አማካሪውን እንጂ ራሳቸውን አያመሰግኑም። የተሰጣቸው ምክር ባይሠራላቸው ደግሞ አማካሪውን እየወቀሱና እየኮነኑ ይኖራሉ። ስለዚህ ምክር ፈላጊዎች መፍትሔ ወደማግኘት እንዲደርሱ መርዳት እንጂ መፍትሔ ለመስጠት ጥረት ማድረግ ተገቢ አካሄድ አይደለም።

ምክር ፈላጊዎች በፊት ያደርጉ የነበሩትን ድርጊቶችን በመተው አዳዲስ ገንቢ የሆኑ ድርጊቶችን ማድረግ ሲጀምሩ ሁለንተናዊ ሕይወታቸው እየተለወጠ ይሄዳል። አንድ ተገቢ ያልሆነ ድርጊትን መተው በራሱ ብዙ የሕይወት ለውጦችን ያስከትላል። ስለዚህ ምክር ፈላጊዎች ደረጃ በደረጃ ተገቢ ያልሆኑትን ድርጊቶችን መተውና ተገቢዎቹን መለማመድ እንዲችሉ፣ ከእነርሱ ጋር በመጓዝ አስፈላጊውን *ምሪት* መስጠቱ ለመልካም ውጤት ቀጣይነት ወሳኝ ነው። አማካሪው ምሪት ከሚሰጥባቸው መንገዶች አንዱ ምክር ፈላጊዎች ስለድርጊቶቻቸው ምንነትና እያንዳንዱ ድርጊት በሕይወታቸውና በሌሎች ላይ አሁን እንዲሁም በቀጣይነት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ማሳየት ነው። ከዚሁ ጋር ቀድሞና አሁን ከሚያደርጉት በተቃራኒ ቢያደርጉ ደግሞ ሊያገኙ የሚችሉአቸውን ዘላቂነት ያላቸውን ጥቅሞችን እንዲያዩ ማድረግ ድርጊታቸውን ለመለወጥ የልብ መነሳሳት እንዲኖራቸው ያግዛቸዋል።

አስተሳሰብ የምክር ፈላጊዎችን ድርጊት እንደሚወስን ሁሉ አዳዲስ ልምምዶችም ምክር ፈላጊዎች ስለራሳቸው የተለየ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ። መጥፎ ድርጊቶችን ሲያደርጉ በነበሩበት ሁኔታ አሁን ራሳቸውን አይመለከቱም። እነዚህ መልካም ልምምዶች በሌሎች ሰዎችም ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል።

የምክር ፈላጊዎች ችግር አንድ ብቻ አይደለም። ለብቻው ተነጥሎ የሚታይ የለም። ችግሮች ተያያዥነት አላቸው። ለምሳሌ የአንድ ምክር ፈላጊ ዋነኛ ችግር የሥራ አለመሳካት ቢሆን ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የገንዘብ ችግር፣ ከሰዎች ጋር መግባባት አለመቻል፣ የሰዎች ጣልቃ ገብነትና



የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ። አማካሪ፣ ምክር ፈላጊዎች ዋና ነው ብለው ከሚያቀርቡት ችግር ጋር ሌላ አብሮ ተጓዥ እንዳላቸው በመረዳት እነዚህን ችግሮች ይፈትሻል። የእነርሱን ችግሮች ካለሰና ከተገነዘበ በኋላ ሁሉንም በአንድ ጊዜ ለመፍታት ጥረት አያደርግም። ችግሮቹን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የአንዱ መፈታት ለሌሎች ችግሮች መፍትሔ በመፈለግ እንጻር መሠረት የሚጥሉትን መርጦ ከእነርሱ ይጀምራል። የአንዱ ችግር መፈታት፣ ምክር ፈላጊዎች በዚያው ሂደት ሌሎችን እንዲፈቱ ግንዛቤና ክህሎት ይሰጣቸዋል።

ምክር ፈላጊዎች ለችግራቸው መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉትን አማራጭ ሐሳቦችን ሁሉ እንዲዘረዝር መርዳት ተገቢ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ የሚፈለገውን አማራጭ መፍትሔ እንዲያገኙ መምራት ጠቃሚ ነው። እነዚህ የቀረቡት አማራጭ መፍትሔዎች ምን ያህል ከችግሩ ጋር ተዛማጅነት እንዳላቸውና ዓውዳዊ ተግባራዊነት እንደሚኖራቸው መገምገም ያስፈልጋል። ምክር ፈላጊዎቹ የእያንዳንዱን አማራጭ የመፍትሔ ሐሳብ ጥቅምና ጉዳት በማቅረብ ይገመግማሉ። በዚህ ሂደት አማካሪው አስፈላጊውን ግንዛቤ የማስጨበጥና እይታ የማስፋት *ሥራዎችን* ይሠራል። ከዚያም ከቀረቡት የመፍትሔ ሐሳቦች እጅግ የተሻለውን ማለትም ተገቢውን ዋጋ በማስከፈል ዘላቂነት ያለውን ጥቅም የሚያመጣውን ይመርጣል።

ምክር ፈላጊዎች በዚህ ወቅት የሚወስዱአቸው ውሳኔዎች ምናልባት ከልባቸው ሳይሆን ስለሚችል ወይም በቂ ግንዛቤ ሳያገኙ ስለሚሆን መፈተሽ ያስፈልጋል። በመሠረተ ሐሳብ ምክር ፈላጊዎች ውጫዊ ጫናዎች ሳይደረግባቸው ለሁኔታው በቂና ሚዛናዊ ግንዛቤ በማግኘት የወሰኑት ሲሆን ለተግባራዊነቱ የሚኖራቸው መሰጠት ይጨምራል።

እንግዲህ አማካሪ የምክር ፈላጊዎችን ስሜት፣ አስተሳሰብና ድርጊት በጥልቀት በመመርመር፣ ተገቢውን ግንዛቤ እንዲያገኙ በማድረግና በእያንዳንዱ ነገር ላይ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች ከታወቁ በኋላ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል መወያየት ቀጣይ እርምጃ ይሆናል። በማማከር ሂደት ሰፊውን ጊዜ የሚወስደው፣ የምክር ፈላጊዎችን ችግሮች በጥልቀት ተገንዝቦ ገንቢ መፍትሔዎችን ማፍለቅ ነው። በመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ በተስማሙበት የማማከር ክፍለ ጊዜ ብዛት እርምጃቸውን መወሰን፣ ወይም አሁን መጨመር ወይም መቀነስ የሚያስፈልጋቸው ከሆነም እንደ ሁኔታው በመስማማት መወሰን ይጠበቅባቸዋል።

### *3.12. የማማከር ውይይትን መደምደም*

የማማከር ውይይትን መደምደም በሁለት ዓይነት መልኩ ይከናወናል። የመጀመሪያው አማካሪውና ምክር ፈላጊዎች በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ የሚያደርጉትን ውይይት መደምደም ነው። ሁለቱ በወሰኑት መሠረት ለአንድ ሰዓት ወይም ለሃምሳ ደቂቃዎች ከተገናኙ በኋላ የዕለቱን ውይይታቸውን ይደመድማሉ። በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ እንደተገለጸው አንዳንድ ጊዜ ምክር ፈላጊዎች በመጀመሪያዎቹ ደቂቃዎች ዋናውን

የልባቸውን አሳብ አውጥተው ሳይናገሩ ይቆዩና በመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ላይ መናገር ሲጀምሩ ይችላሉ:: እንዲህ ሲሆን ጊዜውን ከማራዘም ይልቅ አሳቡን በመመዝገብ በሚቀጥለው ቀጠሮአቸው እንደሚቀጥሉ በመስማማት በተባለው ጊዜ መደምደም ያስፈልጋል:: አማካሪ የዕለቱን የማማከር ሂደት ሲደመድም ምክር ፈላጊዎች ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ከቁነፈሉ ቶሎ ከመዝጋት ይልቅ ተገቢውን የማዳን እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል::

አንዳንድ ጊዜ አማካሪው የምክር ፈላጊዎቹ ችግር ውስብስብ መሆኑንና ከአቅሙ በላይ እንደሆነ ሲገነዘብ ወደ ሌሎች አማካሪዎች መምራት ይገባዋል:: በምክር ፈላጊዎች ላይ የሚታዩ ምልክቶች ከፍተኛ የአእምሮ መታወክን የሚያሳዩ ሲሆኑ ደግሞ ወደ ሥነአእምሮ ሐኪም መምራት ይጠበቃል:: ከአዕምሮ መታወክ ምልክቶች የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው:-

- ✓ ከፍተኛ የመንፈስ ጭንቀት!
- ✓ ያልተለመደና ሌሎች የማይሰሙትን ድምጽ መስማት፣
- ✓ ያልተለመደና ሌሎች ሰዎች የማያዩትን ነገሮች ማየት!
- ✓ ከፍተኛና ሚዛኑን የሳተ የበደለኛነት ስሜት መስማት፣
- ✓ የተለየና ተጨባጭ መንስኤ የሌለው ፍርሃት፣
- ✓ ከመጠን በላይ የሆነ ተስፋ መቁረጥ ወይም ትካዜ፣
- ✓ ከተጨባጭ እውነታ ውጭ መናገርና ማድረግ!
- ✓ ከሌሎች ሰዎች መገለልና ከማንኛውም ማሕበራዊ ግንኙነት ውጭ መሆን!
- ✓ ሰራስና ለሌሎች የሚያሰጋ ድርጊት ለመፈጸም አመልካች ሁኔታዎች መኖር::

ሁለተኛው አጠቃላይ የማማከር ሂደቱን መደምደም ነው:: አማካሪውና ምክር ፈላጊው በስምምነታቸው መሠረት አንድ ላይ ለተወሰኑ የማማከር ክፍለ ጊዜያት አብረው ካሳለፉ በኋላ መደምደም ይገባቸዋል:: ተጀምረው ያላለቁ ተግባሮች ካሉ እንደ አስፈላጊነቱ የውይይት ክፍለ ጊዜያትን መጨመር የሚቻል ቢሆንም በተወሰነው ወቅት ማቆም ጠቃሚነት አለው:: የማማከር ግንኙነቱ ቀጣይነት ሲኖረው እንደሚገባ የሚታመንበት ሲሆን የተጀመረውን ሂደት ጨርሶ ወደፊት እንደ አመቺነቱ በአዲስ ሁኔታ መጀመሩ ይመረጣል:: የአማካሪና የምክር ፈላጊዎች ግንኙነት በጊዜ የተገደበ በመሆኑ መደምደም አለበት እንጂ ሁለቱ በመፈለጋቸው ምክንያት ዝም ብሎ መቀጠል የለበትም::

በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ የማማከር ግንኙነት የሚደመደመው ሁለቱ ያቀዱት ዕቅድ ተግባራዊ ሲሆን ነው:: በመጀመሪያ ላይ በማማከር ግንኙነት ሂደት እንዲመጣ የተፈለገው ውጤት ሲገኝ፣ ዓላማው ግቡን ሲመታ ግንኙነቱ ይቋረጣል:: የማማከር ዋና ዓላማው፣ የምክር ፈላጊዎችን ችግሮች ሁሉ መፍታት ሳይሆን በአንድ ጉዳይ ላይ ምክር ፈላጊዎች መፍትሔዎችን አግኝተው በቀጣይነት በሕይወታቸው የሚገጥሙአቸውን ተግዳሮቶች ገንቢ በሆኑ መንገዶች መያዝ እንዲችሉ መርዳት ነው:: ምክር ፈላጊዎቹ በሂደቱ



በሚያገኙት ክህሎት ሕይወታቸውን በተሻለ መንገድ መምራት መጀመራቸው በራሱ አንድ ዓላማ ነው::

አንዳንድ ጊዜ የማማከር ግንኙነት መጀመሪያ በታቀደው መሠረት እንዳይቋረጥ የሚያደርጉ ተገቢ ያልሆኑ ሁኔታዎች ይኖራሉ:: የማማከር ሂደት የታለመውን ግብ ከመታ በኋላም እንዲቀጥል ከሚደረግባቸው ሁኔታዎች መካከል አማካሪ ከምክር ፈላጊዎቹ ጋር ለራሱ ጉዳይ/ጥቅም/ ግንኙነቱን መቀጠል ሲፈልግ ወይም ምክር ፈላጊዎች ከአማካሪው ጋር ግንኙነታቸውን ጠብቀው መቆየት ሲፈልጉ! አማካሪው ተገቢውን እርምጃ ሳይወስድ መቅረት በዋነኛነት የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው::

አማካሪ አንድን የማማከር ግንኙነት ሂደት በሚደመድምበት ወቅት ከምክር ፈላጊዎች ጋር ሆኖ በሂደቱ የተገኙትን ውጤቶችና ታቅደው ተግባራዊ ያልሆኑትን ነገሮች መገምገም አለበት:: በግንኙነት ሂደቱ ውስጥ የተገኙትን መልካም ውጤቶችን ምክር ፈላጊዎች በቀጣይነት እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉ አስፈላጊው ዕቅድ መኖሩን ይገመግማል:: እንደ አስፈላጊነቱ ግንኙነቱ ሲቋረጥ ምክር ፈላጊዎች ሊከተሉት ስለሚያስፈልጋቸው ዕቅድ እንዲሠራ ሁኔታዎችን ያመቻቻል:: በዚህ ሂደት ውስጥ ያልተፈቱ የምክር ፈላጊዎች ችግሮችም ተለይተው ይወጣሉ:: ምክር ፈላጊዎች ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ ማግኘት የሚችሉባቸውን አማራጭ መንገዶችን ይፈልጋሉ:: ከእነዚህም በዋናነት የሚጠቀሰው ወደ ሌላ የተሻለ ወይም በቂ የማማከር ብቃት ወዳለው አማካሪ መምራት ነው:: ይህም በእነርሱ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን አማካሪው ፍላጎታቸውን መሠረት በማድረግ ወደ ሌሎች መምራት ይጠበቅበታል::

እንግዲህ የማማከር ግንኙነት የሚጀምረው አማካሪውና ምክር ፈላጊዎች በቀጠሮአቸው መሠረት ሲገናኙ ነው:: በዚህ ግንኙነት በአንድ ጊዜ ለአንድ ሰዓት ያህል ይወያያሉ:: ከዚያም በሳምንት ወይም እንደ ምክር ፈላጊዎቹ ችግር ሁኔታ ከሳምንት ባነሰ ወይም በበለጠ ጊዜ በተከታታይነት ለተወሰኑ ጊዜያት ይገናኛሉ:: የግንኙነታቸው ሂደት ምክር ፈላጊዎች ለመጡበት ችግር መፍትሔ እስኪያገኙ ድረስ ይቆያል:: የአንዳንድ ምክር ፈላጊዎች ችግሮች በአጭር ጊዜ የሌሎች ደግሞ በረጅም ጊዜ ግንኙነት የሚፈቱ ናቸው:: አማካሪ እነዚህን ችግሮች የሚያስተናግደው እንደ ማማከር ብቃቱና እንዳለው ጊዜ ሁኔታ ነው:: የምክር ፈላጊዎች ችግር ውስብስብ በሚሆንበት ጊዜ ወደ ሌሎች አማካሪዎች መምራት ያስፈልጋል::

## ምዕራፍ 4

## የማማከር ዘዴዎች

በዚህ ክፍል ውስጥ የማማከር ዘዴዎችን እንመለከታለን። በማማከር አገልግሎት የምንጠቀምባቸው የተለያዩ የማማከር ዘዴዎች አሉ። እያንዳንዱ አማካሪ ከምክር ፈላጊዎቹ ችግር ጋር የሚሄዱትን፣ የተሻለ እውቀትና ልምድ ያዳበረበትን፣ እንደሚከተለው የማማከር ጽንሰ-ሐሳብና ፍልስፍና እንዲሁም እንደ ዓውዳዊ ውጤታማነታቸው መርጦ መጠቀም ይችላል። የማማከር ዘዴዎቹን እንደ አስፈላጊነታቸው ይጠቀምባቸዋል እንጂ የግድ ሁሉንም በአንድ ጊዜ እንዲጠቀም የሚያስገድዱ ሁኔታዎች የሉም። ለአንዳንድ ምክር ፈላጊዎች የተጠቀምነውና ውጤታማ ያደረገን ዘዴ በሌላ ጊዜ ለሌሎች ብናውል ወደ መልካም ውጤት የሚያመራን ላይሆን ይችላል። ስለዚህ መቼ፣ ምን ዓይነት ዘዴና ከማን ጋር መጠቀም እንደሚያስፈልግ አማካሪው ለይቶ የሚያወጣቸው ነገሮች ይሆናሉ።

ብዙ አማካሪዎች ብዙውን ጊዜ ከሚጠቀሙባቸው የማማከር ዘዴዎች መካከል ጥቂቶቹን በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን።

### *ዘዴ1፡ ትኩረት መስጠት*

ምክር ፈላጊዎችን በትክክል ለመረዳት አማካሪ ለእነርሱ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል። ይህ ደግሞ በአካልና በሥነልቦና ደረጃ ሊከናወን የሚችል ጉዳይ ነው። አማካሪ ለምክር ፈላጊዎች ትኩረት መስጠቱን በአካሉ ማሳየት ይችላል። ይህ ከአቀማመጥ ይጀምራል። አማካሪ ከምክር ፈላጊዎቹ ጋር ሲቀመጥ እግሩን አነባብሮ ባይቀመጥ የተሻለ ነው። እግርን አነባብሮ መቀመጥ በአንዳንድ ባሕሎች አሉታዊ ትርጉም ስላለውና በአነባብሮ ለረጅም ጊዜ መቀመጥ ስለማይቻል ካሬ የሆነ አቀማመጥ ይመረጣል። ከፊት ክፍት በሆነ ሁኔታ ወደ ምክር ፈላጊዎቹ ትንሽ ዘንበል ብሎ አነርሱን ፊት ለፊት ማየት በሚቻልበት ሁኔታ ዘና ብሎ መቀመጥ ይደገፋል። ለአቀማመጥ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ከምክር ፈላጊዎች ጋር ተገቢውን ተግባቦት ለመፍጠር ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ታስቦ ነው።

ከአቀማመጥ አንጻር የማማከር ሂደቱ የሚደረገው ቢሮ ውስጥ ከሆነ ከምክር ፈላጊዎቹ በ45 ዲግሪ ማዕዘን መቀመጥ ይመረጣል። ይህ ከምክር ፈላጊዎች ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ የመፋጠጥ ዓይነት አቀማመጥን ለማስወገድ እንዲሁም ከጎን ከሆነ ደግሞ ተገቢ ያልሆነ ወሰን መጣስ እንዳይከሰት እንዲሁም ከጎን ሆኖ ከአነርሱ ጋር በመተያየት መወያየት አዳጋች ስለሚሆን ነው።

በሥነልቦና ለምክር ፈላጊዎች ትኩረት መስጠት የሚለው አማካሪው አነርሱን ለማዳመጥ ውስጣዊ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባው የሚያሳስብ ነጥብ ነው። አማካሪው ከምክር ፈላጊዎቹ ጋር መሆኑ ብቻ ተዓምር አይፈጥርም። በአካል ብቻ ሳይሆን በአእምሮውም ከአነርሱ ጋር ሲሆን



ሊጠቅማቸው ይችላል። በአካል ከእነርሱ ጋር ሆኖ አእምሮው ግን ሌሎች ጉዳዮችን የሚያስተናግድ ከሆነ ምክር ፈላጊዎች እንዲሁ በከንቱ ጊዜያቸውን ያባክናሉ። ስለዚህ አማካሪው ለምክር ፈላጊዎቹ ያልተቋረጠ ትኩረት ለመስጠት «ውስጡን መሰብሰብ» አለበት። ወደ አእምሮው የሚመጡትን ወይም ጣልቃ የሚገቡትን ጉዳዮች ማስተናገድ የለበትም። ምክር ፈላጊዎች ሲናገሩ አነርሱን የሚሰማቸው እየመሰለ በሐሳቡ ግን ሌሎች ጉዳዮችን ከማስላሰል ተግባር ወጥቶ ሥርዓት ገዝቶ በእነርሱ ላይ ብቻ ማተኮር ይኖርበታል። አማካሪው ሌሎች በውስጡ የሚያውኩትን ሐሳቦች ትቶ ወይም *የአየር ጣቢያዎችን ሁሉ ዘግቶ* ለምክር ፈላጊዎቹ ብቻ ክፍት መሆንን ማሳደግ ይገባዋል። በእርግጥ ይህ በአንድ ጊዜ የሚሆን ነገር ሳይሆን ራስን መግዛት በመለማመድ ውስጥ የሚያድግ ችሎታ ነው።

### *ዘዴ2፡ ጥያቄዎችን መጠየቅ*

ስለምክር ፈላጊዎች መሠረታዊ መረጃዎችን ለማግኘት ጥያቄዎችን መጠየቅ ተገቢ ነው። አማካሪ ምክር ፈላጊዎች የሚናገሩት ሐሳብ ካልገባውም ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ለማግኘት ይጠይቃል። አማካሪ ምክር ፈላጊዎች «አዎን» ወይም «አይደለም» በማለት የሚመልሱትን ዓይነት ጥያቄዎችን በብዛት ባይጠይቅ ይመረጣል። ለምሳሌ «ትምህርት እየተማርክ ነው?» ወይም «አባትና እናትህ በሕይወት አሉ?» የሚሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ «አዎን» ወይም «አይደለም» የሚል ምላሽ ስለሚያስከትል ስለምክር ፈላጊዎች ብዙ ጠቃሚ መረጃዎችን አይሰጡንም። ከዚህ በተሻለ ሁኔታ ብዙ መረጃዎችን ሊያስገኙ የሚችሉ እንዲሁም ምክር ፈላጊዎች ራሳቸውን በሚገባ መግለጽ እንዲችሉ ዕድል የሚሰጡ ክፍት የሆኑ ጥያቄዎች ይመረጣሉ። ለምሳሌ «እስቲ ስለትምህርትህ ንገረኝ» «ስለቤተሰብህ ሁኔታ ማወቅ ለማማከሩ ሂደት ጠቃሚ በመሆኑ እስቲ ስለእነርሱ ንገረኝ» ማለት ይቻላል። እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ ምክር ፈላጊዎች ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚያስቡትን ወይም ለመናገር የሚፈልጉትን ክፍል እንዲናገሩ ዕድል ይሰጣቸዋል። ከዚያ በኋላ ተከታታይ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሰፊ ግንዛቤ ማግኘት ይቻላል።

ከአቀራረብ አንጻር አማካሪ የሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ቀጥተኛ፣ ግልጽና አጭር ቢሆኑ የተሻለ ነው። በአንድ ጊዜ ብዙ ተደራራቢ ጥያቄዎችን መጠየቅ ምክር ፈላጊዎችን ግራ ያጋባል። ስለዚህ ተራ በተራ እነርሱ ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋና የእውቀት/ችሎታ/ ደረጃ አንድ ክፍት ጥያቄ ማቅረብ ያስፈልጋል።

በማማከር ግንኙነት ውስጥ ገንቢ ያልሆነ ሊጠየቅ የማይገባ አንድ ጥያቄ አለ። ምክር ፈላጊዎች «ለምን?» የሚል ጥያቄ መጠየቅን አይፈልጉም፣ እንዲህ ቢጠየቁም ተገቢውን ምላሽ አይሰጡም። ይህ ዓይነት ጥያቄ ምክር ፈላጊዎች በየዋህነት ራሳቸውን ገልፀው እንዳይናገሩ ነገር ግን ለሆነው ወይም ላደረጉት ነገር ራሳቸውን ለመከላከል መከራከሪያ ሐሳቦችን እንዲያቀርቡ ይጋብዛቸዋል። ለምሳሌ አንድ ምክር ፈላጊ *በተገቢው ዕድሜ* ማግባት ሲገባው *ዘግይቶ* ስለዚህ ጉዳይ ለማማከር ወደ አማካሪ ቢመጣና

አማካሪው ደግሞ «እስካሁን ድረስ ለምን እጮኛ መያዝ አቃተህ?» ብሎ ቢጠይቀው ምክር ፈላጊው የልቡን ሐሳብ ለአማካሪው የሚነግረው ይመስላችኋልን? ይህ ዓይነቱ ጥያቄ ምክር ፈላጊውን በክርክር መንፈስ ውስጥ የሚያበገባ ነው:: «እስቲ ስለጓደኝነት ታሪክህ አጫውተኝ» ብሎ መጠየቁ ምክር ፈላጊው ራሱን እንዲገልጽ ይጋብዘዋል:: ስለዚህ «ለምን?» የሚል ጥያቄን ከማማከር ግንኙነት ውስጥ በማስወገድና በዚህ ጥያቄ ለማግኘት የሚፈለገውን መረጃ በሌላ መልክ በማቅረብ የተሻለ ውጤትን ለማግኘት ይቻላል::

አማካሪ ምክር ፈላጊዎችን ጥያቄ በሚጠይቅበት ጊዜ ባሕላዊ ዓውዱን ግንዛቤ ውስጥ ቢያስገባ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ ጥያቄዎችን ለይቶ ለማወቅ ይረዳዋል:: በአንዳንድ ባሕሎች ጥያቄዎች በቀጥታ ፊት ለፊት አይጠየቁም:: ለምሳሌ የትዳር ጉዳይን የሚያማክር አማካሪ ስለባልና ሚስት የወሲብ ግንኙነት ለማወቅ ቢፈልግ «የወሲብ ግንኙነታችሁ ምን ይመስላል?» ብሎ መጠየቅ እንደ ነውር ሲቆጠር ይችላል:: «የአልጋችሁ ሁኔታ እንዴት ነው?» ወይም «የባልና ሚስት ነገራችሁ ምን ይመስላል? እስቲ ግለጹልኝ» ብሎ ቢጠይቅ ግን የለዘበ አቀራረብ ስለሆነ ተገቢውን ምላሽ ያገኛል::

እንግዲህ አማካሪ ተገቢ ጥያቄዎችን ገንቢ በሆነ አቀራራብ መጠቀም ቢችል ብዙ መሠረታዊ መረጃዎችንና ማብራሪያዎችን ያገኛል:: የጥያቄዎቹ ይዘት፣ ምክር ፈላጊዎች ለመመለስ በሚችሉበት የግንኙነት ደረጃ ላይ መሆናቸውንም ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት:: በግንኙነቱ ጅማሬ አካባቢ፣ ግንኙነት ሲጠነክርና በግንኙነቱ መደምደሚያ አካባቢ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ለይቶ ማወቅ ሂደቱን ምቹ ያደርገዋል:: ምክር ፈላጊዎች ለተጠየቁት ጥያቄዎች በንግግር ወይም ንግግራዊ ባልሆነ ሁኔታ ምላሽ ሲሰጡ ስለሚችሉ በሁለቱም የሚተላለፉትን መልዕክቶች መከታተል አስፈላጊ ነው::

### ዘዴ3: ማዳመጥ

ማዳመጥ ምክር ፈላጊዎችን ለመረዳት የሚያስፈልግ ዘዴ ነው:: አማካሪ ለምክር ፈላጊዎች እጅግ ጠቃሚ ጥያቄዎችን ቢያቀርብና እነርሱም ራሳቸውን በሚገባ ቢገልጹ ተገቢው ማዳመጥ የማይኖር ከሆነ ውይይቱ የእነርሱን ችግር ሲፈታ የሚችል አይሆንም:: ማዳመጥ አማካሪውንና ምክር ፈላጊዎችን ውስጥ ለውስጥ የሚያገናኝ የማይታይ ሽቦ ነው:: አማካሪ ምክር ፈላጊዎች የሚናገሩትን ብቻ ሳይሆን ለመናገር ያልፈለጉትንም ነገሮች ያዳምጣል::

ምክር ፈላጊዎች በሚናገሩበት ጊዜ አማካሪ ሲያዳምጥ የተለያዩ ዓይነት ነጥቦችን መከታተል ይችላል:: አማካሪ በተገቢው ማዳመጥ ውስጥ ከሆነ የምክር ፈላጊዎችን:-

- √ ዓውዱን ያዳምጣል:: ምክር ፈላጊዎች የትና በምን ዓይነት እውነታ ውስጥ እንደሚገኙ ያዳምጣል:: አካባቢያዊ እውነታዎችንና ምክር



ፈላጊዎቹ ከእነዚህ እውነታዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ይከታተላል::
- √ ድርጊቶችን ያዳምጣል:: ምክር ፈላጊዎች ሕይወታቸውን በሚፈልጉት መልካም ሁኔታ እንዳይመሩ እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች ለይቶ ማውጣት ይችላል::
- √ ፍልቀ-ስሜትን ያዳምጣል:: ምክር ፈላጊዎች ሲናገሩ በቃላት ወይም በአካላቸው የሚገልጹአቸውን የተለያዩ ፍልቀ-ስሜቶችን (ቁጣ፣ ጭንቀት፣ ፍርሃት፣ ሐዘን፣ ደስታ፣ የመሳሰሉትን) ይከታተላል::
- √ አስተሳሰብን ያዳምጣል:: ምክር ፈላጊዎች ስለሚናገሩት ነገር የሚያስቡትን ሐሳብ፣ የአስተሳሰባቸው ቀመር፣ ስለራሳቸውና ስለዓለማቸው ያላቸውን እይታ እንዲሁም ስለወደፊት ያላቸው እይታ በተስፋ የተሞላ ወይም ጨለምተኝነት መሆኑን፣ የአስተሳሰብ ተከታታይነት መኖሩንና አለመኖሩን ያዳምጣል::
- √ የሚደጋገሙ ዋና ዋና ሐሳቦችን ያዳምጣል:: ምክር ፈላጊዎች በሚናገሩት ንግግር ውስጥ የሚደጋገሙ ሐሳቦች ይገኛሉ:: እነዚህ ሐሳቦች የአማካሪውን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በመሆናቸው ክትትልና ተጨማሪ ማብራሪያ ያስፈልጋቸዋል::
- √ ትርጉሞችን ያዳምጣል:: ምክር ፈላጊዎች ታሪኮቻቸውን ሲናገሩ ለእነዚያ ታሪኮች የሚሰጡት ትርጉም ይኖራቸዋል:: ታሪኩ ለእነርሱ ያለውን ትርጉም ያዳምጣል:: እነዚህን ትርጉሞች በመረዳት እንደ አስፈላጊነቱ የተለየ ወይም ተጨማሪ ትርጉሞችንም ማየት እንዲችሉ ያግዛቸዋል::

በመጨረሻም አማካሪው በእርሱና በምክር ፈላጊዎች መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ይከታተላል:: አማካሪው ለሚናገራቸውና ለሚያሳያቸው ድርጊቶች ምክር ፈላጊዎች የሚሰጡትን አሳቦች፣ የሚያሳዩትን ስሜቶችና የሚያደርጉትን ድርጊቶች በመከታተል «አሁን» እየተከሰተ ያለውን እውነታ ያስሳል:: በዚህ ሁኔታ ያገኛቸውን መረጃዎች ምክር ፈላጊዎችን ለመርዳት ይጠቀምበታል::

### ዘዴ4: መልሶ ማንጸባረቅ

አማካሪ የምክር ፈላጊዎችን ሐሳብ ከእነርሱ ሰምቶ ዝም ብሎ አይቀበልም:: የተረዳውን ሐሳብና የተገነዘበውን ስሜታቸውን መልሶ በራሱ አገላለጽ ለምክር ፈላጊዎች ይገልጻል:: በማማከር ውይይት ወቅት የተነሡትን ሐሳቦችንና የተገለጹትን ስሜቶች ሁሉ ሳይሆን ዋና ዋና የሆኑትን ሐሳቦች በተገቢው ጊዜ መልሶ ይገልጻቸዋል:: «በዚያ ሁኔታ ውስጥ ማለፍ ያሳዘነህ ይመስላል»፤ «በአንቺ ላይ በተፈጸመው በደል ምክንያት ከፍተኛ ሐዘን ተሰምቶሻል»፤ «አንተ ስትናገር እንደገባኝ ከሆነ...» እያሉ የምክር ፈላጊዎችን ሐሳብና ስሜት መልሶ መግለጽ ነው:: ምክር ፈላጊዎች የሚሰማቸውን ስሜቶች ለመረዳት የፍልቀ-ስሜት ዝርዝሮችንና እያንዳንዳቸው የሚገለጹባቸውን ዋና ዋና መንገዶችንና ምልክቶችን ማወቅ ጠቃሚ ነው::

ለምክር ፈላጊዎች አንድን ሐሳብ መልሶ ከመግለጽ ቀደም ብሎ የትኞቹ ሐሳቦች ለእነርሱ ጠቃሚ እንደሆኑ መለየት ያሻል፡፡ ከዚያም የተባሉትን ሐሳቦች እንዳሉ ወይም ሐሳቦቹ የሚያመለክቱትን መልዕክት መግለጽ ይቻላል፡፡ በመልሶ ማንፀባረቅ ሂደት አማካሪው በራሱ አገላለጽ ሲናገራቸው ትክክል ያልሆኑ ነጥቦች ሲኖሩ ምክር ፈላጊዎቹ ለማስተካከል ዕድል ያገኛሉ፡፡ አንድ አማካሪ እንደ ምክር ፈላጊዎቹ ሁኔታ «የአንተ ሐሳብ እንደገባኝ ከሆነ የአባት ሞት የሚያሳዝነው የእርሱ አባትነት በፍቅር የተገለጸ ሲሆን ነው»፣ «አሁን የምትዪው ለአንቺ ወንድ ሁሉ እንደ ቀድሞ ጓደኛሽ ከሃዲ ነው»፣ «በአንተ መረዳት ገንዘብ ማግኘት እንጂ መማር ዋጋ የለውም ማለት ነው» እያለ መረዳቱን ለእነርሱ ማንፀባረቅ ይችላል፡፡

ምክር ፈላጊዎች ከተናገሩ በኋላ ዋና ሐሳባቸውን መልሶ ማንጸባረቅ ለማማከር ሂደት ጠቃሚነት አለው፡፡ አማካሪው የእነርሱን ሐሳብና ስሜት በትክክል መረዳቱን ያረጋግጣል፣ እነርሱ ለገጠሟቸው ሁኔታዎች የሚሰጡትን ትርጉሞች ለማወቅ ይረዳል እንዲሁም አማካሪው ከእነርሱ ጋር በመሆን የሚናገሩትን ሐሳብና የሚገልጹትን ስሜት እየተከታተለና እየተረዳ መሆኑን በመገንዘብ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያደፋፍራቸዋል፡፡ ምክር ፈላጊዎች መናገር ያልፈለጉትንም ሐሳብ እንዲናገሩ መንገድ ይከፍታል፡፡ ለምሳሌ አንድ ምክር ፈላጊ ከሥራ በመባረሩ ደስ ብሎት እያለ እንደ አዘነ ሊናገር ይችላል፡፡ አማካሪው ግን «አሁን ለመሰከትህ ከሥራ በመባረር ደስተኛ ትመስላለህ» ብሎ መልሶ ሲያንጸባርቅ «አዎን ነኝ፡፡ ምክንያቱም ...» ብሎ ለመናገር ዕድል ያገኛል፡፡

አማካሪ መልሶ ማንጸባረቅን በተለያዩ መልኮች ማድረግ ይችላል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ አማካሪው ሐሳቦችን ገምግሞ ያገኘውን ጭብጥ ሐሳብ ወይም የታሪኮችን ትርጉም፣ ምክር ፈላጊዎችን ሊደግፍ በሚችል መልክ ሊያንፀባርቅ ይችላል፡፡ ምክር ፈላጊዎች ተጨማሪ ማብራሪያ ሊሰጡ በሚያስችላቸው መንገድ ወይም አማካሪው የምክር ፈላጊዎችን ሐሳብ እንደተረዳ በሚያሳይ መልኩ ማንፀባረቅ ይችላል፡፡

### *ዘዴ5: ማደፋፈር*

ማደፋፈር ምክር ፈላጊዎች በማማከር ሂደቱ ወደፊት መሄድ እንዲችሉ ኃይል የሚሰጣቸው ምላሽ ነው፡፡ በማማከር ግንኙነት ውስጥ ምክር ፈላጊዎች ሐሳባቸውን ወይም ስሜታቸውን ለመግለጽ የሚፈሩበትና ቆም የሚሉበት ጊዜ ይፈጠራል፡፡ በጣም አስፈላጊ ወይም የችግራቸው ዋና ሐሳብ ወይም መንስኤ የሆኑትን ነገሮች ቶሎ ለመግለጽ ፈቃደኞች የማይሆኑበት ጊዜ ያጋጥማል፡፡ እዚህ ላይ አማካሪ፣ ምክር ፈላጊዎች ስለችግራቸው ቁልፍ የሆኑ መረጃዎችን ቶሎ ለመስጠት የማይፈልጉበት ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ምክር ፈላጊዎች፣ በማማከር ግንኙነቱ የሚረዱ እነርሱ ሆነው እያሉ የችግራቸውን ዳር ዳር ወይም ላይ ላዩን እንጂ ዋናውን የማይናገሩበት ምክንያት በርካታ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-



- √ ምክር ፈላጊዎቹ ከምን ተነስተው ምን መናገር እንደሚገባቸው ካለማወቅ የተነሣ እዚህም እዚያም ይነካካሉ፡፡
- √ ምክር ፈላጊዎቹ የሆነ ችግር እንዳላቸው እንጂ ችግሩ ምን እንደሆነ በግልጽ ሳያውቁ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ «የእኔ ችግር ይህ ነው»፣ «መንስኤውም ይህ ነው» ብለው መናገር ያዳግታቸዋል፡፡
- √ አማካሪው ችግራቸውን ተረድቶ መፍትሔ በመስጠቱ ሂደት ብቃት እንዳለውና እንደሌለው ለማወቅ ጊዜ ለመውሰድ ይሆናል፡፡
- √ ችግራቸው ወይም ከችግራቸው ጋር በተያያዘ መልኩ መናገር የሚፈልጉት ነገር አሳፋሪ እንደሆነ በማሰብ አማካሪው በዚህ ጉዳይ ላይ የሚላቸውን ነገሮች ለማጤን ቆም ይላሉ፡፡ የአማካሪውን አመለካከት ቀድሞ ማወቅ ይፈልጋሉ፡፡
- √ አማካሪው ምስጢራቸውን በትክክል እንደሚጠብቅ ካለማረጋገጣቸው የተነሣ ፈርተው ዋናውን ሐሳብ ከመነካካት ዝምታን ይመርጣሉ፡፡

ምክር ፈላጊዎች በማማከር ሂደት ወደፊት መሄድ ሲያቅታቸው አማካሪው ሐሳባቸውንና ስሜታቸውን እንዲገልጹ ሊያደፋፍራቸው ይገባል፡፡ ማደፋፈር የሚቻለው «አይዞሽ ተናገሪ» በማለት ብቻ ሳይሆን ምስጢራቸውን መናገር እንዲችሉ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ ምክር ፈላጊዎች ዋና ችግራቸውን ለአማካሪው በመናገር ላይ እያሉ ዝም ማለት ይጀምራሉ፡፡ የምክር ፈላጊዎች ዝምታ ብዙ ትርጉምና ምክንያት አለው፡፡ ከእነዚህም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-

- ✓ ምክር ፈላጊዎች ስለተናገሩት ነገር መልሰው እያሰላሰሉ ይሆናል፡፡ በተናገሩት ነገር በውስጣቸው የሚሰማቸውን ስሜት ወይም ሐሳብ በማጤን የሚቀጥለውን እርምጃ እያሰቡ ይሆናል፡፡
- ✓ ሐሳባቸውን እየገለጹ እያለ ሌላ ሐሳብ ሲመጣላቸው ከመናገራቸው በፊት ለማሰላሰል ዝም ይላሉ፡፡
- ✓ ምክር ፈላጊዎች ለአማካሪው በነገሩት ጉዳይ ሐፍረት ሲሰማቸውም ዝም ይላሉ፡፡ በአእምሮአቸው «እንዲህ ያለውን ጉድ ባልነግረው ኖሮ...» እያሉ ያስባሉ፡፡
- ✓ ምክር ፈላጊዎች በአንድ ጊዜ ለመናገር የፈለጉትን ሐሳብ በመጨረሳቸው ወደሚቀጥለው እርምጃ ከመሄዳቸው በፊት ሐሳባቸውን በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ዝም ይላሉ፡፡ ዝምታን ወደ ሌላ ሐሳብ የመሸጋገሪያ ድልድይ አድርገው ለመጠቀም ይሆናል፡፡
- ✓ ምክር ፈላጊዎች የአማካሪውን ቅስቀሳ ፈልገው ይሆናል፡፡
- ✓ የተጀመረው የማማከር ክፍለ ጊዜ ለዛሬ ቢበቃ ጥሩ ነው፣ ጊዜውም እያለቀ ስለሆነ ይበቃኛል ማለታቸው ሊሆን ይችላል፡፡

ምክር ፈላጊዎች በማማከር ሂደት ውስጥ በድንገት ዝም ሲሉ አማካሪ ቶሎ መናገር እንዲጀምሩ መቀስቀስ የለበትም፡፡ ዝምታ አስፈላጊ የሚሆንበት ወቅት ይኖራል፡፡ «ዝምታ ወርቅ ነው» የሚለው አባባል በማማከርም

ግንኙነት ይሠራል:: በዝምታ ወቅት ምክር ፈላጊዎች በአእምሮአቸው ውስጥ ብዙ ነገሮችን ያሰላስላሉ:: ምናልባት የዝምታው ወቅት ከመጠን በላይ ረጅም በሚሆንበት ጊዜ አማካሪው «በዝምታ ወቅት ሰው ብዙ ነገሮችን ያሰላስላል፣ ምን እያሰብክ ነው?» ብሎ በመጠየቅ እያሰቡት ያለውን ነገር እንዲገልጹ ማበረታታት ይቻላል:: «አንዳንድ ጊዜ ውስጣዊ ስሜትን ለመጀመሪያ ጊዜ መግለጽ ይከብዳል፣ ሆኖም መገለጹ ለመፍትሔ መንገድ ይከፍታል» ብሎ ማደፋፈርም ይቻላል::

ማደፋፈር፣ ምክር ፈላጊዎች ሊያደርጉት የሚገባውን መልካም እርምጃ ትክክለኛነት ከማረጋገጥም አንጻር ይታያል:: አማካሪ እንደ አስፈላጊነቱ የእነርሱን ሐሳብና ድርጊት ያደፋፍራል:: በዓውዳቸው እያደረጉት ያለው ነገር ትክክል መሆኑን በመግለጽ ወደፊትም በዚሁ መልክ መቀጠል እንዳለባቸው የማረጋገጫ ሐሳብ ይሰጣል:: ምክር ፈላጊዎቹን በቀጥታ «እንዲህ አድርጉ» ባይልም በሐሳቡ ወይም በድርጊቱ ትክክለኛነት በማመን ቀጣይነት ቢኖረው ለእነርሱ እንደሚጠቅማቸው ያሳያል:: አማካሪ፣ ምክር ፈላጊዎች አንድን ነገር እንዲያደርጉ ሊያደፋፍራቸው ጥንቃቄ ማድረግ አለበት:: ምክንያቱም አማካሪ በግንኙነቱ ውስጥ እንደ «ባለሥልጣን» ስለሚታይ እርሱ የሚናገራቸው ነገሮች በምክር ፈላጊዎች ዘንድ ተቀባይነት ስለሚኖራቸው ነው::

## *ዘዴ6: መተርጎም*

አማካሪ ከምክር ፈላጊዎች የሚያገኘውን መረጃ ይተረጉማል:: መረጃዎቹ፣ ምክር ፈላጊዎች በቃላት ከሚናገሩት ወይም ንግግራዊ ባልሆኑ የሰውነታቸው እንቅስቃሴዎች የሚገልጹት ይሆናል:: መተርጎም የሚሰው ሐሳብ ከፊት ለፊት ከሚናገረውና ከሚደረገው በስተጀርባ ያለውን መሠረታዊ አስተሳሰብና ዓላማ ለማግኘት የሚደረግ እርምጃ ነው:: አማካሪ የምክር ፈላጊዎች አስተሳሰብና ድርጊቶች ምን እንደሆኑ ያሳያቸዋል:: በዚህም ምክር ፈላጊዎች ራሳቸውን፣ ያሉበትን ዓውድ፣ ሐሳባቸውንና ድርጊታቸውን ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ እንዲገነዘቡ ያግዛቸዋል::

አማካሪ፣ የምክር ፈላጊዎችን ንግግርና ድርጊት በሚተረጉምበት ጊዜ ሊሳሳት ይችላል:: ስለዚህ «እንዲህ ይመስለኛል» የሚለውን አባባል መጠቀም አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም ትርጉሙ ፍጹም ባለመሆኑ በምክር ፈላጊዎቹ ሊታረም እንደሚችል ያመለክታል:: አንዳንድ ጊዜ ምክር ፈላጊዎች ትክክለኛ የሆነውንም ትርጉም ለመቀበል ዝግጁዎች ላይሆኑ ይችላሉ:: በዚህ ዓይነት መልክ አስበውት ስለማያውቁ ቶሎ ትርጉሙን ላይቀበሉ ስለሚችሉ ቀስ በቀስ ወደዚያ ዓይነት ግንዛቤ እንዲመጡ መምራት ያስፈልጋል:: ምክር ፈላጊዎች ትርጉሙን እንደ ራሳቸው አድርገው ካልተቀበሉት ምንም ጥቅም ስለማይኖረው በእነርሱ እርምጃ መሄድ ይጠቅማል:: ከራሳቸው ውጭ የመጣ አድርገውም እንዳይወስዱት «ይህ ነገር እንዲህ ይሆን?»፣ «ይህን ነገር በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተመልክተሽ ነበር ወይ?» ብሎ መጠየቅ ምክር ፈላጊዎች በራሳቸው ትርጉሙን እንዲያገኙት ይመራቸዋል::



ሁኔታው በሚያመችበት ዓውድ ምክር ፈላጊዎች ካመጡት ጉዳይ አንጻር የሥነልቦና ፈተና የሚፈተኑበት ጊዜ ይኖራል:: ለምሳሌ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለመተጫጨት አስበው፣ በስብእናቸው እንደሚጣጣሙ ለማወቅ ቢፈልጉ አማካሪው የስብእና ፈተና ሊሰጣቸው ወይም እንዲሰጣቸው ሊያደርግ ይችላል:: ከዚያም ፈተናዎቹን ይተረጉማቸዋል፣ ለእነርሱ ሊገባቸው በሚችል ቋንቋ ይገልጽላቸዋል::

## *ዘዴ7: መጋፈጥ*

ምክር ፈላጊዎች በሕይወታቸው ውስጥ መስተካከል የሚገባው አስተሳሰብና ድርጊት ይኖራቸዋል:: አንዳንዶቹ ነገሮች እነርሱ የሚያውቁት ሊሆን አንዳንዶቹ ግን እነርሱም በትክክል ያልተገነዘቡት ነጥቦች ናቸው:: አሁን እየተከተሉት ያለው የሕይወት ዘይቤ ወይም አስተሳሰብና ድርጊት በሕይወታቸው ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በትክክል መረዳትና አስፈላጊውን ገንቢ እርምጃ መውሰድ እንዲችሉ የሚያግዛቸው ዘዴ ነው::

የምክር ፈላጊዎች ሐሳብና ድርጊት ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን መገምገም የሚቻለው በእነርሱ ወይም በሌሎች ላይ አሁን እና ወደፊት የሚያስከትለውን ውጤት ከመመልከት አንጻር ነው:: እነርሱ መኖር የሚፈልጉትን ሕይወት እንዳይኖሩ ወይም የሕይወት ሕልማቸውን ከግብ እንዳያደርሱ እንቅፋት የሆኑባቸውን ትክክለኛ ያልሆኑ አስተሳሰቦችን መሰወጥ እንዲችሉ መልሶ ለእነርሱ ማሳየት ነው:: ይህ ምክር ፈላጊዎች ለስራሳቸውና ለሰሁኔታዎች ያላቸውን እይታ ለማስተካከል የሚረዳ ስልት ነው::

እማካሪ ምክር ፈላጊዎች፣ በሚናገሩትና በድርጊታቸው መካከል የሚቃረን ነገር መኖሩን ያሳያቸዋል:: የሚናገሩትን የማያደርጉ ሲሆን በሁለቱ መካከል ያለውን ክፍተት ከፊታቸው ያስቀምጥላቸዋል:: ምክር ፈላጊዎች በሕይወታቸው ውስጥ ያሉትን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በግልጽ ማወቅና መቀበል እንዲችሉ ያግዛቸዋል:: ከዚህ አንጻር አማካሪ፣ ምክር ፈላጊዎች በጎውን ጎናቸውን ብቻ እንዲያዩ እያደረግም፤ ደካማ ጎናቸውንም በማየት በሂደት ማስተካከል እንዲችሉ ይመራቸዋል:: በዚህ ሂደት አማካሪው ለምክር ፈላጊዎች እንደ መስታወት በመሆን ትክክለኛ ማንነታቸውን ያሳያቸዋል:: የእማካሪው ሚና መስታወት ሆኖ ማሳየት እንጂ የምክር ፈላጊዎችን ደካማ ነገር ማስወገድ አይችልም:: የራሳቸውን ስህተት ማረም፣ አፍራሽ አስተሳሰቦችን መለወጥ፣ በንግግርና በተግባራቸው መካከል ያለውን ክፍተት ማጥበብ/መሙላት፣ አሁንና ወደፊት የሚጠቅማቸውን እርምጃ መውሰድ የምክር ፈላጊዎቹ ኃላፊነትና ድርሻ ነው::

እማካሪ መጋፈጥን መጠቀም የሚጀምረው ከምክር ፈላጊዎች ጋር ተገቢውን ግንኙነት ከመሠረተ በኋላ ነው:: ሰዎች የራሳቸውን ስህተትና ደካማ ጎን ለመቀበል ዝግጁዎች ስለማይሆኑ በግንኙነቱ ውስጥ ለዚህ ዝግጁ

መሆናቸውን ማጤን ያስፈልጋል። ተገቢው ግንኙነት ካልተመሠረተና ዝግጅት ካልተደረገ ፊት ለፊት የሚታየውን ስህተታቸውን ከመቀበል ይልቅ ራሳቸውን ለመከላከል ክርክር ይጀምራሉ። አንድ ጊዜ ከመጋቢ ተልኮ ከመጣ ምክር ፈላጊ ጋር ተገናኘንና ውይይት ጀመርን። እንደ ዋና ችግር ይዞ የመጣው ጉዳይ በሥራ ቦታ ከአሠሪዎቹ ጋር መግባባት አለመቻሉ ነበር። ለዚህም እንደ ዋና ምክንያት ያቀረበው የአሠሪዎቹ ክፉ ባሕርይ መሆኑን ነው። የችግሩ መንስኤ ግን የእርሱ ባሕርይ እንደሆነ በመረዳት ያንን ለእርሱ ስነግረው በቁጣ ስሜት ተሞልቶ ከእኔ ጋር መከራከር ጀመረ። ያንን የአንድ ጊዜ ግንኙነታችንን እንደ ምንም ብለን ደምድመን ስሌላ ጊዜ ቀጠሮ ይዘን ተለያየን። ምክር ፈላጊው በቀጠሮ መሠረት ሳይመጣ ቀረ። ከዚያም በኋላ እስካሁን ድረስ አልተገናኘንም። ስዚህ ምክንያቱ መጋፈጥን ግንኙነታችን በደንብ ላይመሠረት መጠቀሜ ነበር። ስለሆነም የማማከር ዘዴዎችን በየትኛው የግንኙነት ሂደት መጠቀም ገንቢ ውጤት እንደሚያመጣ በቅድሚያ መረዳት አስፈላጊ ነው።

በክርስቲያናዊ የማማከር ግንኙነት ውስጥ ያስ አማካሪ፣ አማኝ የሆኑ ምክር ፈላጊዎች በሕይወታቸው የፈጸሙት ኃጢአት/በደል በሚኖርበት ጊዜ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ንስሐ ገብተው ሕይወታቸውን ከእግዚአብሔር፣ ከራሳቸውና ከሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት እንዲያስተካክሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። በዚህ ሂደት ንስሐ ቢገቡ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር እንደሚላቸውም እንዲያምኑ መርዳት ነው (1ዮሐ1፡7)።

አማካሪ፣ ምክር ፈላጊዎችን በሚጋፈጥበት ጊዜ «እውነትን በፍቅር» መግለጽ የሚለውን መርህ ቢከተል ተገቢውን ውጤት ያመጣል (ኤፌ4:15)።፡ አማካሪ ለምክር ፈላጊዎች እውነትን በሚገልጽበት ጊዜ አቀራረቡ ለስላሳና በፍቅር መሆን አለበት። ለዚህ መልካም ምሳሌ የሚሆን አንድ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ በ(2ሳሙ12:1-7) ላይ እናገኛለን።

በወቅቱ የአገር መሪ የነበረው ንጉሥ ዳዊት ከአንድ ታማኝ ወታደሩ ሚስት ጋር ዝሙት ፈጸመ። ይህ ድርጊቱም እንዳይታወቅበት ይህ ወታደር ከዘመተበት ጦር ሜዳ ተመልሶ ከሚስቱ ጋር እንዲተኛ ለማድረግ ጠራው፣ አስከረውና ወደ ቤቱ እንዲሄድ ነገረው። ወታደሩ ወዳጆቹ በጦር ሜዳ በግዳጅ ላይ እያሉ እርሱ ቤቱ እንደማያድር ነገረውና እምቢ አለ። ከዚያም ዳዊት ለጦር አዛዡ ይህን ወታደር ሞቅ ባለው ውጊያ ፊት ለፊት እንዲያቆመው የትዕዛዝ ደብዳቤ ጻፈ። በዚህ ሁኔታ ኦሪዮን የሚባል ወታደር ተገደለ። ዳዊትም የሟቹን ሚስት ለራሱ ወሰዳት።

ከዚህ በኋላ በአገሩ አንድ የታወቀ ናታን የሚባል ነቢይ ዳዊትን ለመጋፈጥ ሄደ። ናታን እጅግ ጥበብ በተሞላበት መንገድ ዳዊትን አናገረው። ለዳዊት አንድ እጅግ የሚያሳዝን ታሪክ ነገረው (ሙሉ ታሪኩን ከመጽሐፉ ማንበብ ይቻላል)። ታሪኩ አንድ ኢፍትሐዊ ድርጊት የፈጸመ ሰውን ያሳያል። ንጉሥ ዳዊት ታሪኩን ሲሰማው በከፍተኛ ቁጣ ተሞልቶ «ሕያው እግዚአብሔርን! ይህን ያደረገው ሰው ሞት ይገባዋል፤ እንዲህ ያሰውን ነገር



በማድረጉና ባለ ማዘኑም ... አራት ዕጥፍ መክፈል አለበት» በማለት ተናገረ። ይህ ምቹ ሁኔታ ከተመቻቸለት በኋላ ናታን «ያ ሰው አንተ ነህ» አለው። ዳዊት ይህን ሲሰማው «እግዚአብሔርን በጣም በድያለሁ» በማለት ንስሐ ለመግባትና ያጠፋውን ጥፋት ለማስተካከል ውሳኔ አደረገ።

እንደ ናታን አቀራረብ፣ ከምክር ፈላጊዎች ጉዳይ ጋር የተያያዙ ታሪኮችን መጠቀም ጠቃሚ ነው። ተያያዥነት ያላቸው ታሪኮች ምክር ፈላጊዎች ራሳቸውንና ድርጊታቸውን ግልጽ በሆነ ሁኔታ መመልከትና መገንዘብ እንዲችሉ ዕድል ይሰጧቸዋል። መጋፈጥ ምክር ፈላጊዎች ራሳቸው ስህተታቸውን ማየት እንዲችሉ መርዳት ነው። በዚህ ዓይነት መንገድ በራሳቸው ስህተታቸውን ሲገነዘቡ ተገቢውን የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ፈቃደኞች ይሆናሉ። የሚወስዱት እርምጃ ዋጋ የሚያስከፍላቸው እንደሆነ ቢያውቁም በዚህ መንገድ መሄድ ዘለቄታ ያለው ጥቅም እንደሚያመጣ በመረዳታቸው ይቀበላሉ።

### *ዘዴ8: ምሳሌ ከሚሆኑ ሰዎች መማር*

ምክር ፈላጊዎች ችግሮቻቸውን ከመፍታት እንዲሁም የሕይወት ሕልማቸውን ከግብ ከማድረስ አንጻር ከሌሎች ሰዎች የሚማሩት ቁም ነገሮች ይኖራሉ። አማካሪ እንደ ምክር ፈላጊዎቹ ጉዳይ መልካም ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉትን ሰዎች ወደ እነርሱ በማምጣት ከእነርሱ መማር እንዲችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። እነዚህ ለምሳሌነት የሚመረጡ ሰዎች በምክር ፈላጊዎቹ ዓውድ ውስጥ ጠቃሚ ትምህርቶችን ሊያስተምሩ የሚችሉ መሆናቸው በቅድሚያ መጠናት አለበት። ከተቻለ በምክር ፈላጊዎቹ ዓውድ ውስጥ የሚገኙ ቢሆኑ ይመረጣል።

አማካሪ፣ እነዚህን ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉትን ሰዎች በቀጥታ ወደ ማማከር አገልግሎት ሥፍራ ለማምጣት አይችል ይሆናል። ነገር ግን ምክር ፈላጊዎቹ ስለሰዎቹ የሚያሳዩ ፊልሞችን እንዲያዩ፣ መጽሐፍቶችን እንዲያነቡ ማድረግ ወይም አማካሪው ታሪካቸውን ሊተርክላቸው ይችላል። ምክር ፈላጊዎቹ ከእነዚህ ሰዎች ከችግራቸው አንጻር ምን ሊማሩ እንደሚችሉ ጊዜ ወስዶ ማጤን አስፈላጊ ነው። የእነዚህን ሰዎች ታሪክ አንዳስ በመኮረጅ በእነርሱ መንገድ መኖር የማይታሰብ ቢሆንም ከሕይወታቸው መርሆዎችን መማር ይቻላል። በተለይ ከእነርሱ ችግር/ጉዳይ/ ጋር ተያያዥነት ያለውን ነገር ሰዎቹ እንዴት መፍታት ወይም መያዝ እንደቻሉ በመረዳት በሕይወታቸው ተግባራዊ ማድረግ ይችላሉ። አማካሪው ይህን የመማር ሂደትን ያመቻቻል።

አንድ ጊዜ አንድ ወጣት ሳማክር በሕይወቱ ትልቅ ሰው ለመሆን ራእይ እንዳለው ነገረኝ። ነገር ግን ይህን የሕይወት ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉትን ቅድመ ሁኔታዎች በመሥራት ላይ አልነበረም። የሚያስበውና ያለበት እውነታ ተቃራኒ ናቸው። ከዚያም «አማኝ እንደሆነ ነግሮኝ ስለነበረ፣ ለመሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ የምትወደው ወጣት ሰው አለ ወይ?» ብዬ ስጠይቀው «አዎን! እኔ ዮሴፍን እወደዋለሁ» አለኝ። ይህ

በጉዳዩ ላይ ለመሥራት ምቹ ሁኔታዎችን ፈጠረልን፡፡ ወጣቱ ከዮሴፍ ሕይወት መማር የሚችላቸውን ነገሮች አብረን ለማውጣት ሞከርን፡፡ ከዚያም ይህ ወጣት የሕይወት ራእዩን በሂደት ከግብ ለማድረስ አሁን ባለበት ሁኔታ ተገቢውን ሥራ በታማኝነት መሥራት እንዳለበት ተረዳ፡፡ ራእይ አለኝ ብሎ ዝም ብሎ መቀመጥና ለራእይ የማይመች ባሕርይ መለማመድ ተገቢ እንዳልሆነ በመረዳት አቀጣጫውን በመለወጥ መሥራት ጀመረ፡፡

በተለይ በክርስቲያናዊ ማማከር አገልግሎት ውስጥ የሚገኙ አማካሪዎች፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮችን በመጠቀም ምክር ፈላጊዎች ከእነዚያ ሰዎች ታሪክ መማር የሚችሉትን ቁም ነገሮች ማውጣት ይችላሉ፡፡ በሌሎችም ዓውዶች ምክር ፈላጊዎች የሚያውቁአቸውን ሰዎች ወይም አዳዲስ ሰዎችን በተለያዩ መንገዶች በማቅረብ እንዲማሩበት ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ስለዚህ አማካሪ እንደ ዓውዱ የሚመቸውን መንገድ መጠቀም ይችላል፡፡

### ዘዴ9: የቤት ሥራ መስጠት

ምክር ፈላጊዎች በማማከር ክፍለ ጊዜ ያገኙአቸውን ጠቃሚ ሐሳቦች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ወይም አዳዲስ ግንዛቤዎች ማግኘት እንዲችሉ ሊያደርጉ የሚያስፈልጋቸውን የቤት ሥራ መስጠት ነው፡፡ አንድ የማማከር ክፍለ ጊዜ አልቆ በቀጠሮው መሠረት ወደፊት እስኪገናኙ ድረስ በመሐል ምክር ፈላጊዎች የሚሠሩት ሥራ፣ ለማማከር አገልግሎት ፍሬያማነት አስተዋጽኦ አለው፡፡ የሚሰጠው የቤት ሥራ ከጉዳዮቻቸው ጋር የሚገናኝ ይሆናል፡፡ የቤት ሥራ መስጠት ምክር ፈላጊዎች ችግሮቻቸውን ለመፍታት በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚፈጽሙት ሥራ መሆኑን ያሳያል፡፡

አንዳንድ ችግሮች በማማከር ክፍለ ጊዜ ውስጥ የሚፈቱ ነገሮች አይደሉም፡፡ ምክር ፈላጊዎች ከአማካሪው ዘንድ ያገኙትን ግንዛቤዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚፈትሹት በዚህ ሁኔታ ነው፡፡ በጥንቃቄ ታስበው የተሰጡ የቤት ሥራዎች የምክር ፈላጊዎችን ችግር ከመፍታት አንጻር የሚኖራቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡

አንድ ወጣት ምክር ፈላጊ እጮኛ ለመያዝ በመፍራት ዕድሜው ለትዳር ቢደርስም እርምጃ መውሰድ አለመቻሉን በመግለጽ ምክር ለመጠየቅ ቢመጣ እንዴት መርዳት ይቻላል? ይህን ምክር ፈላጊ ለመርዳት ከሚወሰዱ እርምጃዎች አንዱ ከዚህ በፊት ቀርቦአቸው የማያውቃቸውን፣ አቻዎቹ ከሆኑት ተመሳሳይ ጾታ ከሆኑት ጋር ግንኙነት ለመመሥረት ጥረት እንዲያደርግ የቤት ሥራ መስጠት ነው፡፡ ከዚህ እርምጃ የሚመጣውን ውጤት መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን ግንዛቤ በማስገኘት በቀጣይ ደግሞ ተቃራኒ ጾታን መቅረብ እንዲችል መርዳት ነው፡፡ እነዚህን እርምጃዎችን በሚወስድበት ጊዜ ያጋጠሙትን እውነታዎችን ይዞ ይመጣና ከአማካሪው ጋር ይነጋገራል፡፡ በዚህ ዓይነት ሂደት ከተቃራኒ ጾታ ጋር ግንኙነት መመሥረት የሚያስችለውን ብቃት ማሳደግ ይችላል፡፡



አንዳንድ ጊዜ ምክር ፈላጊዎች የተሰጣቸውን የቤት ሥራ በተገቢው ሁኔታ ሳይሠሩ ሊመጡ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ያልሠሩበትን ምክንያት ማስስ አስፈላጊ ነው፡፡ እነርሱ የሚያቀርቡአቸው ምክንያቶች አሳማኝ መሆናቸውንና እንዲሁ ለማስተባበል የሚቀርቡ መሆናቸውን በማረጋገጥ ተገቢውን ትምህርት እንዲያገኙበት መጠቀም ይቻላል፡፡ ምክር ፈላጊዎች በራሳቸው ስንፍና የማይሠሩት ከሆነ በሕይወታቸውም ካሰሙበት ግብ ድረስ እንዳይደርሱ ካደረጉአቸው መሰናክሎች አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ የቤት ሥራ አለመሥራታቸውም የማማከር አጀንዳ የሚሆንበት ሁኔታ ይሆናል፡፡

### ዘዴ10: ንግግራዊ ያልሆኑ ባሕርያትን መከታተል

ምክር ፈላጊዎች ሐሳባቸውን፣ ስሜታቸውንና ድርጊታቸውን በንግግር እንዲሁም በሰውነታቸው እንቅስቃሴ ይገልጻሉ፡፡ የምክር ፈላጊዎች የሰውነት አቋም፣ ትንፋሽ፣ አለባበስ፣ አነጋገር፣ የድምጽ ሁኔታ፣ የቤት/የቢሮ አያያዝ እና የመሳሰሉት የተለያዩ መረጃዎችን ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ የምክር ፈላጊዎች ንግግራዊ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች በንግግር የተገለጹትን የሚደግፉ ወይም የሚቃረኑ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ የሚያሳዩትን መልዕክት ለመረዳት የተከሰቱበትን ዓውድና ባሕላዊ ትርጓሜዎቻቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

እነዚህ ንግግራዊ ያልሆኑ ባሕርያት ብዙ ዓይነት ናቸው፡፡ ከእነዚህም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-

*የአረማመድ ሁኔታ፡-* ምክር ፈላጊዎች በቀጠሮአቸው መሠረት ወደ ማማከር ሥፍራ ሲመጡ በአረማመዳቸው ድምጽ እያሰሙ ወይም እያደቡ ምንም ኮሽታ ሳያሰሙ ሊሄዱ ይችላሉ፡፡ የመጀመሪያው ድፍረትን ወይም ፍርሃትን ለማስወገድ የሚደረግ ተግባር ይሆናል፡፡ ሁለተኛው ግን ተጠራጣሪነትን፣ ፍርሃትን ወይም ከአማካሪው ጋር ለመገናኘት አለመፈለግን ያመለክታል፡፡

*የእጅ አጨባበጥ ሁኔታ፡-* ምክር ፈላጊዎች አማካሪውን ሲጨብጡ ያዝ አድርጎ ቶሎ ለቀቅ የሚያደርጉ ከሆነ «እኔ ከአንተ ጋር መገናኘት አልፈልግም ነበር» ማለቱ ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነት ባሕርይ የሚያሳዩ ምክር ፈላጊዎች ዝምተኞችና አማካሪውን ለመቅረብ የማይፈልጉ ዓይነት ናቸው፡፡ በተቃራኒው አማካሪውን ጠበቅ አድርገው የሚጨብጡ ድፍረት ያላቸው ወይም የበታችነት ስሜታቸውን ለመሸፈን ጥረት የሚያደርጉ ምክር ፈላጊዎች ናቸው፡፡ እንዲሁ ሲታይ እጅ መጨበጥ በሁለት ሰዎች መካከል ያለውን ወዳጅነትና እርስ በርስ ለመፈቃቀድ ዝግጁነት እንዳላቸው ያመለክታል፡፡

*አለባበሱ፡-* የአለባበስ ሁኔታ የሰዎችን ስብእና ባይፈጥርም ስለእነርሱ አስተሳሰብ፣ አመለካከትና ባሕርይ መረጃዎችን ይሰጣል፡፡ ምክር ፈላጊዎች ዘወትር ከሚለብሱት የአለባበስ ሁኔታ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የተለየ ማድረጋቸው እነርሱ በቀጥታ መናገር ያልፈለጉትን መልዕክት

ያስተሳልፋል:: እንደ ባሕሉ ሁኔታ መልበስ ተገቢ ሆኖ እያለ ከዚያ ወጣ ባለ መልኩ ለአለባበሳቸው ልዩ ትኩረት የሚሰጡ ምክር ፈላጊዎች በሕይወታቸው ሁሉ በጣም ጥንቁቅና ነገሮች ሁሉ መሥመር ይዘው እንዲሄዱ የሚሹ ሰዎች ናቸው:: ከሌሎች ሰዎች ልዩ የሆኑትን ልብሶችን ወይም የተለየ አለባበስን የሚያዘወትሩ ሰዎች በሌሎች መስኮች ፈልገው ያልተሳካላቸውን ተቀባይነት በዚህ መንገድ ለማግኘት ጥረት ማድረጋቸውን ያመለክታል:: አድማጭና ተመልካች አጥተው በአለባበሳቸው ትኩረት ለማሳብ አልመው ነው:: በተቃራኒው ደግሞ ለአሰባበሳቸው ምንም ደንታ የሌላቸውና ተገቢውን ምርጫ በማድረግ የማይሰብሱ ሰዎች ደግሞ ግድየለሾችና ትኩረት ሊደረግ ለሚገባው ነገር አስፈላጊውን እርምጃ የማይወስዱ ናቸው::

*የአነጋገር ሁኔታ፡-* ምክር ፈላጊዎች በአነጋገር ሁኔታቸውም መልዕክት ያስተላልፋሉ:: የሙዚቃ መሣሪያ ድምጽ ውፍረትና ቅጥነት የሚያስተላልፈው ዜማ እንዳለው ሁሉ ምክር ፈላጊዎች ሲናገሩ የድምጻቸው መጠን፣ ቅጥነትና ውፍረት የተለያየ መልዕክት አለው:: የጠራ ድምጽ እውነተኛነትንና ድፍረትን ሲያመለክት በዝግታና ራስን በመቆጣጠር መናገር ደግሞ በአእምሮ ውስጥ የሚታገል ሐሳብ መኖሩን ያመለክታል:: ምናልባት እንዳልሳሳት በማለት አስቦ ለመናገር የሚደረግ ጥረት ነው:: አንዳንድ ሐሳቦችን ሲናጋሩ የሚምታታባቸው ወይም ሐሳቦችን የሚደጋግሙ ምክር ፈላጊዎች መናገር የማይፈልጉት ሐሳብ መኖሩን ያሳያል::

ምክር ፈላጊዎች በአእምሮአቸው ውስጥ የሚያስላሰሉት ሐሳብ በሚኖርበት ጊዜ ሲናገሩ ከመደነጋገርም በተጨማሪ እግራቸውን እያቀያየሩ ያጣምራሉ፣ የወንበር መደገፊያዎችን አጥብቀው ይዘው ደግሞ ይለቃሉ፣ እንዲሁም ይቁነጠነጣሉ:: በዚህ ጊዜ አማካሪው በአእምሮአቸው ውሰጥ የሚታገላቸውን ሐሳብ መግለጽ እንዲችሉ ተገቢውን ጥያቄዎች መጠየቅ ይችላል:: «የወንበሩን መደገፊያ አጥብቀህ መያዝህ ምን ማለት ነው?» «ልናገር ወይስ ልተው እያልክ የሚታስበው ነገር ያለ ይመስላል?» «አንዳንድ ጊዜ በአእምሮ ውስጥ የሚታገለውን ሐሳብ መናገር አሳቡን ለማጥራት ያግዛል» በማለት እንደ አመቺነቱ ሐሳብ በማቅረብ የታመቀው ገሃድ እንዲወጣ መርዳት ይችላል::

*ርዕስ መቀያየር፡-* ምክር ፈላጊዎች ከአማካሪው ጋር ሲነጋገሩ ርዕሶችን ወይም አንድን ሐሳብ ሳይጨርሱ ወደ ሌላ ሐሳብ ሊሸጋገሩ ይችላሉ:: እንዲህ ዓይነቱን እርምጃ በድንገት ሊያደርጉት የሚችሉበት ሁኔታ ቢኖርም ሌሎች መልዕክቶች ይኖሩታል:: ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚያስቡትን ሐሳብ ለመግለጽ ሙከራ እያደረጉ ይሆናል:: አማካሪው ችግራቸውን ቶሎ ብሎ እንዲረዳላቸው በማሰብ በአጭር ጊዜ ብዙ ነገሮችን ለመነካካት አስበው ሊሆን ይችላል:: አማካሪው በአንዱ ርዕስ ላይ ብዙ ትኩረት ያልሰጠና ደስ የተሰኘበት ካልመሰላቸው እርሱን ለማስደሰት በማሰብ ሌላ ርዕስ ይቀይራሉ:: ከዚህም በተጨማሪ ምክር ፈላጊዎች ዋና ጉዳይ አካባቢ ሲደርሱ ያንን በመተው ወደ ሌላ ሐሳብ ያልፋሉ:: አማካሪው እንደ ዓውዱ ትክክለኛውን ትርጉም ለማግኘት ጥረት ያደርጋል::



*የመግቢያና የመደምደሚያ ሐሳቦች፡-* ምክር ፈላጊዎች ሲመጡና በማጠቃለያ አካባቢ የሚገልጹት ሐሳብ ስለእነርሱ ብዙ መረጃዎችን ይሰጣል:: ለምሳሌ አንዲት ምክር ፈላጊ ሴት «ወደ አንተ የመጣሁት ባሌ ስለነገረኝ ነው» ብላ ከተናገረች ወደ ማማከር አገልግሎት የመጣችው በራስዋ ፈቃድ ሳይሆን «ሂጂ» ተብላ ነው:: የእርስዋ መልዕክት «እኔ ማማከርን አልፈልገውም» ማለትዋ ነው:: ይህ በቃል ሳይሆን በሰውነት እንቅስቃሴም ሲገለጽ ይችላል:: አማካሪው ለሚያቀርብላት ጥያቄዎች በአንድ ቃል ብቻ መልስ ትሰጣለች ወይም ዝም በማለት እምቢታዋን ትገልጻለች:: ስለዚህ አማካሪ ይህን ሲገነዘብ ምክር ፈላጊዋ በማማከር አገልግሎት ተጠቃሚ እንድትሆን በፈቃድዋ ላይ አስፈላጊውን የማዘጋጀት ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል::

በአንድ የማማከር ክፍለ ጊዜ ወይም አጠቃላይ የማማከር ግንኙነቱ በሚደመደምበት ወቅት ምክር ፈላጊዎች ፈዘዝ ብለው ቁጭ ካሉ አንድ ያልጠበቁት ነገር እንደሆነ ያመለክታል:: «እኔ ማማከርን እንዲህ አልጠበቅኩትም:: ለካስ ይኸው ነው!» ወይም «እንዲህ ያለውን ሐሳብ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እችላለሁ? ባልመጣ ኖሮ ጥሩ ነበር» ማለታቸው ሊሆን ይችላል:: ምክር ፈላጊዎች ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉትን የመፍትሔ ሐሳብ ካገኙ በኋላ «ይህን ተግባራዊ ማድረግ ምን ይመስልሃል?» ብሎ አማካሪው ሊጠይቃቸው በአንደበታቸው «ይህ ቀላል ነገር ነው:: እኔ አደርጋለሁ» ቢሉም የሰውነታቸው እንቅስቃሴ ግን «ከዚህ አሁን ሲውጣ እንጂ የማደርገውን እኔ አውቃለሁ» የሚል መሆኑን ማረጋገጥ ጠቃሚ ነው:: የተገኘውን አማራጭ የመፍትሔ ሐሳብ ተግባራዊ ለማድረግ ምን ያህል መስጠት እንዳላቸው ለመገምገም ያግዛል::

*የምላስ ወለምታ፡-* ምክር ፈላጊዎች ከአማካሪ ጋር ሲነጋገሩ ድንገት የሚናገሩአቸው ቃላቶች ወይም ሐሳቦች በአእምሮአቸው ውስጥ የተሸሸገውን መረጃ ይናገራል::

*መርሳት ወይም ማስታወስ፡-* ምክር ፈላጊዎች አንድን ታሪክ ወይም ሐሳብ በሚናገሩበት ጊዜ መረሳት የሌለበትን ነጥብ/ሐሳብ ይረሉታል:: በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች የሚያውቁትንም ነገሮች በትክክል አስታውሰው መናገር ሲያቅታቸው ይችላል:: ሆኖም መርሳት መልዕክት አለው:: በአብዛኛው ሰዎች በሕይወታቸው ደስታን የሰጣቸውንና የሚሰጧቸውን ነገሮች አይረሱም:: ክፉ የሆኑ ገጠመኞችን ደግሞ ለማስታወስ ካለመፈለጋቸው የተነሣ ላለማስታወስ ጥረት ስለሚያደርጉ ከቅርብ ትውስታቸው እየራቀ ይሄዳል:: ሰዎች አንድን ነገር ለማስታወስም ሆነ ለመርሳት ዓላማ ይኖራቸዋል:: መርሳት ከዓላማ ጋር የተያያዘ ነገር አለው:: አንድ ምክር ፈላጊ ስለቤተሰቡ እንዲናገር ተጠይቆ የቅርብ ቤተሰብ አባላትን ሁሉ ጠቅሶ የመጨረሻውን ወንድሙን ይረሳል:: ለምንድነው እርሱን የረሳው? ይህ ዝም ብሎ መርሳት ሊሆን ስለማይችል የዚህ መርሳት ዓላማ ምን እንደሆነ መፈተሽ ጠቃሚ መረጃን ይሰጣል::

*በፊት ላይ የሚታዩ ሁኔታዎች፡-* በፊት ላይ የሚታዩ ሁኔታዎች የምክር ፈላጊውን ስሜትና አስተሳሰብ ያሳያሉ። አንድ ሰው ከወትሮ የተለየ ነገር ፊቱ ላይ ሊታይ የሆነ ነገር በውስጡ እንዳለ መገመት አያዳግትም። ለምሳሌ አንድ ጊዜ ነህምያ ስለ አገር ቤት ሁኔታ ከወንድሞቹ በሰማ ጊዜ ውስጡ ከማዘኑ የተነሣ ፊቱ ተለውጦ ነበር። ንጉሡም ይህን በማስተዋል «ሳትታመም ፊትህ ለምን አዘነ? ይህ የልብ ሐዘን ነው እንጂ ሌላ ነገር አይደለም» በማለት አናገረው። በልብ ውስጥ ያለው ስሜት ፊት ላይ ይንጸባረቃል።

በፊት/ግንባር/ ላይ የሚታየው ሁኔታ አሁን ምክር ፈላጊው በውስጡ የሚሰማው ስሜት ብቻ ሳይሆን በመቀጠል ሊያደርግ ያሰበውንም ነገር ሊያመለክት ይችላል። በፊት ላይ የሚታይ ሁኔታ በማሕበራዊ ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። ይህን ሁኔታ ፍርድሉንድ የተባሉ የሥነልቡና ባለሙያ ከባቡር ሐዲድ አቅጣጫ መለወጫ ጋር ያመሳስላል። መለወጫው የባቡሩን አቅጣጫ እንደሚወስን ሁሉ ፊት ላይ የሚታዩ ነገሮችም ሰዎች ለሚሰጡት ምላሽ አስተዋጽኦ አለው። በግንኙነት ውስጥ የፊትህ ንባብ ሌሎች ምን ዓይነት ምላሽ መስጠት እንደሚገባቸው ፍንጭ ይሰጣቸዋል።

ስለሆነም አማካሪ፣ ምክር ፈላጊዎች ከሚናገሩት በተጨማሪ በፊታቸው ላይ የሚታዩ ሁኔታዎችን በመከታተል በውስጣቸው ምን እየተሰማቸው እንደሆነ መረዳት ይችላል። «እንዲህ ስትናገር እፊትህ ላይ የሚታይ ነገር አለ፤ ምን እየተሰማህ ነው?» ብሎ በመጠየቅ፣ ምክር ፈላጊው ስሜቱንና የፊቱን መልዕክት እንዲገልጽ መጋበዝ ጠቃሚ ነው።

እንግዲህ አማካሪው ንግግራዊ ስላልሆኑ የምክር ፈላጊዎች መልዕክት ማስተላለፊያ መንገዶች በቂ እውቀትና ልምድ ኖሮት ከዓውዳቸው ጋር በማገናዘብ መረዳት ከቻለ ተገቢውን መረጃ በመስጠት በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው። ትክክለኛ ትርጉም ካልተሰጣቸው ደግሞ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል። ስለዚህ የመልዕክቶቹ አተረጓጎም ከፍተኛ ጥንቃቄና ማስተዋል በተሞላበት ሁኔታ መደረግ አለበት።



## ምዕራፍ 5

## የማማከር ሥነምግባራት

እያንዳንዱ አገልግሎት የራሱ የሆነ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥነምግባር እንደሚኖረው ሁሉ የማማከር አገልግሎትም የራሱ የሆነ ሥነምግባር አለው። የሙያ ሥነምግባር ማለት አንድ ሰው ሙያዊ የሆነ ሥራ በሚሠራበት ወቅት ሊኖረው የሚገባውን ባሕርይን የማያሳይ መመሪያ ነው። ያ ባለሙያ እውቀቱንና ልምዱን እንዴት መጠቀም እንደሚገባው አቅጣጫ የሚሰጥ የሞራል ደንብና ሥርዓት ነው። የሙያ ሥነምግባር እያንዳንዱ ባለሙያ ተግባሩን፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ ማከናወን እንዲችል የሚያደርግ አሠራር ነው።

በዓውዳችን፣ በዝርዝር የተፃፈ የመንፈሳዊ አገልግሎት ዘርፎች የሥነምግባር ዝርዝር ባይኖርም እያንዳንዱ አገልጋይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ባለው አሠራር ማገልገል እንዳለበት ይጠበቃል። ሆኖም፣ አልፎ አልፎ ካለማወቅ የተነሣ ወይም ሆን ተብሎ በአገልግሎቱ ውስጥ ኢሥነምግባራዊ የሆኑ ድርጊቶች ይፈጸማሉ። ለምሳሌ አንድ አገልጋይ በመድረክ ላይ እያገለገለ የማይገባ ንግግር ቢናገር ወይም የሰዎችን ምስጢር አግባብ ባልሆነ ሁኔታ ቢያወጣ፣ እንዲጠየቅ የሚያስገድደው ወጥነት ያለው የሥነምግባር መመሪያ የለም። አንድ አገልጋይ በመንፈሳዊ አገልግሎት ከእርሱ የሚጠበቀውን ሥነምግባር በሚገባ ተረድቶና ተቀብሎ ቢገባበት ተጠያቂነትን ያጠናክራል።

ለማማከር አገልግሎት የሥነምግባር መመሪያ መኖሩ አስፈላጊ ነው። በዚህ አገልግሎት ውስጥ ሰዎች ገመናቸውን የሚያወጡ፣ ብዙ መቀራረብ በመኖሩ፣ በምስጢር የሚደረግ ግንኙነት በመሆኑና በመሳሰሉት ምክንያቶች ተገቢ የሆነ የሥነምግባር መመሪያ መኖሩ የግድ ነው። የዚህ አስፈላጊነት አማካሪው በተወሰነለት ወሰን ውስጥ በመሆን አገልግሎቱን በሚገባ መስጠት እንዲችልና የምክር ፈላጊዎችን የግል መብት ሳይዳፈር ሥርዓት ባለውና ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ነው። በዚህ ምዕራፍ ዝርዝር የሆኑ የሥነምግባር መመሪያዎች ባይቀርቡም በማማከር አገልግሎት ሥነምግባር ውስጥ ሊነሡ የሚገባቸውን ዋና ዋና ነጥቦችን ያብራራል።

አንድ አማካሪ የማማከር ሥነምግባርን ማወቅ ይጠበቅበታል። እነዚህ ሥነምግባራት ዝርዝራቸው ብዙ ሊሆኑ አጠቃላይ የሆኑ ነጥቦች ከዚህ በታች ተብራርተዋል።

*መረጃ መስጠት፡-* ምክር ፈላጊዎች ወደ ማማከር አገልግሎት በሚመጡበት ጊዜ ማማከር ምን እንደሆነ ትክክለኛ ወይም በቂ ግንዛቤ ላይኖራቸው ስለሚችል አማካሪ ስለማማከር ምንነት ሊገልጽላቸው ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪ በማማከር ውስጥ የሚኖሩ ጥቅሞችና እንዴት ተገቢውን ውሳኔዎችን መወሰን እንደሚችሉ እንዲሁም ሊኖሩ

የሚችሉትን ስጋቶች ማብራራት አለበት:: በእያንዳንዱ የማማከር ሂደት/አርምጃ/ አማካሪ፣ ምክር ፈላጊዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መረጃዎች ይሰጣቸዋል:: አማካሪው መረጃ ሲሰጥ የምክር ፈላጊዎች መረጃውን የመሸከምና የመጠቀም ብቃታቸውን መፈተሽ ይኖርበታል:: በአንድ ጊዜ ከአቅም በላይ የሆነ መረጃን ለምክር ፈላጊዎች መስጠት ተገቢውን ውሳኔ እንዲያደርጉ አያግዛቸውም:: በተለይ በማማከር ወቅት ስለምስጢር አጠባበቅ ሁኔታ መነጋገር እጅግ አስፈላጊ ነው:: ስለዚህ ተገቢውን መረጃ በተገቢው መጠንና ጊዜ መስጠትን መለማመድ ያስፈልጋል::

***ሌሎችን መጥቀም***፦ ለሌሎች መልካም የሆነውን ማድረግ የማማከር ዋና ሥነምግባር ነው:: በማማከር አገልግሎት አማካሪው ለምክር ፈላጊው ሁለንተናዊ ዕድገት በሚጠቅሙ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ይሰጣል:: በማንኛውም መንገድ ምክር ፈላጊው ከሂደቱ የማይጠቀም ከሆነ ግንኙነቱ መቋረጥ አለበት::

በማማከር አገልግሎት ቅድሚያ የሚሰጠው የምክር ፈላጊው ከግንኙነቱ መጠቀሙ ነው:: አማካሪው የራሱን ጥቅም ትቶ ምክር ፈላጊውን መጥቀም አለበት:: በዚህ ግንኙነት በአብዛኛው የሚጠቀመው ምክር ፈላጊው ነው:: የአማካሪው የግል ፍላጎቱ ልቆ መታየት የለበትም:: አማካሪው የሥልጣን ፍላጎቱን ለማርካት ብሎ ምክር ፈላጊውን የመቆጣጠር፣ በራሱ አመለካከት ምክር ፈላጊውን መጠምዘዝ፣ ምክር ፈላጊው ችሎታውንና ብቃቱን እንዲያረጋግጥለት ግፊት ማድረግ፣ በምክር ፈላጊው መወደስን መፈለግና የመሳሰሉትን ተግባሮች መፈጸም አይጠበቅበትም:: በማንኛውም መንገድ ምክር ፈላጊውን ለግል ስውር ፍላጎት ዒላማ መጠቀም ኢሥነምግባራዊ ነው::

***ሌሎችን ለመጉዳት ማንኛውንም እንቅስቃሴ አለማድረግ***፦ አማካሪ በምክር ፈላጊዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያደርጉ ከሚገባቸው ንግግሮችና ተግባሮች ሁሉ መቆጠብ አለበት:: በግንኙነት ሂደቱ ውስጥ ለምክር ፈላጊው ችግር አማራጭ መፍትሔዎች ሲፈለጉ፣ በአጭር ጊዜም ሆነ በረጅም ጊዜ ውስጥ፣ ምክር ፈላጊውንም ሆነ ሌሎች ሰዎችን ሊጎዱ የሚችሉትን መፍትሔዎች ማስወገድ ያስፈልጋል:: ምክር ፈላጊውን ለመጥቀም ሌሎች ሰዎች መጎዳት የለባቸውም:: ለምሳሌ ከዚህ ሐሳብ አንጻር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰውን የኢዮናዳብን ምክር ስንመለከት ኢሥነምግባራዊ ነው::

***የሌሎችን የግል መብት ማክበር***፦ ምክር ፈላጊዎች የራሳቸው የማሰብ ነጻነት፣ ይጠቅመኛል ብለው ያሰቡትን አቅጣጫ የመምረጥ፣ በሚገባቸውና በወደዱት መልክ ሐሳባቸውን የመግለጽና ያልገባቸውን የመተው መብት አላቸው:: አማካሪ ምክር ፈላጊዎች በራሳቸው ውሳኔዎችን በጥንቃቄ አስበውበት እና በሕይወታቸው ላይ የሚያስከትለውን ውጤት አመዛዝነው እንዲወስኑ ያግዛቸዋል:: አማካሪ፣ ለምክር ፈላጊዎች አይወስንላቸውም:: የአማካሪ ድርሻ፣ ምክር ፈላጊዎች አማራጭ መፍትሔዎችን እንዲያቀርቡ፣ እንዲመዝኑና በአጭርና በረጅም ጊዜ የሚጠቅማቸውን እንዲመርጡ መምራት ነው::



አማካሪ በምክር ፈላጊዎች ላይ የራሱን የግል እምነትና አመለካከት መጫን አይገባም:: ነገር ግን የግል አሴቱን ለእነርሱ ማካፈል ይችላል:: ይህን ሲያደርግ የራሱን አሴቶች በግልጽ በመለየት፣ ምክር ፈላጊዎችም የራሳቸውን ለይተው ማውጣት እንዲችሉ መርዳት ተገቢ ነው:: ምክር ፈላጊዎችም፣ በተመሳሳይ መልኩ የራሳቸውንና ከእነዚህም የተነሣ የመጡትን ድርጊቶችን/ባሕርያትን/ እንዲያስሉ ምሳሌነትን ሊያሳያቸው ይችላል:: የምክር ፈላጊዎች አሴት ከአማካሪው ተቃራኒ ቢሆንም እንኳ ማክበር ተገቢ ነው፤ ሆኖም በእነርሱ ሕይወት ላይ የሚያስከትሉት አሉታዊ ተጽዕኖዎች ካሉ በግልጽነት መወያየት ያስፈልጋል:: የእነርሱን አሴት ማክበር ማለት ትክክለኛነታቸውን ማጽደቅ ወይም መቀበል ማለት አይደለም::

አማካሪ ከምክር ፈላጊዎች ጋር ስለመንፈሳዊነት አንስቶ መነጋገር ይችላል:: የእነርሱ መንፈሳዊነት ምን እንደሚመስል፣ በመጀመሪያው የማማከር ወቅት መረጃን ይሰበስባል:: ከዚህ መረጃ በመነሳት ከችግሮቻቸው ጋር የሚገናኝ ጉዳይ ሆኖ ሲያገኘው በማማከር ሂደት ውስጥ በማንሳት በስፋትና በጥልቀት ይመለከታል:: መንፈሳዊነት እንደ አንድ ችግር ወይም እንደ መሠረታዊ መንስኤ የሚታይ ሲሆን አስፈላጊው መፍትሔ እንዲፈለግለት አማራጭ ሐሳቦችን ከምክር ፈላጊዎች ጋር ሆኖ ይፈልጋል:: ሆኖም የራሱን የግል እምነት/መንፈሳዊነት/፣ ተገቢ ባልሆነ መንገድ በምክር ፈላጊዎች ላይ መጫን አይገባውም::

***ፍትሐዊ አቀራረብ***፦ አማካሪ ለሁሉም ምክር ፈላጊዎች ተገቢና እኩል ዓይነት አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል:: ሰዎችን በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በኑሮ ደረጃ ወይም በትምህርት ደረጃ ልዩነት ሳያደርግ ለምክር ፈላጊዎች ደረጃውን የጠበቀ ያለ ምንም አድልዎ መስጠት ይኖርበታል:: ሁሉንም ሰዎች በእኩል ዓይን ማስተናገድ ተገቢ ነው::

***ታማኝነት***፦ ታማኝነት ለማማከር አገልግሎት ግንኙነት አስፈላጊ ባሕርይ ነው:: አማካሪ ለምክር ፈላጊዎች የገባውን ቃል ኪዳን መጠበቅ ይገባል:: ለምክር ፈላጊዎች ተገቢውን አክብሮት መስጠት ከሚታይባቸው መንገዶች አንዱ ታማኝነትን በማሳየት ነው::

***ከወሲብ ግንኙነት መጠበቅ***፦ አማካሪ ከምክር ፈላጊዎቹ ጋር ያለውን ግንኙነት በወሰን ማድረግ አለበት:: አንድ አማካሪ በመጀመሪያ ስለራሱ የወሲብ አስተሳሰቦችና እምነት አጥርቶ ማወቅ ይኖርበታል:: ወሲብ ትክክለኛና ተገቢ ነው ብሎ የሚያምነው በማንና በማን መካከል በምን ዓይነት ሁኔታ ሲፈጸም ነው? ስለተቃራኒና ተመሳሳይ ጾታዎች ግንኙነት ያለው አቋሙ ምን እንደሆነ ለይቶ ማወቅ የሚመጡትን ጉዳዮች እንዴት እንደሚያስተናገድ አቅጣጫ ይሰጡታል:: ምክር ፈላጊዎች ሊያማክሩት በሚፈልጉት በወሲብ ጉዳዮች እንዳይረዳቸው የግል አስተሳሰቡና እምነቱ እንቅፋት የሚሆኑበት ከሆነ ወደ ሌሎች አማካሪዎች መሄድ እንዲችሉ ሊመራቸው ይገባል::

አማካሪ ከምክር ፈላጊዎች ጋር በማንኛውም ሁኔታና ዓይነት የወሲብ ድርጊት መፈጸም ኢ-ሥነምግባራዊ ነው። በሕግም ያስጠይቀዋል። በማማከር ግንኙነት፣ ምክር ፈላጊዎች ከአማካሪው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በጣም የተቀራረበ በመሆኑ አማካሪው ከተቃራኒ ጾታ ጋር በወሲብ ፈተና ውስጥ ሊወድቅ ይችላል። ፈተናው ከምክር ፈላጊዎች ወይም ከአማካሪው ሊመጣ ይችላል። ምክር ፈላጊዎች ከአማካሪው ጋር ወሲብ ለመፈጸም ፈቃደኛ ቢሆኑ እንኳ፣ በማማከር ግንኙነት ውስጥ ከእነርሱ ጋር ወሲብ መፈጸም ተገቢ አይደለም። ሁለቱም ትዳር ያልመሠረቱ ቢሆንም እንኳ በማማከር ግንኙነት ወቅት በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ወይም በተጣለው መሠረት ላይ በመቆም የትዳር ግንኙነት መምሥረትም አይደገፍም። የትዳር ውሳኔ ለማድረግ ከፈልጉ የማማከር ግንኙነትን ካበቁ (ካቋረጡ) በኋላ የተወሰነ ዓመታት ማለፍ አለበት።

*ምስጢር መጠበቅ*፡- የማማከር አገልግሎትን ከሌሎች አገልግሎቶች ልዩ ከሚያደርጉት ዋና ዋና ሐሳቦች መካከል አንዱ ምስጢር መጠበቅ ነው። የማማከር አገልግሎት የምክር ፈላጊዎች ምስጢር የሚጠበቅበት ግንኙነት ነው። አማካሪ የምክር ፈላጊዎችን የግል መረጃዎችን በምስጢር የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት። አማካሪ በማማከር ግንኙነት የሚሰማቸውን መረጃዎች ያለ ምክር ፈላጊዎቹ ፈቃድ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ማካፈል የለበትም።

በማማከር አገልግሎት የሚገኙትን መረጃዎችን ለሦስተኛ አካል ማውጣት የሚቻልባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ይኖራሉ። ከእነዚህም መካከል የሚከተሉትን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

- √ *ምክር ፈላጊዎች በራሳቸው ላይ አደጋ እንደሚያስከትሉ መረጃ ሲኖር* አማካሪው እነርሱን ለማዳን ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል። ለምሳሌ አንድ ምክር ፈላጊ የገጠመውን የሕይወት ችግር ለመፍታት ስለማይችል ራሱን ለማጥፋት ውሳኔ ማድረጉን ከገለጸ፣ አማካሪው ይህን ሰው ለማዳን ሲል መረጃውን ለሦስተኛ ወገን አስፈላጊውን የሆነውን ያህል መግለጽ ይችላል።

- √ *ምክር ፈላጊዎች በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት ለማድረስ ውሳኔ ያደረጉ መሆናቸው ሲታወቅ*፡- ምክር ፈላጊው ሌሎች ሰዎችን የሚጎዳ ስለመሆኑ በሚሰማበት ጊዜ ሊጠቁ የታሰቡት ለሕይወታቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አስፈላጊውን መረጃ በተገቢው መንገድ ያወጣል። እንዲህ ዓይነት መረጃዎች፣ አማካሪውና ምክር ፈላጊዎች በሚኖሩበት ዓውድ፣ መውጣታቸው በሕግ የሚደገፍ ሲሆኑና የሕሲና ጉዳይም ሆኖ ሲገኝ ነው።

- √ *ለሱፐርቪዥን*፡- አማካሪው ከሌላ የበላይ ተመልካች ወይም ሌሎች አማካሪዎች ጋር አብሮ በሚሠራበት ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ የምክር ፈላጊዎችን ታሪክ ለእነርሱ ሊያቀርብ ይችላል። ይህም የሚደረገው የአማካሪውን ሥራ ለመከታተል፣ ከጉዳዮቹ ትምህርት ለማግኘትና



አንዳንድ አስቸጋሪ ጉዳዮችን በጋራ ሆነው ለመፍታት ያመች ዘንድ ነው። ይህ ሁኔታ እንደሚኖር ለምክር ፈላጊዎቹ በቅድሚያ ሊነገራቸውና በሂደቱ ላይ መስማማት አለባቸው። በዚህ ሂደት የሚሳተፉ አማካሪዎች ሁሉ ምስጢርን ይጠብቃሉ።

- √ *ሕግ የሚፈቅድ/የሚያስገድድ ሲሆን*፡- አንዳንድ ሕግ እንዲገለጡ የሚፈቅዳቸው/የሚያስገድዳቸው/ ነገሮች በሚኖሩበት ጊዜ የምክር ፈላጊዎችን ምስጢር ለተገቢው አካል ማውጣት ይቻላል። ለምሳሌ ያህል ልጆችን/አረጋውያንን/ ማንገላታት የተፈጸመ ሲሆን፣ ሌሎች ሰዎችን ሊበትን የሚችል ተላላፊ በሽታ ሲኖር፣ በምክር ፈላጊዎቹ ላይ በጦር መሣሪያ የተፈጸመ ቁስል በሚኖርበት ሁኔታ፣ ምስጢር ማውጣቱ እንደ ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊት አይቆጠርም።

- √ *በምክር ፈላጊዎች ፈቃድ*፡- አማካሪው የምክር ፈላጊዎችን የተወሰነ ታሪክ በምሳሌነት ሌሎችን ለማስተማር ወይም ለሥነጽሑፍ ለመጠቀም እንዲችል ፈቃድ ሊሰጡት ይችላሉ። በዚህ ሁኔታ አማካሪው ታሪኩን፣ የእነርሱን ማንነት በግልጽ በማያሳውቅ መንገድ መጠቀም ይችላል። ያለ ምክር ፈላጊዎቹ ፈቃድ በማማከር ወቅት የሚገኙትን ታሪኮች መጠቀም ኢ-ሥነምግባራዊ ከመሆኑም ባሻገር አገልግሎቱን ከፉኛ ይጎዳል።

አማካሪ የምክር ፈላጊዎችን ምስጢር በሚያወጣበት ጊዜ *(1)* ምስጢሩን አለማውጣት ምስጢሩን በማውጣት ከሚመጣው ጉዳት ይልቅ በልጦ ሊታይ፣ *(2)* ምስጢሩ ሳይወጣ ሲመጣ ያለውን ጉዳት መከላከል የሚቻልበት ሌላ አማራጭ መንገድ ሳይኖር ሊቀር፣ *(3)* ምስጢር ማውጣቱ ሊመጣ ያለውን ጉዳት ሊከላከል የሚችልና አነስተኛ ጉዳት ያለው አማራጭ ሆኖ ሊታይ እና *(4)* ምክር ፈላጊዎች ምስጢሩ እንደሚወጣ በቅድሚያ ሲነገራቸው እንደሆነ ማወቅ ይኖርበታል።

*የራስን ውስንነት መረዳት*፡- አንድ አማካሪ ፍጹም እንደሆነ ሊገነዘብ ይገባል። የሁሉንም ምክር ፈላጊዎች ችግር ለመፍታትና ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚያስችል ብቃት ላይኖረው ይችላል። ስለዚህ የማይችለውን አልችልም ብሎ በግልጽ በመናገር ወደ ሌሎች አማካሪዎች መምራት ይጠበቅበታል። በማማከር አገልግሎት ተገቢውን ሥልጠና ካላገኘ በአንድ የትምህርት/ሙያ መስክ እውቅና ስላገኘ ብቻ ብቃት ያለው አማካሪ ሊያሰኘው አይችልም። እንደ አስፈላጊነቱ የሙያ ብቃት ደረጃውን፣ ለምክር ፈላጊዎች ማሳወቅ ይኖርበታል።

እስካሁን ድረስ ከማማከር ትርጉም ተነስተን የተመለከትናቸው ነጥቦች ለማማከር አገልግሎት ብቁ ሊያደርጉን የሚችሉ መሠረታዊ ናቸው። አንድ አማካሪ፣ የማማከርን ትክክለኛ ትርጉም ማወቅ፣ በሰራሱ ባሕርይ ጥናት ማድረግ፣ ማማከር ከየት ተነስቶ የት እንደሚያበቃ ማቀድ እንዳለበትና፣

ሲያማክር ሊጠቀምባቸው ስለሚገባቸው ነገሮች ጠቅሰናል። ምክር ፈላጊዎች ንግግራዊና ንግግራዊ ባልሆኑ አካላዊ እንቅስቃሴዎች መልዕክት ማስተላለፍ እንደሚችሉና አማካሪ በማማከር ወቅት አማካሪ ሊያከብራቸው የሚገባቸውን መሠረታዊ ሥነምግባራት ተመልክተናል።

በሚቀጥሉት ተከታታይ ምዕራፎች ውስጥ ደግሞ ወጣቶችንና የጋብቻ ችግር ያላቸውን ምክር ፈላጊዎችን እንዴት ማማከር እንደምንችል እንመለከታለን። ወጣቶች እነ ማን ናቸው? ምን ዓይነት ባሕርያት አላቸው? ምን ዓይነት አማካሪን ይፈልጋሉ? እንዴትስ ልናማክራቸው እንችላለን? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሙከራ እናደርጋለን። በዚህ ዘመን ያለውን ትውልድ ለመቅረጽ የሚረዳውን ይህን አገልግሎት ለማወቅ ወደሚቀጥለው ምዕራፍ አብረን እንሂድ!



## ምዕራፍ 6

## ወጣቶችን ማማከር

### *6.1. ወጣቶች እነማን ናቸው?*

አንድ ጊዜ አርተር ጀርስልድ የተባለ የዕድገት ሥነልቡና ባለሙያ ጎልማሶች ሁለት ጥያቄዎች ጠየቃቸው። የመጀመሪያው፣ ወጣት ለመሆን እንደገና ዕድል ቢሰጣቸው ወጣትነትን በተለየ ሁኔታ እንዴት እንደሚኖሩ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዕድል ቢሰጣቸውስ አሁን በቀሰሙት ልምድ ተመልሰው ያንን ዘመን ለመኖር መፈለጋቸውን ነበር። ጎልማሶቹ እንደገና ወጣት የመሆን ዕድል ቢሰጣቸው ተመልሰው ወጣትነትን በተለየ ሁኔታ እንደሚኖሩት ተናግረው ነበር። ሆኖም አሁን ወጣት መሆን እንደማይፈልጉ ገለጹለት። የወጣትነት ዘመን ብዙ አማራጮች የሚገኙበት ጊዜ ነው። ወጣትነት ብዙ ዕድሎችን ይዟል። ወጣቶች በፈለጉት አቅጣጫ ለመጓዝ መንገዳቸው ሰፊ ነው። ሆኖም ለብዙዎች የመከራና የፈተና ጊዜ ነው። ስለዚህ ብዙ ሰዎች ያንን ወቅት እንደገና ለመኖር አይፈልጉም።

አንድ አማካሪ ወጣቶችን ለማማከር በቅድሚያ ስለወጣትነት ጊዜ፣ ስለወጣቶች ባሕርያት፣ የወጣትነትን ጊዜ ከሌሎች የዕድሜ ክልሎች ልዩ የሚያደርጉና ወጣቶችን ለማማከር የሚረዱ የማማከር ዘዴዎችን ማወቅ ይጠበቅበታል። የወጣቶችን ሥነልቡና መረዳት እነርሱን ለማማከር አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው። ወጣቶችን በማማከር የሚያገለግል አማካሪ ብዙ ትርፍ በሚያስገኝ የንግድ ሥራ ላይ እንደ ተሰማራ ባለ ሀብት ነው። ምክንያቱም ወጣቶች ብዙ ዕድሎች ስላሉአቸው ወደፊት ለራሳቸውና ለሌሎች የበረከት ምክንያት ይሆናሉ።

አንድ ጊዜ ሶቅራጥስ የሚባል የግሪክ ፈላስፋ ወደ አቴና ከፍተኛ ሥፍራዎች የመውጣት ዕድል ቢያገኝ ድምጹን ከፍ በማድረግ የአቴና ነዋሪዎች ለመበልጸግ ብዙ እንደሚሠሩ ሁሉ ነገ ሁሉን ለሚያወርሱለት ወጣቱ ትውልድ ለምን ትኩረት እንደማይሰጡ እንደሚጠይቃቸው ተናግሮ ነበር። ወጣቶች *የዛሬ አበቦች የነገ ፍሬዎች ናቸው። የዛሬ ትኩስ ኃይል የነገ አገር ተረካቢዎች* በመሆናቸው እነርሱን ለማማከር የሚባክነው ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ ከሁሉም ይልቅ ትልቅ ብድራት ያለው ሥራ ነው።

### *6.2. የወጣትነት ዘመን ልዩ ባሕርያት*

#### *የወጣትነት ወቅት የሽግግር ጊዜ ነው*

የወጣትነት ዕድሜ ከልጅነት ወደ ጎልማሳነት ሽግግር የሚደረግበት ወቅት ነው። በስሜት፣ በአካል፣ በአእምሮና በማህበራዊ ሕይወታቸው እየበሰሉ የጎልማሳነት ባሕርይን ለመያዝ የሚታገሉበት ጊዜ ነው። ወቅቱ ፈጣን ለውጥ የሚከሰትበት ዕድሜ ነው። ይህ የወጣትነት ዕድሜ እንደየ

አገሩና ባሕል የተሰያየ ቢሆንም ከአካላዊ ዕድገት አንጻር ከ13 ዓመት አካባቢ ጀምሮ እስከ 20ዎቹ አጋማሽ ድረስ የሚሄድ ይሆናል።

በዚህ የወጣትነት ዕድሜ ከሚከሰቱ ለውጦች መካከል አንዱ ፈጣን የሆነ የአካል ዕድገት ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት ልጅ ይባል የነበረው ሰው አሁን «ትልቅ» ይሆናል። ከልጅነት እልፎ ልጅ መውለድ ወደሚችልበት ደረጃ ያድጋል። አካላዊ ለውጥን በተመለከተ ከሚከሰቱ ለውጦች መካከል በሴቶች የወር አበባ መታየት አንዱ ነው። ስለዚህ ሁኔታ አስፈላጊውን እውቀት ከቤተሰብ ወይም ከትምህርት ቤት ወይም ከሌሎች ትምህርት ሰጪ ተቋማት ያላገኘች ሴት ልጅ በሰውነቷ ላይ ደም ስታይ ድንጋጤና ግራ መጋባት እንደሚመጣበት መገመት እያዳግትም። የወር አበባ በ12-14 ዓመት መካከል ሊመጣ ይችላል። በወንዶችም የወንድ ዘር ማፍሰስ እንደ በሽታ ወይም እንደ መጥፎ ነገር ታይቶ ግራ መጋባት ሊያስከትል ይችላል። በወንዶች ፈጣን የአካል ዕድገት የሚታየው በ14-16 ዓመት አካባቢ ነው።

ወጣቶች በአካል ዕድገታቸው ከሌሎች እቻዎቻቸው መቅደም ወይም መዘግየት የራሱ ተጽዕኖ አለው። በሴቶች በኩል አጅግ አጭር ወይም ወፍራም መሆን ተቀባይነት እንደሚያሳጣቸው በማሰብ እንዲጨነቁ ሊያደርጋቸው ይችላል። የአንዳንዶቹ ችግር ጊዜያዊ ቢሆኑም የአካላቸውን ሁኔታ በጸጋ ካልተቀበሉት በሴላው ሕይወታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከትላል። ለምሳሌ በዚህ የሚጨነቁ ከሆነ በትምህርታቸው የነበራቸውን ውጤት ሊቀንሱ ይችላሉ። እንግዲህ የወጣቶች አማካሪ የወጣቶችን የአካል ዕድገታቸውንና እያንዳንዱ ለውጥ በሕይወታቸው ላይ ያለውን ምልከታ በማወቅ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይጠበቅበታል።

*የወጣትነት ጊዜ የወሲብ ፍላጎት የሚጎለብትበት ወቅት ነው*

ከአካል ዕድገት የተነሣ ወጣቶች ለአቅመ አዳምና ሔዋን ደርሰዋል። በሁለት ተቃራኒ ጾታዎች መካከል ያለው ግንኙነት እንዲሁ ለጨዋታ ብቻ መሆኑ ይቀራል። ሁለቱም ጾታዎች በወሲብ ይሳሳባሉ። ከዚህም የተነሣ በፍቅር መያዝ፣ ተቀጣጥሮ መገናኘት፣ እልፎ እልፎ መተቃቀፍና በመነካካት የወሲብ ስሜት ለማርካት ጥረት ማድረግ ይታያል። ከዚህም ባለፈ ሁኔታ አልፎ አልፎ የወሲብ ግንኙነትን ሊፈጽሙ ይችላሉ።

በተለይ በዓውዳችን ወጣቶች ከተቃራኒ ጾታ ጋር በነጻነት አብሮ መውጣት ያልተለመደ ነገር ቢሆንም አሁን እንደ «ባሕል» እየሆነ ይገኛል። ይህ ለትዳር ጓደኛ ምርጫ ሊረዳ የሚችል መንገድ ቢሆንም ወደማይፈልጉት የወሲብ ግንኙነት ሊመራቸው ስለሚችል ወሰናቸውን ጠብቆ እንዴት አብረው መውጣት እንደሚችሉ መማር ይጠቅማቸዋል። የተቃራኒ ጾታ ግንኙነትን በተመለከተ ግልጽና በቂ የሆነ ትምህርት በቤተሰብ፣ በሃይማኖት ተቋማትና በትምህርት ቤት አይሰጥም። ወጣቶችን የሚያማክሩ አማካሪዎች በግልና በቡድን ለወጣቶች ይህን ትምህርት ቢያስተምሩ ብዙዎች በዚህ ድርጊት ሳይጎዱ ሕይወታቸውን እንዲመሩ ያስችላቸዋል።



በክርስቲያናዊ ማማከር ዓውድ ከጋብቻ በፊት በማንኛውም ዓይነት መንገድ ወሲብን መፈጸም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት በፍጹም ትክክል አይደለም። በአእምሮ ተቃራኒ ጾታን እያሰቡ ከእርሱ ወይም ከእርሰዋ ጋር ወሲብ መፈጸም በአካል ወሲብን ከማድረግ የተለየ ቢሆንም ኃጢአት ነው (ማቴ5:28)። ከሐሳብ አልፎ መዳራት ውስጥ ከተገባ ደግሞ ወሲብ ለመፈጸም ዝግጅት መጀመር እንደሆነ ቢታሰብም እዚያው ላይ ቢያበቃም የወሲብ ስሜት እርካታ ሲፈጸም ስለሚችል ትክክል አይደለም። በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የቅድመ ጋብቻ የወሲብ ግንኙነትም ኃጢአት ነው (የሐሥ.15:20፣ 1ቆሮ.6:9፣13፣18፤ ገላ5:19፣ኤፌ.5:3፣ ቆላ3:5፣ 1ተሰ4:3)። አንድ ወንድና አንዲት ሴት ወደፊት እንገባለን ምንም አይደለም ብለው ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈጸማቸው ለአሁንም ሆነ በወደፊት የትዳር ሕይወታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው።

በአብዛኛው ከጋብቻ በፊት የሚፈጸመው የወሲብ ግንኙነት የእውነተኛ ፍቅር መግለጫ ሳይሆን የወሲብ ምንነትን በተግባር ለማወቅ የሚመነጭ ከፍተኛ ፍላጎትና ጉጉት ነው። የቅድመ ጋብቻ ወሲብ ያልተፈለጉ ውጤቶችን ያስከትላል። በተለይ በሴቶች ላይ ያልታቀደ እርግዝና ሊያስከትል ይችላል። ይህ ሊሆን ደግሞ በፍቅር ያበዱላቸው ይመስሉ የነበሩ ወንዶች የውጤቱ ተካፋዮች ለመሆን ፈቃደኞች አይሆኑም። ይህ ደግሞ በሴቶች ልጆች ላይ ሥነልቦናዊና ማሕበራዊ ችግሮችን ያመጣል። ስለዚህ የወጣቶች አማካሪዎች፣ ወጣቶች የወሲብ ስሜታቸውን በመግዛት እስከ ትዳር ድረስ እንዴት መሄድ እንደሚገባቸው በማስተማርና ከእነርሱ ጋር «በመጓዝ» መርዳት ይጠበቅባቸዋል።[1]

*የወጣትነት ጊዜ እምቅ ችሎታ የሚታይበት ወቅት ነው*

በወጣትነት ወቅት በሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ብዙ እምቅ ችሎታዎች ይታያሉ። ወጣቶች እምቅ ችሎታ ቢኖራቸውም በቂ የሕይወት ልምድና እውቀት ስለሌላቸው እምቅ ችሎታቸውን ሳይጠቀሙበት ሊቀሩ ይችላሉ። ይህ ብቻም ሳይሆን ወጣቶች ያላቸውን ችሎታ ለመልካም ነገር ወይም ለክፉ ዓላማ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በዚህ ወቅት በሕይወታቸው ላይ እራሳቸው ለመወሰን እርምጃ የሚወስዱበትም ወቅት በመሆኑ ችሎታቸውን ለቀሪው የሕይወት ዘመናቸው መሠረት ለመጣል የሚጠቀሙበት እንዲሆን ከእነርሱ ጋር ሆኖ የሚመራቸው አማካሪ ያስፈልጋቸዋል። በውስጣቸው ያለውን ችሎታ ለይቶ ማወቅና እንዴት በሥራ ላይ በማዋል ራሳቸውንና ኅብረተሰቡን መጥቀም እንደሚችሉ አቅጣጫ ጠቋሚን ይፈልጋሉ።

---

[1]ወሲብን እንዲሁም ወጣቶችን በሚመለከት ለፊ ማብራሪያ ለማግኘት በደራሲው የተጻፉትን: *ጋብቻን እንዴት ልጀምር?* እንዲሁም *ወጣቶችን የመምራት ጥበብ* የሚሉትን መጽሐፍት ማንበብ ጠቃሚ ነው።

ወጣቶች እምቅ ችሎታቸውን እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸው ተገቢውን ምክር ቢያገኙ በተገቢው *ሥራ* ላይ መሠማራት ይችላሉ:: ወላጆቻቸውን በሥራ በማገዝም ልምድን ይቀስማሉ:: የወላጆቻቸውን ሀብትና ንብረትን ከማባከን ይልቅ በመቆጠብና ለጊዜያዊ የስሜት እርካታ ብቻ ሳይሆን በዘላቂነት በሚጠቅማቸው ነገር ላይ በማዋል ኃላፊነትን ይማራሉ:: ጊዜያቸውን በአግባቡ በመጠቀም ነገ መልካም ፍሬ በሚያስገኝ *ሥራ* ላይ ይሠማራሉ:: እንግዲህ እስተዋይ እማካሪ የወጣቶችን እምቅ ችሎታ በመገንዘብና በተገቢው ሁኔታ በመጠቀም፣ ሕይወታቸው በተለያዩ ውጣ ውረዶች ሳይቆላስል ወደ ጎልማሳነት ሕይወት እንዲሸጋገሩ ሁኔታዎችን *ያመቻችላቸዋል*::

ወጣቶች ራእይ ካላቸው *ራዕያቸውን* እውን ለማድረግ የሚያስችላቸው ብዙ ዕድል ይኖራቸዋል:: የማማከር አገልግሎቱ ይህን ራእያቸውን እንዴት ወደ ተግባር መለወጥ እንደሚችሉ ያግዛቸዋል:: ወጣቶች ወደ ጎልማሳነት ሕይወት በደስታና በስኬት ለመሸጋገር በጊዜው መከፈል የሚገባቸውን ዋጋ መክፈላቸው የግድ ነው:: ዋጋ ሳይከፈልበት መልካም ውጤት አይገኝም:: በድካም ሳይዘራ ፍሬውን በደስታ ማጨድ በለማይቻል ከችሎታቸው አንጻር በትጋት መሥራት ይጠበቅባቸዋል:: እንግዲህ ከዚህ አንጻር ራእይ የሌላቸው ራእይ እንዲኖራቸው እንዲሁም ራእይ ያላቸው ደግሞ እንዴት የተለያዩ መሰናክሎችን አልፈው ወደ ግባቸው መድረስ እንደሚችሉ አስፈላጊውን እገዛ ከማማከር አገልግሎት ያገኛሉ::

*የወጣትነት ጊዜ ነጻነት የሚፈለግበት ወቅት ነው*

በወጣትነት ዕድሜ ነጻነት ለማግኘት ትግል ይደረጋል:: ወጣቶች እንደ ልጅነት ወቅት ሙሉ በሙሉ በወላጆቻቸው መመራትን አይፈልጉም:: ከወላጆቻቸው ቁጥጥር ወጥተው በራሳቸው ራሳቸውን መምራት ከመፈለጋቸው የተነሣ ወላጆች ተገቢውን *የመልቀቅ ሥራ* ካላደረጉ አሳስፈላጊ ነገሮች ይከሰታሉ:: ወጣቶች ነጻነት ቢፈልጉም ወላጆቻቸው እያስፈልጉአቸውም ማለት አይደለም:: የወላጆች የቅርብ ክትትልና እገዛ በጣም አስፈላጊ ነው:: ወጣቶች በአብዛኛው ከቤት ውጭ ስለሚያዘወትሩ በሥነልቦናቸውና በማህበራዊ ሕይወታቸው ከቤተሰብ ጋር ያለውን ግንኙነት ያላሉትና ከውጭ ጋር የጀመሩትን ኅብረት ያጠብቃሉ:: ለራሳቸው ሕይወት ኃላፊነት መውሰድን ይለማመዳሉ:: ስለዚህ ወላጆች በቅርብ ርቀት ሆነው ቢከታተሏቸው እንጂ እንደ ልጅነት ዘመናቸው *ቢቆጣጠሩአቸው* ለጎልማሳነት ሕይወት እያዘጋጇቸው አይደለም::

ወጣቶች የጎልማሳነትን ኃላፊነት ለመቀበል ሲሉ በልጅነት ወቅት በወላጆቻቸው ላይ የነበራቸውን ጎይነት መደገፍ ይተዋሉ፣ በወላጅ ላይ መጣበቅን በማላላት ከአቻዎቻቸው ጋር ወዳጅነትን በመፍጠር ራሳቸውን መምራት ይቀጥላሉ:: ወጣቶች ከወላጆቻቸው ጉያ ወጥተው ራሳቸው ወላጆች ለመሆን ይዘጋጃሉ:: ከወላጅ ቁጥጥር ሥር መውጣት የሚለው ሐሳብ ወላጆችና ወጣቶች ተስማምተው በመካከላቸው ያለውን ወሰን ማበጀት ማለት ነው:: ወጣቶቹ የሚያስቡትን ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ፣



ለሥራቸው፣ ለስሜታቸው፣ ለማህበራዊ ግንኙነቶቻቸውና ለሥነምግባራዊ ሕይወታቸው ውሳኔዎችን በራሳቸው እንዲወስኑ ማድረግ ማለት ነው:: ለሚመጣው ውጤት ተጠያቂዎች መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ማለት ነው:: ነጻ መውጣት ማለት ወላጆችን እምቢ ብሎ እንደ ግል ምኞት መኖር ማለት አይደለም:: የወላጆችን ምክር ማዳመጥን ችላ ማለትም አይደለም፤ ነገር ግን ሁለቱ ወገን ተስማምቶ ሕይወት በራስ ለመምራት ኃላፊነት በመውሰድ *ቤት መውጣት* እንደ ማለት ነው::

ልጅ ወጣት በመሆኑ ከአባትና ከእናቱ ጋር ያለው የወላጅነትና ልጅነት ግንኙነትን አያቋርጥም:: ልጅ መሆን በዕድሜ የሚሻር አይደለም:: ወጣት ሆነ ጎልማሳ ቢሆን ለወላጆቹ ልጅ ነው:: ስለዚህ ወጣቶች በማንኛውም የዕድሜ፣ የትምህርት፣ የሥራ፣ የክብር ደረጃ ላይ ቢሆኑ ለአባትና ለእናት የሚገባቸውን አክብሮት መስጠት አለባቸው:: ወላጆችን ማክበር ማለትለእነርሱ የሚገባቸውን ዋጋ መስጠት፣ መንከባከብ፣ ተገቢ ሥፍራን መስጠትና ሲናገሩ ማዳመጥን እንጂ እነርሱ ለሚናገሩት ለማንኛውም ነገር ሁሉ እሺ እያሉ መታዘዝ ማለት አይደለም:: እምቢ ሲባልም አክብሮትን በሚያሳይ አቀራረብ ማድረግ ግንኙነቱ ጤናማ እንዲሆን ያደርጋል::

ወጣቶች ወደ ጎልማሳነት ሕይወት ለመሸጋገር ኃላፊነት እንዲወስዱ በሚደረገው ሂደት ሁለት ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ:: አንዱ ችግር ከቤተሰብ በኩል የሚታይ ሲሆን ሌላው ከራሳቸው ከወጣቶች አንጻር የሚፈጠር ነው:: አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸው ወጣቶች ቢሆኑም ከቤታቸው እንዲወጡ አይፈልጉም:: ወላጆች ለወጣት ልጆቻቸው ነጻነት በመስጠት ራሳቸውን ችለው እንዳይወጡ የሚፈልጉበት ምክንያቶች የተለያዩ ናቸው::

የመጀመሪያው ምክንያት፣ ልጆቹ ወጣቶች ቢሆኑም በወላጆቻቸው እይታ አሁንም ልጆች ናቸው መባልና በራሳቸው ቢሄዱ ይጎዳሉ ብሎ ማሰብ ነው:: በልጅነት ወቅት የሚያደርጉላቸውን ጥንቃቄዎች ጎልማሳ ከሆኑ በኋላም አያቋርጡም:: ወላጆች ወጣት ልጆቻቸው የእነርሱን ምክር ተቀብለው እነርሱ ባሉት መስመር ብቻ እንዲሄዱ ይፈልጋሉ:: የወላጆች ሐሳብ ከዓላማ አንጻር መልካም ቢሆንም ከጥቅም አንጻር ግን ወጣቶች ኃላፊነት ተለምቶአቸው በእግራቸው እንዳይቆሙ የሚያደርግ ሥርዓት ነው:: ከዕድሜውም አንጻር ወጣቶች ነጻነት የሚፈልጉ በመሆናቸው ከወላጆች ጋር ተገቢ ያልሆነ ግብግብ እንዲፈጥር ያደርጋል:: በሰላም ባይቻል በዓመጽ ከቤት መውጣትን ያስከትላል:: ወጣቶች ሁልጊዜ ከወላጆቻቸው ጋር መኖር ስለማይገባቸውና የሚያዋጣው በጉያ ሥር መሸሸግ ሳይሆን በዓለም ውስጥ በራሳቸው ኃላፊነት ወስደው መኖር እንዲችሉ አስፈላጊውን ትጥቅ ለጥቶ መሸኘት ነው::

ሁለተኛው ምክንያት፣ አንዳንድ ወላጆች ወጣት ልጆቻቸው የእነርሱ ተንከባካቢ ሆነው እንዲኖሩ መፈለግ ነው:: ወላጆች በሕይወታቸው ማግኘት ያልቻሉትን የግንኙነት እርካታ ከልጆቻቸው ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት ወጣቶቹ ቤታቸውን ለቅቀው በመውጣት የራሳቸውን ሕይወት እንዲመሩ

አይፈቅዱም:: የሕይወታቸውን ባዶነት የሚሞሉት ልጆቻቸው ይሆኑና እነርሱ ከወጡ ባዶነታቸው ተመልሶ ስለሚመጣባቸው ለመልቀቅ ይፈራሉ:: ስለዚህ በለስለስ አቀራረብ «ያለ አንተ/ያለ አንቺ/ ምን አለኝ?»[1] «እጠገቤ ሆነህ ብታገለግለኝ ትባረካለህ» «እኔ ከአንቺ ተለይቼ የምኖር አይመስለኝም» እያሉ በወጣት ልጆቻቸው ላይ የሥነልቡና ጫና ያሳድራሉ:: ከዚያም፣ ወጣቶቹ ሕይወታቸውን በራሳቸው መምራት፣ ትዳር መመሥረት እና ከቤተሰብ ርቀው መማር ወይም መሥራትን ትተው የወላጆቻቸው አገልጋዮች ይሆናሉ:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ ወላጆቻቸው (አባት ወይም እናት ወይም ሁለቱ) በልጆቻቸው ላይ የፈጸሙትን በደል የሚያስተውሉት ብዙ ዕድሎች ካመለጡአቸው በኋላ ይሆናል::

አንዳንድ ወጣቶችም ከወላጆቻቸው ቤት እንዳይወጡ በመከልከል ብቻ ሳይሆን ራሳቸው ከወላጆቻቸው ጉያና ጥበቃ ሥር ወጥተው በራሳቸው ሕይወታቸውን መምራትን አይፈልጉም:: በቤተሰብ ላይ ጥገኛ ሆኖ መኖርን እንደ አንድ የሕይወት ዘይቤ በመቁጠር እንደ ልጅነታቸው ሁኔታ ይቀጥላሉ:: ራሳቸውን ችለው መኖር የሚችሉበትም ሁኔታ ምቹ ሆኖ እያለ ከቤተሰብ ጋር መኖርን ይመርጣሉ:: ከቤተሰብ ተለይቶ ራስን ችሎ መውጣት እንደ ሞት ያስፈራቸዋል:: እንዲህ ዓይነት ችግር ያለባቸው ወጣቶች፣ ወላጅ ቀስ በቀስ በመምራት ራሳቸውን እንዲችሉ መርዳት ይጠበቅበታል:: የወጣቶች አማካሪ ደግሞ የችግሩ መንስኤ የሆኑትን ነገሮች በመፈተሽ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል::

*በወጣትነት ወቅት የእምነት አመለካከት ይለወጣል*

ልጆች በልጅነት ወቅት ስለእምነት የነበራቸው አመለካከት ወጣት ሲሆኑ ይለወጣል:: በልጅነት ወቅት የወላጆቻቸውን እምነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይከተሉ ነበር:: ሲያድጉ ግን ቀድሞ በልጅነት የተቀበሉትን እምነት መጠየቅና መመርመር ይጀምራሉ:: ይህ ሁኔታ ሊወገዝ የሚገባው ሳይሆን የዕድገት ውጤት በመሆኑ በገንቢ ጎኑ መታየት አለበት:: የወላጆችን እምነት አስተምህሮዎችን፣ ተግባራዊ ጥቅሙን እና ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነትን ማጥናት ይፈልጋሉ::

ወጣቶች የወላጆቻቸውን እምነት እንዳይከተሉ እንቅፋት ከሚሆኑ ነገሮች አንዱ የእምነቱ ትምህርትና ተግባር አለመጣጣም ነው:: የእምነቱ ተከታዮች ትምህርቱን በሕይወታቸው በተግባር ሲኖሩበት አለማየታቸው ነው:: እንዲህ ሲሆን ወጣቶች ወላጆቻቸውን፣ የእምነቱን ተከታዮች እንዲሁም የእምነቱን አስተማሪዎች መንቀፍ ይጀምራሉ:: አልፎ አልፎ በእምነቱ ውስጥ የተሐድሶ እንቅስቃሴ እንዲጀመር ምክንያት ይሆናሉ::

ወጣቶች ለውጥ ፈላጊዎች በመሆናቸው ለብዙ ዘመናት ሰዎች ተቀብለው የኖሩትን የሃይማኖት ሕግና ሥርዓት መለወጥ ይሻሉ:: ሃይማኖት ለሥርዓት ብቻ የሚፈጸም ሳይሆን የሰዎችን የዕለት ተዕለት ችግሮችን ለመፍታት የሚያግዝ ተቋም እንዲሆን ይፈልጋሉ:: ስለዚህ የቀደመውን ሥርዓት ለውጠው ለዘመኑ ትውልድ በሚመች ሁኔታ



እንዲዋቀር ጥረት ያደርጋሉ:: ይህ አካሄድና እይታቸው ደግሞ ከቀደሙት የእምነቱ ወግ አጥባቂዎች ጋር ያጋጫቸዋል:: እንደሚፈልጉት ካልሄደላቸው በራሳቸው አዲስ እምነት ይጀምራሉ ወይም ወደ ሌላ እምነት ክፍል ይሄዳሉ:: ይህ አካሄድ ደግሞ የወላጅ እምነት ቀጣይነት እንዳይኖረው ስለሚያደርግ የቀደመውም ትውልድ ተጠቃሚ አይሆንም:: እምነቱን የሚረከብ አዲስ ትውልድ ያስፈልጋልና::

ስለዚህ ወጣቶች ስለእምነት ጥያቄ ሲያነሱ ወላጆች በፍቅርና በጥበብ ማስተናገድ ይገባቸዋል:: የእምነት ድርጅቱም መሠረታዊ የሆነውን የእምነቱን አስተምህሮ በማይነካ መንገድ ለወጣቶች በሚመች ሁኔታ ሥርዓቶችን ለመለወጥ ፈቃደኛ መሆን አለበት:: ይህ ካልሆነ የእምነቱ ክፍል የወጣቶቹን ፍላጎት የማያማላ ሆኖ ይሳላል:: በእምነቱና በወጣቱ ትውልድ መካከል አለመጣጣም ይፈጠራል:: በአያሌ አብያተ ክርስቲያናት በወላጆችና በወጣቶች መካከል ክፍተትና የልብ መራራቅ ይታያል:: ወጣቶቹ በገንቢ መስኮች ላይ ተሠማርተው ጊዜያቸውን በትርፋማ ሥራ ላይ እንዳያውሉ ጊዜያቸው በጭቅጭቅ ያልቅባቸዋል:: ስለዚህ በክርስቲያናዊ ማማከር የሚያገለግሉ አማካሪዎች ይህን ክፍተት ለመሙላት ሚዛናዊ ትምህርትና ምክር በመስጠት ማገልገል ይገባቸዋል::

ወጣቶች ወላጆቻቸው የሚከተሉት እምነት መንፈሳዊ ጥማታቸውን የማያረካ ከሆነ ወደ ሌላ እምነት ይሄዳሉ:: በተለይ ወጣቶች ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን የሚነካ ትምህርት ስለሚፈልጉ እንዲህ ዓይነት አቅርቦት ያላቸው የእምነት ክፍሎች ወጣቶቹን ይማርካሉ:: አንዳንድ ጊዜ ወጣቶች የእምነታቸውን ጥማት የሚያረካላቸው እየመሰላቸው ትምህርታቸውን በጥንቃቄ ሳያጤኑ በስህተት ትምህርት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ:: ስለዚህ አብያተ ክርስቲያናት ለወጣቶች መሠረታዊ መንፈሳዊ ጥማታቸውን በሚያረካ ደረጃ ተገቢ ትምህርት ለማቅረብ ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋቸዋል:: ወጣቶች ለትምህርቱ ይዘት እንደሚያስቡ ሁሉ ለአቀራረቡም ትኩረት ስለሚሰጡ፣ ይዘቱና አቀራረቡ ለእነርሱ የሚመጥን እና እነርሱ በሚፈልጉት ሁኔታ እንዲሆን ሊታሰብበት ይገባል:: ይዘቱ ትዕዛዛዊ ሳይሆን ሕይወታቸውን ፍሬያማ በሆነ መንገድ መምራት እንዲችሉ የሚያዘጋጃቸው ቢሆን ይመረጣል:: ከዚህ አንጻር ክርስቲያናዊ አማካሪ ወጣቶች ምን ዓይነትና እንዴት መማር እንደሚፈልጉ ወጣቶችን ለሚያገለግሉ አስፈላጊውን ምክር መስጠት ይችላል::

አንዳንድ ጊዜ ወጣቶች በሌሎች የሕይወት መስኮች በሚያደርጉት ትግል ይሸነፉና የራሳቸውን ማንነት ለማግኘት ሲሉ ወደ መንፈሳዊ ነገር ዘወር ሊሉ ይችላሉ:: ለእምነቱ የተሰጡ መስለው በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ይሞክራሉ! ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሙሉ ጊዜያቸውን ለመስጠት «እግዚአብሔር ለአገልግሎት ጠርቶኛል» በማለት ሊመጡ ይችላሉ:: በመንፈሳዊነት ሽፋን ማንነትን ወይም ሥራን ለማግኘት መፈለግ ጤናማ አካሄድ ባለመሆኑ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ያሉ ወጣቶች ትክክለኛ ማንነታቸውን አግኝተው የሕይወታቸውን ራእይ በግልጽ መለየት እንዲችሉ መርዳት ያስፈልጋል:: የመንፈሳዊ አገልግሎት ጥሪ

ወጣቶችን የሚያገለግሉና የሚያማክሩ አገልጋዮች ወጣቶችን ለመርዳት ከፈለጉ ወጣቶቹ ያሉበትን ሁኔታ አውቀው ሊቀበሉአቸው ያስፈልጋል። አንዲት ወጣት ባንድ ወቅት «የወጣቶች አገልጋይ ስለወጣቶች የሚያውቀውን ተጨባጭ እውነታ መቀበል አለበት። የወጣቶችን ሐሳብና አመለካከት አክብሮና ተቀብሎ መሄድ ካልቻለ በግሉ አመለካከትና እይታ እነርሱን ማገልገልም ሆነ መጥቀም አይችልም። ስለዚህ በእነርሱ ዓውድ ውስጥ ገብቶ አለተሳሰባቸውን፣ ስሜታቸውንና ወቅታዊ ችግሮቻቸውን በቅድሚያ መገንዘብ አለበት» ያለችው ትዝ ይለኛል። ከዚህ ሐሳብ የምንረዳው ወጣቶችን ለማማከር ወጣቶቹ ያሉበትን ዓለም ማወቅና መቀበል አስፈላጊ መሆኑን ነው። ስለዚህ ወጣቶችን የሚያማክሩ ሰዎች በዚህ ቅድመ ሁኔታ ዕውቀት ራሳቸውን ማስለመድ ይጠበቅባቸዋል።

*የወጣቶችን ችግር በወጣቶቹ አይታ ማየት የሚችል መሆን አለበት*

ወጣቶች ችግሮቻቸውን ከራሳቸው እይታ የሚያይና የሚረዳን አማካሪ ይፈልጋሉ። ወጣቶች የራሳቸውን ዓለም የሚረዱት ከጎልማሶች በተለየ ሁኔታ ነው። አማካሪ የወጣቶቹን ችግር በራሱ መነጽር ሳይሆን በወጣቶቹ መነጽር በማየትና በመረዳት እነርሱን ለመርዳት ጥረት የሚያደርግ ሲሆን ወጣቶቹ ራሳቸውን ይገልጹለታል። ወጣቶች ወደ አማካሪ በሚመጡበት ጊዜ ችግሮቻቸውን በራሳቸው ቋንቋና አገላለጽ ይናገራሉ። የወጣትነት ዕድሜ ፍላጎት፣ ቋንቋ፣ ስሜትና አነጋገር ከጎልማሳ ለየት ያለ ነው። አማካሪ ጎልማሳ ከሆነ በወጣትነት መንገድ ያስፈበት ቢሆንም አሁን ባለበት ሁኔታ ችግሩ ላይገባው ይችላል። ስለዚህ በራሱ ልምድና እውቀት ሳይሆን ራሱን ወደ እነርሱ ዓለም በማውረድ፣ ሁኔታቸውን በእነርሱ አይታ ከተረዳ በኋላ፣ እነርሱን ከችግራቸው ለማውጣት ዕድል ያገኛል። አማካሪው፣ የራሱ ልምድና እውቀት የሚጠቅመው ችግራቸውን በእነርሱ እይታ ከተመለከተ በኋላ ነው።

*ወጣቶችን የሚያዳምጥ መሆን አለበት*

ወጣቶች ብዙ የሚሰብካቸውን ሳይሆን ብዙ የሚያዳምጣቸውን አማካሪ ይፈልጋሉ። ማማከር በራሱ መስበክ ወይም ማስተማር ስላልሆነ አማካሪ እንደ ሰባኪ ከሆነ ምክር ፈላጊዎችን መርዳት አይችልም። ጎልማሳ አማካሪ፣ ብዙ ልምድ ለሌላቸው ወጣቶች የሚመክረው ወይም የሚሰብከው ብዙ ቁም ነገሮች ሊኖሩት ይችላሉ ነገር ግን በማማከር አገልግሎት ለወጣቶቹ የብዙ ዓመት ልምዱን እንዲሰብካቸው ሳይሆን እነርሱን እንዲያዳምጣቸው ይፈለጋል።

የወጣቶቹን ችግሮች በሚገባ ካዳመጠ በኋላ ልምዱን በመጠቀም መልካም አቅጣጫ ሊጠቁማቸው ይችላል። ወጣቶችን «ችግርህ ምንድነው?»፣ «ይህን እንዴት መፍታት ታስባለህ?» ብሎ የሚጠይቃቸውን፣ አድምጦአቸውም ወደ ትክክለኛ መፍትሔ የሚመራቸውን እንጂ መፍትሔውን የሚነግራቸውን አማካሪ አይፈልጉም። በእነርሱ ፍጥነት



አብሮ በመጓዝ እያዳመጣቸው ቁም ነገርን ጣል እያደረገ የሚሄድ አማካሪ ተፈላጊነት አለው። ከአድማጭነት ባሕርዩም የተነሣ እነርሱን መርዳት ይችላል።

*ወጣቶች ዓውዳቸውን እንዲረዱ መምራት የሚችል መሆን አለበት*

አማካሪ፣ ወጣት ምክር ፈላጊዎች ችግሮቻቸውንና መንስኤአቸውን በበቂ ሁኔታ ከመረዳታቸው በፊት ብዙ ምክር ከመስጠት መታቀብ አስፈላጊ ነው። ወጣቶች ችግሮቻቸውንና ዓውዱን በሚገባ እንዲገነዘቡ የሚረዳቸው አማካሪ ካገኙ ለራሳቸው ችግር መፍትሔ መፈለግ ይችላሉ። ወጣቶች በራሳቸው ለሚያገኙት መፍትሔ፣ ልምድና እውቀት ያለው አማካሪ ከሚሰጣቸው ምክር የበለጠ ትርጉም ይኖራቸዋል። ስለዚህ ለወጣቶች ምክር ከመስጠት ችግራቸውንና ዓውዳቸውን በሚገባ ተረድተው ራሳቸው መፍትሔ መፈለግ እንዲችሉ መርዳት ውጤታማ ያደርጋል።

አንዳንድ ጊዜ፣ ልምድ ያለው አማካሪ፣ የወጣት ምክር ፈላጊዎችን ችግር ቶሎ ሊረዳ ይችላል። ምክር ፈላጊዎቹ ችግራቸውና መንስኤዎቹ ምን እንደሆኑ በቂ ግንዛቤ ላይኖራቸው ስለሚችል በዚህ ወቅት ቶሎ መፍትሔ ለጥቶ ከመሸኘት ይልቅ ምክር ፈላጊዎቹ ችግሮቻቸውንና መንስኤዎቹን ቆፍረው እንዲያገኙ መርዳት ያስፈልጋል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ወጣቶችን ማማከር ጊዜንና ትዕግሥትን ይጠይቃል።

*ወጣቶችን አንደ ልጆች አሳንሶ የማይቆጥር መሆን አለበት*

ወጣቶች ሲጋ ጎልማሶች እንጂ ልጆች እንደሆኑ መቆጠርን አይፈልጉም። በእርግጥ ጥቂት የልጅነት እርሾ ቢኖርባቸውም ከልጅነት ወቅት አልፈዋል። ወጣቶች እንደ ማንኛውም ጎልማሳ በራሳቸው የመወሰን ሙሉ ነጻነት ስላላቸው ሰዎች ሁሉ እንደ ሙሉ ሰው እንዲቆጥሩአቸው ይሻሉ። ስለዚህ የወጣቶች አማካሪ፣ ወጣቶች ጎልማሶች ወደ መሆን እያደጉና በራሳቸው የመወሰን ነጻነት ያላቸው እንደሆኑ የሚረዳ መሆን አለበት። በዚህ ሁኔታ የሚቀበልና መብታቸውን የሚያከብር ከእነርሱ ጋር ሆኖ ማማከር ይችላል።

*ወጣቶችን በልዩነታቸው የሚያከብራቸው መሆን አለበት*

ወጣቶች አጠቃላይ የሆነ የጋራ ባሕርይ እንዳላቸው ሁሉ አያንዳንዱን ወጣት ከሌላው ልዩ የሚያደርጉ ባሕርያቶች አሉ። አማካሪ፣ ለጋራ ፍላጎቶቻቸው/ባሕሪያት/ ብቻ ሳይሆን ለግል ፍላጎቶቻቸውም ትኩረት የሚሰጥ ሊሆን ይገባል። የወጣትነት ዕድሜ የምኞትና የትልልቅ ራእዮች ወቅት ነው። አብዛኛዎቹ ወጣቶች ራእይ ቢኖራቸውም ከተጨባጭ እውነታቸው ጋር የተያያዘ አይደለም። ስለዚህ ወጣቶች ራእያቸውን ከእውቀታቸውና በአካባቢያቸው ከሚገኘው ሀብት ጋር በማቀናጀት ማስተካከልና መሥራት እንዲችሉ ለመርዳት የምክር ፈላጊውን የግልና ዓውዳዊ ልዩነት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

ወጣቶች ለወደፊት ያላቸው ትልልቅ ሕልሞችና መልካም ተስፋዎች ለማማከር አገልግሎት በር ከፋቾች ናቸው። አማካሪው፣ ወጣቶቹ እነዚህን ሕልሞች ይዘው መቀመጣቸው ብቻ በቂ አለመሆኑን በማሳየት፣ ምን መሥራትና መሆን እንደሚገባቸው ለመጠቆም ዕድል ያገኛል። በወጣትነት ዘመን የተረገዘው ሕልም በጎልማሳነት ጊዜ ይወለዳል።

ወጣቶች በወጣትነት ዕድሜያቸው ተመሳሳይ ባሕርያት ቢኖራቸውም ከተለያየ ቤተሰብ ሁኔታ ስለሚመጡ በአስተዳደጋቸው፣ በችሎታቸው፣ በፍላጎታቸው፣ በራእያቸው፣ በልምምዳቸውና በሌሎችም ጉዳዮች ይለያያሉ። ስለዚህ ወጣቶችን ሁሉ በአንድ ዓይነት መልክ መመልከት አስፈላጊ የሚሆንበት ሁኔታ ቢኖርም በማማከር ጊዜ ግን ልዩነታቸውን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለመርዳት መሞከር ፍሬያማነት ይኖረዋል።

እንግዲህ ወጣቶችን ማማከር ዋጋ የሚያስከፍል አገልግሎት ቢሆንም ከረጅም ጊዜ በኋላ የሚታጨድ መልካም ብድራት አለው። ወጣቶችን በማማከር የሚያገለግሉ አማካሪዎች የወጣቶችን የዕድሜ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ ራሳቸውን በወጣቶች ዐውድ ውስጥ በመክተት ያለብዙ መከራ ወደ ጎልማሳነት ሕይወት እንዲሸጋገሩ በማድረግ የበኩላቸውን ድርሻ መጫወት ይችላሉ።

በሚቀጥለው ምዕራፍ የጋብቻ ችግር ያለባቸውን ባለትዳሮችን ስለማማከር እንመለከታለን። ጋብቻ መልካም እንዲሆንና ባልና ሚስት በደስታና በእርካታ አብረው እንዲኖሩ፣ ችግር ሲያጋጥማቸውም ገንቢ በሆነ መንገድ ችግሩን መፍታት እንዲችሉ የማማከር አገልግሎት ከፍ ያለ ጠቀሜታ ይሰጣል። አማካሪ፣ ችግር ያለባቸውን ባለትዳሮች ለማማከር፣ የጋብቻ ችግሮችንና መንስኤዎቻቸውን ማወቅ እና እንዴት ማማከር እንደሚችል በቂ እውቀት ሊኖረው ያስፈልጋል። በምዕራፉ ውስጥ እነዚህንና የመሳሰሉ ሁኔታዎችን በሰፋት እንመለከታለን።



## ምዕራፍ 7

## የጋብቻ ችግሮችን ማማከር

ጋብቻ የአንድ ወንድና የአንዲት ሴት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የዕድሜ ልክ የቃል ኪዳን ጥምረት ነው። አንድ ወንድና አንዲት ሴት ሕጋዊ በሆነ ሁኔታ የጋብቻ ቃልኪዳን ከፈጸሙበት ጊዜ ጀምሮ ባልና ሚስት ይባላሉ። ባልና ሚስት ሆኑ ማለት ሁለቱም የተናጠል ኑሮአቸውን፣ ወዳጆቻቸውንና ወላጆቻቸውን ትተው ተጣበቁ ከዚያም አንድ ሥጋ ሆኑ ማለት ነው። የትዳር ሕይወት የዕድሜ ልክ ጥምረት በመሆኑ ደስተኛና እርካታ ያለበት እንዲሆን ይፈለጋል። ማንም ጋብቻን ሲመሠርት በግሉ በተናጠል ከሚኖረው ሕይወት የተሻለ ምቹና መልካም ሕይወት ለመኖር አስቦ ነው። ማንም ለጭቅጭቅና ለመለያየት ፈልጎ ቢጋብቻ አይጣመርም።

እያንዳንዱ ተጋቢ ለጋብቻ ያለው ዓላማ መልካም ከሆነ ጋብቻ ምቹ ሥፍራ እንዲሆን ተገቢውን ሥራ መሥራት አለበት። በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ብዙ ውጣ ውረዶች ይኖራሉ። የመጠንና የዓይነት ልዩነት ካልሆነ በስተቀር ችግር (ግጭት) የሌለበት ጋብቻ በዚህ ዓለም አልተመሠረተም፣ ሊመሠረትም አይችልም። ሆኖም ሁሉም ጋብቻ በግጭት ምክንያት አይፈርስም። አንዳንዶች ግጭትን በዘዴ በመያዝና ገንቢ በሆነ መንገድ በመፍታት ማግኘት ከጋብቻ የሚገኘውን ደስታና ሰላም እያገኙ ይኖራሉ። አንዳንዶች ደግሞ የጋብቻ ዘመናቸውን በጭቅጭቅ ይጨርሳሉ። ሌሎች ደግሞ ችግራቸውን መፍታት ባለመቻላቸው ምክንያት ጋብቻቸውን ያፈርሳሉ።

ባልና ሚስት በጋብቻ ጉዞአቸው ችግር ሊያጋጥማቸው ብቻ ሳይሆን ከሚኖሩት በላይ ደስተኛ ሕይወት ለመኖር ከፈለጉ የጋብቻ ማማከር አገልግሎትን ሊያገኙ ይገባል፤ በዚህ አገልግሎት ችግሮቻቸውን መፍታትና የተሻለ ግንኙነት ሲያዳብሩ ይችላሉ። የጋብቻ ማማከር አገልግሎት ውጥረት በሰፈነበት ጋብቻ ውስጥ መሠረታዊ የግንኙነት ዘዴዎችን በመጠቀም ገንቢ ለውጦችን ለማምጣት የሚረዳ ሙያዊ እገዛ ነው። የአገልግሎቱ ዓላማ ባልና ሚስት አንዱ ለሌላው በመኖር ደስታና ሰላም የሰፈነበት የጋብቻ ሕይወት እንዲኖሩ መርዳት ነው። የጋብቻ ችግሮችን ለማማከር የሚያግዙ ጠቃሚ አካሄዶች አሉ።

### *7.1. የጋብቻ ችግሮችን ለይቶ ማውጣት*

የጋብቻ ጉዳይን እንዴት እንደምናማክር ከማብራራት በፊት ዋና ዋና የሚባሉትን በጋብቻ ውስጥ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለይቶ ማወቅ ጠቃሚ ነው። ስለሆነም በአብዛኛው በዓውዳችን የሚታዩትን እነዚህን የጋብቻ ችግሮችና መንስኤዎች ምን ምን እንደሆኑ በዚህ ክፍል እንመለከታለን።

*የፍልቀ-ስሜት ችግሮች*

የፍልቀ-ስሜት ችግሮች ከባልና ሚስት ስሜት ጋር የተያያዙ ችግሮች ናቸው። አንድ ወንድና አንዲት ሴት በጋብቻ ከተጣመሩ በኋላ አስቀድሞ በመካከላቸው የነበረው የስሜት መንተክተክ ወይም የፍቅር ግለት ይቀንሳል። በወግ በማዕረግ ሠርገው፣ የፍቅር ቃል ኪዳን ገብተው ከተጋቡ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ እውነተኛው የጋብቻ ሕይወት ሲጀመር ቀድሞ የነበረው የፍቅር ስሜት ግለት ቀስ በቀስ ይቀንሳል። ባል እንደ ቀድሞው «አበድኩልሽ፣ ሞትኩልሽ» ማለቱን ይቀንሳል። «እወድሻለሁ» ማለትንም ሲያቆም ይችላል። ሚስትም እንዲሁ። ከዚህም የተነሣ በመካከላቸው የነበረው የቀድሞ ፍቅር እንደጠፋ በማሰብ ግጭት ሲጀመር ይችላል።

ብዙ ባሎችና ሚስቶች በእውነተኛ ፍቅርና በአፍላ ፍቅር መካከል ያለውን ልዩነት በትክክል ባለማስተዋላቸው በዚህ ጉዳይ ግራ ይጋባሉ። ፍቅር የፍልቀ-ስሜት አንዱ ክፍል ነው። እውነተኛው በቃላትና በተግባር ይገለጻል። አፍላ ፍቅር ግን በአብዛኛው ራስ ወዳድነት ያለበትና በስሜት ጣሪያ ላይ የደረሰ፣ ዘላቂነት የሌለው ፍቅር ነው። የአፍላ ፍቅር ስሜት አስደናቂና ልብን የሚያስፈነድቅ፣ ዘወትር የገነት ሕይወት የሚመስል ሕይወት ውስጥ ለማስገባት ጥረት የሚያደርግ ነው፣ እውነተኛ ፍቅር ግን በእርጋታ የተሞላ ሲሆን ባልና ሚስት አንዱ ሌላውን በመርዳት፣ ይቅር በመባባል፣ አንዱ የሌላውን ጉድለት በመሙላትና በማስገን ይገለጻል። በመጀመሪያዎቹ የጋብቻ ሳምንታት ወይም ወራት ከፍተኛ የፍቅር ስሜት ግለት ይኖራል። ይህ በጋብቻ የሕይወት ዘመንም አልፎ አልፎ ሲከሰት ይችላል። ብቅ ጥልቅ የሚል እንጂ ዘወትር የሚኖር አይደለም።

ጋብቻን ክፉኛ ሊጎዳና ሊያበላሽ የሚችለው የፍቅር ስሜት ግለት መቀነስ ሳይሆን የእውነተኛው ፍቅር ከጋብቻ ሕይወት መጥፋት ነው። አንዳንድ ጊዜ የፍቅር ስሜት ግለት መቀነስ የእውነተኛው ፍቅር መቀነስ ምልክት ይሆናል። ሁለቱም ፍቅራቸውን በተገቢው መንገድ እየገለጹ ካላሳደጉ በስተቀር ስሜቱ ሲጠፋ መፈቃቀርን በተግባር መግለጽም ይጠፋል። እርስ በርስ ሲነቃቀፉና ሲሰዳደቡ እንዲሁም የኃይል ጥቃት ሲኖር ፍቅራቸው እየከሰመ ይሄዳል። ፍቅር፣ እንደ ችግኝ እንክብካቤ ካላገኘ ይቀጭጫል ወይም ይደርቃል። በጋብቻ ውስጥ እውነተኛ ፍቅር ከጠፋ፣ ፍቅርን የተራበው ወገን ፍቅርን ፍለጋ ከጋብቻ ውጭ ይሄዳል።

የባል ፍቅር ሲቀዘቅዝ፣ ሚስት በምናቧ ወደ ኋላ ትሄድና ያኔ ይወዳትና ፍቅሩንም ይገልጽላት በነበረ ጊዜ የነበራትን ደስታና እርካታ መናፈቅ ትጀምራለች። በዚህ ብቻ ሳታበቃ ይህን አግኝታ ያጣችውን የፍቅር እርካታ በእጇ ሊያስገባላት የሚችል ሌላ ሰው ትፈልጋለች። በፍለጋዋ በእንደበቱ የሚያስብላትና የሚጠነቀቅላት የሚመስል ሰው ሲያጋጥማት እምቢ ብላ ማለፍ ያዳግታታል። ከባልዋ ያላገኘችውን ደስታና እርካታ ለማግኘት ስትል ከጋብቻ ውጭ ወሲብን ለመፈጸም ትደፍራለች። ይህ ደግሞ የእርሷን በተለይ የጋብቻ ሕይወቷን ክፉኛ ይጎዳል። ባልም እንዲሁ ቢያደርግ ውጤቱ



ተመሳሳይ ነው። በጋብቻ ውስጥ የፍቅር እርካታ ያላገኘው ወገን በሐሳብ ወይም በድርጊት ወደ ውጭ መውጣቱ የታወቀ ነው።

ስለዚህ በጋብቻ ግንኙነታቸው ውስጥ እውነተኛውን ፍቅር መለማመድ ወይም ፍቅራቸውን ማሳደግ ያልቻሉ ባልና ሚስት ወደ ጋብቻ አማካሪ ቢሄዱ መፍትሔ ያገኛሉ። በራሳቸው ዓውድ ፍቅራቸውን እንዴት ማሳደግ እንደሚችሉ ጥበብን ይማራሉ።

*የወሲብ ግንኙነት ችግሮች*[2]

በዚህ ዘመን፣ የመገናኛ ብዙኃን ስለወሲብ ብዙ ያልተቀደሱ ሐሳቦችንና ድርጊቶችን ያቀርባሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፣ ወሲብ ለሰው ልጆች መልካም ሆኖ እንደተሰጠና መፈጸም ያለበትም በጋብቻ ውስጥ ብቻ መሆኑን ያስተምራል። በጋብቻ የተጣመሩ ባልና ሚስት በወሲብ ግንኙነት ተገቢውን እርካታ ማግኘት ይገባቸዋል። ነገር ግን ብዙዎች በወሲብ ግንኙነት ደስተኞች አለመሆናቸው ችግሩ በስፋት መኖሩን ያመለክታል። ስለወሲብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንጻር የሚከተሉትን ሐሳቦች መናገር ይቻላል:-

- √ ባልና ሚስት የወሲብ ፍላጎት አላቸው። ሁለቱም ይህ ፍላጎት እንዲኖራቸው ተደርገው የተፈጠሩ ናቸው (ዘፍ1:26-27)
- √ ባልና ሚስት አንዱ የሌላውን ፍላጎት ማርካት ይገባቸዋል እንጂ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ማሰብ የለባቸውም። አንዱ ለሌላው ሰውነቱን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን ይጠበቅበታል (ዘፍ3:16፣ 1ቆሮ7:3)
- √ ባልና ሚስት ተስማምተው ካልሆነ በስተቀር አንዱ ራሱን ለሌላው ቢከለክል ለፈተና ያጋልጣቸዋል (1ቆሮ7:5)
- √ በጋብቻ ውስጥ ባልና ሚስት የወሲብ እርካታ እንዲያገኙ አንዱ ሌላውን እንዴት ደስ ማሰኘት እንደሚገባው ሊያስብ ይገባል (1ቆሮ7:33-34)
- √ ማንኛውም ከጋብቻ ውጭ የሚደረግ ወሲብ ኃጢአት በመሆኑ ባልና ሚስት ለእርስ በርሳቸው ታማኞች ሆነው መኖር ይጠበቅባቸዋል (ዕብ13:4)። ዝሙት፣ የሚፈለገውን እርካታና ደስታ አይሰጥም (ምሳ5:15፣ 18-21)
- √ የወሲብ ግንኙነት ዘር ለመተካትም ነው (ዘፍ1:28)

አብዛኛውን ጊዜ በባልና በሚስት መካከል የወሲብ ችግር የሚጀምረው በሠርጋቸው ምሽት የመጀመሪያውን የወሲብ ግንኙነት ሲፈጽሙ ነው። ችግሩ ካለማወቅ ሲሆን ስለሚችል ማስተካከል ይቻላል። አስፈላጊው የቅድመ ወሲብ ዝግጅት ሳይደረግ ወሲብ ለመፈጸም የሚደረገው ጥረት ሴቷን ሲያሳምማት ወይም የሚፈለገውን እርካታ እንዳታገኝ ሲያደርጋት

---

[2] በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ቢያስፈልግዎ *የጋብቻ ችግሮችና የመፍትሔ ቁልፎች* በከበደ በከሬ፣ የሚለውን መጽሐፍ ማንበብ ይችላሉ።

ይችላል። አንዳንድ ጊዜም ወንዶች ከሚፈጠርባቸው ድንጋጤ ወይም ፍርሃት የተነሣ ግንኙነት ማድረግ ሲያቅታቸው ይችላል።

በባልና ሚስት መካከል ከሚፈጠረው የወሲብ ችግር ሌላው፣ አንዱ ሌላውን የያለማርካት ችግር ነው። በግንኙነት ጊዜ ሁለቱም ተመጣጣኝ እርካታ ሊያገኙ ይገባል፣ ይህን በሚያጡበት ወቅት የሐዘንና የብቸኝነት ስሜት ይሰማቸዋል። የወሲብ እርካታ ያላገኘው ወገን በዚህ ችግር ይጎዳል። የወሲብ ግንኙነት በአንድ ጊዜ የሚፈጸም ተግባር ሳይሆን ሂደት ነው። ባልና ሚስት የመጨረሻ የእርካታ ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት በተለያዩ የፍቅር ጨዋታዎች ውስጥ ማለፍ ይጠበቅባቸዋል። የቃላት ጨዋታ ሲለዋወጡ፣ አንድ ላይ ሆነው አካላቸውን ሲተሻሹ፣ በፍቅር ሲጎሻሸሙ እና ሲሳሳሙ ይችላሉ። የወንድ የወሲብ ስሜት ቶሎ የሚቀሰቀስና ወደ እርካታ የሚሮጥ መሆኑ የተፈጥሮ ጉዳይ ነው፣ የሴት ግን ረዘም ላለ ጊዜ የፍቅር ጨዋታን በማድረግ ማዘጋጀትን ይፈልጋል። ባል ለሚስቱ ፍላጎት ተገቢውን ትኩረት የማይሰጥ ከሆነ እርስዋ ከመዘጋጀትዋ በፊት ወሲብ ሲፈጽምባት ይችላል።

የወሲብ ግንኙነት እውቀት፣ ቅንጅት፣ ጥበብ፣ ትዕግስትና ልምድን ይጠይቃል። ቻልተኝነት፣ ራስ ወዳድነትና ፍርሃት በሂደት የሚፈጸመውን የግንኙነት እርካታን ያውኩታል። በወሲብ ግንኙነት ጊዜ ተገቢው ቅንጅት ካልተደረገ በስተቀር ባል ቶሎ ረክቶ መቀዝቀዝ ሲጀምር ሚስት ገና በመሞቅ ላይ ልትሆን ትችላለች። ሚስት የመጨረሻው የፍቅር ስሜት ግለት ወይም ጡዘት ላይ መድረስ ካልቻለች ባልዋ እንደማይወዳትና ሁለቱ እንደማይጣጣሙ ይሰማታል። ይህ ደግሞ የፍቅር ግንኙነትዋን እንድታላላና ትዳርዋን ለማፍረስ ምክንያት ሲሆን ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ስለወሲብ ግንኙነት ያላት አመለካከት የተበላሸ ይሆናል። ተገቢ ያልሆነ ልምምድ ወደ ተሳሳተ አመለካከት ሲያመራ ይችላል። ሚስት፣ ባልዋ በተደጋጋሚ ለእርስዋ የወሲብ ስሜት ተገቢውን አጸፋ የማይሰጥና በግንኙነት ጊዜም የማያረካት ከሆነች ከእርሱ ጋር ወሲብ ላለመፈጸም የተለያዩ ምክንያቶችን ታቀርባለች። በዚህ ጉዳይ ላይ በግልጽነት ለመወያየት ድፍረት ስለማይኖር እውነቱን አትነግረውም። በዚህ ምክንያት በጋብቻ ውስጥ ንትርክና ጭቅጭቅ ይፈጠራል።

ስለዚህ እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ወርቃማውን ትዕዛዝ ማክበር ጠቃሚ ነው። ባልና ሚስት ለግላቸው የሚፈልጉትን ለትዳር ጓደኛቸው መስጠትን መለማመድ አለባቸው። አንዱ ለሌላው ማሰብ በሚጀምሩበት ጊዜ በመካከላቸው ሁለቱንም በተመጣጣኝ ሁኔታ ሊያረካ የሚችል የወሲብ ግንኙነት ሊኖር ይችላል።

በጋብቻ ሕይወት አንዱ ለሌላው ታማኝ በማይሆንበት ጊዜ የተለያዩ መንፈሳዊ፣ ማህበራዊና አካላዊ ችግሮች ይከሰታሉ። ለጋብቻ ታማኝ አለመሆን በመጀመሪያ እግዚአብሔርን ያሳዝናል። የተቀደሰውን ጋብቻ ማርከስ ኃጢአት ነው (1ቆሮ6:18፣ ዕብ13:4)። ለእርስ በርስ ታማኝ አለመሆን ቅንዓት፣ ጥላቻና አለመተማመንን ይፈጥራል። ከጋብቻ ውጭ የወሲብ እርካታ የሚያገኝ ወገን ካለ ታማኝ የሆነው ወገን ደግሞ ፍላጎቱ



ሳይሟላለት ይቀራል። ከጋብቻ ውጭ ወሲብ የሚፈጽም ሰው፣ ከትዳር ጓደኛው ተገቢውን የወሲብ እርካታ ማግኘትም ሆነ መስጠት ያቅተዋል። ታማኝ ያልሆነው በወለጡ ሁኔታው «ይታወቅብኝ ይሆን?» እያለ ስለሚጨነቅ የትዳር ጓደኛውን ማርካታ ይሳነዋል። ሚስት ከጋብቻ ውጭ ወዳጅነት ከጀመረች ባልዋን መናቅ ትጀምራለች። ከወትሮዋ የተለየ ባሕርይ ታሳያለች። «አንተን ብሎ ወንድ ወይም ባል» ትላለች። በዚህ ጊዜ ያልታሰበ የትዳር ግጭት ይቀሰቀሳል።

በጋብቻ ሕይወት ለትዳር ጓደኛ ታማኝ አለመሆን ሌሎች ተጨማሪ ኃጢአቶችን ያስከትላል። ታማኝነቱን ያጎደለው ወገን ከመዋሸት፣ ከማታለል፣ ቤተሰብን ትቶ ከመሄድ ወይም ከመግደል አይመለስም። ከጋብቻ ውጭ የወሲብ ግንኙነት የፈጸመው ንጉሡ ዳዊት የራሱን ኃጢአት ለመደበቅ ብሎ ብዙ ተከታታይ የሆኑ ኃጢአቶችን ፈጸመ። ዋሸ፣ አታለለ፣ በመጨረሻም ለትዳሩና ለአገሩ ታማኝ የነበረውን የቤርሳቤህን ባል አስገደለ (2ሳሙ11:1-24)። የዚህ ኃጢአት ውጤት በዳዊት ቤተሰብ ላይ ያመጣው መዘዝ ክፉ ነበር። አምኖን በእህቱ ትዕማር ላይ ተገቢ ያልሆነ የወሲብ ጥቃት ፈጸመ (2ሳሙ13) ከዚህም በመነሳት የትዕማር ወንድም አምኖንን አስገደለ። በንጉሡ ቤተሰብ ሌሎች ችግሮችም ተከሰቱ።

ወዶ አንዱ ለሌላው ታማኝ ካለልሆነ አንድነቱ ይላላና የቃል ኪዳን ክሩን ለመበጠስ ይዳርጋል። ጋብቻው በፍች ካልፈረሰ ደግሞ ዘወትር በሚያፈስ ቤት ውስጥ እንደሚኖር ሰው በግጭት እየታመሱ ሲኖሩ ይችላሉ። ታማኝ ያልሆነ ወገን ወደ ትዳሩ የተለያዩ የአባለዘር በሽታዎችን ይዞ ሲመጣ ይችላል። የትዳር ጓደኛውንም የጥቃት ሰለባ ያደርጋል። ስለዚህ በጋብቻ ውስጥ የሚኖረው የወሲብ እርካታ ማጣት ችግር ከጋብቻ ውጭ ወሲብ በመፈጸም አይፈታም። ይልቅስ ውስብስብ ችግሮች ውስጥ የሚያስገባ እርምጃ ይሆናል። ስለዚህ የወሲብ አለመጣጣምን ችግር በማማከር አገልግሎት ለመፍታት እርምጃ መውሰዱ ይመከራል።

*ከገንዘብ ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ችግሮች*

በሀገራችን በተለይ በቤተክርስቲያን በገንዘብ አያያዝ በኩል ስንት ባለትዳሮች እንደሚጋጩ የተደረገ ጥናት ባይኖርም አያሌ እንደሆኑ በሥልጠናዎችና በማማከር ወቅት ከሚነሱ ውይይቶች ለማስተዋል ችያለሁ። የጋብቻ ትምህርት በተለያዩ ቦታዎች በሚሰጥበት ወቅት ወንዶችና ሴቶች ከሚያነሱአቸው ጥያቄዎችና ሁለቱም ወገኖች ለመስማማት ከሚቸገሩባቸው ጉዳዮች መካከል እንደ ዋነኛ ጉዳይ የሚጠቀሰው የገንዘብ አስተዳደር ነው። አንዳንዶች የደረሰባቸውን ይገልጻሉ፣ ሌሎች የሰሙትንና ያዩትን ታሪክ ይናገራሉ፣ በእርግጥ በዚህ በድሕረ ዘመናዊነት ወቅት በገንዘብ አያያዝ ጉዳይ እንዲህ ያለ ችግር ይከሰታል ብሎ መጠራጠር ያዳግታል። ባልና ሚስት በገንዘብ አያያዝ በሚኖራቸው ልዩነት ትዳራቸው አደጋ ላይ ሲወድቅ ይችላል ወይም በጋብቻቸው ውስጥ ሲኖራቸው የሚገባውን እርካታና ደስታ ሳይለማመዱ ሲቀሩ ይችላሉ። ስለዚህ የገንዘብ አስተዳደር ችግር ለጋብቻ ችግር መንስኤ በመሆኑ ባልና ሚስት ገንዘባቸውን

እንዴት ማስተዳደር እንደሚገባቸው መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ባደረገ ሁኔታ መምከር ጠቃሚ ይሆናል።

በገንዘብ አጠቃቀም ዙሪያ የሚነሱ ችግሮች፡-

ባልና ሚስት በገንዘብ አጠቃቀም ዙሪያ ሊወስዱአቸው የሚገባቸውን እርምጃዎች በዝርዝር ከመግለጽ አስቀድሞ በባለትዳሮቹ መካከል እየተገበረ የሚገኘውን ሁኔታ መመልከት ተገቢ ይሆናል።

*የወር ገቢን ከትዳር ጓደኛ መደበቅ፡-* አንዳንድ ባሎች የወር ደመወዛቸው ምን ያህል እንደሆነ ለሚስቶቻቸው አይገልጹም። በዓውዳችን «የወንድ ደመወዝና የሴት ዕድሜ አይጠየቅም» ይባላል። ግን ለምን? የወር ደመወዛቸውን ሲቀበሉ ለቤት ወጪ ያስፈልጋል ብለው የሚገምቱትን ያህል ጣል ያደርጉና በቀረው ገንዘብ የወደዱትን የሚያደርጉ ባሎች አሉ። ደመወዛቸውን ከሚስቶቻቸው መደበቃቸው ብዙ መልዕክት ሊኖረው ይችላል። ከእነዚህም ምክንያቶች የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው። ባሎች፣

- √ ሚስቶቻቸው የደመወዛቸውን መጠን በማወቅ እንዳይገምቷአቸው የራሳቸውን ምስጢር ለመደበቅ ሲሉ፣
- √ ሚስቶቻቸው ገንዘቡን ምን ላይ እንዳዋሉት እንዳይጠይቋአቸውና ያለምንም ተጠያቂነት ገንዘቡን እንደሚፈልጉት ለመጠቀም እንዲያመቻቸው ለማድረግ ሲሉ፣
- √ ሆን ብለው ሳይሆን በሚያዩትና በሚሰሙት እንዲህ ማድረግ የሚጠበቅባቸው እንደሆነ በማሰብ እና የሕይወት ዘይቤ እንደሆነ በመቁጠር፣
- √ ሚስቶች ሁሉን ነገር ማወቅ አይገባቸውም ስለሚባል፣
- √ ሠርተው የሚያገኙትን ገንዘብ ሚስቶች የመጋራት መብት እንዳላቸው በአለመቀበል፣
- √ ከሚስቶቻቸው መረጃውን በመደበቅ፣ እነርሱን ለመቆጣጠር በማሰብ ይሆናል።

አንዳንድ ባሎች የቤት ወጪ ምን ያህል እንደሆነ ከሚስቶቻቸው ጋር በመነጋገር ስለማያደርጉ የሚበቃውን ገንዘብ ለሚስቶቻቸው አይሰጡም። ከዚህም የተነሳ ሚስቶች በጣም ይቸገራሉ። ለወር «ይበቃል» ብለው ያሰቡትን ለሚስቶቻቸው ወርወር ያደርጉና በቀረው ልባቸው የፈቀደውን ነገር ያደርጉበታል። በአንድ የጋብቻ ትምህርት ወቅት አንዲት እህት «ከተጋባን 20 ዓመታችን ነው። እስካሁን ድረስ የባለቤቴ ደመወዝ ስንት እንደነበር እና አሁን ምን ያህል እንደሚያገኝ አላውቅም። እርሱ አይነግረኝም፣ እኔም አልጠይቀውም። ለወር ይበቃል ብሎ የሚያስበውን ይሰጣል። ገንዘቡ እስኪበቃ ድረስ እንጠቀምበታለን። ለቤት የሚያስፈልጉ ነገሮች ወሩ ሳይደርስ እንዳያልቁ በጣም ጭንቅ ይለኛል» ያለችው ትዝ ይለኛል።



ትንሽ ገንዘብ ብቻ ወርወር በማድረግ የቤተሰብ ኃላፊነታቸውን እንደተወጡ የሚያስቡ እነዚህ ባሎች ወደ ቤት ሲመጡ ጣፋጭና ጥሩ ምግብን ይጠብቃሉ። ትንሽ ብር ይዘው ወደ ምግብ ቤት ቢሄዱ ጣፋጭ ምግብ መብላት እንደማይችሉ ያውቃሉ። በትንሽ ብር መብላት የሚችሉት ከገንዘቡ መጠን ጋር ተመጣጣኝ ጥራት ያለውን ምግብ ብቻ ነው። የምግቡ ጥራት በጨመረ መጠን የሚከፈለውም ገንዘብ መጠን ይጨምራል። በሰላሳ ብር የሚሸጠውን ምግብ በአምስት ብር ለመብላት የሚያስቡ ሰዎች ካሉ ቀልደኞች ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ ለሚስቶቻቸው ትንሽ ገንዘብ ሰጥተው ጥሩ ምግብ የሚጠብቁ ባሎች ቀላጅ ወይም አምባገነን ናቸው። ስለዚህ ባሎች ከቤታቸው ውስጥ ያለውን ችግር ጠጋ ብለው ማየት ይገባቸዋል። ያልዘሩትን ለማጨድ እንደሚያስቡ ሰዎች ባይሆኑ የተሻለ ነው። ባሎች የጋራ የሆነውን ነገር የራሳቸው ብቻ እንደሆነ በማሰብ በወር ገቢአቸው ላይ እንደልባቸው ከማዘዝ ይልቅ ለቤተሰብ የሚያስፈልገውን በቂ ገንዘብ መመደብ ይኖርባቸዋል። ገንዘቡ እያላቸው ለሚስቶቻቸው የሚገባውን ገንዘብ ሳይሰጡ ሚስቶቻቸውን በኑሮ ጫና የሚያስጨንቁ ባሎች ሰብዓዊ ሀሲና የላቸውም፣ አዕምሮአቸውም ትክክለኛ ባልሆኑ ባሕላዊ አመለካከቶች የተሞላና ሚስቶቻቸውን የማይወዱ ናቸው። እንዲህ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ባሎች ሊለወጡ ይገባቸዋል፣ በሚስቶቻቸው ላይ እያደረሱት ላለው በደል ንስሐ ሊገቡና ይቅርታ ሊጠይቁ፣ ለወደፊቱም ደግመው ላለማድረግ የፍቅር ቃልኪዳን ሊገቡ ይገባቸዋል።

በዓውዳችን፣ በአብዛኛው ባሎች በውጭ ሥራ ተሰማርተው ገቢ የሚያስገኙ በመሆናቸው የገቢ ምንጭ ናቸው ከሚል እንጂ ገቢ ያላቸው አንዳንድ ሚስቶችም ገቢያቸውን ከባሎቻቸው አይደብቁም ለማለት አይደለም። ከቅድመ ጋብቻ ጀምረው የትዳር ጓደኞቻውን (የባላቸውን) ገቢ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው የራሳቸውን ገቢ ግን ለፈለጉበት ዓላማ እየተጠቀሙበት ለመጠየቅ የማይፈልጉ ሚስቶች አሉ። ባሎች የደመወዛቸውን መጠን ለማወቅ ሲጠይቁ «ምን አገባህ?» የተባሉበት ሁኔታ አለ። ባል ወይም ሚስት ገቢአቸውን (ደመወዛቸውን) ከትዳር ጓደኛቸው መደበቅ የሁለቱም ችግር ሊሆን ስለሚችል ሁለቱም በሚገባ ሊያስቡበት ይገባል።

*ገቢን በእኩል ደረጃ አለመጠቀም፡-* አንዳንድ ባሎችና ሚስቶች ሁለቱም ገቢ ሲኖራቸው በአጠቃቀም በኩል ግን የጋራ የሆነ ዕቅድ የላቸውም። ይህ ብቻ ሳይሆን ሚስት በባል ደመወዝ ላይ የማዘዝ ሥልጣን አይታይም። ባል ግን በሚስት ደመወዝ ላይ ለማዘዝ ጥረት ያደርጋል። በአንድ ሥልጠና ላይ አንዲት እህት «እኔና ባለቤቴ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ከቤት ውጭ እንሠራለን። የእኔን ደመወዝ ለቤት ውስጥ ወጪዎች እንጠቀምበታለን። የእርሱ ደመወዝ ግን ለራሱ ነው። በእኔ ደመወዝ ላይ ሁለታችን እናዛለን፣ በእርሱ ደመወዝ ላይ ግን እኔ ማዘዝ አልችልም። እርሱ ገንዘቡን ደስ ባለኝ መንገድ ይጠቀምበታል» በማለት አምርራ ትናገር ነበር።

ባልና ሚስት በሕጋዊ መንገድ ተጋብተው በጋራ ያፈሩት ገንዘብና ንብረት የጋራ መሆኑን የማያምን ባል ቢኖር ምን ማድረግ ይገባል?

በዓውዳችን ባል የንብረት ወይም የገንዘብ አስተዳዳሪ ብቻ ሳይሆን የሚስትም የበላይ እንደሆነ መታሰብ ብቻ ሳይሆን በተግባርም እየተፈጸም ያለ ጉዳይ እንደሆነ ለማስተዋል እንችላለን። በአባቶቻችንና በእናቶቻችን ዘመን አባቶቻችን ሚስቶቻቸውን ጭምር የራሳቸው ንብረት እንደሆኑ ያስቡ ነበር። አሁንም ቢሆን የዚህ ዓይነት አመለካከት ያላቸው አንዳንድ ባሎች አይጠፉም። እንዲህ ዓይነት አመለካከት የሚንጸባረቀው ሠለጠንን (ተማርን) በሚሉ ዘንድ ጭምር ነው። እንግዲህ ሚስቶቻቸው የገዛ ንብረቶቻቸው እንደሆኑ የሚያስቡ ባሎች «በጋራ ያፈራነው ነው»፣ «ገንዘቡ የጋራ ነው»፣ «በጋራም ማስተዳደር ይገባናል» ብሎ የሚያስብ አዕምሮ የላቸውም። አዕምሮአቸው የተሞላው «ባል የገንዘብ ብቻ ሳይሆን የሚስቱም አዛዥ ነው» በሚል ሐሳብ ነው።

*ቤተሰብን በመርዳት ውሳኔ አለመስማማት፦* የባልና ሚስት ቤተሰቦች የገንዘብ እርዳታ ሲያስፈልጋቸው ተገቢውን ምላሽ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል፤ ነገር ግን ባልና ሚስት እርዳታው በምን ሁኔታ መከናወን እንደሚገባው ስምምነት አይታይባቸውም። «የሁለታችንም ቤተሰቦች የእኛን እርዳታ ይፈልጋሉ። ባለቤቴ ግን ለራሱ ቤተሰብ እንጂ ለእኔ ቤተሰብ ትኩረት አይሰጥም። የራሱን ቤተሰብ ያለ እኔ ፈቃድ ይረዳል። የእኔ ቤተሰብ ግን እንዲረዳ አሳብ ሳቀርብ «ገንዘብ የለንም» በማለት አይረዳቸውም። ውስጤ እየተቆጣና እያዘነ ቢሆንም ነገር ግን ትዳሬን አፍርሼ ልጆቼን አልበትንም ብዬ ከእርሱ ጋር እኖራለሁ» የሚሉ ሚስቶች አሉ።

የምንኖረው በአዳጊ አገር እንደ መሆኑ መጠን ብዙ ወላጆች ከልጆቻቸው ድጋፍን ይፈልጋሉ። ልጆች የራሳቸውን ትዳር ከመሠረቱ በኋላም ወላጆች ከልጆቻቸው ድጋፍ ሊፈልጉ ይችላሉ። ባልና ሚስት ከሚያገኙት ገቢ ለወላጆቻቸው እርዳታ ሲውል የሚችል ገንዘብ በየወሩ ቢቆጥቡ መልካም ነው። መረዳት ያለበት ደግሞ የባል ወይም የሚስት ወገን ብቻ ሳይሆን የሁለቱም ወገን እርዳታ ባስፈለጋቸው ጊዜ ሊታሰቡ ይገባል፤ የጋራ ቤተሰቦቻቸው ናቸውና። ሁለቱም በመስማማት መርዳት ይገባቸዋል እንጂ አንዱ የራሱን ወላጅ ብቻ በግልጽ ወይም በምስጢር የሚረዳ ከሆነ የትዳር ሕይወታቸው ይናጋል።

*ገንዘብን ከትዳር ጓደኛ መደበቅ፦* አንዳንድ ባሎች ወይም ሚስቶች ገንዘብን ከትዳር ጓደኛቸው ይደብቃሉ። እኔ ባደግኩበት አካባቢ በብዙ ባለትዳሮች ቤት የባል ሳጥን የሚባል ነበር/እስካሁንም አልተተወም። በዚህ ሳጥን ውስጥ ባል የፈለገውን ነገር በድብቅ ያስቀምጣል። ባል ሳጥኑን ይቆልፍና መክፈቻውን ራሱ ይይዛል። ማንም የቤተሰብ አባል መክፈቻውን ቢያገኝ እንኳ ይህችን ሳጥን መክፈት አይፈቀድለትም። ሚስት በዚያ ሳጥን ውስጥ ምን እንዳለ አታውቅም። በዚህ ዘመን በአብዛኛው ባል ወይም ሚስት ገንዘብን የሚደብቁት በባንክ በግላቸው የቁጠባ ሒሳብ ከፍተው በማጠራቀም ነው። ከዚህ የተነሣ አንዱ ለሌላው (ለትዳር ጓደኛው) የወር ገቢው ምን ያህል እንደሆነ በግልጽ አያሳውቅም።



አንዲት ሴት «በቅርብ ጊዜ ባለቤቴ ውጭ ሀገር ለሥራ ጉዳይ ሲሄድ የእርሱን ዶክሜንቶች ሳገላብጥ አንድ የባንክ ሂሳብ ደብተር አየሁ። ደብተሩ የራሱ ነው። በየወሩ ከእኔ ደብቆ የሚያስቀምጠው ገንዘብ ነበር። በ15 ዓመት የትዳር ሕይወታችን ውስጥ ብዙ ገንዘብ አጠራቅሟል። ይህን ሳይ ልቤ እጅግ በጣም አዘነ፣ ራሴን መቆጣጠር ተሳነኝ። ከሄደበት ሲመለስ የባንክ ደብተሩን ማየቴን አልነገርኩትም። አሁን ከእርሱ ጋር ለመኖር ያለኝ መሰጠት በጣም እየቀነሰ ነው። እርሱ እንደ ዱሮው የማላውቀው መስሎት መደበቁን ቀጥሏል ምን ባደርግ ይሻለኛል?» ያለችው በብዙ ትዳሮች ውስጥ ያለ ችግር ነው። ከትዳር ጓደኛ የሚደበቅ ምስጢር የሚባል ነገር ሊኖር አይገባም፣ ለቤተሰቡ ለአሁንም ሆነ ለወደፊት ሕይወት የሚጠቅም ነው ቢባል እንኳ መደበቅ ለትዳር መፍረስ መንስኤ ስለሚሆን መገላለጥ ይገባል።

*ገንዘብን ለግል ጥቅም ብቻ ማባከን፦* አንዳንድ ባሎች ወይም ሚስቶች የሚያገኙትን ገቢ ለቤተሰባቸው ጠቀሜታ ከማዋል ይልቅ ለግል ፍላጎታቸው ብቻ በማዋል ቤተሰባቸውን ይጎዳሉ። አንድ ጊዜ አንድ ሰው «ባለቤቴ የወር ደመወዜን ታውቃለች። ለወር ለትራንስፖርትና ለጥቃቅን ወጪዎች ከሚያስፈልገኝ ጥቂት ገንዘብ በስተቀር ሌላውን ለባለቤቴ እሰጣታለሁ። በእጄ ምንም አላስቀርም። እርስዋ ግን የተቀበለችውን ገንዘብ ለጋራ ጥቅም ከማዋል ይልቅ በየወሩ አዳዲስ ልብስ ትገዛበታለች። የምትገዛቸው የቅባት ዓይነቶች ብዙና ውድ ናቸው። እየተራብን እርስዋ ሌላ ነገር ትገዛበታለች። እኔ አዲስ ልብስ አልቀይርም። ልጆቻችን በትምህርት ቤት በመሆናቸው ዩኒፎርም ስለሚለብሱ ለጊዜው ተገላግለናል። ቢመከራት አትሰማኝም። ለሁላችን በማይጠቅም ነገር ላይ ገንዘብ ማባከንዋ እጅግ ያስቆጣኛል። አንዳንድ ጊዜ የራሴን ገንዘብ ባልሰጣትና እኔ ለቤት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ገዝቼ ባመጣ እነርሱን ወስዳ እትሸጣቸውም እያልኩኝ አስባለሁ። ምን ባደርግ ይሻለኛል?» አለ።

እንዲህ ዓይነት ታሪኮች ለታነቡ የተለያየ ሐሳብ ወደ አእምሮአችሁ ሊመጣ ይችላል። ከዚህ ምሳሌ የራሳችሁ የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ለመመልከት ዕድል እንደሚታገኙ ተስፋ አደርጋለሁ። በጋብቻ ውስጥ አንዱ ወገን መልካም ነው ብሎ ለራሱ የሚከተለው የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ሁኔታ ሌላውን የትዳር ጓደኛ እንዳይጎዳ መሆን አለበት። ካልሆነ ግን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ በጋብቻው ላይ አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ ይኖረዋል። በብዙ ጋብቻ ውስጥ፣ በባልና ሚስት መካከል፣ ገንዘብን በተመለከተ የተለያየ ችግር መኖሩን ከቀረቡት ጥቂት ምሳሌዎች መገንዘብ እንችላለን። በመሠረቱ፣ የገንዘብ አያያዝንና አጠቃቀምን በተመለከተ በብዙ ትዳሮች ውስጥ አለመስማማት ያለ ቢሆንም የችግሩ መጠን ግን ይለያያል።

የጋብቻ ኑሮ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ፣ ከገንዘብ ጋር የተቆራኘ ነው። ስለዚህ ባልና ሚስት ብዙ ጊዜያቸውን ስለ ገንዘብ በማሰብ ሊያጠፉ ይችላሉ። ገንዘብ የሚያስገኝ ሥራ በመሥራት ወይም በገንዘብ ተጠቅመው ገንዘብን ለማትረፍ ጥረት እንደሚያደርጉ ማስተዋል ይቻላል። ለጋብቻ የገንዘብ አስፈላጊነት ጥርጥር የለውም። ነገር ግን ለኑሮአቸው ምን

ያህል ገንዘብ ይበቃቸዋል? የሚለው ጥያቄ ቢነሳ ሁሉንም የሚያስማማ ምላሽ ማግኘት አስቸጋሪ ነው:: «ምን ያህል ገንዘብ ይበቃል?» የሚለው ጥያቄ መልስ እንደ አካባቢው ሁኔታና እንደ ባለትዳሮቹ ፍላጎት የተለያየ ይሆናል:: የገንዘብ በቂነት እንደ አጠቃቀም እንጂ እንደ ገቢው መብዛት ወይም ማነስ እንዳልሆነም መገንዘብ አስፈላጊ ነው::

ገንዘብ ለመልካም ጋብቻ ከሚያስፈልጉ ዋና ዋና ነገሮች መካከል አንዱ ነው:: ሆኖም የገንዘብ መኖር ብቻውን ለጋብቻ ስኬት ቀጥተኛ የሆነ ድርሻ የለውም:: ገንዘብ የጋብቻ ግንኙነትን የሚገነባ ወይም የሚያፈርስ ሊሆን ይችላል:: ውጤቱ እንደ አያያዙ ሁኔታ ነው:: የባልና የሚስት የገንዘብ አያያዝ ሁኔታ መልካም ከሆነ ግንኙነታቸው የተሻለ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል:: ሁለቱ በአያያዝ የማይስማሙ ከሆነ ግን ገንዘብ ቢኖራቸውም የአያያዝ ልዩነቱ በመካከላቸው የማያባራ ግጭት እንዲፈጠር ያደርጋል:: ስለዚህ በገንዘብ አያያዝ የአለመስማማት ችግር በጋብቻ ጉዞ የማይደርቅ ቁስል ይሆናል::

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ባልና ሚስት ምንም ገንዘብ በሌላቸው ጊዜ ተስማምተው ይኖሩና ገንዘብ ሲያገኙ ግን እንደሚጋጩ ተስተውሏል:: ኑሮአቸው ዝቅተኛ በሆነበት ወቅት በፍቅር ይኖሩና ገንዘብ አግኝተው ሲሳካላቸው በትዳራቸው ውስጥ ብጥብጥ ይፈጠራል:: በዚያም ምክንያት አንዳንድ ባሎችና ሚስቶች «ምንም ባልነበረን ጊዜ ፍቅራችን የሞቀ ነበር፣ አሁን ግን ገንዘብ መጣና ፍቅራችንን ሰረቀብን» ብለው ሲናገሩ ተደምጠዋል:: ነገር ግን በመካከላቸው ያለውን ፍቅር የሰረቀባቸው ገንዘብ ሳይሆን እነርሱ ስለገንዘብ ያላቸው አመለካከት፣ የገንዘብ አያያዛቸውና የአጠቃቀማቸው ሁኔታ ነው:: አያያዝና አጠቃቀም ካላወቁበት ገንዘብ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል::

በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ገንዘብ ማጣት ወይም ብዙ ገንዘብ ማግኘት የራሱን ተግዳሮትና ችግር ይዞ ይመጣል:: ጠቢቡ ሰለሞን፣ ደሃ ወይም ሀብታም መሆን መልካም እንዳልሆነ፣ የሰው ልጅ ለመሠረታዊ ፍላጎቱ የሚያስፈልገውን ነገር አግኝቶ ቢኖር ግን ጤናማ ሕይወት ሊኖረው እንደሚችል የተናገረውን ማስተዋል ይገባል (ምሳ30:8-9):: ባልና ሚስት ከድህነታቸው ወቅት ይልቅ ገንዘብ ሲያገኙ የሚያልፉበት የተግዳሮት መንገድ ይበዛል:: ድህነት ከባለጠግነት ይመረጣል ለማለት ሳይሆን ገንዘብ ሲመጣ የብዙ ምርጫዎች ዕድል ይዞ ስለሚመጣ ባልና ሚስት በገንዘብ አጠቃቀም ጉዳይ ላይ ክፉኛ ሲጋጩ ይችላሉ:: ታዲያ መፍትሔው ምንድነው? ቢባል «ከባለጠግነት ይልቅ ድህነት ይሻላል» አይደለም፤ ነገር ግን ገንዘብን እንዴት ማስተዳደርና መጠቀም እንደሚቻል በሁለቱም መካከል እምንታ ያለው የጋራ የሆነ ስምምነት ማዘጋጀት ነው::

የገንዘብ ጉዳይ ለምን የጋብቻ ግጭት መንስኤ ይሆናል?

በጋብቻ ውስጥ ገንዘብ ማጣትና ማግኘት እንዲሁም የተገኘው የሚያዝበት ሁኔታ ላይ ስምምነት ባለመፈጠሩ ግጭት ይከሰታል:: ለምን?



ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ሐሳቦችን መስጠት ይቻላል:: ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው አቅርቤአለሁ::

*(1) ራስ ወዳድነት፡-* ማንኛውም ሰው በተፈጥሮ ራሱን የማስቀደም ዝንባሌ አለው:: ከዚህም የተነሣ ባለትዳሮች አንዱ ለሌላው ከማሰብ ይልቅ ለግል (ለራስ) ቅድሚያ የመስጠት አዝማሚያ ሊያሳዩ ይችላሉ:: የተገኘው ገንዘብ በጋራ ለጋራ ፍላጎት እንዲውል ካልተደረገና «ለእኔ ይሁን» የሚል የራስ ወዳድነት ሁኔታ ካለ በመካከላቸው ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ ነው:: በአገራችን ሁኔታ በአብዛኛው ባልና ሚስት፣ የሁለታቸውንም ፍላጎት ማሟላት የሚያስችል ገቢ ስለማይኖራቸው ባላቸው ላይ በጋራ ካልወሰኑ መጋጨት ይከሰታል::

*(2) ከወላጆች የተገኘ ትምህርትና ልምድ መለያየት፡-* ባልና ሚስት ያደጉት ከሁለት የተለያዩ ወላጆች ጋር እና በተለያየ አካባቢ ነው:: ስለንብረት አስተዳደርና ገንዘብ አወጣጥ የተለያየ አመለካከት ካላቸውና የሚከተሉት የሕይወት ዘይቤያቸው አንድ ካልሆነ ቤተሰብ የመጡ ናቸው:: እነዚህ ከተለያየ የቤተሰብ ሁኔታ የሚመጡ ባልና ሚስት የተለያየ አመለካከትና ዘይቤ ይዘው ይመጣሉ:: እነዚህን የቅድመ-ጋብቻ አመለካከቶች ማስታረቅና ማቀራረብ የሚቻል ቢሆንም የሁለቱ ፈቃደኝነትና ለትዳራቸው ያለው መስጠት ውጤቱን ይወስነዋል::

እኔ የገበሬ ልጅ ስለነበርኩ እቤታችን ውስጥ ገንዘብ እንደ ብርቅ ነበር የሚታየው:: ወላጆቼ የነበራቸው ሀብት በዓይነት እንጂ በጥሬ ገንዘብ አልነበረም:: ስለዚህ ገንዘብን በምናገኝበት ጊዜ በጥንቃቄ እንይዝ ነበር:: ባለቤቴ ደግሞ የመጣችሁ መለስተኛ ንግድ ካለው ቤተሰብ ስለነበር በእጅዋ ብዙ ገንዘብ ይዛ ታውቃለች:: በእርስዋ ቤተሰብ ውስጥ የሚያስፈልገው ነገር ወዲያውኑ ገንዘብ ይዞ ሄዶ ከሱቅ ገዝቶ ማምጣት የተለመደ ነው:: በእኔ ቤተሰብ ግን የምንፈልገውን ነገር ለማግኘት በዓይነት ያለውን ዕቃ አስቀድሞ ወደ ጥሬ ገንዘብ ለመለወጥ መድከም ያስፈልግ ነበር:: ለእኔ ጥቂት ገንዘብ እንደ ትልቅ ነገር ሲሆን ለባለቤቴ ግን ጉዳይ አይለጣትም:: እንዲህ ዓይነቱ የአመለካከት ልዩነት በጋብቻ ሕይወት ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል::

*(3) የሕይወት ፍልስፍና መለያየት፡-* ባልና ሚስት ካደጉበት ቤተሰብ ካገኙት አመለካከት በተጨማሪ በትምህርታቸው ልዩነት ምክንያት ስለ ገንዘብ የሚኖራቸው የሕይወት ፍልስፍና ይለያያል:: በተለይ ገንዘብን ከእግዚአብሔር አደራ እንደ ተቀበለ ሰው ለመጠቀምና ለማስተዳደር ጥረት በሚደረግበት ጊዜ በመካከላቸው ልዩነት ይፈጠራል:: አንደኛው ገንዘብን ለሆነ ነገር ከመጠቀማቸው በፊት የእግዚአብሔር ሐሳብ ምን እንደሆነ እንጠይቅ ሲል ሌላው ደግሞ እግዚአብሔር በሰጠን አእምሮ እንደ ፍላጎታችን እንጠቀምበት፣ ምን ጸሎት ያስፈልጋል ይላል:: አንደኛው ገንዘብን ከመንፈሳዊነት/ከእምነት/ ጋር ሲያያይዝ ሌላው ደግሞ ገንዘብ ምንም መንፈሳዊ ንክኪ የሌለው የመገልገያ መሣሪያ እንደሆነ ያስባል:: በዚህ ጊዜ ግጭት ይፈጠራል::

*(4) ገንዘብ ሁልጊዜ የሚነሳ ጉዳይ መሆኑ፦* ባልና ሚስት ስለ አንዳንድ ጉዳዮች በቀላሉ ተነጋግረውበት ያበቃሉ። አንዳንድ ጉዳዮች ወዲያውኑ የሚረሡ አጀንዳዎች ይሆናሉ። የገንዘብ ጉዳይ ግን በየዕለቱ ሊያነሱት የሚገባቸውና ለፊ ውይይት የሚሻ በመሆኑ ለግጭት ሊያነሣሣ ሰፊ ዕድል አለው። ባልና ሚስት በሌሎች በብዙ ነገሮች ሳይስማሙበት አብረው መኖር ሲችሉ በገንዘብ ጉዳይ ግን ሳይስማሙ አብረው ለመኖር እጅግ አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል።

*(5) የባልና ሚስት የባሕርይ ልዩነት፦* ይህ ሐሳብ በተራ ቁጥር 2 ባልና ሚስት ስለገንዘብ የሚኖራቸው አመለካከት የተለያየ መሆን ለግጭት መንስኤ እንደሚሆን ከተገለፀው ጋር ይያያዛል። አንደኛው ገንዘብን እንጠቀም ሲል ሌላኛው ደግሞ ገንዘብን እንቆጥብ ይላል። በመጠቀምና በመቆጠብ መካከል ያለውን ሚዛን መጠበቅ አስፈላጊ ቢሆንም ሚዛኑን መጠበቁ ግን ከባድ ነው። ሚዛን መጠበቅ ከሚያስቸግርበት ምክንያቶች አንዱ፣ ባልና ሚስት «በተፈጥሮ» ያላቸው ባሕርይ መጠቀም ወይም መቆጠብ በሰሆነ ሚዛናዊ የማይሆን መሆኑ ነው። ቆጣቢ የሆነው ገንዘብ ማስቀመጥን ይወዳል፣ የተቀመጠው ሲቀንስ ይጨነቃል፣ አሁን በገንዘቡ ቢጠቀምበት ለወደፊት ምንም ዋስትና አይኖርም ብሎ ያስባል። በገንዘብ መጠቀምን የሚወደው የትዳር ጓደኛ ደግሞ አሁን ባለው ገንዘብ በመጠቀሙ ደስ ይለዋል፣ መቆጠብን እንደዋና ነገር አይመለከትም። «ዛሬ በልተን ጠጥተን ደስ ይበለን፣ ለነገ እንጨነቅ» በሚል መርሕ የሚኖር ሰው ይሆናል። ይህ ዓይነቱ የባሕርይ ልዩነት ለግጭት መንስኤ ይሆናል።

ከባሕርይ ጋር በተገናኘ ሁኔታ ሌላው የሚነሳው የባሕርይ ልዩነት ንፉግነትና ቸርነት ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ የሚጠየቅ ጥያቄ አለ። አንደኛው የትዳር ጓደኛ ቸር ቢሆንና ገንዘብ ለሰዎች ቢሰጥ ምን ችግር አለው? የሚል ነው። ባልና ሚስት ስለገንዘብ አጠቃቀም ያላቸው አመለካከት የተለያየ መሆን በተለይ የመጠቀምና የመቆጠብ ጉዳይ በመካከላቸው ግጭት እንዲፈጠር እንደሚያደርግ ተመልክተናል። በሌላ በኩል ግን የራሱ የሆነ ጥቅም አለው። አንዱ ቸር ሌላው ግን ንፉግ ሲሆን ሚዛን የጠበቀ የገንዘብ አያያዝ እንዲኖራቸው ይረዳል። ሁለቱ ቸሮች ወይም ሁለቱ ንፉጎች ቢሆኑ በትዳር ሕይወታቸው ከፍተኛ ችግር ይፈጠራል። ስለዚህ ልዩነታቸው ጠቃሚ እንደሆነም መታሰብ አለበት። ቆጣቢው ቸሩን ይጠብቃል፣ እንዲሁም ቸሩ ቆጣቢውን ገንዘብን መጠቀም እንዲችል ያበረታታል።

*(6) ለገንዘብ የሚሰጠው ዋጋ ልዩነት፦* ባል ወይም ሚስት እንዳቸው ስለገንዘብ ዋጋ የሚሰማቸው ስሜት ወይም የሚሰጡት ሥፍራ ከሌላው የትዳር ጓደኛ የተለየ ይሆናል። ለአንዳቸው ገንዘብ የሚፈለገው ነገር የሚገዛበት፣ ለጠቀሜታ የሚውል መሣሪያ ነው። ሌላኛው ወገን ደግሞ ገንዘብን እንደ የማህበራዊ ደረጃ፣ ዋስትና፣ ደስታና የኃይል ምንጭ አድርጎ ሊመለከት ይችላል። ሁለተኛው ዓይነት አመለካከት ያላቸው ባለትዳሮች ገንዘብን ይቆጥባሉ፣ ከጓደኞቻቸው ለመብለጥ ውድድር ውስጥ ይገባሉ፣ ገንዘብን እንደ ነጻነት ማግኛ መሣሪያ አድርገው ያስባሉ። በአንዳንዶች ገንዘብ



እንደ ደስታ ምንጭ ተደርጎ ይታሰባል። አንዳንድ ባሎች ወይም ሚስቶች ገንዘብ ለሕይወታቸውና ለትዳራቸው ዋስትና የሚሆንላቸው እየመሰላቸው ገንዘብ ለማግኘትና ለማጠራቀም ቀንና ሌሊት ይለፋሉ። ገንዘብ ለማግኘት መትጋት እጅግ መልካም ነው። ሆኖም ከሚገባው በላይ ለገንዘብ ሥፍራ ከሰጡ፣ ገንዘብ የሚጠቀሙበት መሆኑ ቀርቶ እምላካቸው ይሆናል። የገንዘብ ባሪያ መሆን ለሕይወት እርካታና ደስታን አይሰጥም። ባልና ሚስት ገንዘብ ሊያደርግላቸው የሚችለውንና የማይችለውን ነገር ለይተው ማወቅ ይገባቸዋል። የገንዘብ ኃይል ወይም ችሎታ ውስን ነው። ከሁለቱ አንዳቸው ገንዘብን እንደ ተራ ነገር ሲቆጥር ሌላው ደግሞ ሕይወት እንደሆነ ካሰበ በአጠቃቀሙ ላይ ልዩነት ይፈጠራል። የግጭት መንስኤም ይሆናል።

## የገንዘብ አያያዝ መርሆዎች

ባልና ሚስት ስለ ገንዘብ የሚኖራቸው አመለካከትና አጠቃቀማቸው የጋብቻ ሕይወታቸውን እንዳይጎዳ መሠረታዊ የሆኑ መርሆዎችን መከተል ይገባቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ እነዚህን መርሆዎች በመከተል ገንዘብ የትዳር ግንኙነታቸውን እንዳይጎዳ መከላከልና ለጋራ እርካታና ደስታ እንዲሆን መጠቀም ይችላሉ።

*መርህ 1፡ በጋብቻ ውስጥ ለገንዘብ ትክክለኛውን ሥፍራ መስጠት፦* ይህ ሐሳብ የገንዘብ አመጣጥንና አወጣጥን የሚያመለክት ነው። ባልና ሚስት ያላቸውን ገንዘብ በምሥጋና፣ በፈሪሃ እግዚአብሔር፣ በጽድቅና በፍቅር ተስማምተው ቢጠቀሙበት በሕይወታቸው ደስታን ያገኛሉ። ባልና ሚስት ገንዘብ ለማግኘት ብለው የእግዚአብሔርን ጽድቅ መተላለፍ አይገባቸውም። ያለ ጽድቅ የተገኘ ገንዘብ የህሊና ወቀሳ ያመጣል። ተገቢ ባልሆነ መንገድ የመጣ ገንዘብ ራሱ «ሌቦች» እያለ ይወቅሳል። ለጋብቻ ጣፋጭ ጣዕም ፍቅር እንጂ ገንዘብ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል (ምሳ. 15:16-17፣ ምሳ.16:8)። ባልና ሚስት ከገንዘብ ይልቅ ለትዳር ግንኙነታቸው ቅድሚያ መስጠት አለባቸው (ምሳ.22:1)። ባልና ሚስት በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት በመልካም ሁኔታ መጠበቃቸው መልካም ስም ማፍራታቸው ብዙ ገንዘብ ከማፍራት የበለጠ ነው። ሰዎች መልካም ምሳሌነት ያላቸውን ባለትዳሮች ያከብራሉ። ከእነርሱም ሕይወት ብዙ ቁምነገሮችን ይማራሉ። ገንዘብ ጠፊ ነው፣ መልካም ስም ግን ለትውልድ እየታወሰ ይኖራል። ስለዚህ ከብዙ ገንዘብ ይልቅ መልካም ምሳሌነት ያለው የጋብቻ ሕይወት በመኖር ለብዙዎች መታነጽ ምክንያት መሆን ይመረጣል።

*መርህ 2፡ ኑሮዬ ይበቃኛል ማለትን መማር* (ፊልጵ.4:11)። አገልጋዮች ብቻ ሳይሆኑ ባልና ሚስትም በሕይወታቸው በተለይ በኑሮ ደረጃቸው ይበቃኛል ማለትን መማር አለባቸው። «ኑሮዬ ይበቃኛል» ማለት ገንዘብ ለማግኘት ተግተው መሥራትን መተው ማለት አይደለም። ነገር ግን ለኑሮ የሚያስፈልገውን ነገር ለማግኘት እየሠሩ ባገኙት ውጤት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ መኖር ነው፣ ይህ ከሆኑት በላይ ወደተሻለ ደረጃ ለመድረስ ጥረት ማድረግንም ያካትታል። አንዳንዶች «ኑሮዬ ይበቃኛል» የሚለውን ሐሳብ፣ የዕድገት እንቅፋት እንደሆነ አድርገው እንደሚተረጉሙት

አይደለም። ሰዎች በሁለንተናዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ዕድገቱ ግን ከሕይወት እርካታ ጋር አብሮ መሄድ አለበት። ሰዎች ለሚሠሩት ሥራ ገንዘብ ያገኛሉ። ባገኙት ገንዘብ የማይረኩ ከሆነና ከዚያ በላይ ሊያገኙ እንደሚረኩ የሚያስቡ ከሆነ፣ ፍላጎት ጣሪያ ስለማይኖረው ዕድሜ ልካቸውን እርካታ ሳያገኙ ያከትማሉ። ስለዚህ ባገኙት ጥቂት ነገር ወይም በደረሱበት ደረጃ ደስ እያላቸው፣ የበለጠ ለመሥራትና ለማግኘት ጥረት ማድረግ ይበጃቸዋል።

*መርህ 3: የባለአደራነት መንፈስ መኖር፡-* ባልና ሚስት በእጃቸው ያለው ንብረትና ገንዘብ እንደ ባለአደራ የተሰጣቸው እንጂ የራሳቸው አለመሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል። ስለዚህ የተሰጣቸውን ሲጠቀሙበት በአግባቡ፣ በጥበብና በማስተዋል ለሚጠቅም ነገር ማዋል አስፈላጊ ነው። ገንዘብ ቢኖራቸውም እንደ እግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ በሥራ ላይ ማዋልና ተጠያቂነት የሚሰማው ዓይነት ሰው መሆን ይገባቸዋል (ሉቃ.16:9-11)።

*መርህ 4: ብድርን በጥንቃቄ ማስተናገድ፡-* ባልና ሚስት እንደገቢያቸው መጠን መኖር አለባቸው እንጂ መክፈል የማይችሉበት ዕዳ ውስጥ መግባት አይገባቸውም (ምሳ.6:1-3)። ባልና ሚስት ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለሌላ ሰው ብለው መክፈል የማይችሉት ዕዳ ውስጥ ከመግባት መቆጠብ እንዳለባቸው የእግዚአብሔር ቃል ያሳስባል። ለሌላ ሰው ዕዳ ውስጥ ከገቡ ወይም ዋስ ከሆኑና ገንዘቡን መክፈል ካልቻሉ ድህነት ውስጥ ይገባሉ።

ስለዚህ ባልና ሚስት እጅግ አስፈላጊ እና የግድ ካልሆነ በስተቀር ገንዘብ መበደር የለባቸውም። የሚበደሩ ከሆነ መክፈል የሚችሉት መጠን ሊሆን ይገባል (ዘጸ.22:14-15፣ 2ነገ.4:3፣ 6:5፣ ምሳ.22:7፣ ማቴ.5:42፣ 21:1-3)። ባልና ሚስት ብድር ውስጥ ገብተው የአበዳሪ ባሪያ ከመሆን ራሳቸውን ቢቆጥቡና ባላቸው ነገር ተወስነው ለመኖር ቢችሉ የተሻለ ነው። ሆኖም ብድር የሚወስዱት ዘላቂነት ያለውን ነገር ለመግዛት (ለምሳሌ የመኖሪያ ቤት ለመሥራት ወይም ለመግዛት) ከሆነ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም መክፈል የሚችሉት መሆን አለበት። ተራ ቁሳቁሶችን ለመግዛት፣ በዓላትን ለማክበር፣ ድንገት የሚመጣን እንግዳ ለማስተናገድና ለመሳሰሉት ስኑሮ መሠረታዊ ላልሆኑ ነገሮች ገንዘብን መበደር መልካም ካለመሆኑም በላይ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል።

ባልና ሚስት የአገልግሎት ዕዳዎችን ሁሉ በወቅቱ መክፈል ይኖርባቸዋል እንጂ ባለመክፈል የሚጠየቁበት ዕዳ መኖር የለበትም (ሮሜ.13:8)። የመንግሥት ግብር፣ የመብራት፣ የቤት ኪራይ፣ የውኃ፣ የስልክ ወጪዎች በወቅቱ ሊከፍሉ ይገባቸዋል ማለት ነው።

*መርህ 5: በገንዘብ ጉዳዮች ላይ መነጋገር፡-* ባልና ሚስት ገቢአቸው አነስተኛ ወይም ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሁልጊዜ እየተወያዩ ገንዘቡን እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸው ዘዴ መቀየስ ከቻሉ በትዳር ውስጥ ሊመጣ የሚችለው ጭቅጭቅና ግጭት ይቀንሳል። ሁለቱም



በአኩልነት ሐሳባቸውን በመግለጽ፣ በየዕለቱ በሚያወጡት ገንዘብ ላይ የጋራ ውሳኔ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ውይይታቸው፣ የተገኘውን ገንዘብ እንዴት እንደሚጠቀሙ ወደፊት ደግሞ እንዴት ገንዘብ ማግኘት እንደሚችሉና እንደሚጠቀሙበት የሚያካትት ይሆናል። በዚህ ሁኔታ ቤተሰቡ የገንዘብ ዕቅድ ይኖረዋል ማለት ነው። ባልና ሚስት ስለገንዘብ ውይይት ለማድረግ በሚፈልጉበት ጊዜ ፍላጎቱ ወይም ውይይቱ ስኬታማ እንዳይሆን የሚያደርጉ የተለያዩ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ። ከእነዚህም ዋነኛው በገንዘብ ጉዳይ ላይ ቁጭ ብሎ በለስላሳ ስሜት መነጋገር አለመቻል ነው። የገንዘብ ጉዳይ ሲነሳ ስሜታቸው የሚለዋወጥባቸው አሉ፣ ከዚያም መጥፎ ቃላትን መለዋወጥ ይጀመርና ወደታለበው ግብ አይደረስም።

ባልና ሚስት ከገንዘብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በሚነጋገሩበት ጊዜ በቀጥታ ስለገንዘብ ከመነጋገር ይልቅ ገንዘብን መነሻ አድርገው ወደ ሌላ ጉዳይ ውስጥ ሊገቡ ውይይቱ ስኬታማ አይሆንም። በትዳር ግንኙነት ውስጥ የሚታዩትን ሌሎች ጉዳዮች በገንዘብ ውይይት ውስጥ ጣልቃ ማስገባት የተለመደ ነው። ባልና ሚስት፣ በመካከላቸው ሌሎች ያልተፈቱ የግንኙነት ችግሮች እያሉ ስለገንዘብ ቢነጋገሩ እነዚህ ችግሮች በውይይቱ መሐል ጣልቃ ገብተው ወደ ተገቢው ውሳኔ እንዳይደርሱ እንቅፋት ይሆናሉ። ከዚህም በተጨማሪ እያንዳንዱ ወገን በገንዘብ ጉዳይ ላይ ውይይት ለማድረግ በለስላሳ ስሜት ውስጥ መሆኑንና ለሰላማዊ አካባቢያዊ ሁኔታዎች መኖራቸውን መረዳት ይገባዋል። ባልና ሚስት ስለቁጠባና ስለወደፊት ዕቅድ የገንዘብ ችግር ሊያጋጥማቸው እና አሁን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው በማሰብ በሚጨነቁበት ወቅት የገንዘብ ውይይት ማንሳት ተገቢ አይደለም።

ባልና ሚስት ስለ ገንዘብ ውይይት በሚያደርጉበት ጊዜ ታማኝነታቸውና መተማመናቸው እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ባሕርያት ናቸው። እነዚህ ባሕርያት ለግንኙነት መሠረታዊ ናቸው። በአብዛኛው በዓውዳችን የሚታየው ችግር፣ ባልና ሚስት በገንዘብ ጉዳይ ላይ አንዱ ለሌላው ግልጽና ታማኝ አለመሆን ነው። የገንዘብ ጉዳይ ምስጢራዊ በሚሆንበት ጊዜ ጋብቻ አስደሳች አይሆንም። አማራጭ የሚሆን ነገር እስኪገኝ ድረስ እንደ መቆያ ቦታ ይሆናል እንጂ ሁለቱም በደስታ የሚኖሩበት ዓይነት ኅብረት አይሆንም። ስለዚህ ባልና ሚስት ስለገንዘብ አጠቃቀም ያላቸውን አመለካከትና አቋማቸውን በግልጽ መነጋገራቸው ጥቅም እንጂ ጉዳት እንደሌለው ሊያውቁ ይገባቸዋል።

ባልና ሚስት በገንዘብ ጉዳይ ላይ እንዲጋጩ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ እያንዳንዳቸው ካደጉበት ቤተሰብና አካባቢ ይዘው የመጡት እሴት መሆኑን ተመልክተናል። ስለገንዘብ ጉዳዮች በሚወያዩበት ጊዜ እያንዳንዳቸው ስለገንዘብ ያላቸውን አመለካከት፣ እሴትና ልምምዳቸውን ለሌላው ቢያካፍሉ፣ አንዱ ሌላውን ለማወቅ ዕድል ያገኛል። ይህ ውይይት የእያንዳንዱ ጠንካራና ደካማ ጎን የሚታይበት መድረክም ይሆናል። የውይይቱ ዓላማ አንዱ ሌላውን ወይም አንዱ የሌላውን ቤተሰብና ማሕበረሰብ ለመተቸት አይሆንም፤ ነገር ግን ማን ምን ዓይነት እሴትና

ልምምድ ይዞ መጣ? የሚለውን ሐሳብ በመለየትና ተገቢ የሆነውን አቅጣጫ መርጦ ለመከተል የሚያስችል ስልት ለመንደፍ ያስችል ዘንድ ነው።

ለአዲስ ተጋቢዎች፣ ስለ ገንዘብ ጉዳይ አንስቶ፣ ለጉዳዩ በቂ ጊዜ ሰጥቶ መወያየት፣ ፍቅር የሚያቀዘቅዝ ጉዳይ ሊመስላቸው ይችላል። አፍላ ፍቅራቸውን መቼ ጨረሱና ወደ የዕለት ተዕለት ትዳር ጉዳይ ውስጥ ይገባል ሊያስብል ይችላል። ስለገንዘብ መወያየት የፍቅር መቀነስ ምክንያት አይሆንም። ነገር ግን ፍቅር እንዲቀዘቅዝ ሊያደርጉ የሚችሉትን ነገሮች ከወዲሁ ለመከላከል የሚደረግ ተገቢ እርምጃ ነው። በፍቅር ውስጥ ሆኖ ስለ ገንዘብ በመነጋገር ማቀድ ይቻላል። ተገቢም ነው።

*መርህ 6፡ በገንዘብ ጉዳይ ላይ በጋራ መወሰን፦* እንግዲህ ባልና ሚስትን የሚያጣላው ገንዘብ ሳይሆን የገንዘብ አያያዝና አወሳሰን ጉዳይ ነው። አንዳቸው ወይም ሁለቱ የሚያመጡትን ገንዘብ እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸው መስማማት ሲገባቸው ይህን ማድረግ ያቅታቸዋል። «እንዴት እንጠቀምበት?» ለሚለው ጥያቄ የጋራ የሆነ ምላሽ አይኖራቸውም። ባልና ሚስት ያፈሩትን ገንዘብ የሚጠቀሙበት የገንዘብ አጠቃቀም መመሪያ ከሌላቸው በገንዘብ አጠቃቀም ላይ ሳያቋርጡ መጋጨታቸው አይቀሬ ነው። ባልና ሚስት እያንዳንዳቸው «በገንዘብ ላይ ውሳኔ መስጠት ያለበት ማን ነው?» ብለው ይጠይቃሉ። ታዲያ ገንዘብን የሚቆጣጠረው ማን ሊሆን ይገባል? ባል ወይስ ሚስት?

ባል ወይም ሚስት፣ አንደኛው ያለሌላው ፈቃድና ውሳኔ ገንዘብን ቢጠቀም ወይም ለሌላ ሰው አሳልፎ ቢሰጥ ስርቆት ነው። ምክንያቱም ገንዘቡ የጋራ ገንዘብ ስለሆነ፣ ያለስምምነት በገንዘቡ ላይ ማዘዝ አይገባም። ስርቆቱ ቢፈጸም የሚወዱትን የቅርብ ወዳጃቸውን ወይም የሥጋቸውን አካል ገንዘብ እንደመስረቅ ይቆጠራል። እስቲ አስቡ! ጓደኛችሁ ገንዘብ ቢሰርቅባችሁ ምን ይሰማችኋል? የምታምኑት ጓደኛችሁ እምነታችሁን በመጠቀም ገንዘብ ቢወስድባችሁ በጣም እንደሚያሳዝናችሁ የታወቀ ነው። ባል ወይም ሚስት፣ አንዱ የሌላውን ፈቃድ ሳያገኝ፣ በጋራ ንብረት ላይ እንደፈለገው ቢጠቀም ሰርቆ እንደመጠቀም ያህል ነው። እንግዲህ ያለሚስቶቻቸው ፈቃድ የጋራ ገንዘባቸውን የሚጠቀሙ ባሎች ወይም ሰባሎቻቸው ሳያሳውቁ የጋራ ገንዘብ እንደሚፈልጉት የሚያደርጉ ሚስቶች አንዳቸው ሌላኛውን እየሰረቁ እንደሆነ ይወቁ። ባል ወይም ሚስት ለስርቆቱ ያመቻቸው ዘንድ፣ አንዱ የሌላውን ባሕርይ ሊያመካኝ ይችላል። የባል ወይም የሚስት ባሕርይ ምንም ይሁን ምን እርስ በርስ መነጋገርና በተስማሙበት ሁኔታ ገንዘብን መጠቀም ይገባቸዋል።

ባልና ሚስት ደስተኛና እርኪ የትዳር ሕይወት እንዲኖራቸው በገንዘብ ጉዳይ ላይ በጋራ መወሰን ይኖርባቸዋል። በገንዘብ ጉዳይ ላይ በጋራ መወሰን ለትዳር ስኬት አንዱና ዋና ቁልፍ ነው። አንዱ ያለ ትዳር ጓደኛው ስምምነትና ፈቃድ ገንዘብን መጠቀም ወይም መቆጠብ የለበትም። እንዲህ ከተደረገ በባልና ሚስት መካከል መልካም መግባባት አይኖርም። ባልና



ሚስት በገንዘብ ላይ ለመወሰን እኩል መብትና ሥልጣን አላቸው። በስምምነት ለማድረግ ፈቃደኛ የማይሆን የትዳር ጓደኛ ዘወትር ጭቅጭቅ በተሞላበት ግንኙነት ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ሰው እንደሆነ ሊገነዘብ ይገባዋል።

የባልና ሚስት አንድ ሥጋ የመሆን ምስጢር ከሚገለጥባቸው መንገዶች አንዱ በገንዘብና በንብረት አስተዳደር ላይ መስማማታቸው ነው። ከመጋባታቸው በፊት በሕግ ያስመዘገቡት ንብረት ከሌለ በስተቀር ባልና ሚስት «ይህ የእኔ፣ ይህ የእርሱ ወይም የእርስዋ» ማለት አይገባቸውም። እንዲህ ካለ «የአንድ ሥጋ ይሆናሉ» መርሕ መጣሱን ያመለክታል። ባልና ሚስት በጋብቻቸው ውስጥ ስለገንዘብ/ንብረት ባላቸው አመለካከትና በአጠቃቀም ዘይቤአቸው ተመሳሳይ አቋም ከሌላቸው በመካከላቸው መልካም ግንኙነትን ለመፍጠር አዳጋች ይሆናል። በዚህ ጉዳይ ላይ ባልና ሚስት ተመሳሳይ አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግ ከባድ ነው። ነገር ግን ሁለቱን የሚያስማማ መመሪያ በማውጣት መጠቀም ይገባቸዋል።

*መርህ 7፡ ኃላፊነትን መከፋፈል፦* የገንዘብ አስተዳደር የባል ወይም የሚስት ብቻ ሳይሆን የሁለቱም ኃላፊነት ነው። ሁለቱም በገንዘብ አጠቃቀም ሂደትና ውሳኔ ላይ እኩል ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል። ምን እየሆነ እንደሆነም ሙሉ እውቀት ሊኖራቸው ተገቢ ነው። ሆኖም በስምምነት አንዳቸው ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። በገንዘብ አያያዝና አስተዳደር ባልና ሚስት እኩል ጸጋ ወይም ችሎታ ላይኖራቸው ስለሚችል በቂ ችሎታ ያለው ተቀዳሚ ሚና እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ ነው። ባልና ሚስት የየራሳቸው የሆነ ስጦታ/ችሎታ/ ስለሚኖራቸው፣ እያንዳንዱ ከፍተኛ ችሎታ በሚጠይቅ የቤተሰብ ኃላፊነት ላይ ቢሠማራ ገንቢ ውጤት ያለው ሥራ ይሠራል። ከሁለት አንዳቸው የአባካኝነት ባሕርይ ካለበት፣ ገንዘብን መያዝ ወይም መቆጣጠር ያለበት በገንዘብ አያያዝ ስጦታ ያለው ቢሆን ይመረጣል። የገንዘብ አስተዳደርን ለሚችለው የትዳር ጓደኛ መስጠት፣ ብዙ የትዳር ቀውሶችን ይከላከላል። ያለ ስጦታ መሥራት፣ ውጤታማ የሆነ ሥራ እንዳይሠራ ያደርጋልና።

*መርህ 8፡ የገንዘብ ዕቅድ ማዘጋጀት፦* ባልና ሚስት የቤተሰባቸውን የገንዘብ ዕቅድ በማውጣት ቢመሩ ለአሁንም ለወደፊትም ይጠቅማቸዋል። ሁለቱ ተነጋግረው ለቤተሰባቸው ይጠቅማል ብለው የሚያስቡትን የገንዘብ ዕቅድ ይነድፋሉ። በዚህ ዕቅዳቸው ውስጥ ቤት ለመሥራት ወይም መኪና ለመግዛት ወይም በንግድ ሥራ ላይ ለመሰማራት ወይም ለልጆቻቸው ጥቅም በሚሆን መልኩ ገንዘባቸውን ለመጠቀም ሊያቅዱ ይችላሉ። ይህን ዕቅድ ሁለቱም ተነጋግረው ቢያዘጋጁ፣ ተመሳሳይ እይታ እንዲኖራቸውና የተስማሙበት የአጠቃቀም ሥርዓት እንዲኖራቸው ለማድረግ ይረዳቸዋል። በዚህ ዕቅድ ውስጥ የሁለቱም ፍላጎት ይንጸባረቃል። ዕቅዱ አንዱ በሌላው ላይ በኃይል የጫነው ዓይነት ሳይሆን ሁለቱም በገዛ ፈቃዳቸው የተስማሙበት ይሆናል። ዕቅዳቸው ለአጭርና ለረጅም ጊዜ ተብሎ ሊሰይ ይችላል። እንደ አስፈላጊነቱም በጊዜ ርዝመት ማሻሻል ይችላሉ። በዚህ

ሁኔታ የተዘጋጀ ዕቅድ፣ በገንዘብ አጠቃቀም ዙሪያ ስባልና ሚስት «ትክክለ» የሆነ አቅጣጫን ይለጣቸዋል።

የገንዘብ ዕቅድ ለማውጣት፣ ባልና ሚስት በሚያገኙት ገንዘብ ምን ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ ቅደም ተከተል ያለው ዝርዝር ለማዘጋጀት ቁጭ ማለት ይጠበቅባቸዋል። ባልና ሚስት ለየብቻቸው በገንዘባቸው ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ በየግል ከዘረዘሩ በኋላ ሁለቱ በአንድ ላይ ተቀምጠው በማነጻጸር፣ በጋራ የሚስማሙባቸውን ዕቅዶች ቅደም ተከተል ያስይዛሉ። እነዚህን በቅደም ተከተል የሆኑትን ዕቅዶች የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ በማለት ይከፍላሉ። የዕቅድ ቅደም ተከተሎች እንደ የባለትዳሮቹና እንደ የገቢ ምንጫቸው ሁኔታ የተለያየ ሊሆን ይችላል።

የገንዘብ አጠቃቀማችን ያለዕቅድ ከሆነ ገንዘብን በተገቢ ሁኔታ መጠቀም አስቸጋሪ ነው። ዕቅድ አስፈላጊ እንደሆነ የእግዚአብሔርም ቃል ያረጋግጥልናል። ለሌሎች ነገሮች እንደምናቅድ ሁሉ ለገንዘብም ማቀድ ያስፈልገናል (ምሳ.20:18፣ ሉቃ.14:28)። «የበጎችህን መልክ አስተውለህ እወቅ፣ በከብቶችህም ላይ ልብህን አኑር፣ ባለጠግነት ለዘላለም አይኖርምና ዘውድም ስትውልድ ሁሉ አይጸናምና» (ምሳ.27:23-24)። በዚህ ጥቅስ መሠረት አንድ ሰው ምንም ያህል ባለጠጋ ሆኖ ንብረቱን ግን በሚገባ የማይጠብቅና በዕቅድ የማይጠቀምበት ከሆነ፣ ከጊዜ በኋላ ያለውን ማጣቱ አይቀሬ ነው። ስለዚህ ንብረትን በቅርበት ሆኖ መከታተልና አስፈላጊውን እንክብካቤ በማድረግ መያዝ ተገቢ ነው።

*መርህ 9: በቤተሰብ በጀት መተዳደርን መማር:-* በገንዘብ አያያዝ ላይ ባልና ሚስት የሚስማሙበትን መመሪያ ማውጣት ብዙ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ይከላከላል። ገንዘብን ዘላቂ ጥቅም ሊሰጥ በሚችልና በትዳር ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማያመጣ ሁኔታ ለመጠቀም፣ ባልና ሚስት ኑሮአቸውን በዕቅድና በበጀት መምራት ይገባቸዋል። በጀት፣ ገቢያቸውንና ወጪዎቻቸውን በዝርዝር ለማወቅ ይረዳል። በበጀት በመመራት የሚኖሩ ጥቅሞች:- (1) ባልና ሚስት ወጪዎቻቸውን ከገቢዎቻቸው ጋር እንዲያመጣጥኑ ያግዛቸዋል። (2) ባልና ሚስት ገንዘባቸውን በቅድሚያ ምን ላይ ማዋል እንደሚገባቸው እንዲወስኑ ይረዳቸዋል። (3) ባልና ሚስት ገንዘባቸውን ካጠፉ በኋላ ገንዘቡ የት ሄደ? በማለት እንዳይጨቃጨቁ ይከላከልላቸዋል፣ ገንዘባቸው የት መሄድ እንዳለበትም ቀድመው እንዲያውቁት ይረዳቸዋል። (4) በገንዘብ አያያዝ ላይ ቀውስ እንዳይመጣና በመካከላቸውም ግጭት እንዳይፈጠር ይከላከላል። (5) በገንዘብ አጠቃቀም ላይ በግብታዊነት ሳይሆን በሥርዓትና ራሳቸውን በመግዛት እንዲጠቀሙበት ያግዛቸዋል።

ከባልና ከሚስት የሚገኘው ማንኛውም ገቢ በሚገባ መታወቅ አለበት። ባልና ሚስት ምን ያህል ወጪ እንደሚያወጡ ከማለባቸው በፊት ምን ያህል ገቢ እንዳላቸው ማወቅ አለባቸው። የሌላቸውን ነገር ወጪ ማድረግ አይችሉም። ገቢ የሚባለው ገንዘብ ወይም በዓይነት በእርግጠኝነት የሚመጣው እንጂ በተስፋ የሚጠበቀው አይደለም። ባልና ሚስት በየወሩ



የሚያገኙትን ደመወዝ፣ ከባንክ ገንዘብ ካላቸው የባንክ የወለድ መጠን፣ የንግድ ድርጅት ካላቸው የሚያገኙትን የተጣራ ትርፍና በሌላ ወገን የሚመጡ ገቢዎች ካሉ ሁሉንም በገቢ ርዕስ ማድረግ ያስፈልጋል።

ባልና ሚስት የቤተሰብ በጀታቸውን በሚያዘጋጁበት ወቅት ተጨባጭ እውነታዎችን መሠረት በማድረግ ካዘጋጁ ተግባራዊነቱ ቀላል ይሆናል። አንዳንድ ያልተጠበቁ ሁኔታዎች ከበጀት ውጭ ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ በጀት በሚዘጋጅበት ጊዜ ማለብ ተገቢ ነው። አንዳንድ ድንገተኛ ጉዳዮች የገንዘብ ችግር በሚያጋጥምበት ወቅት ሊመጡ ይችላሉ። በጀት ሲደረግ ለድንገተኛ ክስተቶች አስፈላጊውን መጠባበቂያ በመጨመር ዝግጅት ማድረግ ይጠቅማል።

*መርህ 10: ገንዘብን መቆጠብ:-* ገንዘብን መቆጠብ ጥበብ ነው። በደህና ጊዜ የሚገኘውን ገንዘብ ለክፉ ቀን ማስቀመጥ ወይም ለዛሬ ፍላጎት የሚበቃውን ወጪ በማድረግ ለነገ መቆጠብ ብልህነት ነው። በገንዘብ አያያዝ ላይ ችግር ያለበት የትዳር ጓደኛ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ (እንድትወስድ) ማድረግ፣ ችግር ከመጣ በኋላ ከመነታረክና ትዳርን ከማፍረስ ይጠብቃል። ገንዘብን ለመቆጠብ ጥሩ መፍትሔ የሚሆነው ጥቃቅን ወጪዎችን ለመቆጣጠር ጥረት ማድረግ ነው። በአንድ በርሜል ውስጥ ውኃ ሞልተን ከሥሩ በትንሽ ምስማር ብንበሳው ውኃው ቀስ በቀስ እየፈሰሰ ማለቁ አይቀርም። ውኃው በጠብታ የሚያልቅ አይመስልም። ካልተደፈነ በጊዜ ብዛት ውኃው ያልቃል።

ሀብትም ካልተቆጠበ እንዲሁ ነው። በሳንቲሞችና በብር ደረጃ ወጪ የሚደረግ ገንዘብ ሳይታወቅ ያልቃል። ገንዘብ ሳይታወቅ የሚያልቀው ለጥቃቅን ነገሮች በሚደረግ ወጪ ምክንያት ነው። ባለትዳሮች ለትላልቅ ነገሮች ገንዘብ ለማውጣት ሲፈልጉ ብዙ አስበውበት ነው። ነገር ግን ጥቃቅን ወጪዎችን በተመለከተ ብዙ አይጎዳም እያሉ ስለሚያወጡ ድርጊቱ በጀት ያቃውሳል። ስለዚህ ጥቃቅን ወጪዎችን በማስተዋል መቆጣጠርና እያንዳንዱን ሳንቲም በበጀት አቅጣጫ አስበውበት መጠቀም ገንዘብን ለመቆጣጠር ይረዳል።

ጥቃቅን የሚባሉ ወጪዎች ገንዘብን ሊያባክኑ ወይም መቅኖ ሊያሳጡ ይችላሉ። በተቃራኒው ደግሞ ጥቂት በጥቂት መቆጠብ ገንዘብን ለማብዛት ይረዳል። ባልና ሚስት በወር ከሚያገኙት ገቢ፣ በየወሩ ጥቂት ጥቂት በመቆጠብ በዓመታት ውስጥ ብዙ ገንዘብ ማጠራቀም ይችላሉ። ቁጠባ በጥቂት ገንዘብ ይጀመራል። ጥቂት ነውና ምንም ጥቅም የለውም ማለት አይገባም። የተወሰነ ገንዘብ በመቆጠብ ጀምሩ፤ ለውጡ በረጅም ዓመታት ውስጥ ይታያል። ጥቂት በጥቂት መቆጠብ ወይም ማጠራቀም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። «በችኮላ የምትከማች ሀብት ትጎድላለች፣ ጥቂት በጥቂት የተከማቸች ግን ትበዛለች» (ምሳ.13:11)። መቆጠብ መልካም ነው። ምክንያቱም የተቆጠበ ገንዘብ በችግር ጊዜ ይጠቅማል። በየዕለቱ አንድ ብር መቆጠብ ቢቻል፣ በዓመት ሦስት መቶ ስልሳ አምስት ብር ማጠራቀም እንደሚቻል መገንዘብ ተገቢ ነው።

*መርሀ 11: ገንዘብ በጋራ ወይም በየግል ማጠራቀም፡-* ባልና ሚስት ገንዘባቸውን ባንክ ሲያስቀምጡ በማን ስም ማስቀመጥ አለባቸው? በዚህ ጥያቄ ዙሪያ የተለያዩ አማራጮችን መጠቀም ይችላሉ:: የመጀመሪያው አማራጭ፣ በሁለቱ ጥምር ስም (በጥምር ፊርማ እና/ወይም በሚል) ተከፍቶ ሁለቱ ተስማምተው በሁለቱ ወይም በአንዳቸው ፊርማ ገንዘቡን ማውጣት በሚችሉበት ሁኔታ ማድረግ ነው:: ሁለተኛው አማራጭ ሁለቱ በመስማማት በአንዳቸው ብቻ እንዲተዳደር ማድረግ ነው:: ሦስተኛው አማራጭ፣ እያንዳንዳቸው በየግላቸው የቁጠባ ሂሳብ ከፍተው፣ የሚቆጠበውን ገንዘብ አካፍለው ለየብቻ ማጠራቀም ነው:: ከእነዚህ አማራጮች መካከል ሁለቱ የሚመቻቸውንና የተስማሙበትን አማራጭ ሞክረው ካልተስማማቸው በሂደት መለወጥ ይችላሉ:: ዋናው ጉዳይ፣ ሁለቱ በእኩልነት ደረጃ ተወያይተው፣ በበጎ ፈቃዳቸው መምረጥ መቻላቸው ነው:: አማራጮቹ የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን ቢኖራቸውም እመቺ የሚሆነው ግን በጥምር ስም ተከፍቶ በእና/ወይም የሚንቀሳቀሰው የቁጠባ ሒሳብ ቢኖራቸው ነው:: በመካከላቸው ያለመተማመን ካለ፣ ገንዘባቸውን በጥምር ፊርማ ማንቀሳቀስ በሚችሉበት ሁኔታ ማድረግ ተገቢ ነው::

*መርሀ 12: የማማከር አገልግሎትን ማግኘት፡-* ባልና ሚስት በገንዘብ ጉዳይ ላይ ተነጋግረው መስማማት ሲያቅታቸው ወይም የየግላቸውንና የጋራ ዓውድና ፍላጎት ያገናዘበ ዕቅድ ማዘጋጀት በማይችሉበት ጊዜ ሊያግዛቸው ወደሚችል ባለሙያ እንዲሄዱ ይመከራል:: ከዚያም ተገቢውን ምክር አግኝተው ችግራቸውን መፍታት ይችላሉ:: አንድን ጉዳይ ገንቢ በሆነ ሁኔታ መፍታት አለመቻላቸው ጉዳዩ መፍትሔ የለውም ማለት ስላይደለ ባለሙያን ማማከር ከብዙ ኪሣራ ያድናል::

*የወዳጆችና የወላጆች (ዘመዶች) ጣልቃ መግባት*

ጋብቻ መልካም እንዲሆን መሠረታዊ ሁኔታዎቹ መሟላት አለባቸው:: ጋብቻ ማለት መተው፣ መጣበቅና አንድ ሥጋ መሆን ማለት ነው:: በጋብቻ ለመጣመር የፈለጉ ወንድና ሴት በመጀመሪያ የሚወበዱት እርምጃ ወዳጆቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን መተው ነው:: መተው ማለት ከሌሎች ሰዎች ጋር ካለ ጥብቅ ግንኙነት ወይም ትስስር መለየትና ለትዳር ጓደኛቸው ተገቢውን ትኩረት መስጠት ማለት ነው:: በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ፣ የባል ወይም የሚስት ቤተሰቦች በልጆቻቸው የትዳር ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት የለባቸውም::

ወላጆች በልጆቻቸው ጋብቻ ውስጥ የሚኖራቸው ግንኙነት ወሰኑን ጠብቆ ሊሆን ይገባል:: እንዱ ለሌላው ቤተሰብ ወይም ወላጅና ዘመድ ተገቢውን እንክብካቤና እክብሮት መስጠት ይገባዋል:: ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ውበጥ የተጠቀሰችው ሩት የምትባል ሴት ባልዋ ከሞተባት በኋላ ምራትዋን ለመንከባከብ ያሳየችው ውሳኔ የሚደነቅ ነው (ሩት1:16-17)::



በጋብቻ ውስጥ ለሚፈጠሩ ችግሮች የባልና ሚስት ቤተሰቦች መንስኤ የሚሆኑት በቀጥታ ጣልቃ በመግባት ላይሆን ይችላል:: ሁለቱም ተጋቢዎች የመጡበት የማሕበረሰብ ደረጃ፣ እምነት ወይም ጎሳ የተለያየ ከሆነ ወይም የአንዳቸው አመጣጥ ከዝቅተኛ የኅብረተሰብ ክፍል ሲሆን የመናናቅ ስሜት ሊታይ ይችላል:: የአንዱ ወላጅ የሌላውን ቤተሰብ ሊንቅ ይችላል:: ከዚህም የተነሣ አንዱ ለሌላው ቤተሰብ ያለው እይታ ይበላሻል:: ቤተሰብን አብሮ ለመጎብኘት አይፈልጉም::

ባልና ሚስት የሆኑ ልጆቻቸውን፣ ከመጋባታቸው በፊት እንደሚያዩአቸው እንደ ትናንሽ ልጆች መቆጣጠርና ማስተዳደር የሚፈልጉ ወላጆች ለጋብቻ ችግር መንስኤዎች ናቸው:: ልጆች ምን ጊዜም ለወላጆቻቸው ልጆች መሆናቸው ባይካድም የራሳቸውን ትዳር ከመሠረቱ በኋላ ግን ጠቃሚና በጎ ምክር ከመስጠት ባሻገር ለመቆጣጠር መፈለግ መልካም አይደለም:: የወላጆችና የባለትዳር ልጆቻቸው የኑሮ ዘይቤ በጣም የተለያየ ሊሆን ይችላል:: ልጆች ከተጋቡ በኋላ በነጻነትና እንደ እግዚአብሔር ቃል መልካም ሆኖ በታያቸው ሁኔታ ለመኖር መብት አላቸው:: ስለዚህ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋብቻ በኋላ ተገቢውን ወሰን ጠብቀው ሊኖሩ ይገባል:: በጋብቻ ያሉ ልጆቻቸውን እንደ *እኩዮቻቸው* ሊያዩ እንጂ እንደ ልጅነት ዘመናቸው በሚፈልጉት ሁኔታ ለማዘዝ መሞከር ትክክል አይደለም::

ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር የጠበቀ ግንኙነት በሚኖራቸው ጊዜ ችግር ይፈጠራል:: አንዳንድ ጊዜ አባት ወይም እናት በሞት ወይም በሁኔታዎች ቢለይ ከልጆች ጋር የቀረው ወላጅ ከሟቹ ወይም ከተለየው የትዳር ጓደኛ ጋር የነበረውን ግንኙነት ከልጆቻቸው ጋር ይመሠርታል:: አባት ሚስቱን ካጣ ሴት ልጁን እንደ ሚስቱ፣ እናትም ወንድ ልጅዋን እንደ ባልዋ በመቁጠር ከልጅነት ያለፈ የሕይወት መተሳሰር ያለበት ግንኙነት ያበጃሉ:: ይህ ግንኙነት የትዳር ጓደኛን ከማጣት የሚመጣውን ብቸኝነት ለማስወገድ ሳይታወቅ የሚመሠረት ግንኙነት ነው:: ልጆች ትዳር ከመሠረቱ ብቸኝነቱ ተመልሶ ሊመጣ እንደሚችል በማሰብ ልጆቹ እንዳያገቡ ሊከለክሉ ይሞክራሉ:: ይህ ካልተሳካ ደግሞ ካገቡም በኋላ ከእነርሱ ላለመለየት ጥረት ያደርጋሉ:: እንዲህ ዓይነት ባሕርይ ያለው ወላጅ ልጆቹ ከትዳር ጓደኛቸው ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳይመሠርቱ ያደርጋል:: ከዚህ የተነሣ ያገቡት ሰው «እኔን ነው ወይስ አባትህን/እናትህን ነው ያገባሽው/ያገባኸው?» የሚል ጥያቄ ያስነሳል፣ ግጭትንም ይፈጥራል::

*ከልጆች ጋር ተያይዘው የሚመጡ ችግሮች*

ልጆች፣ አባትና እናት (ባልና ሚስት) ለዘለቄታው አንድ ላይ ተሳስረው መኖር እንዲችሉ የማሰሪያ ኃይል አላቸው:: በተቃራኒው ደግሞ በጋብቻ ውስጥ ሁከትና ግጭት እንዲፈጠር፣ መለያየት እንዲመጣ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ:: ልጆችን መውለድ አለመቻል፣ በልጆች አስተዳደግ ላይ አለመስማማት፣ ልጅ ለመውለድ አለመስማማት፣ ልጆችን አበላልጦ መውደድ፣ ልጆች ራሳቸውን ከቻሉ በኋላ መውጣት ወይም አለመውጣት ጉዳይ ከልጆች ጋር የተያያዙ ችግሮች ናቸው:: እነዚህን ችግሮች በዝርዝር

ለማወቅ የጋብቻ ችግሮችና የመፍትሔ ቁልፎች[3] የሚለውን መጽሐፍ ማንበብ ጠቃሚ ነው።

### *7.2. የጋብቻ ችግሮችን ለማማከር የሚረዱ ሀሳቦች*

በዚህ ክፍል፣ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም የጋብቻ ችግሮች ለማማከር የሚቻልባቸውን ስልቶች እንመለከታለን። እነዚህንም ሐሳቦች በሁለት ክፍለን እናያለን። በመጀመሪያ፣ ከወሲብ ጋር የተያያዘ ችግር ያለባቸውን ለማማከር የሚቻልባቸውን ዘዴዎች እናያለን። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ሌሎች ችግሮች ያሉባቸውን ባለትዳሮች እንዴት መርዳት እንደሚቻል በዝርዝር እንመለከታለን።

#### *ሀ. ከወሲብ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ማማከር*

ይህን በተመለከተ በምዕራፍ አራት ሥር የተጠቀሰ ሲሆን፣ አንድ አማካሪ እነዚህን የማማከር ዘዴዎች በመጠቀም የጋብቻ ችግሮችን ለማማከር ይችላል። ሆኖም ጥንዶችን በሚያማክርበት ጊዜ ዘዴዎቹን እንዴት አድርጎ መጠቀም እንደሚገባው በጥንቃቄ ሊያጤን ይገባል። በጋብቻ ማማከር ውስጥ የሚነሱ የወሲብ ችግሮችም ሆኑ ሌሎች ጉዳዮች በተገቢው ሁኔታ ካልተያዙ፣ የባልና ሚስትን ግንኙነት ሊያፈርሱ ይችላሉ። ስለሆነም የወሲብ ችግርን ለማማከር የሚረዱ ሐሳቦችን በቅድሚያ ከተመለከትን በኋላ ወደ ሌሎች ችግሮች እንመለሰባቸዋለን።

ወሲብ የአስተሳሰብና የስብእና መግለጫ ስለሆነ የወሲብ ችግሮችን በቀላሉ ግልጽ አድርጎ መናገር ወይም መግለጽ አዳጋች ይሆናል። የወሲብ ችግር የእውቀት፣ የልምድ፣ የስብእና አለመጣጣም፣ እና የአመለካከት ወይም የመንፈሳዊ ችግር ነጸብራቅ ሊሆን ይችላል። ሰዎች ማንነታቸውን በሚሠሩት ሥራ እንደሚገልጹ ሁሉ በወሲብ አፈጻጸምም ይገልጹታል። አንዳንድ ጊዜ የወሲብ ችግር የሰብእና ግጭት ውጤት ሊሆን ይችላል። ይህ ሲሆን አማካሪው መንስኤውን በዝርዝር ለማወቅ በቂ ጊዜ ወስዶ መፈተሽ ይገባዋል።

ስለወሲብ ችግሮች መወያየት ለጋራ ግንዛቤና አዲስ አመለካከት እንዲፈጠር ሊረዳ እንደሚችል በመገንዘብ ችግሩ ያለባቸው ባልና ሚስት ችግራቸውን ለእግዚአብሔርና ለሰው መናገር ይረዳቸዋል። ስለዚህ ምክር ፈላጊዎች ችግሮቻቸውን በነጻነት መናገርና ማብራራት እንዲችሉ አማካሪው ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ያለ ምንም ፍርሃት እንዲናገሩ ሊያደፋፍራቸው ይገባል። ባልና ሚስት የወሲብ ግንኙነት ችግራቸውን በአንድ ጊዜ ግንኙነት ለመግለጽ ፈቃደኛ ስለማይሆኑ፣ ተገቢውን ጊዜ በመስጠትና ውይይቱን ከቀላል ነገር መጀመር ይገባዋል። ቀስ በቀስም በሚሰማቸው ነጻነት መጠን ችግሩን እንዲገልጹ መምራት የተሻለ ውጤት ይኖረዋል።

---

[3] ከበደ በከሬ፡ *የጋብቻ ችግሮችና የመፍትሔ ቁልፎች*፡፡ አአ 1996 ዓ.ም.



የጸታ ትምህርት ለወሲብ ግንኙነት ችግሮች መፍትሔ ሊሰጥ እንደሚችል መረዳት ጠቃሚ ነው። ትምህርት ችግር ፈቺ ነው። ባልና ሚስት ተገቢውን ትምህርት ቢያገኙ የችግራቸውን ምንነት፣ መንስኤዎቹንና የመፍትሔ መንገዶቹን ለማወቅ ትልቅ ዕድል ይኖራቸዋል። በትምህርቱ ወቅት ባልና ሚስት ከችግራቸው ጋር የተያያዙትን የተለያዩ ጥያቄዎችን አንስተው መጠየቅና መልስ ማግኘት ይችላሉ። ባልና ሚስት ስለወሲብ አካላቸው ተገቢውን ግንዛቤ ሲያገኙ ለራሳቸው እርካታና ለእግዚአብሔር ክብር መጠቀም ይችላሉ። የጋብቻ አማካሪ፣ ባልና ሚስት በአንድ ላይ ሆነው የሚያነቡትን መጽሐፍ፣ የተለያዩ ጽሑፎችንና የሚያዩአቸውን ፊልሞች ሊጠቁማቸው ይችላል።

የሰዎችን መንፈሳዊ ዕድገትና ግንዛቤ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ስለ ወሲብ ያላቸውን አመለካከት ማስተካከል አስፈላጊ ነው። ክርስቲያናዊ ያልሆኑ አይታዎች ካልተስተካከሉ፣ በሕይወታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማድረጋቸውን ይቀጥላሉ። ባልና ሚስት የእግዚአብሔር ቃል ስለወሲብ የሚያስተምረውን ትምህርት በሕይወታቸው ተግባራዊ ለማድረግ መስጠት ይኖርባቸዋል።

#### *ለ. አጠቃላይ የጋብቻ ችግሮችን ለማማከር የሚረዱ ሐሳቦች*

ባልና ሚስትን በተሳካ ሁኔታ ለማማከር የሚከተሉትን መሠረታዊ እውነታዎች መረዳት አስፈላጊ ነው።

*ማንኛውም ጋብቻ ችግር አለው።* መጠኑና ዓይነቱ ይለያይ እንጂ ማንኛውም ቤተሰብ የጋብቻ ችግር አለው። ሆኖም ሁሉም ባሎችና ሚስቶች ስለ ችግሩ ያላቸው ግንዛቤ ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ወደ ማማከር አገልግሎት ሲመጡ አንዱ ችግራቸውን ሲያሳንስ ሌላው ያተልቃል። አንዱ የችግሩ መንስኤ ሌላው ወገን እንጂ ራሱ እንዳልሆነ ያስባል። በባልና ሚስት መካከል ችግር ሲፈጠር፣ ሁለቱም ለችግሩ መጀመርና ማደግ የየራሳቸው ሚና አላቸው። አንዳንድ ጊዜ የባልና ሚስት ችግር ከሁለታቸው አልፎ ሌሎች የቤተሰብ አባላትንና ቤተዘመድንም ሊነካካ ይችላል። ስለዚህ ችግሩን ለመፍታት በሚደረገው ጥረት እንደ አስፈላጊነቱ ከባልና ሚስት በተጨማሪ ሌሎች ሰዎች እንዲገኙ የሚፈለግበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

ስለዚህ የጋብቻ ችግሮችን በሚገባ ለማማከር የሚከተሉትን አጠቃላይ ደረጃዎችን መከተል ጠቃሚ ይሆናል።

*መረጃዎችን መሰብሰብ፦* አንድ የጋብቻ አማካሪ በሚገባ ለማማከር አስቀድሞ ተገቢ መረጃዎችን መሰብሰብ ይኖርበታል። ከሚፈለጉ መረጃዎች መካከል የሚከተሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፦

- ለምን ተጋቡ?
- የጋብቻ ችግራቸው መቼ/እንዴት/ ተጀመረ?
- እስካሁን ድረስ የትዳር ችግራቸውን ለማን ያካፍላሉ/ማንን ያማክራሉ?/
- እያንዳንዳቸው የትዳራችን ዋነኛ ችግር ነው ብለው የሚያስቡት/የሚናገሩት/ ነገር ምንድነው?
- ስለፍች ምን አስተሳሰብና አመለካከት አላቸው?
- በትዳራቸው ውስጥ ያሉ መልካምና ክፉ ነገሮች ምንድናቸው?
- የወሲብ ሕይወታቸው ምን ይመስላል?
- ቤታቸውን እንዴት ያስተዳድራሉ?
- በጋብቻ ውስጥ ያለመተማመን የተከሰተበት ሁኔታ ነበርን?
- በትዳር ሕይወታቸው ጣልቃ የሚገባ ሦስተኛ ወገን አለን?
- የትዳር ችግራቸውን ለመፍታት ያላቸው ቁርጠኝነት ምን ያህል ነው?

የጋብቻ አማካሪው በእነዚህና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ጥያቄ በማቅረብ በቂ የሆነ ግንዛቤ ማግኘት አለበት፡፡ ከዚያ በኋላ ችግሮቻቸውን ለመፍታት የሚረዳቸውን አማራጭ የመፍትሔ ሐሳቦችን በማውጣጣት ሂደት ያግዛቸዋል፡፡ መረጃዎቹን ሳይሰበስብ ለችግሩ መፍትሔ ለመስጠት ቢቻኮል ስሜቱን ለመግለጽ ካልሆነ በቀር ተገቢና ዘላቂነት ያለውን መፍትሔ እንዲያገኙ ሲረዳቸው አይችልም፡፡

*ባልን በጥሞና ማዳመጥ፡-* የባልን ንግግር በጥሞና ማዳመጥና መከታተል ስሜቱን ለመረዳትና ለመደበቅ የሚሞክረውን ለመገንዘብ ይረዳል፡፡ ባል የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ ከሆነና እርሱ የሚያመጣውን ገቢ ሚስት በምስጋና ከመቀበል ይልቅ የምታጉረመርም ከሆነ ስሜቱ ሊጎዳ ይችላል፡፡ ልጆች የእናትን (ሚስት) ትኩረት በመሳብ አባት (ባል) ብቻውን ቤት ውስጥ እንዲኖር ተደርጎ ሊሆን ይችላል፡፡ ከሥራ ወደ ቤት ሲገባ በቂ እረፍት ማግኘት የሚችልበት የተመቻቸ ሁኔታ አይገኝም ይሆናል፡፡ የባል ችግር ብዙ ዓይነት መልክ ሊኖረው ስለሚችል አማካሪ የባልን መሠረታዊ ችግር ለመረዳት /ተገቢውን መረጃ ለማግኘት/ በሚገባ ሊያዳምጠው ይገባል፡፡

*ባልና ሚስትን አኩል ማሳተፍ፡-* አንዳንድ ጊዜ ባልና ሚስትን በተናጠል ማማከር የተሻለ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ አንዳንድ ጊዜም ባልና ሚስትን በአንድ ላይ ለማማከር ፈቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ ለየብቻ የማማከር ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ የጋብቻ ጉዳይ ሲሆን ግን ባልና ሚስትን በአንድ ላይ ማማከር ይመረጣል፡፡ ከእነርሱ ባሻገር የቤተሰብ አባላትን የሚያካትት ችግር ሆኖ ሲገኝ ቤተሰብን ሁሉ በአንድ ላይ ማማከር የሚመረጥበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

ቤተሰብን የሚያካትት ሲሆን በመጀመሪያ በባል ወይም በሚስት መጀመር፣ ከዚያም ሌላውን የትዳር ጓደኛ፣ ቀጥሎም የቤተሰብ አባላትን በአስፈላጊ ሥፍራ ላይ በማካተት ማማከር ይቻላል፡፡ በጋብቻ ችግሮች ዙሪያ



ሁለቱን በአንድ ላይ ማማከሩ፣ አንዱን ብቻ ከማማከር የተሻለ ፍሬ ይኖረዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ባልና ሚስት ወደ ተለያዩ አማካሪዎች ሊሄዱ ይችላሉ፡፡ ባል አንዱ ዘንድ ሲሄድ፣ ሚስት ደግሞ ሌላው ጋ ትሄዳለች፡፡ ሁለቱ የሄዱባቸው የተለያዩ አማካሪዎች ተመሳሳይ የማማከር ብቃት ካላቸው፣ ባልና ሚስት የግልና የጋራ ሕይወታቸውን በሚገባ ማየት እንዲችሉ ሊረዱአቸው ይችላሉ፡፡ አማካሪዎቹ የግል ምክራቸውን የሚሰግሱ ዓይነት ከሆኑ ግን ውስብስብ ችግሮች እንዲፈጠሩባቸው ምክንያት ይሆናሉ፡፡ ለየብቻ ተለያይተው ወደ ተለያዩ አማካሪዎች መሄዱ የሚመረጥ አይደለም፡፡

በዓውዳችን አብዛኛውን ጊዜ ወደ ጋብቻ ማማከር አገልግሎት ቀድመው የሚመጡት ሚስቶች ናቸው፡፡ ባል ወደ ጋብቻ አማካሪ ከመምጣቱ በፊት ሌሎች አማራጮችን ይጠቀማል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲከሰት ባልን ቀስ በቀስ ወደ ማማከር ሂደት ለማስገባት ሙከራ ማድረግ ይመረጣል፡፡ ለሚስቱ ወይም ለአማካሪው ብሎ ሳይሆን ለራሱ ብሎ እንዲመጣ የሚያደርግ ስልትን መጠቀም የተሻለ ውጤት ይኖረዋል፡፡ አማካሪ ባልን ወይም ያልመጣውን የትዳር ጓደኛ፣ በመጣው ምክር ፈላጊ በኩል ወይም አጭር ማስታወሻ በመላክ እንዲመጣ መጋበዝ ይችላል፡፡ ባል ወይም ሚስት ወደ ማማከር አገልግሎት ለመምጣት ፈቃደኞች ካልሆኑ ስለጋብቻቸው ችግርና የሚሰማቸውን ስሜት በደብዳቤ እንዲገልጹ መጠየቅ ይቻላል፡፡ እንዲህ ዓይነት ጅምር ቀስ በቀስ በአካል እንዲገኝ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ይሆናል፡፡

*ታምቀው የቆዩትን ስሜቶች እንዲተነፍሱ መርዳት፡-* በባልና ሚስት መካከል ችግር ሲፈጠር እያንዳንዳቸው የሚሰማቸው ስሜት ይኖራል፡፡ ይህን ስሜታቸውን በአግባቡ ለመግለጽ የሚያስችል ሁኔታ በቤት ውስጥ ባለመኖሩ አምቀው ይይዛሉ፡፡ ስሜትን በተገቢው መንገድ መግለጽ አለመቻል ደግሞ ሌሎች ችግሮችን እየወለደ ይሄዳል፡፡ ለምሳሌ ባልና ሚስት በአንድ ጉዳይ ላይ ተጋጭተው ለሳምንት ያህል፣ ዝም ዝም ተባብለው፣ ሌላ አዲስ ግጭት በመካከላቸው ቢፈጠር አጸፋዊ ምላሽ የሚሰጠው ለአዲሱ ብቻ ሳይሆን ያለፈውንም ግጭት /ስሜት/ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ስሜቶች ከታመቁ ቀላል ችግር እየተባባሰና ውስብስብ እየሆነ ይቀጥላል፡፡

ስለዚህ ባልና ሚስት ወደ ማማከር አገልግሎት መጥተው ስለችግሮቻቸው በሚያወሩበት ጊዜ ሐሳባቸውን ከማዳመጥ ጎን ለጎን በችግሮቻቸው ዙሪያ የተሰማቸውን ስሜት በመጠየቅ መግለጽ እንዲችሉ ዕድል መስጠት ጠቃሚ ነው፡፡ ለምሳሌ አማካሪው ያወሩትን መነሻ በማድረግ «ባለቤቴ ይሰድበኛል ብለሽ ነበር፡፡ እርሱ እንዲህ ዓይነት ነገር ሲያደርግ በውስጥሽ ምን ይሰማሻል?»፣ «አባክሽን እንዲህ አድርጊልኝ ስላት አንተው ራስህ አድርግ ትለኛለች ብለህ ነበር፡፡ እርስዋ እንዲህ ዓይነት ምላሽ ስትሰጥህ ምን ይሰማሃል?» ብሎ በመጠየቅ፣ ባልና ሚስት የሚሰማቸውን ስሜት እንዲገልጹ መምራት ይችላል፡፡

አንዳንድ ጊዜ፣ ባልና ሚስት በችግሮቻቸው ዙሪያ ስሜቶቻቸውን መግለጽ ሲጀምሩ ችግሩ አሁን እንደሆነባቸው ያህል ይሰማቸውና እዚያው

እርስ በርሳቸው መፋጠጥ ይጀምራሉ። ግጭቱ እንደ «ትኩስ» ይሆናል። እንዲህ ሲሆን አማካሪው ሳይደናገር በቀስታ ወደ መረጋጋት ይመራቸዋል። ሆኖም «በቃ ተውት፣ ይህ ምንም አይደለም» በማለት ስሜታቸውን ገልጸው እንዳይጨርሱ ማደናቀፍ የለበትም። እያንዳንዳቸው ስሜታቸውን በሚገልጹበት ጊዜ እንዴት መግለጽ እንደሚገባቸው አስቀድሞ ምክር መስጠት ተገቢ ነው። ይህም ሆኖ እያለ የአገላለጽ ስሜቱ ኃይለኛ ሆኖ ማደናገርን የሚፈጥር ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ዝም ብሎ በማዳመጥና በመከታተል ማስጨረስ ይሻላል። እነርሱ ሲጨርሱ፣ በሂደቱ ውስጥ በሆነው ጉዳይ ላይ የማለሳለል ጊዜ መውሰድ ይጠቅማል። አልፎ አልፎ የስሜቶቹ መገለጽ በራሱ ለጋብቻቸው ችግር መፍትሔ ሊሆን ይችላል።

*የጋብቻን ችግር ለመፍታት በቂ ጊዜ መስጠት፦* የጋብቻ ችግሮችን ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ለመፍታት ተገቢውን ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል። ችግሮች ቀስ በቀስ ያድጋሉ። ዕድገታቸው ቀስ በቀስ እንደሚሄድ ሁሉ የሚቀረፉትም ቀስ በቀስ ነው። ለማደግ ብዙ ወራትን ወይም ዓመታት የፈጀን ችግር በአንድ ጊዜ ወይም በአጭር ጊዜ መፍታት ያዳግታል። ስለሆነም የባልና የሚስትን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት፣ እንደ ችግሩ መጠንና ጥልቀት የሚበቃ ጊዜ መመደብ አስፈላጊ ነው። በማማከር ክፍለ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ባልና ሚስት ከማማከር ያገኙትን ግንዛቤ በግል ሕይወታቸው ተግባራዊ ሲያደርጉ ችግሩ እየተፈታ ይሄዳል። ይህን ለማድረግ የባልና ሚስት እንዲሁም የጋብቻ አማካሪን ፈቃደኝነትና መስጠትን ይጠይቃል። ለችግሩ መፍትሔ ለማግኘት በችኮላ የሚደረገው ሩጫ ለጊዜያዊ ማስታገሻነት የሚረዳ ካልሆነ በቀር የችግራቸውን መሠረታዊ መንስኤ የሚዳስስና የሚፈታ ሂደት አይሆንም።

*ባልና ሚስት ራሳቸውን እንዲያውቁ መርዳት፦* ባልና ሚስት ስለራሳቸው ያላቸው አይታ በትዳር ሕይወታቸው ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። አንዳቸው ሌላውን በትክክል ከመረዳታቸው በፊት ስለራሳቸው ያላቸው አስተሳሰብና አመለካከት ተጨባጭነት ያለው መሆን አለበት። ለግል ሕይወታቸው ያላቸው መሠፈርት የተበላሸ ቢሆን ሌላውንም የሚያዩበት አይታ ትክክል አይሆንም። አንዳንዶች ራሳቸውን ለመፈተሽ ጊዜ አይኖራቸውም፤ አንዳንዶች ግን ራሳቸውን ለመመርመር ጊዜ ይሰጣሉ። ራሳቸውን የሚመረምሩቱ የሚጠቀሙባቸው መመዘኛዎች ራሳቸውን ከሆኑት በታች አሳንሰው እንዲመለከቱ የሚያደርጉ ናቸው። የራሳቸውን ስህተትና ድክመት ለማየት ትልቅ አጉሊ መነጽር ያላቸው ይመስላሉ። በተቃራኒው ደግሞ ከሆኑት በላይ ራሳቸውን የሚገምቱ ሰዎች ይኖራሉ። ስለዚህ በተስተካከለ ሁኔታ ራሳቸውን መረዳት እንዲችሉ መርዳት፣ የትዳር ችግሮቻቸው መፍትሔ እንዲያገኝ ይረዳል።

አንዳንድ ጊዜ በጋብቻ ውስጥ ለሚታየው ችግር ምንጩ ባል ወይም ሚስት ወይም ሁለቱም በልጅነታቸው ጊዜ ያሳለፉት ሕይወት ይሆናል። በልጅነት ወቅት የኖሩት ኑሮ ራሳቸውን በትክክል እንዳይመለከቱ ካደረጋቸው ያንኑ አስተሳሰብ ይዘው ያድጋሉ። የተማሩና በአካባቢያቸው እንደ ትልቅ ሰው የሚቆጠሩ ቢሆንም በውስጣቸው ያላቸው አይታ ጥንት



ይነገራቸው የነበረው አስተሳሰብ ነው። በውስጣቸው አሁንም «ትንሽና ምስኪን የሆነ ልጅ» አስተሳሰብ ተሸክመዋል። ራሳቸውን ሁሌም ከዚህ አንጻር ይመለከታሉ።

ስለዚህ ለአማካሪው፣ ባል ወይም ሚስት ወይም ሁለቱም፣ የበታችነት ስሜት ይሰማቸው እንደሆነ መከታተልና ማወቅ፣ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ያግዘዋል። በጋብቻ ሕይወት አንዱ የበታችነት ስሜት የሚሰማው ከሆነ ጥሩ ወዳጃሞች ሆነው አብረው ለመኖር የማይችሉበት ሁኔታ ይበዛል። የባል ወይም የሚስት ምላሾች በውስጥ ያሉትን የበታችነት ስሜት የሚያንፀባርቅ ሁኔታ ይሆናል። ለምሳሌ ባል፣ ሚስት አቤት ውስጥ ለምትሠራቸው ሥራዎች ተገቢውን ትኩረትና ምስጋና ከመስጠት ይልቅ እንደ ከንቱ ሥራ የሚቆጥር ከሆነ ሚስት ለቤተሰቡ ምንም አስተዋጽኦ እንደሌላት ታስባለች። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ከወላጆችዋም ይደርስባት የነበረ ጉዳይ ከሆነ ደግሞ የባልዋ ምላሽ ያንን የሚያጸድቅላት ይሆናል።

ሚስት ብቻ ስትሆን ባልም የበታችነት ስሜት ሊሰማው ይችላል። ለምሳሌ በወሲብ ግንኙነት ሚስቱን በተደጋጋሚ ማርካት የማይችልበት ሁኔታ ሲፈጠር ሚስቱ «ከአንተ ጋር መተኛት አፈልጋለሁ፤ ነገር ግን ምን ዋጋ አለው? ጀምሬ ከማቋረጥ ቢተው ይሻለኛል» ብትለው ባል ስሜቱ ይጎዳል። የእርስዋ ሐሳብ በራሱ ጥቃት ባይመስልም እርሱ ግን ዱሮ የሠፈር ልጆች ሲመቱት ወደ አባቱ መጥቶ ሲነግረው «አንተ ወንድ አይደለህም! ለምን አታስያቸውም ነበር። አንተን ባልወልድ ይሻለኝ ነበር» ይለው የነበረው ነገር ትዝ ይለውና በጣም ይጎዳበታል። እነዚህን ነገሮች ሲያሰላስል ለራሱ ያለው አይታ እየተበላሸበት ይሄዳል፣ ከሚስቱም ጋር ያለው ግንኙነት ይበላሻል። ከዚህም የተነሣ ዝምታን ያበዛል። በሥራ የመጠመድ ባሕርይን ያስያል። ማታ በጊዜ ከመግባት ይልቅ ውጭ ያመሻል። በተለያዩ ሱሶች ለመጠመድ የተጋለጠ ይሆናል። ከወትሮ በተለየ ሁኔታ ይቆጣል/ይበሳጫል። በኃይልና በጉልበት በመጠቀም ቤተሰብን ያስፈራራል። እንዲሁም አልፎ አልፎ ከሌሎች ተቃራኒ ጾታዎች ጋር ግንኙነት ሊፈጥር ይችላል። እነዚህ ባሕርያት ደግሞ በጋብቻ ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አላቸው።

የጋብቻ አማካሪ፣ በትዳር ግንኙነታቸው ውስጥ ከላይ የተጠቀሱትን ምልክቶች በሚያይበት ጊዜ፣ አንዳቸው ወይም ሁለታቸው ለራሳቸው ከሚኖራቸው አይታ የተነሣ የተከሰተ ጉዳይ እንደሆነ ሊያስብ ይችላል። እንዲህ ዓይነት መረዳት በሚኖርበት ጊዜ ችግሩ ያለበትን ሰው ለብቻው ማማከር አስፈላጊ ይሆናል። ለራስ ያለው አይታ መልካም ከሆነ ሌሎችንም በጥሩ ሁኔታ የመመልከት ሁኔታ ይፈጠራል፤ ሌላው መጥፎ ነገር ቢያደርግ እንኳ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለመቀበል የተዘጋጀ ልብ ይኖራል።

*የባልና ሚስትን መንፈሳዊ ብስለት ማጤን፦* ባልና ሚስት ተመሳሳይ እምነት ሳይኖራቸው ሲቀር የሚኖረው ልዩነት ምን እንደሆነና በትዳራቸው ላይ የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽዕኖ መለየት አስፈላጊ ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ተመሳሳይ እምነት ኖሮአቸውም ብስለታቸው ሊለያይ ስለሚችል

ያንን ልዩነታቸውን መረዳት ችግሮቻቸውን ለመፍታት ይጠቅማል። እንዳንድ ጊዜ ደግሞ የመንፈሳዊ ብስለት ልዩነት በራሱ የችግራቸው መንስኤ ሊሆን ይችላል። አንደኛው ባለትዳር ወሲብ መልካም እንደሆነ ሲያምን፣ ሌላኛው ደግሞ ርኩስት አድርጎ ሊረዳ ይችላል። እንደኛው የኢኮኖሚ ችግር ቢኖርም ለቤተክርስቲያን አሥራት መክፈል የግድ ነው የሚል አስተሳሰብ ሲኖረው ሌላኛው ደግሞ «እግዚአብሔር ለእኛስ እያስብም እንዴ? አስቀድመን ለልጆቻችን ዳቦ እንግዛ፤ አሥራት ከዚያ በኋላ ይታሰባል» የሚል አቋም ይኖረዋል።

ባልና ሚስት በችግሮቻቸው ዙሪያ ያላቸው አስተሳሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለው ከሆነ በእነዚያ ጉዳዮች ላይ ተገቢውን ትምህርት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ጠቃሚ ነው። ተገቢውን ትምህርት ከተቀበሉ በኋላ ማማከር የተማሩትን ነገር እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉ ለመነጋገር ያመቻል። እንዲህ ማድረግ የማይቻልበት ሁኔታ ሲኖር ደግሞ ስለጉዳዩ በደንብ የሚያብራሩትን መጽሐፎች እንዲያነቡ የቤት ሥራ በመስጠት በማማከር ወቅት አብሮ መነጋገር ይቻላል። የጋብቻ አማካሪ እንደ ዓውዱ የሚሻለውን መንገድ በመከተል ምክር ፈላጊዎቹን መርዳት ይችላል።

እንዳንድ ጊዜ ባልና ሚስት ስለ እምነት ያላቸው አስተሳሰብ ጋብቻቸውን ሊጎዳ ይችላል። እምነታቸው፣ ባሕል ከሚያስተምረው ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ከሌለው አስተሳሰብ ነጻ ያላወጣቸው ይሆናል። በክርስቶስ መኖር አርነት እንደሆነ በሕይወታቸው ለመስማመድ ይቸገራሉ። አልፎ አልፎ ደግሞ ሰብዓዊ ድርሻቸውን ሳይወጡ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደሚሠራላቸው ያስባሉ። ስለዚህ የጋብቻ አማካሪ በእምነታቸው በትዳራቸው ውስጥ ያለውን በጎና አሉታዊ ተጽዕኖ ማጤንና ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ መርዳት አለበት።

የባልና ሚስትን ሚና ማጤን- ትዳር መልካም እንዲሆን ባልና ሚስት የየራሳቸውን ድርሻ ማበርከት ይገባቸዋል። የእያንዳንዳቸው ድርሻ ምንድነው? የሚለው እንደ ዐውዱ የሚለያይ ቢሆንም ተገቢ የሆነ መደጋገፍ ባለበት ሁኔታ ሚናቸውን አውቀው ቢፈፅሙ ትዳርን ስኬታማ ያደርጋል። ባልና ሚስት በትዳር ግንኙነት ውስጥ በሚኖራቸው ሚና መጣጣም ካልቻሉ ዘላቂነት ያለው መግባባት አይኖርም። ባል በሚስቱ እንዲሁም ሚስት በባልዋ ላይ ጥገኛ በመሆን ለመኖር መሞከር፣ ለቤተሰብ ሕይወት መልካምነት አንዱ ብቻ እንዲሠራ ያደርጋል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ደግሞ አንዱ ወገን ብቻ ተጠቃሚ ሲሆን ሌላው ወገን እንደሚጎዳ ማጤን ይገባል።

አንድ የጋብቻ አማካሪ ለብዙ ሰዓታት የባልና ሚስትን ችግር ቢያዳምጥ መሸከም እስከሚያቅተው ድረስ ብዙ መረጃዎችን ሊሰጡት ይችላሉ። ከዚህም የተነሣ ከየትኛው ችግር መጀመር እንዳለበት ግራ መጋባት ያጋጥማል። ከዚህኛው ችግር መጀመር አለበት የሚል ወጥ መመሪያ መስጠት አይቻልም። ነገር ግን እንደ ባልና ሚስት ችግር ሁኔታና ስለሌሎች



ችግሮች መፍትሔ መሠረት ሊጥል ከሚችለው መጀመር የተሻለ ይሆናል። ምክር ፈላጊዎቹ ራሳቸው ችግሮቻቸውን መፍታት እንደሚችሉ በማስወቅ፣ እነርሱን በማስታጠቅና ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ ትኩረት ማድረግ ጠቃሚ ነው።

የማማከር ውይይት ተካሄዶ የሚገኘው መፍትሔ በባልና ሚስት መልካም ፈቃድና የጋራ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ሁሉ መፍትሔው ከተገኘ በኋላ የመጠቀሙም ጉዳይ እንዲሁ ነው። ስለዚህ የጋብቻ አማካሪ፣ ምክር ፈላጊዎቹ የደረሰቡትን ውሳኔዎች እንዲያከብሩና ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማደፋፈር ይጠበቅበታል።

በዚህ መጽሐፍ ላይ አስተያየት ቢኖራችሁ ወይም በግልም ሆነ በቡድን በተለያዩ ሥነልቦናዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ የማማከር አገልግሎት እንዲሁም ሥልጠና ቢያስፈልጋችሁ በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ትችላላችሁ።

Trust Counseling Center

P. O. Box 121174

Addis Ababa, Ethiopia

Tel: 251-911-316756

Email: kebede_zewditu@yahoo.com

## ዋቢ መጻሕፍት


Adams, Gerald R. et al. *Adolescent Life Experiences*. 3rd ed., Pacific Grove, CA: Brooks/Cole Publishing Company, 1994

Alfred Adler. *Co-operation between the sexes: Writings on Women and Men, Love and Marriage, and Sexuality*. New York: W.W. Norton & Company, Inc., 1978.

Augsburger, David W. *Pastoral Counseling Across Cultures*. Philadelphia: The Westminster Press. 1986.

------. *Civil Code of the Empire of* Ethiopia. Proclamation No. 165 of 1960.

Collins, Gary R. *Christian Counseling*. Word Publishing. 1984.

Clinebell, Howard. *Basic Types of Pastoral Care and Counseling: Resources for the Ministry of Healing & Growth*. Nashville, Abingdon Press. 1984.

Estadt, Barry; Blanchette, Melvin; Compton, John. *Pastoral Counseling*. 2nd ed. NJ: Prentice Hall, Englewood Cliffs, 1991. P. 146.

Friedman, Edwin H. *Generation to Generation: Family Process in Church and Synagogue*. NY: The Guilford Press. 1985.

Kebede Bekere. A Model for Pastoral Counseling in Ethiopian Context. Harrisonburg, VA: Eastern Mennonite University. (A Paper for Multicultural Counseling. Unpublished). 2001.

McDomald, Gordon. *Magnificent Marriage*. 8th ed., IL, Wheaton: Tyndale House Publishers, Inc., 1996.

Stone, S.C. and Sheltezer B. *Fundamentals of Counseling*. 3rd ed. Boston: Houghton Miffin Company, 1980.

TAG. *A Biblical Approach to Marriage and Family in Africa*. Kenya, Kijabe: Kijabe Printing Press, 1996.

ከበደ በከሬ፡ *የጋብቻ ችግሮችና የመፍትሔ ቁልፎች*፡፡ አአ 1996 ዓ.ም.

ከበደ በከሬ፡ *ጋብቻን እንዴት ልጀምር? የቅድመ ጋብቻ የምክር አገልግሎት*፡፡ አአ. 1995 ዓ.ም.

ከበደ በከሬ፡ *ወጣቶችን የመምራት ጥበብ*፡፡ አአ. 1998 ዓ.ም.